# የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነ ኢንጅነር ኃይሉ ሻወል (131 ሰዎች) በተከሰሱበት ወንጀል የሰጠው ውሳኔ

መስከረም 2000

አዲስ አበባ

2ኛ ወንጀል ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 43246

መጋቢት 21 ቀን 1999

ዳኞች፡- አዲል አህመድ

ልዑል ገ/ማርያም

መሐመድ አሚን ሣኒ

ከሣሽ፡- ፌ/ዐ/ህግ ሽመልስ ከማል፣ ሚካኤል ተክሉ፣ አብራሃ ተጠምቀ ቀርበናል

ተከሣሽ፡- እነ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል

1. አቶ ኃይሉ ሻውል ግዛው
2. አቶ አባይነህ ብርሃኑ በላይ
3. ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ አደራው
4. አቶ ግዛቸው ሽፈራው በላይነህ
5. ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ወ/ገብርኤል
6. አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል ፋጌ
7. አቶ ስለሺ ጠና ወ/ዮሐንስ
8. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ቦንገር
9. ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ ወርዶፋ
10. ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም እንዳለ
11. ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ባዬሼ
12. ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ደሜ
13. አቶ አስቻለው ከተማ ጌታሁን
14. ዶ/ር ታዴዎስ ቦጋለ ደገፉ
15. አቶ ገ/ፃዲቅ ኃ/ማርያም አርገጤ
16. አቶ አስፋ ሀ/ወልድ ተ/ሀይመኖት
17. አቶ ብሩክ ከበደ ወ/ማርያም
18. አቶ መስፍን አማን /በመስጠሩ በሌለበት/
19. አቶ ታምራት ታረቀኝ ዳኜ

Scanned by CamScanner

20. አቶ አንዱአለም አራጌ ዋሴ
21. ወ/ሮ ንግስት ገ/ሕይወት ወርቁ
22. አቶ ደበበ እሸቱ ረታ
23. አቶ የኔነህ ሙላቱ ተክሉ
24. አቶ ማሙሸት አማረ ድልነሴ
25. አቶ ስለሺ አንዳርጌ በዛብህ
26. መ/ቃ አለማየሁ የኔነህ ብዙነህ
27. አቶ ሀብታሙ ገ/ሕይወት አመዴ
28. አቶ አስራት ጣሴ ሰብስቤ
29. አቶ በድሩ አደም በረና
30. ኮ/ል ታምሩ ጉልላት ወ/ማርያም
31. አቶ በቀለ ግርማ ዘውዴ
32. አቶ ወንድወሰን ፀጋ ገ/ስላሴ ክሱ ተነስቷል
33. አቶ አንተነህ ሙሉጌታ ታምሩ
34. አቶ መላኩ ፋንታዬ ሳህሌ
35. አቶ ታዴዎስ በየነ በላይነህ
36. መ/ቃ ግርማ አማረ ካሳ
37. አቶ አለማየሁ መሰለ ሔኖክ
38. ወ/ት ሰብለወርቅ ታደሰ ፋንታዬ
39. አቶ እስክንድር ነጋ ፋንታ
40. አቶ አንደርጋቸው ፅጌ ኃ/ማርያም /በሌለበት/
41. ዶ/ር ነገደ ጎበዜ /በሌለበት/
42. አቶ ሰለሞን በቀለ /በሌለበት/
43. አቶ ክፍሉ ታደሰ /በሌለበት/
44. አቶ ብርሃነ መዋ /በሌለበት/
45. ዶ/ር ማሞ ሙጬ /በሌለበት/
46. አቶ አብርሃ በላይ /በሌለበት/
47. ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ /በሌለበት/



Scanned by CamScanner

48. አቶ ያሬድ ጥበቡ /በሌለበት/

49. አቶ ምርጫው ስንሻው /በሌለበት/

50. አቶ ታማኝ በየነ /በሌለበት/

51. አቶ ኤልያስ ክፍሌ /በሌለበት/

52. አቶ ዳዊት ከበደ /በሌለበት/

53. አቶ ሊሻን ግዛው /በሌለበት/

54. አቶ ንጉሴ መንገሻ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

55. አቶ አዲሱ መንገሻ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

56. አቶ ሰለሞን ክፍሌ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

57. ወ/ሮ ትዝታ በላቸው /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

58. ወ/ሮ አዳነች ፍስሃዬ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

59. አቶ ካሣ ከበደ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

60. ዶ/ር ሞገስ ወ/ማሪያም /በሌለበት/

61. አቶ ፋሲል በለጠ /በሌለበት/

62. አቶ አረጋዊ በርሄ /በሌለበት/

63. አቶ ሰለሞን ተካልኝ /በሌለበት/

64. አቶ ኤሣያስ ልሳኑ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

65. አቶ ተፈራ ዘውዴ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

66. አቶ ከፈለኝ ማሞ /በሌለበት/

67. አቶ ጥላሁን ማሩ /በሌለበት/ ክሱ ተነስቷል

68. ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ /በሌለበት/

69. አቶ ጌታቸው ጋረደው/በሌለበት/

70. ፋሲል የሕትመትና ማስታወቂያ ድርጅት

71. አቶ ፋሲል የኔአለም አገኘሁ

72. አቶ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን ተገኝ

73. ሲሳይ የሕትመትና የማስታወቂያ ድርጅት

74. አቶ ሲሳይ አጌና ጎሌ

75. አቶ አንዱአለም አየለ ሰገሰ



Scanned by CamScanner

76. ሠርካለም አሳታሚ ድርጅት

77. ወ/ሮ ሠርካለም ፋሲል ወልደሰላሴ

78. አቶ ወናክስገድ ዘለቀ ተሰማ

79. አቶ ዘላለም ገብሬ /በመሰወሩ በሌለበት/

80. አቶ ደረጀ ሀብተወልድ ይመኑ

81. አቶ ናርዶስ መአዛ ገብረሃና

82. አቶ ዳዊት ፋሲል ወልደሰላሴ

83. ዘካርያስ አሳታሚ

84. አቶ ዘካሪያስ ተስፋዬ አርጌ

85. አቶ አብይ ግዛው /በሌለበት/

86. ዓባይ አሳታሚ

87. አቶ መስፍን ተስፋዬ ጎበና

88. አረጋዊ ህትመትና ማስታወቂያ

89. አቶ ዳዊት ከበደ ባህታ

90. አቶ ፈለቀ ጥበቡ አብርሃም

91. ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት/በሌለበት/

92. አቶ ካሣሁን ከበደ ኪሮስ

93. አቶ ክፍሌ ሙላት /በሌለበት/

94. አቶ ዳንኤል በቀለ ሙሉጌታ

95. አቶ ነፃነት ደምሴ በላይ

96. አቶ መስፍን ዴቤሣ ዳዲ

97. አቶ ብርሃኑ አለማየሁ ታደሰ /ቻይና/

98. አቶ ውድነህ ጀዲ ሲረሳ

99. አቶ ወንድሙ ደሣለኝ ፋንታዬ ክሱ ተነስቷል

100. አቶ ሰለሞን አበበ አለነ ክሱ ተነስቷል

101. ወ/ት መንበረ ቸርነት አያልቅበት ክሱ ተነስቷል

102. ወጣት አብርሃም አብዩ መደርቶ ክሱ ተነስቷል

103. ወ/ሮ ዝናሽ ሞገስ ዋጋው ክሱ ተነስቷል

104. ወጣት ቢኒያም ታደሰ ደበሳይ ክሱ ተነስቷል
105. አቶ ፍቃዱ ደቤሣ ዳዲ ክሱ ተነስቷል
106. ወ/ሮ ክብነሽ ሐብቴ በላይነህ ክሱ ተነስቷል
107. አቶ ታየ ጌታቸው አባቴ
108. አቶ እዮብ በቀለ አረጋ
109. አቶ መሐመድ ሰማን ሞሣ
110. አቶ ካሣ ታደሰ ዘውዴ
111. ወጣት ፍቃዱ አሰፋ ወ/ሚካኤል
112. አቶ መላኩ ኡንቻ አጌ
113. አብዮት ዋቅጅራ በየነ
114. ወጣት ምናለ ገብሬ አለዬ
115. አቶ መብራቱ ከበደ ሰማን
116. አቶ ገዛኸኝ ተስፋዬ ረጋሳ
117. አቶ ዳንኤል በሪሁን ይማም
118. ወ/ት ቅድስት በቀለ ክንፈ
119. አቶ ተስፋዬ ጋንታ ኡቹባ
120. አቶ ተፈሪ በርሔ አማኑኤል ክሱ ተነስቷል
121. ወጣት ገ/መድህን ተፈሪ በርሔ ክሱ ተነስቷል
122. አቶ ተስፋዬ ታሪኩ በዛብህ
123. አቶ ዋልታ ንጉስ አስናቀ
124. አቶ ሙሉ ጋሹ ወንድሙ
125. አቶ አንተነህ ጌትነት አያሌው
126. አቶ ውድነህ ተመስገን አከሌ
127. አቶ ወንድሜነህ ደሳለኝ ቱሉ
128. የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
129. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ - መድህን
130. የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ሊግ
131. ቀስተ ደመና ኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የማህበራዊ ፍትህ ንቅናቄ

0031147/016

የጅማ ዩኒቨርስቲ ቤ/መ ጽሐፍት Library Jimma University



Scanned by CamScanner

ይኸ መዝገብ የተቀጠረው የተሰሙ ምስክሮች ማስረጃዎችን አጠቃላይ የቀረቡ በአቃቢ ህግ በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችን መርምሮ ተገቢውን ብይን ለመስጠት ነው በዚሁ መሠረት መዝገቡን ተመርምሮአል አቃቢ ህግ ከላይ በተጠቀሱት ተከሣሾች ላይ መጀመሪያ 7 ክሶችን አቅርቦ የነበረ ቢሆንም በማሻሻል ባቀረበው ክስ በክስ ማመልከቻው ተራ ቁጥር 4 ላይ የተገለፀውን ያነሣ ሲሆን መጀመሪያ ቀርቦ በነበረው ክስ 7ኛ ላይ አቅርቦት የነበረውን የዘር ማጥፋት ወንጀልም ሙከራ በሚል በማሻሻል አቅረቧል አቃቢ ህግ መጀመሪያ ባቀረበው ክስ በ131 ተከሣሾች ላይ ክስ ያቀረበ ቢሆንም ክሱ በሂደት ላይ እያለ በክስ ማመልከቻ በተራ ቁጥር 32 54 55 56 57 58 59 64 65 67 99 100 101 102 103 104 105 106 120 እና 121ኛ ተከሣሾች ላይ ክሱን ያነሣ ሲሆን በሌሎች ተከሣሾች ላይ የቀረበው ክስ እንደሚከተለው ይነበባል 1ኛ ክስ በሁሉም ተከሣሾች ላይ ከ1ኛ - 131ኛ በተከሣሾ ላይ የቀረበው ክስ እንደሚከተለው ይነበባል።

<u>1ኛ ክስ</u>

<u>በሁሉም ተከሣሾች ላይ</u>

<u>(ከ1ኛ እስከ 131ኛ)</u>

<u>ወንጀሉ</u>

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 38፣ 34፣ 27(1) እና 238(2)/258 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በህገመንግሥትና በህገመንግሥት ሥርዓት ላይ ወንጀል መፈጸም፣

<u>የወንጀሉ ዝርዝር</u>

1ኛ. ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱት ተከሣሾች የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ-መድህን (ኢዴአፓ መድህን)፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሊግ (ኢዴሊ) እና የቀስተ ደመና የዲሞክራሲና የማሕበራዊ ፍትሕ ንቅናቄ (ቀስተ ደመና) ተብለው ህገመንግስታዊ ስርዓቱን አክብረው ለመስራት በተመዘገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ ከቆዩ በኋላ ከጥቅምት 29 ቀን 1997



Scanned by CamScanner

ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ለብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ የሚያገለግል ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በአህጽሮት «ቅንጅት» የሚል የጋራ ጥምረት መድረክ መስርተው ይህንኑ መድረክ ለህገወጥ አላማቸው መጠቀሚያ በማድረግ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥትና ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበውና ይህ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሀሳባቸው በመስማማት ከጥቅምት 29 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ህዳር 5 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በተለይም ጎረቤት አገር ከሆነው የኤርትራ መንግሥት ጋር ጦርነት በሚያሰጋበት ጊዜ፣

1. ከግንቦት 7/97 ምርጫ በፊት በምርጫ ዝግጅት ስም «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት በህዝብ ፈቃድ የጸደቀ ሳይሆን በህዝቡ ላይ በሀይል የተጫነ ህገ መንግሥት ነው» «ህገ አራዊት ነው» «ገዢው ፓርቲ ስልጣን የያዘው በህዝብ ፈቃድ ሳይሆን በጠመንጃ ሀይል ነው» «ኢህአዴግና ሰላማዊ ትግል አይተዋወቁም» «ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም፣ ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ አቅም የለውም» «ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ አይካሄድም» ስለሆነም በምርጫው ማግስት ህዝባዊ አመጽ በማስነሳት በህጉ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ የመንግሥት ስልጣን እንይዛለን ብለው ሲዝቱና የምርጫውን ውጤት በህገወጥ መንገድ ለማስቀየር አባላቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ህጋዊ የሆነውን መንገድ ትተው ለአመጽና ለህገወጥ እንቅስቃሴ እንዲዘጋጁ ሲያነሳሱ በመቆየታቸው፣

2. ግንቦት 7 ቀን 1997 የድምጽ መስጠቱ ስነስርአት ተጠናቆ የምርጫው ውጤት በምርጫ ቦርድ ከመገለጹ በፊት ሙሉ በሙሉ አሸናፊ የሆኑበትን አዲስ አበባን ጨምሮ በአጠቃላይ በአገሪቱ «ምርጫው ተጭበርብሯል» «የምርጫ ቦርድ ነጻና ገለልተኛ አይደለም»፣ «የምርጫ ቦርድ ፍትሀዊ ምርጫ ለማካሄድ ፍላጎትም ችሎታም የለውም» በማለት፣ በህግ ከተቀመጠው የስልጣን አያያዝ ስርአት ውጭ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ በመንግስትና በምርጫ ቦርድ ላይ ተደጋጋሚ ዛቻ ሲያደርጉ፣ እንዲሁም በወቅቱ በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊዎች መካከል ከምርጫው ጋር በተያያዘ ሲፈጠሩ በሚችሉ አነስተኛ ስህተቶች ምክንያት ሁከትና ብጥብጥ



Scanned by CamScanner

እንዳይነሳና ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል እንዲቻል በመንግስት የወጣውን ሰላማዊ ሰልፍ ያለማድረግ እገዳን ባለማክበር አባላቶቻቸውን ደጋፊዎቻቸውን ለአመጽ ተግባት ሲያነሳሱ በመቆየታቸው፣

3. ይህንኑ የዛቻና ህዝቡን የማነሳሳት ተግባር ተከትሎ በአዲስ አበባ ባስነሱትና በመሩት አመጽ ሰኔ 1/97 በ26 ዜጎች ላይ የሞት በ15 ዜጎች ላይ የአካል ጉዳት እንዲሁም ግምቱ ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የመንግስትና የግል ንብረት የወደመበትን ውጤት እንዲከሰት በማድረጋቸው፣

4. ይህ የአመጽ ተግባር መንግስት ህግና ስርአትን ለማስከበር በወሰደው እርምጃ ከከሸፈ በኋላ ሰኔ 3 እና ሰኔ 6 ቀን ባደረጉት የሰስትዮሽ ስምምነት አመጽን የሚያወግዝና የምርጫ ችግሮችን በምርጫ ህጉ በተመለከተው መሰረት አግባብ ባላቸው የህግ አካላት ማለትም «የምርጫ ቦርድ» እና «ፍርድ ቤት» የሚሰጠውን ውሳኔ ለማክበርና ለውሳኔው ተገዢ ለመሆን ከተስማሙ በኋላ ቀደም ብለው የተነሱበትን ህገመንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን የማፍረስ አላማ ለማስፈጸም በማሰብ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ማጣራት በማካሄድ ላይ ባለበት ጊዜ «የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም»፣ «የምርጫ ቦርድ የገዢው ፓርቲ መሳሪያ ነው» በማለት ውሳኔውን እንቀበልም በማለት ምርጫ ቦርድ ለእነሱ በሚመች መልኩ ብቻ እንዲወስንላቸው በምርጫ ቦርድ ላይ የዛቻ ተግባር ሲፈጽሙ እንደሁም ህዝቡን ለአመጽ ሲቀሰቅሱና ሲያዘጋጁ በመቆየታቸው፣

5. የምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤቱን ካሳወቀም በኋላ አሸናፊ አለመሆናቸውን ሲያውቁ ለምርጫ ቦርድ ውሳኔ ተገዢ መሆን ሲገባቸው የምርጫ ቦርድ ውሳኔን አንቀበልም፣ ወደፍርድቤትም አንሄድም፣ በማለት ስልጣን ባለው ህጋዊ አካል የተገለጸውን የምርጫውን ውጤት ውድቅ በሚያደርግ መልኩ እና ህገመንግስቱ የማይፈቅደውን «የብሄራዊ አንድነት መንግስት» እንዲመሰረት እንታገላለን በማለት እንዲሁም ፓርላማ ለመግባት ህገመንግስታዊ



Scanned by CamScanner

ስርአቱን የሚያፈርስ ቅድመሁኔታ በማስቀመጥ እነዚህን ህገመንግስታዊ ስርአቱን የሚያፈርሱ ሀሳባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ በመንግስት ላይ የዛቻ ተግባርና ህዝቡንም ተዘጋጅተህ ጠብቀን በማለት ለአመጽ የማነሳሳት ተግባራትን ሲፈጽሙ በመቆየታቸው፣

6. ይህንኑ ህገመንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለማፍረስ ያቀረቡት ሀሳብ በመንግስት ተቀባይነት እንዲያገኝ በተደጋጋሚ ሲፈጽሙት የቆዩት ዛቻ የተፈለገውን ውጤት ሳያስገኝ በመቅረቱ ሀሳባቸውን በሀይል ተግባራዊ ለማድረግ ከጥቅምት 19/98 ጀምሮ በመንግስት ላይ ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጫና በማድረግ መንግስትን ለማሽመድመድ አስበውና አቅደው ተግባራዊ የሚሆን የአመጽ መርሀግብር በመዘርጋት በመንቀሳቀሳቸውና በዚሁ ምክንያት አባላቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ባሉበት በአዲስ አበባ ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ጀምሮ በ55 በተመረጡ ቦታዎች በአንድ ጊዜ እንዲሁም በየክልሉ አመጽና ረብሻ በመፍጠር፣ አባላቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው የህዝቡን ጸጥታና ሰላም የማስከበር ሀላፊነት ያለባቸውን የፖሊስ አባላትና ጽጥታ አስከባሪዎች ትእዛዝ እንዳይቀበሉ መመሪያ በመስጠት በጸጥታ አስከባሪዎች ላይ ተኩስ እንዲከፈት ቦንብ እንዲወረወር እና በተለያዩ የስለት መሳሪያዎች በመጠቀም፣ በድንጋይና ጎማ በማቃጠል መንገድ በመዝጋት ጸጥታ አስከባሪዎች ህግና ስርአትን እንዳያስከብሩ መሰናክል በመፍጠር ረብሻና አመጽ በማስነሳታቸውና በዚህም በጸጥታ አስከባሪዎችና በሲቪል ዜጎች ላይ በደረሰው ጉዳት በ34 ሰዎች ላይ የሞት እንዲሁም በ167 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት እንዲሁም ግምቱ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆን ንብረት እንዲወድም ምክንያት በመሆናቸው፣

2ኛ. ከ40ኛ እስከ 69ነኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች በዚህ ክስ ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የወንጀል አድራጎትና ሀሳብ የራሳቸው በማድረግ ህገወጥ እንቅስቃሴያቸውን ለማካሄድ የሚረዱ ጽሁፎችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት፣ የገንዘብና ማቴሪያላዊ ድጋፍ በማሰባሰብና ህገመንግስታዊ ስርአቱ እንዲፈርስ አለምአቀፍ ተጽእኖ በመንግስት ላይ እንዲያርፍ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ በመቆየታቸው፣



Scanned by CamScanner

3ኛ. ከ70ኛ እስከ 90ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች በዚህ ክስ ከ1ኛ እስከ 39ኛ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የወንጀል አድራጎትና ሀሳብ የራሳቸው በማድረግ «የሶስተኛው ዙር ምርጫ ተጭበርብሯል»፣ «ህዝቡ በአመጽ ድምጹን ማስከበር አለበት» በማለት፣ በመንግስትና በባለስልጣኖቹ ላይ ህዝቡ ጥርጣሬ እንዲያድርበት የሀሰት ወሬዎችን በመንዛት፣ በህዝቦች መካከል የእርስ በርስ ግጭት እንዲፈጸም የሚያደርግ መልእክት በማስተላለፍ፤ ህዝቡን ለአመጽ ሲቀሰቅሱና ሲያነሳሱ በመቆየታቸው፣

4ኛ. ከ91ኛ እስከ 95ተኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች በዚህ ክስ ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የወንጀል አድራጎት ሀሳብ የራሳቸው በማድረግ የሚወክሉትን ማህበር ከተመሰረተበት አላማና ተግባር ውጪ በመንቀሳቀስ ለዚህ ወንጀል ማስፈጸሚያና መጠቀሚያ በማድረግ በማህበራቱ ስም ውሳኔ በማሳለፍ፣ መግለጫ በማውጣት፣ በመቀስቀስ የማህበሩ አባላቶች የአመጽ ተግባሩን እንዲደግፉ በማነሳሳታቸውና አመራር በመስጠታቸው፣ ወጣቶች የአመጽ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በመገፋፋታቸውና በመደገፋቸው፣

5ኛ ከ96ተኛ እስከ 121ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች በዚህ ክስ ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የወንጀል አድራጎት ሀሳብና ፍላጎት የራሳቸው በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ጀምሮ የተቀሰቀሰውን አመጽ በመምራትና በማስተባበር በተግባራዊ አፈጻጸም ላም ተሳትፈው በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት በማድረሳቸው፣

6ኛ. ከ121ኛ እስከ 127ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች በዚህ ክስ ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የወንጀል አድራጎት ሀሳብና ፈላጎት የራሳቸው በማድረግ በምስራቅ ጎጃምና በሰሜን ሸዋ በህገመንግስቱ በተቋቋሙ አካላቶች ላይ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ የሽፍታ ቡድን ሲያደራጁ በመገኘታቸው፣

7ኛ. ከ128ኛ እስከ 131ኛ የተጠቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች ለወንጀሉ አፈጻጸም መጠቀሚያ በመሆናቸው፣ ሁሉም ተከሳሾች ህገመንግስቱንና በህገመንግስቱ መሰረት የተቋቋመውን ስርአት ለማፍረስ በአድማና በግብረአበርነት በፈጸሙት የሙከራ ወንጀል ተከሰዋል።



Scanned by CamScanner

## 2ኛ ክስ

## ከ1ኛ እስከ 39ነኛ እና ከ96ኛ እስከ 131ኛ ተከሳሾች ላይ

## ወንጀሉ

በ1996 ኣ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣38፣34፣239 የተደነገገውን በመተላለፍ፡ በህገ መንግስት ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባሩን እንዳያከናውን የማሰናከል ድርጊት መፈጸም

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሾች በአድማ በህገመንግስቱ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ ለማድረግና ይህ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሀሳባቸው በመስማማት፣

1. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሶስተኛ ጊዜ በአገራችን የተካሄደው ምርጫ ከመደረጉ በፊትም ሆነ ከግንቦት 7 ቀን 1997 ድምጽ መስጠት በኂላ በምርጫ ውድድር የማያሸንፉ ከሆነ በአገሪቱ ውስጥ ሁከት የሚቀሰቅሱ መሆናቸውን በመዛት በህገመንግስቱ መሰረት ምርጫን ለማስፈጸም የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በነጻነት ውሳኔ እንዳይሰጥ ለማደናቀፍ በመሞከራቸው፣
2. መንግስት የተጣለበትን ተግባራትና ሀላፊነቶች በስልጣኑ በተገቢው መንገድ እንዳያከናውን ህዝቡ በቤት ውስጥ በመቆየት ህገወጥ የስራ ማቆም አድማ እንዲያደርግ ጥሪ በማቅረባቸውና ከዚህም የተነሳ በሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታ ላይ ሁከት በመፈጠር ኢኮኖሚው እንዲናጋ በማድረጋቸው፣

የመንግስት አካላት ስልጣንና ተግባር አፈጻጸም ማሰናከል ወንጀለ ተከሰዋል፡፡

## 3ኛ ክስ

## ከ1ኛ እስከ 39ነኛ እና ከ96ኛ እስከ 131ኛ ተከሳሾች

## ወንጀሉ

በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣38፣34፣240(2)/258 የተደነገገውን በመተላለፍ፡ በመንግስት ላይ የትጥቅ አመጽ የማነሳሳት የማደራጀትና የመምራት ወንጀል መፈጸም

## የወንጀሉ ዝርዝር

1. ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ በተሰኘ ድርጅት ስር ተሰባስበው በህገመንግስቱ በተቋቋሙ አካላት ላይ የትጥቅ



Scanned by CamScanner

አመጽ እንዲነሳ አስበውና ይህ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሀሳባቸው በመስማማት የትጥቅ አመጽ የሚያነሱ ሀይሎችን በማደራጀትና በመምራት ከጥቅምት 21 ቀን 1998 ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን የአመጽ እንቅስቃሴ በማነሳሳት በተለይ ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ጀምሮ በአደስ አበባና በአንዳንድ የክልል አካባቢዎች ሕዝብ የጦር መሳሪያ ይዞ በህገመንግስቱ በተቋቋሙ አካላት ወይም ባለስልጣኖች ላይ የትጥቅ አመጽ እንዲያነሳ በማደራጀትና በመምራት የወንጀል ተግባር እንዲፈጸም በማድረጋቸው፣

2. ከ96ኛ እስከ 121ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች ከ1ኛ እስከ 39ነኛ በተጠቀሱት ተከሳሾች ተደራጅተው እና አመራር ተቀብለው በመንግስት ላይ ጦር መሳሪያ ይዘው አመጽ በማንሳታቸው፣

3. ከ128ኛ እስከ 131ኛ የተጠቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች ለወንጀሉ አፈጻጸም መጠቀሚያ በመሆናቸው፣በ34 ሰዎች ላይ የሞት እንዲሁም በ167 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት እንደሁም ግምቱ ብር 1 ቢሊዮን የሆነ ንብረት እንዲወድም በማድረጋቸው በአድማ በፈጸሙት ወንጀል ተከሰዋል።

## 4ኛ ክስ

## ከ1ኛ እስከ 39ነኛ እና ከ70ኛ እስከ 90ኛ እና ከ128ኛ እስከ 131ኛ ተከሳሾች ላይ

## ወንጀሉ

በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣38፣241 የተደነገገውን በመተላለፍ የአገሪቱን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል መፈጸም

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሾች ከጥቅምት 29/97 እስከ ህዳር 5/98 ድረስ ባለው ጊዜ የአገሪቱን አንድነት እንዲፈርስ አስበውና ይህ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሀሳባቸው በመስማማት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስትን በሚጻረር መልኩ የአገሪቱ ህዝቦች አንድነት እንዲፈርስ ዘረኛ እና የአስተሳሰብ ነጻነትን የሚጋፋ ቅስቀሳና የአመጽ ጥሪ በማስተላለፍ



Scanned by CamScanner

የኢህአዲግ አባላቶችንና ደጋፊዎችን እንዲያገሉ ጥሪ በማድረግ በአድማና በግብረ አበርነት በፈጸሙት ወንጀል ተከሰዋል።

**5ኛ ክስ**

**ከ1ኛ እስከ 39ነኛ እና ከ70ኛ እስከ 90ኛ እና ከ128ኛ እስከ 131ኛ ተከሳሾች ላይ**

**ወንጀሉ**

በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣38፣34፣247(ሀ)(ሐ)/258 የተደነገገውን በመተላለፍ የአገር መከላከያ ሀይልን የመጉዳት ወንጀል መፈጸም

**የወንጀሉ ዝርዝር**

1. ከ1ኛ እስከ 39ነኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ በተሰኘ ድርጅት ስር ተሰባስበው እና ድርጅቱን ለህገወጥ አላማቸው መጠቀሚያ በማድረግ ከጥቅምት 29 ቀን 1997 እስከ ህዳር 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ የመከላከያ ሰራዊት ተሽከርካሪን በማቃጠል፣ በተለይ በአገሪቱ ውስጥ የውጭ አገር መንግስት ጦርነት በሚያስጋበት ጊዜ ወታደሩ የጦር አገልግሎቱን ከመፈጸም እምቢተኛ እንዲሆን ወታደራዊ አመጽ እንዲያስነሳ እና እንዲከዳ በግልጽ በማነሳሳት እና በማደፋፈር፣
2. ከ70ኛ እስከ 90ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ የሀሰት ወሬ በማውራት የመከላከያ ሰራዊቱ እንደከፋፈልና የመከላከያ ሰራዊቱ በመንግስት ላይ እንቢተኛ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ሲቀሰቅሱና ሲያነሳሱ በመቆየታቸው፣ በአድማ በቀጥታና በእጅ አዙር በፈጸሙት የአገር መከላከያ ሀይልን የመጉዳት ወንጀል ሙከራ ተከሰዋል።

**6ኛ ክስ**

**ከ1ኛ እስከ 39ነኛ እና ከ128ኛ እስከ 131ኛ ተከሳሾች ላይ**

**ወንጀሉ**

በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ራፐብሊክ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 38፣34፣248(ለ)/258 የተደነገገውን በመተላለፍ በመንግስት ላይ ከፍ ያለ የከዳት ወንጀል መፈጸም

**የወንጀሉ ዝርዝር**

ተከሳሾች ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በተሰኘ ድርጅት ስር ተሰባስበው እና አድማ በማድረግ ድርጅቱን ለህገወጥ አላማቸው መጠቀሚያ አድርገው ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት



Scanned by CamScanner

የሚያደርገው የኤርትራ መንግስት እና በኤርትራ መንግስት የሚደገፈው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር እንዲቀናው ለማድረግ አስበውና የወንጀል ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሀሳባቸው በመስማማት የአገሪቱን የውጭ ወራሪ የመቋቋም አቅም የሚያፈርስ አመጽ እንዲነሳ በማድረግና የእነዚህን የኢትዮጵያ ጠላቶች ድርጊት በመደገፍ በፈጸሙት ከፍ ያለ ከዳት ወንጀል ተከሰዋል፡፡

## 7ኛ ክስ

## ከ1ኛ እስከ 39ነኛ እና ከ70ኛ እስከ 90ኛ እና ከ96ኛ እስከ 131ኛ ተከሳሾች ላይ

## ወንጀሉ

በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 38፣ 34፣ 27/1 እና 269(ሀ) የተደነገገውን በመተላለፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈጸም፣

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሣሾች ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ በተሰኘ ድርጅት ስር ተሰባስበው እና አድማ በማድረግ ከጥቅምት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. እስከ ህዳር 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት በአንድ ጐሣ የመጡ ናቸው የሚሉዋቸው ላይ ጥቃት በመሰንዘር እና በማጥላላት እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅት አባል እና ደጋፊ የሆኑትን ህዝቡ እንዲያገል አመራር በመስጠት እነዚህን የህብረተሰቡ ክፍሎች ለማጥፋት በማሰብ እና ይህ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት በመቀበል በሙሉ ሀሣባቸው በመስማማት የጥፋት ድርጊቱ እንዲፈፀም በማደራጀት እና ትዕዛዝ መስጠታቸው በግብረአበርነት በፈፀሙት የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል፡፡

በተከሣሾች ላይ የቀረቡት ክሶች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ ክሱ እና ማስረጃዎቹ ለተከሣሾች ለሚመለከታቸው ተከሣሾች በችሎት እንዲደርሣቸው ከተደረገ በኋላ ክሱ ከባድ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በራሣቸው ጠበቃ ማቆም የማይችሉ ተከሣሾች ካሉ ፍ/ቤቱ ጠበቃ የሚመድብላቸው መሆኑ በተደጋጋሚ ችሎቱ ላይ ቢገለጽም በጣም ጥቂት ተከሣሾች በግላቸው ጠበቃ በማቆም ከመከላከል ውጭ ሌሎች በጠቅላላ በግላቸው ያለ ጠበቃ ተከራክረዋል

በዚሁ መሠረትም በክሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞም ሆነ እምነት ክህደት ሲጠየቁ አብዛኞቹ ሀሣባቸውን በዝምታ የገለፁ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የክህደት ቃል እንደሰጡ የመዘገበ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ለክሱ ተቃውሞ ያቀረቡ ሲሆን ተቃውሞው በብይን ውድቅ ከሆነ በኋላ እምነት ክህደት ሲጠየቁ የወንጀሉን አልፈፀምንም ጥፋተኞችም አይደለንም በማለት የክህደት ቃላቸውን አስመዝግበዋል አቃቤ ህግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 136 መሠረት ክሱን እንዲከፍት ከተደረገ በኋላ ከላይ የተመለከቱትን ክሶች ለማስረዳት 19 የቪዲዮ ካሴቶችን በማቀርብ ችሎቱ የተመለከተ ሲሆን 2 የኦዲዮ ካሴቶችንም አድምጦአል በሺዎች ገጽ የሚቆጠር የሰነድ ማስረጃ ጋዜጦች እና ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን የማስረጃዎቹ ይዘት በአጭሩ እንደሚከተለው ሰፍሮአል አቃቤ ህግ ካቀረባቸው እና ችሎቱ ከተመለከታቸው 19 ካሴቶች ከፊሎቹ በ1997 ዓ.ም. ከተካሄደው ምርጫ በፊት በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ቅንጅት ለምርጫው ቅስቀሳ እና ከምርጫ ጋር ተያይዞ ባጋጠሙ ችግሮች የተሰጡ መግለጫዎች ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ ከምርጫ በኋላ ከቅንጅቱ የተሰጡ መግለጫዎች የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት ስብሰባዎች ቅንጅቱ በጠራው ስብሰባ በየወረዳዎቹ ሲከናወኑ የነበሩ ስብሰባዎች እና የመሳሰሉት ናቸው አንድ ካሴት ደግሞ የኢትዮ ኤርትራን ጉዳይ በማስመልከት የተጠራው ሰልፍን የሚያሳይ ነው ችሎቱ በመጀመሪያ የተመለከተው የቪዲዮ ካሴት ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ የካቲት 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ሰሜን ሆቴል ህዝብን በማሸማቀቅ እና በማጭበርበር ለመመረጥ መሞከር ወንጀል ነው በሚል ያዘጋጀው ሲሆን መግለጫው 25ኛው ተከሣሽ ከሆነው ስለሺ አንዳርጌ ሲነበብ በቪዲዮ ለመመልከት ተችሎአል አቃቤ ህግ ይህን ካሴት 1ኛ እና 2ኛ ላይ የተመለከቱትን ክሶች ያስረዳል በማለት ያመለከተ ሲሆን በመግለጫው የተነሱት ነጥቦች በርካታ ሲሆኑ በአጭሩ ለማስቀመጥ በምርጫ ሂደቱ ተከስተዋል ያላቸውን በርካታ ችግሮች የተዘረዘሩ ሲሆን ከነዚህም ለምሣሌ የደርግን መንግስት በጨፍጫፊነት ወንጀሉ ለፍርድ እያቀረብኩ ነው የሚለው ይህ መንግስት ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ውስጥ ለውስጥ ያፈናቸው እና አድራሻቸው ያጠፋቸው ገድሎ የጣላቸው ዜጎች ምናልባት እንደ ደርግ ቀረርቶ እና መግለጫ አልወጣባቸው ይሆናል እንጂ ቁጥር የሌላቸው ናቸው የኢህአዴግ ሹማምንት እና ካድሬዎች በእንደዚህ አይነት ድርጊቶች የህዝብን ትግል ሊገቱ አምባገነናዊ ስርዓቱንም እንዲቀጥል ሲያደርጉ እንደማይቻላቸው የተገነዘቡት አይመስልም የህዝብ አመጽ ውኃ ሙላት ነው ኢህአዴግ እራሱ እየገፋ ሕዝብን እንዲያምጽ ቢያደርግ ተጠቃሚ አይሆንም ምርጫ ቦርድ ለማይገባቸው ሰዎች እና ህጻናት ሣይቀር የምዝገባ ካርድ እየሰጠ መሆኑን ሲታይ ቦርዱ ምን ያህል የተዛባ አሠራር እና ወገናዊነት እንዳለው ጉልህ ማስረጃ ነው ምርጫ ቦርድ

031147/016

ቤ/መጽሐፍት
Library



Scanned by CamScanner

እራሱ ከኢህአዴግ መሰናዊ አሠራር ውጪ ባለመሆኑ እርምጃ ሊወስድ አልቻለም በማለት ከገለፀ በኋላ መጪውን ምርጫ ፍትሐዊ እና ዲሞክራሲያዊ ማድረግ የሚቻለው የህዝቡ እንቢ ባይነት ሲኖር ብቻ ነው ህዝቡ መብቱን ለመስከበር በህብረት በመነሳት እና የምርጫው ቅድመ ዝግጅት እና ምርጫው ፍትሃዊ እንዲሆን በጥቆማ በማጋለጡ እና በሠሳሰለው ከመሣተፍ ባሻገር የተዛባውን ምርጫም ለማስቀልበስ ከመነሣት ከወዲሁ ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ ቅንጅት ጥሪ ያስተላልፋል በማለት በመግለጫው ይጠቅሳል የመግለጫው ሙሉ ቃል ከመዝገቡ ጋር ተያይዞአል መግለጫው ከተነበበ በኋላ ለተከሣሾች ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ የቀረበ ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ ኢንጅንር ሐይሉ ሻወል በሰጠው ምላሽ ኢህአዴግ በየቦታው ያስቀመጣቸው ነፍሰገዳዮች ዛሬም እየገደሉ ነው ህግን የማያውቁ ከህግ በላይ እየሆኑ ነው አስተዳደርን የማያውቁ ቡድኖች እንደ ማፍያ እያደራጁ ህዝቡን እያስፈጁ ነው ነፍሰ ገዳይ ጋር ኔጐሼሽን የለንም ነፍሰ ገደዮችን ከየአካባቢው ያንሣ ኢህአዴግ ላያሸንፍ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተጣልቶ ሌላ አደጋ እና ችግር እንደሚመጣ እናውቃለን ማንም ስልጣን የያዘ በቀላሉ ለቆ አያውቅም ኢህአዴግ እንለቃለን አይልም እናስለቅቀዋለን ህዝብ ያስለቅቀዋል እንጂ አይለቅም በማለት መናገሩን ተመልክተናል 4ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራውም ምርጫ ቦርድ አሁን እየተካሄደ ያለውን አፈና ያውቀዋል ግድያውንም አፈናውንም ያውቀዋል የፍትህ ስርአቱ ደግሞ ኢህአዴግ ለኢዲሞክራሲያዊነት የሚጠቀምበት ትልቁ ግዙፍ አካል ነው የፍትህ ስርአቱ እንዱ የኢህአዴግ መወቅር ሣይሆን አይቀርም ምርጫ ቦርድ፡ መፍትሄ ለመስጠት አልቻለም ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱን ትግል ማካሄድ ነው ያለበት በማለት ሲናገር 9ኛው ተከሣሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌም ስልጣን የያዘው መንግስት ወዶ እና ፈቅዶ ስልጣን እንደማይለቅ እናውቃለን የስልጣን ባለቤት ህዝብ መሆኑን ይህንን ስልጣኑን ለማስከበር ህዝቡ እንደምንቀሳቀስ መግለፁን መመለከት ተችሎአል 10ኛ ተከሣሽ ፕሮፌሰር መስፍንም ትግል እኮ ማስፈራራት መገደልን ይጨምራል ለህዝቡ የስል ጣን ባለቤትነት እታገላለሁ የሚል ህዝብ ከዚህ አረመኒያዊ አገዛዝ ስልጣንን ፈልቅቄ አወጣለሁ ስላለ ይኸ ማስፈራራት ግድያው የማይቀር ነው አስበለዚያማ ትግል የለም በቅርቡ በጆርጂያ እና ዩክሬን የተደረገውት እንደምሣሌ እናያቸዋለን እነዚህ የበለጠ ትምህርት ይሆኑ ነበር ለእኛም ለወያኔም ማለቱን 20ኛ ተከሣሽ እንዱ አለም አራጌም እንደ ጥያቄም አስተያየትም በማለት እንዲህ አይነቱን ህገወጥ እንባገነናዊ መንግስት ማስወገድ

የሚቻለው በህዝባዊ ሰላማዊ አመጽ ነው ለምን በዚህ አትጣጫ አይሰራም ህዝቡን ለምን አናዘጋጀውም በጥይት ከሚከራከር ጋር በጨዋነት መከራከር ያስቸግራል በማለት መናገሩን በቀረበው የቪዲዮ ማስረጃ ለመመልከት ችለናል ችሎቱ፡ የተመለከተው 2ኛ ቪዲዮ ካሴት 1ኛ እና 2ኛ የወንጀል ክሶችን እንደሚያስረዳለት አቃቤ ህግ የገለፀ ሲሆን ይኸ ካሴት ታህሣስ 24 ቀን 1997 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ የተደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ የያዘ ሲሆን 19ኛ ተከሣሽ ታምራት ታረቀኝ አምባገነናዊ ስርአት እስካለ ድረስ ሰላም ሊኖር አይችልም በአምባገነን ስርአት ሰላም አይገኝም በማለት መፈክር ሲያሰማ የነበረ መሆኑን 1ኛው ተከሣሽ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወልም ህዝቡ በየቦታው በየመንደሩ እራሱን እያደራጀ ጠመንጃ አንፈራም ወንድም ወንድሙ ሲያዝ ለምን ያዝከው እኔ አለሁ አትሄድም እያለ በመንግስት ደረጃ ግን የአገራችንን ህልውና እንኳን ማስከበር አልቻልንም የተነገረን ረሀብ ነው ችግር ነው ስለዚህ አለም የሚያዘንን ማክበር ውሻ እንኳን ያከርፋል ጌታውንም እኮ ይነክሳል እኛ እስከመቼ ነው ውሻ ሆነን የምንኖረው እናንተ እኮ በየቀኑ በትናንሽ ባለስልጣናት የሚደርስባችሁን የማናውቅ አይምሰላችሁ ትልቁን ባለስልጣን ለማውረድ መጀመሪያ ትንሹን ባለስልጣን እንበሊ ማለት መብትን ማስከበር ያስፈልጋል ህዝብ ተባብሮ ካልተነሣ ከባርነት አንወጣም አንድነት ማለት በየጉጡ መከፋፈል አይደለም በየጉጡ ተራ በተራ ከተነሣን ተራ በተራ እናልቃለን በአንድነት ከተነሣን ግን የትኛውም ጠመንጃ የህዝብን ሀይል አይመልስም በብዙ ሀገር ሰምኑን ያየነው ሊያስተምረን ይገባል ባለ ስልጣኖች ተሰባስበው እዛ ቁጭ ብለው የለ አዋቂ ያወጡትን ፕሮግራም ተቀበሉ ይሉናል አንቀበልም ስልጣናችሁን አገር አጥፊ ወስዶባችኋል ስልጣናችሁን አገር አስገንጣይ ወስዶባችኋል እኛ የምንፈልገው ይኸንን መንግስት ማረም አይቻልም ስለዚህ እሱን ከስልጣን ለማውረድ መጀመር አለባቸሁ ዛሬውኑ የእናንተ ብቻ ሣይሆን የኢትዮጵያን ህልውና ማስከበር መጀመር አለባችሁ ህዝብ በየቦታው የህዝብን ስልጣን ማሣየት ችሎአል እኛ ከማን አንሰን ነው ይኸንን ማድረግ የማንችለው ከማን ህዝብ በታች ነን አፍሪካ ኤሲያ ሁሉም ቀድሞን ሄዶአል አደራ የምላችሁ እንጀምር ዛሬውኑ እንጠናከር እንተባበር እንደጋገፍ ዛሬውኑ በአንድነት ከታች እስከ ላይ ያለውን ባለስልጣን እናወርደዋለን በማለት ለተሰብሣቢው ህዝብ ንግግር ማድረጉን ከካሴቱ መመልከት ይቻላል 1ኛ 2ኛ 5ኛ እና 7ኛ ክሶችን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበው 3ኛ ቪዲዮ ካሴት ቅንጅት በደብረ ማርቆስ እና በደጀን ከተማ ያደረገው የምርጫ ቅስቀሣ ሲሆን በዚህ ካሴት 2ኛው ተከሣሽ አባይነህ ብርሃኑ 9ኛ ተከሣሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ እና 122ኛ ተከሣሽ ተስፋዬ ታሪኩ የሚታዩ ሲሆን መጋቢት 3 ቀን 1997 ዓ.ም. ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ ደብረማርቆስ ከተማ ባደረገው ንግግር ኢህአዴግ ሣያሸንፍ

አሸነፍኩኝ ቢልም የኢትዮጵያ ህዝብ መከላከያ ሰራዊቱን እንደ አይን ብሌን የምናየው በመሆኑ የመከላከያ ሰራዊት የህዝብ አለኝታ ነው እንባገነንነትን ለኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሰፍናል ብለን አንጠራጠርም ሰራዊቱም ህዝቡን ለመበደል የቆመ አይደለም አሁን በቅርብ ጊዜ ሁለት አገሮች ግፈኞች ያልመረጠውን መርጠሀል ብለው ስልጣን ላይ ሲያስቀምጡ ህዝቡ ሆ ብሎ ወጥቶ የነኛን ሰዎች ሁኔታ አስቀልብሶአል ይኸውም ሁላችሁም እንደምታወቁት ዩክሬን የሚባል አገር እና ጆርጂያ የሚባል አገር ሰሞኑን ደግሞ ሊባኖስ አገር ውስጥ እንደዚሁ አምጾ የማይፈልገውን ስርአት አባሮአል ታዲያ ከአጭበረበራችሁ ደግሞ ይኸ ህዝብ አይለቃቸውም እና በሰላም ልቀቁ ድምፁንም አክብሩለት በማለት ለህዝቡ መቀስቀሱን ተመልክተናል 1ኛ እና 6ኛ ክሶችን ያስረዳል በማለት በ4ኛነት የቀረበው የቪዲዮ ካሴት 1ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል አሜሪካን ፕሬስ ክለብ ያደረጉት ንግግር ሲሆን ንግግሩ የተደረገው በእንግሊዝኛ ሆኖ ሣለ በኤርትራ ቴሌቪዥን በአማርኛ የተተረጐመውን በማስረጃነት የቀረበ በመሆኑ 1ኛ ተከሣሽ በችሎት ላይ ይኸ ቪዲዮ ካሴት በሚታይበት ግዜ እኔ ንግግሩን ያደረኩት በእንግሊዝኛ ነው በማለት ለችሎቱ በመጠቆሙ በዚህ ካሴት ተከሣሹ በእንግሊዝኛ ከተነገረው ውስጥ የሚሰማውን እና የሚቻለውን ያህል ተተርጉሞ እንዲቀርብ የታዘዘ ሲሆን ትርጉም ተብሎ የመጣው በአማርኛ በሻቢያ ሬዲዮ በአማርኛ የተተረጐመውን ጭምር ያካተተ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ይኸንን ክፍል የማይቀበለው ሲሆን በእንግሊዝኛ ለተናገረው እና የተተረጐመው ሲታይ ደግሞ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ለችሎቱ ያገኘውን ብቻ በማስረጃነት ወስደናል በዚህ ላይ ለማዳመጥ እንደሚቻለው 1ኛው ተከሣሽ እኛ የምንፈልገው ለወጥ ነው ከህዝቡ ጐን ቆመን ለውጡን እንከታተላለን ዲሞክራሲን ኢትዮጵያ ውስጥ እናሰፍናለን እመኑኝ በጥቂት ወራት ውስጥ ይኸ ይሆናል አንዳንዶቻችን ያኔ ከተገናኘን እንነጋገርበታለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ የኢትዮጵያ ታሪክ አሁን መለወጥ አለበት ከአምስት እና ከአራት አመታት በኋላ አይደለም በማለት የተናገረውን ለማድመጥ ችለናል በ5ኛ የታየው የቪዲዮ ካሴት የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ያደረገውን ስብሰባ ሲሆን ይኸ ካሴት 1ኛ እና 2ኛ የወንጀል ክሶችን እንደሚያስረዳለት አቃቤ ህግ ለችሎቱ ገልጾአል በዚህ ስብሰባ ለማየት እንደተቻለው ከኢህአዴግ ጋር የተጀመረው ድርድር መቀጠል አለበት ወይስ ሊቋረጥ ይገባል በማለት የተደረገ ውይይት ሲሆን በዚህ ውይይት 7ኛ ተከሣሽ ስለሺ ጠና የህዝብ ድምጽ ይከበር የሚለውን አጀንዳ ሣይከተት አሁን በቀረበው ሁኔታ ወደ ድርድር ብንገባ ሰሎች ማንኛ

Scanned by CamScanner

ቸውንም እርምጃዎች መውሰድ አንችልም ስለዚህ ድርድሩ ይኸንን እርምጃዎች እንዳንወስድ የሚያግደን ነው የህዝብ ድምጽ ይከበር ማለት ባልተቻለበት ሁኔታ ድርድር ውስጥ መግባት ወንጀለኞች ሊያደርገን ነው በመሆኑም ድርድሩ ይቋረጥ ማለቱን ድርድሩ እንዲቋረጥ በውይይት ከተወሰነ በኋላ 2ኛው ተከሣሽ አባይነህ ብርሃኑ ወደ ውይይቱ ወይም ድርድሩ የመጣነው ምን እርምጃ አቋርጠን ነበር ያንን እርምጃ አሁን እንዴት እንደገና ኢን ቱ ቢንግ እናምጣው በማለት ለውይይት ማቅረቡን 9ኛ ተከሣሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌም ፓርላማ መግባት እና ያለመግባት ውሣኔ ሣይሰጠው ህዝብን ወደ አድማ መጥራት አይቻልም ፓርላማ እንገባለን የምንል ከሆነ ሰላማዊ ትግል በየት በኩል መሄድ አለበት የሚል ነገር ነው የሚመጣው የአድማውን ነገር ያስወጣዋል ማለቱን 5ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ሃይሉ አርአያም ምን ሊደረግ እንደሚችል አሁን መነጋገር አንችልም ልንነጋገር የምንችለው ፓርላማ መግባት እና አለመግባት በሚለው አንድ ውሣኔ ላይ ስንደርስ ነው ምክንያቱም የምንከተለው ስልት መግባት አለመግባት የሚለው ውሣኔያችን ይወስነዋል 11ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ያቆም ኃ/ማርያምም የህዝብ ድምጽ የሚከበርበት ሁኔታ ሣይኖር ወደ ፍ/ቤት ሄደን ፍትህ አላገኘንም በምርጫ ቦርድም ተመሣሣይ ነው በመሆኑም ድርድሩ መቀጠል የለበትም በማለት መናገሩን ከቀረበው የቪዲዮ ማስረጃ ለመመልከት ተችሎአል ፓርላማ መግባት አለመግባት የሚለው እና በ6ኛ የታየው የቪዲዮ ካሴት 1ኛ 2ኛ እና 7ኛ ክሶችን ያስረዱልኛል በማለት አቃቢ ህግ የገለፀ ሲሆን በዚህ ካሴት 4ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ግዛው ሽፈራው ህዝቡ የነበረው አቅጣጫ እንደ ቅንጅት ፓርቲ መግባት እና አለመግባት አጀንዳ አይደለም በጉንደር ጉልቶ የታየው የፖለቲካ አጀንዳ ፍፁም ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ አካሄድ ይኸንን መንግስት ከስልጣን ማውረድ አለማውረድ ነው ትልቁ የፖለቲካ አጀንዳ በማለት ህዝቡ ተናገረ አሁን ያለው ፖለቲካ ማለት ብንገባ ህዝቡ ተስፋ ይቆርጣል ይኸ እኮ ቀልድ አይደለም የፖለቲካ ትግል ነው የምናካሂደው ስርአት ነው የምንለውጠው መስዋዕትነት መክፈል ያስፈልጋል እንደ መሪዎች በማለት መናገሩን 2ኛ ተከሣሽ አባይነህ ብርሃኑ የህዝብ ድምጽ ይከበር ስንል የተዘረፉት የ299 ችግር ብቻ አይደለም 248 ምንም ጥያቄ ያልቀረበባቸው አሉ 299 ወንበሮች ግን ያሸነፍኩባቸው ናቸው እና እነሱን ደግሞ መንግስት ለመመስረት ያስፈልጉኛል ብሎ ኢህዴግ የሚመጣ ከሆነ ይኸንን ሌጅቲማይስ ማድረግ አጭፋሪ መሆን ያለብን አይመስለኝም ያለንን መሣሪያ የህዝብ ድጋፍ ትተን በሀይሉ የተመሰ መንግስት የህዝብን ድምዕ አልደራደርም ያለ መንግስት ፓርላማ ብንገባ ሬታልዩሽኑ ይቀጥላል እኛን አምኖ የሞተ ህዝብ አለ ሞቷል ያልመረጥኩት መንግስት አይመራኝም ብሎ አሁንም እየሞተ ነው የህዝብ ድምጽ ይከበር ስንል የተዘረፍነበንም

ቡታዎች በምንም መልኩ ህጋዊ አናደርግም በማለት መናገሩን 3ኛ ተከሣሽ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቱም ኢ.ህአዴግን እንዴት እናወርደዋለን ዛሬ ያገኘነውን ህዝባዊ ድጋፍ አጥተን እንዴት ነው ኢ.ህአዴግን የምናሸንፈው ይሽንን ታሪካዊ አጋጣሚ ተጠቅመን እንዴት ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ማድረግ እንዳለብን ማሰብ አለብን በማለት መናገሩን 20ኛ ተከሣሽ አንዱአለም አራጌም ጠንካራ ሆነው መታየት እንዳለባቸው ፓርላማ መግባት በሀገሪቱ ሰላም እንደሚያመጣ እና በዚህን ጊዜ የውጭ ኮሚኒቲው ለአንባገነኑ መንግስት ማጉብደዱን እንደሚቀጥል ፓርላማ ካልተገባ ግን መታሰር መሰቃየት ስለሚኖር እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ስለማይኖር የውጭ ኮሚኒቲውም ሆነ ኢ.ህአዴግ ሣይፈልጉ በግድ ወደማይፈለገው ድርድር ይመጣሉ ለውጥ ሊመጣ ሲል ነው የሚያስፈራው ሊነጋ ሲል ነው የሚጨልመው በማለት መናገሩን ከከሰቱ ለመመልከት ተችሎአል 7ኛው ቪ.ዲ.ዮ ካሴት 1ኛ 2ኛ 5ኛ እና 7ኛ ክሶችን ያስረዱልኛል በማለት የቀረበ ሲሆን በዚህ ካሴት በሚታየው ውይይት የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ፓርላማ ለመግባት በርካታ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ለመንግስት ጥያቄ ማቅረቡን ሲሆን ጥያቄዎቹ በሰነድ ማስረጃነትም የቀረቡ ሲሆን ይዘታቸው ወደፊት የሰነድ ማስረጃ ሲታይ የሚታይ ነው በዚህ በቀረበው ውይይት 9ኛ ተከሣሽ ዶ/ር በፍቃደ ደግፌ አንዳንድ ቅድመ ሁኔታ አስቀምጠን ካልተሟላ አንገባም ስንል የግዜ ገደብ ማስቀመጥ የለብንም ወይ የምንፈልገው ይኸ ካልሆነ ለሚቀጥሉት 5 3 አመት እንዲሁ እንቀመጣለን ወይ ይኸንን ነው ወይም የምንፈልገው ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 1ኛው ተከሣሽ ሀይሉ ሻወል በሰጠው ምላሽ ጥያቄው አሣምሽኑ እጃችንን አጣጥፈን እንቀመጣለን ከሚለው ይመስላል ይኸ እንዳልሆነ ሁላችንም በልባችን እናውቃለን በማለት የመለሰውን ማየት ይቻላል የቅድመ ሁኔታዎቹ ዝርዝር ከሰነድ ማስረጃ ጋር ይታያል 8ኛው የቪ.ዲ.ዮ ካሴት ግንቦት 23 ቀን 1997 ዓ.ም. 4ኛው ተከሣሽ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው እና 8ኛው ተከሣሽ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ እና አንድ ግለሰብ የሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሆን በመግለጫው የቀረበው ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በድምጽ ቆጠራ ተከሰተ የተባለውን ችግር በመግለጽ በቅንጅት በኩል የአገሪቱ የምርጫ ህግ የሚጠይቀውን ስርዓት በመከተል ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እስከመጨረሻው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሆኖም በሀይል የተቀማን የህዝብ ድምጽ በማስመለስ ረገድ ወሣኙ ድርሻ ከጉዳዩ ባለቤት ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠበቅ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ እንደማይገባ ኢ.ህዴግ እና ምርጫ ቦርድ የህዝቡን ድምጽ ውሣኔ በአግባቡ ለማስከበር እና ለማክበር ዝግጁ



Scanned by CamScanner

ሆነው እስካልተገኙ ድረስ በሰላማዊ እና ህጋዊ የትግል እንቅስቃሴ የተቀማውን መብት እና ድል ለማስመለስ እንደሚገደድ ህዝቡ ይህንን ሀላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣም ቅንጅት የሰከነ እና የተቀናጀ አመራር ለመስጠት አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀም በሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች በርካታ እና ተከታታይ የተቃውሞ ሰልፎች እንደሚካሄዱ የትምህርት የትራንስፖርት የንግድ እና የማምረት ስራ ከማቆም እርምጃዎች ጀምሮ እስከ ሀገር አቀፍ የስራ ማቆም እርምጃ የሚደርሱ የተለያዩ ሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴዎች እንደሚደረጉ ህዝቡ ከወዲሁ የህሊና ዝግጅት አድርጎ በንቃት እንዲጠባበቅ ጥሪ ማቅረቡን ከመግለጫው መረዳት ይቻላል ጋዜጣዊ መግለጫው በንባብ ከተሰማ በኋላ መግለጫውን ሲከታተሉ በነበሩ ግለሰቦች በቀረበው ጥያቄ በተነሱ ጥያቄዎች የፖለቲካ ጥያቄ ፍ/ቤት ያከትማል ማለት አይቻልም ዩክሬን እና ጆርጂያ የተደረጉት እንቅስቃሴዎች በረከት በራሱ የሚመጣ ስላልመሰለው ህጋዊ ናቸው ብሎአል እና አሁን ህገወጥ ናቸው ሊል አይችልም የሚል እና የመሣሰሉት ይገኙበታል በ9ኛ ቀርቦ የታየው የቪዲዮ ካሴት መስከረም ወር 1998 ዓ.ም. የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ እንደሆነ እና 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን ለማስረዳት በአቃቢ ህጉ የተገለፀ ሲሆን በዚህ ካሴት 6ኛ ሙሉነህ ኢዮኤል እየታገልን ያለነው ሣንፈራ የምንኖርበት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር ነው ጥያቄው ፓርላማ ከመግባት እና ካለመግባት ጋር የሚያያዝ አይደለም ሁሉም ሰራተኛ በቤት ውስጥ በሚቀይበት ግዜ ለሰራተኛው ማስጠንቀቂያ ቢሰጥ በተከታታይ ባሉት ቀናት ውስጥ የምንገልፃቸው ናቸው ህዝቡ ይህንን አይሰራም የመንግስት ሰራተኛም ቢሆን ነፃነት የሚፈልግ ይመስለኛል አንድ ቀን ስለዚህ መከፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁርጠኝነቱን ያሣየ ስለሆነ ቅንጣት ታክል የኢትዮጵያ ህዝብ በፍርሀት አይደናገጥም በማለት መግለጫ የሰጠ ሲሆን 12ኛዋ ተከሣሽ ብርቱካን ሚደቅሣም ቤት በመቆየት ተቃውሞ እንዲያሰማ ጥሪ የቀረበለት የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን በመጥቀስ ህዝቡ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ጥሪውን እንዲደግፍ መግለጫ መስጠቱዋን ተመልክተናል በ10ኛነት ቀርቦ የታየው የቪዲዮ ካሴት ቅንጅት ባዘጋጀው ስብሰባ የወረዳ 23 ያደረገው ፓርላማ መግባት ወይስ አለመግባት በማለት ከወረዳው ደጋፊ ህብረተሰብ ጋር ያደረገው ውይይት ሲሆን ይህ ካሴት 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዳ አቃቢ ህግ ከገለፀ በኋላ ማስረጃውን ችሎቱ የተመለከተ ሲሆን ይኸ በቀረበው ቪዲዮ መድረኩን 1ኛ ተከሣሽ ሀይሉ ሻውል እና 8ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ሲመሩት እንደነበር ተመልክተናል በዚህ ውይይት በድርጅቱ በኩል በተነበበው ጽሁፍ ምርጫው ከፍተኛ የሆነ ማጭበርበር እንደታየበት ህዝቡም ይኸንን መጭበርበር ሲያውቅ ተቃውሞውን ለማሰማት በሰላማዊ መንገድ አደባባይ ሲወጡ

የነፃ ይሆንን ህዝብ በመግደል የንፁሀን ዜጎች ደም እንዲፈስ አድርጉአል ወያኔ ይሄንን ህዝብ በመምታት የንፁሀን ዜጎች ደም እንዲፈስ አድርጉአል በማለት የምርጫ ቦርድም ውጤቱ ወያኔ እንዲሆን እንደፈለገው አድርጉአል በማለት የተነበበ ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ ለተሰብሣቢው ባደረገው ንግግር ፍ/ቤት እንካድ እንካድ በሚለው ሁኔታውን ገምግመነው ፍ/ቤት ፋይዳ የለውም ብለን ወስነናል ፋይዳ የለውም ያልነው ሁላችሁም ፍ/ቤት ሄዳችኋል ፍ/ቤቱ ምን እንደሚመስል አውቃችኋል ስለሱ የምነግራችሁ ምንም ነገር የለም 2ኛ የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽ መነጠቅም የለበትም የሚለውን ወስነን መነጠቅ የለበትም ብለናል ማለቱን በውይይቱም ከተሣታፊው ህብረተሰብ በርካታ መፈክሮች እና አስተያየቶች የተደመጡ ሲሆን ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ እናንተ እንጨት ሁኑለት እኛ ህዝቡ እሣት ሆነን እንከተላችኋለን ስልጣና ስጡን ስልጣና አንድ ቀን ነው እንመራዋለን የሚሉት እና የመሣሰሉትን ለማዳመጥ የሚቻል ሲሆን በመጨረሻም 1ኛው ተከሣሽ ሀይሉ ሻወል ባደረገው ንግግር የምትሉትን በደንብ አትኩረን ሰምተናል የምትፈልጉት ገብቶናል ከሁሉ የገረመኝ ግን የአዲስ አበባ ህዝብ የሚፈልገውን ካገኘ በኂላ ለኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ የሚፈልገውን ስላላገኘ አታገልለታለሁ ማለቱ ትልቅነት ነው ቅድም እንዳልኳችሁ ይሄንን ህዝብ ሣይ ይሄ ህዝብ የፈለገውን መርጦአል ይሄ መንግስት በሀይል የነጠቀውን መመለስ አለበት ዘመዶቻችን ገጠር ያሉትም ነፃነት ያስፈልጋቸዋል ብላችኂል የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ነፃ ካለወጣ የአዲስ አበባ ህዝብ በቁንጽል ነፃ ነኝ ሊል አይችልም ዛሬ ብዙ ሰው የሚሰጋው በዚህ መንግስት ጥንካሬ ነው እውነት ይሄ መንግስት መለኪያዎቹ ቢዘረዘሩ ጠንካራ ነው ወይ የኛ ሀይል ህዝብ ነው እናንተ አለመፍራታችሁ የመጀመሪያው ትልቁ እርምጃ ነው እንቢተኝነት ለማይሆን ነገር ገንቢ ነው እንቢተኝነት የምንፈልገውን እስካላገኘ ድረስ የምንፈልገውን የሚያመጣ ነው እንቢተኝነት ወደ ነፃነት የሚመራን ነው ስለዚህ ነፃነት በባርነት አንቀበልም ሰላም እና ዲሞክራሲ አንድ ናቸው ትግላችሁ ትክክለኛ አመራር መስጠት ከተቻለ ውጤታማ ሊሆን የሚችል የእናንተ ሀይል ብቻ ነው ሌላ ሀይል የለም በየትኛውም አለም መሣሪያ እና የወሰነ ህዝብ ተፋጦ ምን ግዜም ቢሆን ህዝብ ተሸንፎ አያውቅም ዛሬ ሌባን አልሰረክም ገዳይን አልገደልክም ብለን እጃችን የምንሰጥበት ጊዜ አይደለም በምንም አይነት የዚህ ሁሉ ወጣት ልጅ ደም ፈሶ መራብ የማይገባው ተርቦ ብዙ ግዜ መቆየት አንችልም የዚህ ህዝብ ነፃነት እስካልመጣ ድረስ ለኢትዮጵያ ምንም አይነት ልማት ብሎ ቢወራ ፋይዳ የለውም ማደግ ለማይወዱት ነገር አልፈልግም አልቀበልም ማለት ስላማዊ ነው

ህገመንግስታዊ ነው በማለት መናገሩን እና መቀስቀሱን ከካሴቱ ተመለክተናል በ11ኛው የታየ ቪዲዮ ካሴት በወረዳ 1 እና 9 የተደረገ ውይይት ሲሆን ይኸ ካሴት 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዱለት አቃቤ ህግ ከገለፀ በኋላ ችሎቱ ካሴቱን ተመልክቷል የወረዳ 1 እና 9 ላይ የተደረገው ውይይት ውይይቱ በብሄራዊ ሎተሪ አዳራሽ የተደረገ ሲሆን ችሎቱ የተመለከተው ከአዳራሹ ውጭ የተሰበሰበውን ህዝብ የሚያሣይ ገጽታ እና በውይይቱ ግዜ ሲተላለፉ የነበሩትን ሀሣቦች የተነበቡ ሀሣቦች እንዲሁም ከቅንጅት መልዕክት ተብሎ የተነበበውን ነው በካሴት እንደሚታየው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አቶ ደበበ እሸቱ እና ዶ/ር ሀይሉ አርአያ ውይይቱ እየተካሄደ ባለበት ግዜ ወደ አዳራሽ ዘልቀው ሲገቡ የታየ ሲሆን በድርጅት ስም በንባብ ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ፓርላማ መግባት እና ባለመግባት ምርጫው መጭበርበሩን የሀገሪቱ ችግር እጅግ የተወሣሰበ እና ተቆጥረው የማያልቁ መሆኑን በመጥቀስ አሁን አንድን አገዛዝ ለማስወገድ የምናደርገው ጥረት ቢቻል ቢቻል በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ስርአትን ሰላምን ሊያረጋግጥ በሚያስችል መልኩ መደምደም አለበት በማንኛውም መልኩ ወደ ሌላ ዙር የሀገር ውድቀት ወደ ሌላ ዙር የህዝብ ውድቀት ከተገባ እየተከማቹ የመጡት ችግሮች አንደገና እንድንነሣ ያስችሉናል ወይ የሚል ጥያቄም አለ አሁን ወደ ፓርላማ እንግባ አንግባ በሚለው ጥያቄ ዙሪያ አስተያየቶች ስንሰጥ መነሻ ማድረግ ያለብን ይኸንን ነው ተያይዘን እንዳንወድቅ መኖር እንፈልጋለን ማደግ እንፈልጋለን አገራችንን ማቆየት እንፈልጋለን ይኸ ወደ ኋላ የማይመለስ ጥያቄ ነው በአንፃሩ ደግሞ መብታችንን ማስከበር እንፈልጋለን በማንኛውም መልኩ ይኸ አገዛዝ በሀገራችን ህይወት በህዝባችን ህይወት ላይ በዚህ መልኩ እየቀለደ ሊቀጥል አይገባም በማለት ፓርላማ መግባት እና ባለመግባት በሚሉ ነጥቦች የተለያዩ አስተያየቶች በንባብ መልክ ለተሰብሣቢው መሰማቱን መመልከት ይቻላል አቃቤ ህግ የዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ንግግር ነው ያለው ሆኖም ችሎቱ ተናጋሪውን ሣያይ ድምጽ ብቻ በተሰማው ንግግር ዛሬ ቢያንስ በ3 የአዲስ አበባ ወረዳዎች ነበርኩ የአዲስ አበባ ህዝብ ወያኔ ጥቂት ሰዎች ስለገደለ እንደሚያቆመው ያሣያችሁበት ቀን ነው የኢትዮጵያን ወደ ፊት እጣ ተሸከመን ያለነው እኛ ነን በዚህ ምክንያት ቀዝቀዝ እንበል ስንል የፈራን ከመሰላቸው ተሣስተዋል ትዕግስት ፍርሀት አይደለም እንደማትፈሩም አሣይታችኋል እንደማንፈራም አሣይተናል እኛ ሀገር ይዘን ገደል አንገባም እነሱ ይጠፉዋታል እንጂ ከአሁን በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ ካለ ነፃነት እና ዲሞክራሲ መኖር አይችልም ምንም ይሁን ምን ስንወስን አብራችሁን ናችሁ ወይ የሚል ጥያቄ እና ንግግር ከቪዲዮ ካሴቱ ማድመጥ የተቻለ ሲሆን ከተሰብሣቢውም የተለያዩ ንግግሮች ለምሣሌ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ የአፈሙዝ አገዛዝ ሰልችቶታል የሞተው ሞቶ የተረፈው ተርፎ

ስተተኪው ትውልድ ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ መምጣት አለበት ኢህአዴግ ምርጫውን አሸንፍኩ እያለ ነው የሚፎክረው እና የኢትዮጵያ ህዝብ ሁላችንም ተባብረን አልመረጥነህም አንተ ከስልጣ ማትወርድ ፀሀይ አናይም ብለን እንቀመጥ ፓርላማ የምንገባው በአሸናፊነት ብቻ ነው የሚሉ እና የመሣሰሉት ንግግሮችን ለማድመጥ ተችሉአል በ12ኛ ያሣየው ቪዲዮ ካሴትም ከላይ ቀደም በማለት በሁለቱ ካሴቶች እንደተመለከተው ፓርላማ መግባት አለመግባት በማለት በቅንጅት የወረዳ 3 ህብረተሰብን ያወያየበት ሲሆን በዚህ ካሴት መድረኩን ሲመራ የነበረው አንድ የቅንጅት አመራር ሲሆን 34ኛ ተከሣሽ መላኩ ፋንታዬ ውይይቱን ሲያስተባብር የነበረ መሆኑን ከቪዲዮው መመልከት ይቻላይ አቃቤ ህግ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን ያስረዳልኛል በማለት ባቀረበው በዚህ ካሴት ውይይቱን በመድረክ ሲመራ የነበረ ግለሰብ እኛ ያልነው ብሄራዊ አንድነት መንግስት ነው ይኸ ማለት በአንድ አመት ውስጥ ሁሉንም ፓርቲዎች ያካተተ አንድ ግዚያዊ የሽግግር መንግስት ለአንድ አመት ይቋቋም ነው ያልነው በዛ አንድ አመት ግዜ ውስጥ ምርጫ ቦርድ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ የፍትህ አካሉም ተስተካክሎ በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ምርጫ ይደረጋል ምርጫ ቦርድ የኢህአዴግ ጋሻ ነው ብያችኋለሁ እሱ ቀርቶ ሁላችንም የምንስማማበተ ምርጫ ቦርድ ይቋቋማል በማለት ሲናገር የሚታይ ሲሆን በውይይቱ ተሣታፊ ከነበሩት ሰዎች መካከልም ፓርላማ መግባት የለብንም ሴት ወንድ እያንዳንዳችን መዋጋት አለብን እኛ ያጣነው ታግሎ የሚያታግለን ነው ኢህአዴግ በሰላማዊ ትግል እናወርደዋለን ይገድሉናል ይግደሉን የተረፍነው ተርፈን ግን ነፃነታችንን እናስከብራለን ለነገ ነፃነት ልጆቻችንን እናውርሣቸው እኛ እንሙትላቸው ሴቶች መቀነታችሁን ታጠቁ ወንዶች ቀበቶአችሁን ጠበቅ አድርጉ እንኳንስ ለአገር ነፃነት ሰው በሌላም እንኳን ይሞታል ሰው ጥይት አይፈራም የኢትዮጵያ ህዝበ ድሉ ዘንድሮ ነው ነፃ መውጣቱም ዘንድሮ ነው አለበለዚያ ባርነት መግባቱ ነው እንዋጋለን ሰኔ 1 ቀን እኛ የፈራነው ጥይትን ሣይሆን ዝናብን ነበር አሁንም የሞትነው ሞተን ትግላችንን እናሣየው መስከረምንስ ለምን እንጠብቃለን አዲስ አመት ሣይደርስ ትግላችንን እናሣይ ለወያኔ የሚሉ እና ሌሎች በርካታ መፈክሮችን መመልከት ተችሎአል በ13ኛ የታየው የቪዲዮ ካሴት ከግንቦት 29 እስከ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የተከሰተውን አመጽ ከፊል ገጽታ እንደሚያሳይለት እና 1ኛ 2ኛ እና 5ኛ ክሶችን እንደሚያስረዳለት የገለፀ ሲሆን በዚህ በታየው ካሴት የመከላከያ መኪና ሲቃጠል የከተማ አውቶብሶች ላይ

Scanned by CamScanner

የደረሰው ጉዳት በተቋማት ላይ የደረሰው እና የተለያዩ በሮች መስታወቶች መሰባበራቸውን መንገዶች በትላልቅ ድንጋይ እና ዛፎች መዘጋታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አጥር ላይ እንደዚሁም ግቢ ውስጥ በኮተቤ ኮሌጅ አጥር ላይ እና ግቢ ውስጥ ተማሪዎች የቅንጅትን የጣት ምልክት እያሣዩ መፈክር ማሰማታቸውን ከመፈክሮቹ ከፊሎቹ አትነኳም ወይ ይኸ ጥያቄ የአንተ አይደለም ወይ ተራ ሞት ከምንሞት ድምጽ ለተነጠቀው ገበሬ እና ቤተሰባችን አንድ ነገር አድረገን አንድ ሞት አይደለም 10 ሞት ብንሞት ግድ የለምን የሚሉ እና የመሣሰሉት ሲሆኑ 5ኛው ተከሣሽ ዶ/ር ሀይሉ አርአያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስ አካባቢ ከተወሰኑ ወጣቶች ጋር ሲነጋገር በዚህ ካሴት ተመልክተናል በ14ኛ ቀርቦ የታየው ካሴት ከጥቅምት 22 ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ የተቀሰቀሰውን አመጽ የሚያሣይ እና 1ኛ 2ኛ እና 7ኛ ክሶችን እንደማያስረዳለት አቃቢ ህግ የገለፀ ሲሆን በዚህ ካሴት በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የነበረውን የአመፁን ሁኔታ ለመመልከት ተችሎአል ወያኔ ሌባ በማለት በርካታ ወጣቶች ድንጋይ ሲወራወሩ መንገዶቹም በትላልቅ ድንጋይ በመዝጋት ጐማ እና የተለያዩ ነገሮችን በማቃጠል መንገዶች ሲዘጉ ፓሊስ ይኸንኑ ሲከላከል እና አስለቃሽ ጭስ በመወርወር አመፁን ለመበተን ሙከራ ሲያደርግ የታየ ሲሆን በረብሻው ጉዳት የደረሰባቸው የፖሊስ አባላት በፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል ጉዳት ደርሶባቸው ሲታከሙ የነበሩ የፖሊስ አባላትም ታይተዋል የወደመ ግለሰብ ቤት የቀበሌ 13 እና 15 ጽ/ቤት መስታወቶች መሰባበራቸው ሙሉ ለሙሉ የተቃጠሉ እንዲሁም የተሰባበሩ መኪኖች አንድ ገደል ውስጥ የገባ ላንድ ክሮዘር መኪና እና አንድ ያልፈነዳ ቦንብ በመንገድ ላይ መታየቱን በቀረበው የቪዲዮ ማስረጃ ለመመልከት ችለናል በ15ኛው ቀርቦ የታየው ካሴት ግንቦት 97 ዓ.ም. ለተካሄደው ምርጫ የፖለቲካ ድርጅቶች ባካሄዱት ክርክር በ10ኛ ተከሣሽ የተነበበውን ሲሆን በዚህ ካሴት እስከ 16ኛው ደቂቃ ብቻ በማስረጃነት የተመዘገበ ሲሆን አቃቢ ህግ 1ኛ ክስን እንደሚያስረዳለት ገለጾአል በ10ኛ ተከሣሽ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በተነበበው በዚህ ካሴት ተከሣሹ በመንግስት በርካታ የሆኑ ሰብአዊ መብት ጥሰቶች እየተፈፀሙ መሆኑን በህገ መንግስቱ የተካተቱ ሰብአዊ መብራቶችም ለይስሙላ ፈረንጅን ለማታለል ያህል ብቻ የተፃፉ እንደሆነ አገዛዙም በጭራሽ በህጋዊ ስርአት የማያምን እንደሆነ ዲሞክራሲ ግን ከማናቸውም አይነት አገዛዝ የተለየ እና ምስጉን የሚያደርገው በልምድ እና በህግ እራሱን እያረመ እና እያሻሻለ የሚያርም መሆኑን በመጥቀስ የዚህ የአገዛዝ መሠረቱ ህገ አራዊት ነው ጉልበት ነው ስለዚህም ሊሻሻል እንደማይችል 14 አመታት በሙሉ በአለህበት ሂድ ብሎ እንደቆመ የሚወዛወዝ እና ፈቀቅም የማይል ስርአት አገዛዝ እንደሆነ መታረምም ባህሪው እንዳልሆነ በአገዛዝ



Scanned by CamScanner

ለውጥ የሚባለው በአለበት እየተወዘወዘ ቀኝ ኋላ ዙር ሲባል ነው በማለት ያነበበውን መመልከት ችለናል በመቀጠል በ16ኛ ቀርቦ የታየው የቪዲዮ ካሴት ቅንጅት በአሰላ ከተማ ያደረገው ቅስቀሣ ሲሆን ይኸ ካሴት 7ኛ ክስን ያስረዳል በማለት የገለፁ ሲሆን በዚህ ካሴት 29ኛ ተከሣሽ በድሩ አደም በውይይቱ ላይ ተሣታፊ ከሆኑት ግለሰቦች ለቀረበለት ጥያቄዎች ከሰጠው ምላሽ እና ባደረገው ንግግር በአጭሩ ሲቀመጥ ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ግዜ የአንድ ብሄር ማለትም የትግሬ የበላይነት ያለ መሆኑን ይኸውም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ደህንነት ኃላፊው ገቢዎች ሀላፊ የፌዴራል ጉዳይ ሚኒስቴር ትግሬዎች ናቸው ከዚህ ውስጥ ኦሮሞ ምን አለው በማለት መናገሩን ከካሴቱ ለመመልከት ይቻላል በ17ኛ የታየው የቪዲዮ ካሴት በተጨማሪ ማስረጃነት ተመዝግቦ የቀረበ ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዱለት አቃቢ ህግ የገለፀ ሲሆን በዚህ ካሴት ሲነሣ የነበረው የተጀመረው ድርድር ሊቀጥል ይገባል ወይስ ሊቋረጥ ይቋረጥ በሚለው የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት የተደረገ ውይይት ሲሆን 3ኛ ተከሣሽ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ ሁለት ነገሮች ከፊታችን ተደቅነዋል 1ኛ ህዝብ ከኋላችን አለ ድምጼ ተዘርፏል ጽምጼን አስከብሩልኝ የሚል ህዝብ ሀይላችን ያደረግነው ይኸንን ነው እዚህ ጋር አስገድዶ ሊያስፈርመን የፈለገውን ሊያሰራን የኢህአዴግ መንግስት አለ እነዚህ ሁለት ሀይሎች አሉ በዚህ በኩል መንግስትን ተከትለን ብንሄድ ዘላለማዊ ሞት ነው የምንሞተው ስለዚህ የህዝብን መብት ለማስከበር ተነስተን ብንራመድ ምናልባት የሚደርስብን መታሰር ሊሆን ይችላል ቢሮ ሊዘጋብን ይችላል የታሰረ ይፈታል ቢሮ የተዘጋም ይከፈታል ህዝብ እስካለ ድረስ የህዝብን አሌኝታ ትተን ይኸ መንግስት የሚፈልገውን ተከትለን የምንሄድ ከሆነ ግን አስከመጨረሻው ቅንጅት የሚባል ፓርቲ በህዝብ ልብ እስከመጨረሻው ይሞታል ህዝቡ በአለም አቀፍ ደረጃ መጭበርበሩ የተመሰከረለትን ምርጫ በአለም የተሰራጨት ኢትዮጵያዊያን ሌት ተቀን የሚደክሙለትን ኢትዮጵያ ውስጥ ተማሪው ትናንትና ሰኔ 1 ቀን የሞተለትን ዛሬም ተጠባብቆ የሚገኘውን ትልቁን የሰላማዊ ትግል ህዝብ የምንጥልበትን አቅጣጫ ነው ይኸ መንግስት እያስገደደን እየመራን የሄደው ይኸን ጥለን ከሄድን ዛሬ ሞታችንን ማወጅ አለብን ብሎ መናገሩን 4ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ግዛቸው ሺፈራው ይኸ ፓርቲ ህልውናውን ይዞ መቀጠል ከፈለገ የህዝብን ጥያቄ መሠረት አድርጎ መጓዝ አለበት እኔ ትልቁ የህዝብ ጥያቄ ከተስማማንባቸው 8 አጀንዳዎች እና ካልተስማማንባቸው 3 አጀንዳዎች በመሪ አጀንዳ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ

ነው የምለው የህዝብ ድምጽ ተዘርፎአል በዚህ ምክንያት ኢህአዴግ በጉልበት በአምባገነንነት መንግስት ለመመስረት እያኮበኮበ ነው ስለዚህ በዲፕሎማሲ በአንደኛነት የማስቀምጠው የህዝብ ድምጽ መከበር ለዚህ አንገር ደግሞ የሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ የምርጫ ክልሎች መጭበርበርን ነው ይኸንን ጥያቄ ወደ ጎን ትቶ አጀንዳ አቅርበን የህዝብ ጥያቄን ትቶ ድርድሩን መቀጠል ህዝቡን መተው ይመስለኛል ስለዚህ የአውሮፓ ህብረት ሪፖርት የሰለም አቅዋም ህብረተሰብ ይኸንን እያለ ይኸንን ኢህአዴግ አልቀበልም እያለ በጭራሽ ድርድሩን መቀጠል የለብንም ብሎ መናገሩን 2ኛ ተከሣሽ አባይነህ ብርሀኑ ሁሉ ነገር ልክ በልኩ ይሆናል ብለን ማሰቡን ብንተው ይሻላል ዛሬ ኢህአዴግ ትናንትናም እየጠየቀን ያለ እደራደራለሁ ያለው የህዝብን መነሣሣት አይቶ እንጂ በእውነቱ እኛን ከልብ አርቆት መጥቶ ለማነጋገር ተፈልጉ አይደለም ግን ህዝቡ ከረገበ እና ወደየቤቱ እና ወደ የስራው ከተመለሰ በኋላ ወደ አጀንዳ መረጣ ነው የሄደው ህዝብ ድምጹ ይከበር የሚለውን ካልተቀበለ ሌላው ጭፍጫፊ ስለሆነ ድርድሩ መቀጠል የለበትም ማለቱን አቃቤ ህግ ጭብጥ ሲያሲዝ አንተነህ ሙሉጌታ ተናግሮታል በማለት ያስመዘገበው ሆኖም ቪዲዮው ሲታይ 23ኛ ተከሣሽ የሆነው የኔነህ ሙላት የተናገረው ህዝቡን ምን እናድርገው እኔ ባይገርማችሁ በፊት የዛኛው አቋም ደጋፊ ነበርኩኝ ቶታሊ ነው እራሴን የቀየርኩት ህዝቡን ካወያየን በኋላ ቶታሊ የቅንጅት አስተሣሰብ መቀየር አለበት ሌላው ማንሣት የምፈልገው ከኔጎሼሽን ፕሪንስፕሎች የመጀመሪያ ኔሽር አፍሬድ ቱ ዎክ አዌይ መፍራት የለብንም ከሰኔ 1 በፊት ምን ነበር የኢንተርናሽናል ኮሚኒቲው ሀሣብ ቶታሊ እኛን አግልሎን አልነበረምን ሰኔ 1 ተከሰተ የእነዚያ ልጆች ደም ኢንተርናሽናል ኮሚኒቲውን 380 ዲግሪ ነው የቀየራቸው ወደኛ የመጣቸው ዛሬ ኢንተርናሽናል ኮሚኒቲው ምናልባት እኛን ላይደግፈን ይችላል ነገር ግን አንድ ነገር ሲከሰት ሁኔታውን አየተው ወደ እኛ መምጣታቸው አይቀሬ ነው ለምን እንፈራዋለን ማለቱን ከተወያዮቹ አንዷ ደግሞ ህዝብ ድምጼ ይከበርልኝ እያለ ነው የጭቆና አገዛዝ በቅቶኛል ብሎአል ይኸን ደግሞ በተለያየ አጋጣሚ ገልጾአል እስከዛሬ ደግሞ ህዝቡ የፓርቲውን ትዕዛዝ ሲያከብር ቆይቷል ድምጽ ስጠኝ እሽ ተሰለፍ እሽ ታገስ እሽ አሁን ግን የ299 ኙን ጉዳይ ወደ ጎን ትተን ድርድሩን እንቀጥል ቢባል ህዝብ የራሱን አቋም ይወስዳል ትግሉ ይቀጥላል እኛ ከህዝቡ እንነጠላለን ህዝቡ ግን በተለያየ መንገድ በተበታተነ መልክ መስዋትነት በበዛ መልክ ትግሉ ይቀጥላል እኛ ግን ያሰብነውን ሥርዓት ከህዝቡም ጋር ሣንሆን በከንቱ እንደተወደድን ያህል እንነጠላለን ስለዚህ መሆን ያለበት የከፈልነውን የሚያህል መስዋትነት ከፍለን እንደሚገፋ እየነደድን እንደ ሻማ እያበራን ህዝቡን ማታገል መምራት መቻል አለብን አሁንም ቀድሞ አንድ ሲነገር



Scanned by CamScanner

የምሰማው ሀሣብ ነበር ቀጣይ እርምጃ የለም ዝግጅት የለም እንዴ ይኸን ያህል ጊዜ እኮ ስንዘጋጅ ቆይተናል ሰሞኑን እንኳን የስራ ማቆም አድማ አንዱ ነው ሰላማዊ ሰልፍ ሌላው ነው ሌላም ሌላም አለ እንዴት አልተዘጋጀንም ይባላል ድርድሩን አቁመን ስንወጣ ይኸንን እናደርጋለን አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ ይህንን ማድረግ ህዝቡ እኮ እየጠበቀን ነው በማለት መናገራቸውን ከካሴቱ ለመመልከት ተችሎአል በዚህ ካሴት አንዳንድ የምክር ቤት አባላት ድርድሩ እስከ መጨረሻው መቀጠል እንዳለበት ድርድሩ ቢቋረጥ ግን አስከፊ የሆነ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል የህዝብ ድምጽ ይከበር በሚል ሽፋን ድርጅቱ ከሰላማዊ እና ህጋዊ መንግድ ውጭ ሆኖ አደጋ ይኖራል ብለው እንደሚያምኑ ሲገልጹ የነበረ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል በቀረበው ሰነድ ማስረጃ ማሙሽት አመረ የተባለው ተከሣሽ ላእላይ ምክር ቤት አባል ባይሆንም በዚህ የቪዲዮ ካሴት በውይይቱ በተሣተፊነት ታይቶ ይገኛል በ18ኛ የቀረበው ካሴት ፓርላማ መግባት እና ባለመግባት በሚል በላዕላይ ምክር ቤት የተደረገ ስብሰባ ሲሆን በዚህ ካሴት 7ኛ ተከሣሽ ስለሺ ጠና ፓርላማ ያለመግባትን ተከትሎ ሊሠራ የታሰበው ነገር ምን እንደሆነ የዚህ ሀሣብ አቅራቢዎችን እንዲገልጹለት በጥያቄ መልክ ማቅረቡን እና በሚስጥር ተይዟል መባሉ ትርጉም የለውም ማለቱን 20ኛው ተከሣሽ አንዱአለም አራጌ በሰላማዊ ትግል ውስጥ ትልቁ ነገር ህዝብ ነው የትም አገር የተደረጉ ሰላማዊ ትግሎች እና ውጤታቸውን ማየት ትችላላችሁ ከህዝብ ድጋፍ ውጭ አንድም ሰላማዊ ትግል እውን ሆኖ አያውቅም ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ የህዝብን አመኔታ ማግኘት አለበት የህዝቡን ፍላጐት በተለይ የአዲስ አበባ ህዝብ የኔወኪሎች ስለተመረጡ ሌላው ተጭበርብሮ ይቀጥል እያለ ነው ወይ ድምጽ የተጭበረበረው ይቅርና ሣይጭበረበር ወኪሎቹን የመረጠው ህዝብ በዋነኛነት በዚህ መንገድ መቀጠል የለብንም ብሎአል ማለቱን በስብሰባው ከተካፈሉት አንድ ተናጋሪ ደግሞ ሁለተ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ድምጽ ማስጠበቅ የሚለውን በማንሣት እኛ እራሣችን ይኸንን ህዝብ አነሣስተነዋል ፓርላማ ባንገባም ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኙን ድምጽ እናስጠብቃለን በሚል ግፊት ሰጥተነዋል እኛ እራሣችን የሰራነው ስራ አለ ያን ስራ ሰርተን ህዝቡ ከተነሣሣ በኋላ የሚያቀዘቅዝ ነገር ስናደርግ ደግሞ ችግር አለ ይኸም ይጋጫል አሁን የህዝቡ ስሜት ተነሣስቷል አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የደረደራቸው ተከታታይ የሆኑ ህዝባዊ አመጽ እስከመጨረሻው ግብ እስኪያገኝ ድረስ ለመምራት ምን ያህል ዝግጅት አለን ስለዚህ ትግላችንን ወደ ፊት ሊያራምድ የሚችል ጊዜ ስለሚያስፈልገን ህልውናችንን የሚጠብቅ አካሄድ



Scanned by CamScanner

ብንሄድ ይሻላል በመሆኑም ፓርላማ ገብተን የራሳችንን የድርጅት ብቃት እያጠናከርን እና እያጐለበትን ብንሄድ ነገም የምናጣው ነገር አይደለም በማለት መናገሩን አንድ ሌላ ተሰብሳቢም ሰላማዊ ትግል ማለት ደም መፋሰስን የሚያስቆም እና ግጭቶችን ማስወገድ የሚችል መሆኑን ጠቅሶ አሁን በህዝቡ ውስጥ ያለው ስሜት እና የተፈጠረው እኛ አለመግባትን ስንወስን የሰከነ እና ትክክለኛ አጋጣሚ ላይ ያለ አይመስልም በስሜት ውስጥ እንዲገባ አድርገነዋል በስሜት እየሄደ ነው ያለው ኢህአዴግን ጠልቷል ይውደቅ ነው እያለ ያለው በማለት መናገሩን 11ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያምም ብሄራዊ አንድነት መንግስት እስከ አልተቋቋመ ድረስ አንገባም ብንል የኢንተርናሽናል ኮሚኒቲ ስምፖዚ እናገኛለን በማለት መናገሩን ከቀረበው ካሴት ለመመልከት ተችሎአል በ19ኛ እና በመጨረሻ የቀረበው በቪዲዮ ካሴት በተለያዩ ካሴቶች ተቀነጫጭቦ የቀረበ መሆኑን ችሎቱ 5 ደቂቃ አካባቢ ሲያይ መገንዘቡ እና ተቃውሞ በመቅረቡ በችሎት በታየው 5 ደቂቃ ካሴት አዲስ ማስረጃ የያዘ ከሆነ ብቻ በማስረጃነት እንደሚያዝ በታዘዘው መሠረት ከዚሁ አንጻር ካሴቱ ታይቷል ይህ የቀረበው ካሴት ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክሶች ያስረዳል በማለት ያስመዘገበ ሲሆን በካሴቱ የመጀመሪያዎቹ ደቂቃዎች 29ኛ ተከሳሽ በድሩ አደም መስቀል አደባባይ ላይ በተደረገው ሰልፍ በሀይማኖት በጐሣ በዘር በስልጣን በቤተሰብ በአምቻ እና ጋብቻ እየገዛ እያታለለ የሚገኘው አምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት የዛሬ ሣምንት በእናንተ ጡንቻ ወደነበረበት ይመለሣል ማለቱን 4ኛው ተከሣሽ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ይህንን መንግስት ማውረድ አለብን ቦርዱ ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ቴሌቪዥን እና ሬዲዮን ፓርላማውም ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ይህንን ነገር ለማስተካከል ለአንድ አመት እድሜ ግዚያዊ መንግስት እንዲመሰረት በማለት በወረዳ 17 በተሰበሰበው ህዝብ ያደረገው ንግግር ታይቷል በዚህ ወረዳ በዚሁ ቀን በተደረገው ስብሰባ በውይይቱ ተሣታፊ የነበሩ አንድ ግለሰብ ከገጠርም ከክፍለ ሀገርም ሌላውንም ማህበረሰብ መወከል እንችላለን እና እኛ ውሣኔአችንን ካሣተላለፍን በኋላ የእኛ ውሣኔ ወደ ኋላ ተመልሶ የገጠሩን ህብረተሰብ ድጋፍ አግኝቶ ይኸ ህብረተሰብ ተሰባስቦ በአንድነት ይኸንን የተበላሸ ስርአት ከአናት አውርደን ኢትዮጵያን መመስረት ይኖርብናል ማለቱን አንድ ሌላ ግለሰብም ኢህአዴግ አጭበርባሪ ነው አጭበርብሮአለ ከስልጣኑ መወገድ አለበት ብሎ መናገሩን በዚህ በታየው የ5 ደቂቃ የቪዲዮ ክፍል ለመመልከት ተችሏል ቪዲዮ ማስረጃዎችን መመልከት ከተጠናቀቀ በኋላ የኦዲዮ ካሴቶችን ችሎቱ ውስጥ ያዳመጥን ሲሆን አቃቤ ህግ ለችሎቱ እንደገለፀው እነዚህ ካሴቶች 1ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል 2ኛ ተከሣሽ አባይነህ ብርሀኑ 48ኛ ተከሣሽ ያሬድ ጥበቡ 50ኛ ተከሣሽ ታማኝ በየነ 51ኛ ተከሣሽ ኤልያስ ክፍሌ እና 52ኛ ተከሣሽ ዳዊት ከበደ የተባሉት ከትንሣኤ



Scanned by CamScanner

ኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ከመኢአድ ድምጽ ከህብረት ሬድዮ ከኢትዮጵያ ድምጽ ሬድዮ እስቶክሆልም በተለያዩ ጊዜያት ያደረጉት ቃለምልልስ እና 1ኛው ተከሳሽ ነሐሴ 4 ቀን 1997 ዓ.ም. ከመኢሀድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከተናገረው የተወሰደ ነው በማለት የቀረቡ የኦዲዮ ካሴቶች ናቸው ይኸ የኦዲዮ ካሴት በችሎት ሲደመጥ 1ኛ ተከሳሽም ሆነ 2ኛ ተከሳሽ የተሰማው ድምጽን በሚመለከት ምንም አይነት ተቃውሞ ያላቀረቡ በመሆኑ በሚሰማው ቃለምልልስ ጥያቄ አቅራቢው ኢንጅነር ሀይሉ ሻወልን ወይም አቶ አባይነህ ብርሀኑን መጋበዙን ገልጾ ለተደረጉ ቃለ መጠይቆች የተሰጡ ምላሾች ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ስላልቀረበ እና ወደፊት የተሰጡ ምላሾች ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ እስካልቀረበበት ድረስ የተከሳሾች ድምጽ ነው ተብሎ ችሎቱ ወስዶአል በዚህ መሠረት የተሰጠው ቃል መጠየቅ በአጭሩ እንደሚከተለው ሰፍሮአል ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል በአዲስ አበባ ከተማ ነሐሴ 4 ቀን 1997 ዓ.ም. በተደረገው በመኢአድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከተደረገው ንግግር ካደረገው ንግግር የተወሰደ ነው በተባለው ፓርላማ መግባት እና ባለመግባት ሦስት አማራጮች አሉን 1ኛው ጌቶች የሰጡንን ተቀብለን አንገታችንን ደፍተን መሄድ 2ኛው አንቀበልም ብለን በአለን አቅም ሁሉ በሰላማዊ መንገድ መታገል 3ኛው ምርጫው እንደገና መካሄድ አለበት የሚሉት ሲሆኑ አንዱ የሌላኛው ተቀጽላ በመሆኑ ሁለት አማራጮች ብቻ እንደሆኑ መገመት ይቻላል 1ኛ ተቀብለን እንሂድ የሚል ሲሆን ሌላኛው ግዚያዊ መንግስት የሚለው እና እንታገላለን የሚለው ነው ግዚያዊ መንግስት ለ12 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ እና ነፃ ኮርት አቋቁሞ ፍ/ቤቶች የእውነት ነፃ ፍ/ቤቶች እንዲሆኑ ተደርጎ የሚዋቀሩበት ሁኔታ ማመቻቸት ሲሆን ይኸ የምርጫውን ውጤት አንቀበልም የሚለውን አቋማችንን የሚይዝ ነው ተደላድለን ተደራጅተን ተጠናክረን እንመጣለን የሚል ተስፈኝነት እየሰማሁ ነው ኢህአዴግ ይቺን አገር ወደ ዲሞክራሲ ያሸጋግራል ብሎ አይታመንም በምንም አይነት በጠመንጃ እገዛለሁ ከሚል በስተቀር ህዝብ በየቦታው ታስሮአል የቅንጅት የቡድን መሪዎች እና ታዛቢዎች ወረቀት በታኞች ግንባር ግንባራቸውን ተመተው ነው ያለፉት ፍ/ቤት ብንሄድ ማን ነው ወዴት ነው የሚወስዱን ግዜ መፍጀቱስ ይጠቅማል ወይ የሚሉትን እና የመሳሰሉትን ንግግሮች ማዳመጥ ተችሎአል ጠያቂው እራሱን ሲያስተዋውቅ ዳዊት እንደሚባል እየገለፀ ተከሳሽ ኢንጅነር ሀይሉ ሻውልን ከትንሣኤ ሬዲዮ ጋር በተለያዩ ቀናት ባደረገው ቃለ መጠይቅ የምርጫውን ውጤት እንደማይቀበሉ ፍ/ቤትም እንደማይሄዱ የሚቋቋመው



Scanned by CamScanner

ፓርላማም ህገወጥ ነው ማለቱን በግንቦት 7ቱ የተገኘውን ውጤት የኢህአዴግ መንግስት አጨልሞታል እና ይኸንን ህገወጥ ሁኔታ ለመለወጥ የሚደረገው ትግል የምንከፍለው መጽዋትነት ከፍተኛ እንደሆነ እናውቃለን መባሉን ትግሉ የህዝብ ስለሆነ መጨረሻው በአሸናፊነት እንደሚደመደም ለዚህም ዝግጅት አለ መባሉን የትግሉ ስልት በሚዲያ የሚገልጽ አይደለም መባሉን ህዝብ እና ጠመንጃ ሲፋጠጥ አሸናፊው ህዝብ እንደሚሆን ቀውጢ ቀን ሲመጣም ሰራዊቱ ከኛ ጋር ይቆማል መባሉን ህዝቡ ሰልፍ እወጣለሁ ካለ ጠመንጃ መተኮሻ ቦታም አይገኝም በማለት መናገሩን ከክሴቱ ለማዳመጥ ተችሎአል 1ኛው ተከሣሽ ኢንጅነር ሀይሉ ሻውል ከመኢአድ ድምጽ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ድምጽ ሬዲዮ እስቶክሆልም እስዊድን ጋር አድርገውታል በተባለው ቃለ ምልልስም ከላይ ከተደረጉት ቃለ ምልልሶች ጋር ከሞላ ጎደል ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ ማስፈሩን አላስፈለገም 2ኛ ተከሣሽ አባይነህ ብርሀኑ ከመኢአድ ድምጽ እና የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ድርጅት የገለባ ግዜ ነው በተባለ የሬዲዮ ፕሮግራም ባደረገው ቃለ ምልልስ በምርጫው ዙሪያ የሚደረገው ግብግብ በህዝብ አሸናፊነት ተጠናቆ የአምባገነኑ ፀሀይ ስለምትጠልቅ የተጀመረው ትግል ተጠናክሮ እስከ ድል መቀጠል አለበት ይኸ መንግስት በሀይል ስልጣን ላይ ለመቆየት የፈለገ መንግስት እንደመሆኑ ህዝቡ በምንም አይነት ድምፄ ተጭበርብሮ እኔ ያልመረጥኩት መንግስት ሊሆን አይችልም ባለበት ሁኔታ ነው ያለነው በማለት መናገሩን ከክሴቱ ለማዳመጥ ተችሎአል ከሣቸውን በሌሉበት በመታየት ላይ ካሉት አቶ ዳዊት ከበደ እና አቶ ኤልያስ ክፍሌ ጥያቄ ሲያቀርቡ እንደነበር ለማድመጥ ተችሎአል ነፃነት ለኢትዮጵያ ሬዲዮ ድምጽ ተወሰደ በማለት በቀረበው ማስረጃ አቶ ያሬድ ጥበቡ እና አቶ ታማኝ በየነ በአንግድነት በሬድዮ የተጋበዙ መሆኑ ከተገለፀ በኋላ አቶ ያሬድ በተናገረው ንግግር አሁን እንዲህ አይነት አስከፊ ዘረኛ ስርአት ወደ ስልጣን እንዲመጣ አስተዋጾ ያደረኩ ሰው መሆኔን ያህል ያ ወደ ስልጣን የመጣበትን መንገድም እንደሚያውቅ ሰው መጠንም ያ የመጣበትን መንገድ ተጠቅሞ መውረድ እንደሚቻልም እንደሚያውቁት መደረግ አለባቸው በማለት መናገሩን አቶ ታማኝ በየነም ውጭ ያለውን ሀይል ሀገር ቤት ካለው ጋር የማያያዝ ትልቅ ስራ ያስፈልጋል ስራው እንዴት ይካሄድ ለሚለው ይኸንን የተካኑ ሰዎች ያስፈልጋሉ ከአየር ውጭ መነጋገር የሚገባ ስራ ይሆናል ነው የሚለው በማለት መናገሩን ከቀረበው ካሴት ለመረዳት ለማዳመጥ ተችሎአል አቶ ሰለሞን በቀለ ከህብረት ሬዲዮ ጋር አድርገውታል በማለት ከቀረበው ማስረጃ ተቃዋሚ ቡድኖች ቀስ እያሉ የሚሰሩት ስራ አለ እንጂ የሰም ብሎም ተስፋ መቁረጥ ትክክል አይመስለኝም ተማሪዎቹም ሆኑ ሌሎች የሚያንቀሣቅሣቸው ቡድን ቢኖር የሚንቀሣቀሱት እንዲሁ ተነስተው አይደለም አንድ



Scanned by CamScanner

የሚያስተዳድር የምንፈልገው ቡድን እሰ ያ ቡድን ነው በልዩ ልዩ መልኩ ውስጡን እያሰፈ መጠቀሚያ ስለማይኖርበት በአሁኑ ወቅት ተማሪውንም ሆነ ሌላውንም የሚያንቀሳቅሰው ያ ቡድን ነው እና እሰ ብሎ መናገሩን ከካሴቱ ለማዳመጥ ተችሎአል አቃቤ ህግ አዲዮ ካሴቱን ማሰማት ካጠናቀቀ በኋላ የሰነድ ማስረጃዎቹ ትሎት ላይ ምን እንደሚያስረዱለት የገለፀ ሲሆን በዚህ መሠረት የቀረቡት ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው በሰነድ ማስረጃው ተራ ቁጥር 1 ላይ የተገለፀው ሁሉንም ክሶች ያስረዳልኛል በማለት በአቃቤ ህግ የተገለፀው ጥቅምት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በፀደቀው የመመስረቻ ሰነድ 1..መኢ.ህድ 2-ኢ.ዴአፓ መድህን 3-ኢ.ዲ.ሊ. 4-ቀስተዳመና የዲሞክራሲ እና የማህበራዊ ፍትህ ንቅናቄ የተባሉ አራቱ ድርጅቶች በስምምነት ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ የሚለውን ማቋቋማቸውን የሚያሣይ ነው በተራ ቁጥር 2 የቀረበው የሰነድ ማስረጃ የቅንጅት መተዳደሪያ ደንብ ሲሆን ሁሉንም ክሶች ያስረዳል በማለት በአቀረበው በዚህ ሰነድ አንቀጽ 4 ላይ የቅንጅት ምክር ቤት ከፍተኛ የስልጣን አካል መሆኑን እና የቅንጅቱን በሚመለከት ማናቸውም ጉዳዮች ውሣኔ ሰጭ እንደሆነ ተመለክቷል በተራ ቁጥር 3 የቀረበው ሰነድ ሁሉንም ክሶች እንደሚያስረዳለት በአቃቤ ህግ የተገለፀ ሲሆን መስከረም 14/1998 ዓ.ም. አራቱ ድርጅቶች ውህደት ስምምነት የፈፀሙ መሆኑን የሚያሣይ ሰነድ ሲሆን በዚሁ በተዋሀደው ድርጅትም የላዕላይ ምክር ቤት አባላት እና የስራ አስፈፃሚ አባላት እነማን እንደሆኑ የሚያሣይ ሲሆን በዚሁ መሠረት 1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ 5ኛ 6ኛ 7ኛ 8ኛ 9ኛ 11ኛ 12ኛ 13ኛ 14ኛ 15ኛ 16ኛ 17ኛ 18ኛ በሌለበት 19ኛ 20ኛ 21ኛ 22ኛ እና 23ኛ ተከሣሾች የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት መሆናቸውን ከሰነዱ ለመረዳት ይቻላል በክስ ማመልከቻው የ15ኛ ተከሣሽ ስም ገ/ፃድቅ ኃ/ማርያም የሚል ሲሆን ተከሣሹም ችሎት ቀርቦ ማንነቱ ተጣርቶ ስሙን ሲያስመዘግብ ስሙን በክስ ማመልከቻው ላይ በተመለከተው ሁኔታ አስመዝግቦአል ሆኖም ግን አቃቤ ህግ ባቀረበው በዚህ የሰነድ ማስረጃ ገብረፃድቅ የአባት ስም ኃ/ማርያም ማመልከቻው ላይ የተመለከተው ሁኔታ እሱ ሆኖም ግን አቃቤ ህግ ባቀረበው እዚህ የሰነድ ማስረጃ ገ/ፃድቅ የአባት ስም የተለየ በመሆኑ በክስ ማመልከቻው የተጠቀሰው ተከሣሽ በእርግጥ ከሰነድ ማስረጃው የተጠቀሰው ነው ወይ የሚለውን ለማጣራት ችሎቱ ቀጠሮ በመስበር ባለፈው ሳምንት በዋለው ችሎት ሁኔታውን አጣርቷል በዚህ ቀን አቃቤ ህግ ይህንን ሁኔታ እንዲያስረዳ ሲጠየቅ በሰነድ ማስረጃው ስሙ የሚታየው ገ/ፃድቅ የተባለው እና የአባት ስም

የተለየ የሆነው ይኸው ተከሣሽ እንደሆነ ይኸንንም የላዕላይ ምክር ቤት ላዕላይ ምክር ቤት ሲደረጉ የነበሩ የቪዲዮ ካሴቶችን በመመልከት መረዳት እንደሚቻል የገለፀ ሲሆን ተከሣሹም ስለ ሁኔታው ችሎቱ ሲጠይቀው የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባል እንደሆነ እንደነበር የገለፀ በመሆኑ በሰነድ ማስረጃው ግብረሃይት በማለት የአባት ስም የተለየ የአባት ስም የታይፕ ስህተት ከሚሆን ውጭ ተከሣሹ እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል በሰነድ ማስረጃ ተራ ቁጥር 4 እና 5 የተመለከቱት ሰነዶች ቅንጅትን ከውህደት በፊት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴነት ይመሩ የነበሩትን ሲመሩ የነበሩት የሚያሣይ ሰነድ ሲሆን በተራ ቁጥር 6 የተገለፀው ሰነድ ቅንጅት ከውህደት በፊት የምክር ቤት አባላትን የያዘ ሰነድ በዚህ ሰነድ በተራ ቁጥር ሁለት በአጀንዳነት የተያዘው በአዲስ አበባ እና በየክልሉ ስለሚካሄዱ ህዝባዊ ስብሰባዎች የሚል ሲሆን በዝርዝሩም በ21/12/97 እና በ22/12/97 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በሁሉም የምርጫ ወረዳዎች ስብሰባዎች እንዲካሄዱ የስብሰባው አላማም ከእንግዲህ በኋላ የቅንጅት ፖለቲካ እንቅስቃሴ በምን አቅጣጫ ሊራመድ እንደሚገባው ህዝቡ እራሱን ምክር እና አስተያየት እንዲሰጥ የሚል ሆኖ በስብሰባዎቹ አንድ ወጥ የሆነ መልዕክት ለማስተላለፍ እንዲቻል በማዕከል ጽሁፍ እንዲዘጋጅ ጽሁፉንም ለማዘጋጀት እቶ ሙሉነህ ፍቃደኛ ስለሆኑ ተዘጋጅቶ ይሰራጭ በማለት ውሣኔ መተላለፉንም ከሰነዱ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ይኸ ሰነድ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን ያስረዳልኛል በማለት አቃቢ ህግ በመግለጫው አቅርቦአል ከሰነድ ማስረጃው ተራ ቁጥር 7 እስከ 9 የተዘረዘሩ ሰነዶች ቅንጅት ከመስከረም 14/1998 ዓ.ም. ውህደት በፊት በነበረው ቅንጅት ምክር ቤት ውህደቱን በሚመለከት የተደረጉ ስብሰባዎችን የያዘ ቃለጉባኤ ነው በሰነድ ማስረጃው ቁጥር 10 የቅንጅት ማኒፌስቶ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ሰፍሮ የሚገኘው 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዳለት አቃቢ ህግ የገለፀ ሲሆን በዚህ ማኒፌስቶ የተለዩ ኢሹዎች እና ጭብጦችን ያነሣ ሲሆን ከክሱ ጋራ አግባብነት ያለውን ብቻ አይተናል በዚሁ መሠረትም በዚሁ ማኒፌስቶ በአገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል ነፃና ገለልተኛ ተቋም የለም አሁን በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት ገዥው ፓርቲ በህዝቡ ላይ የጫነው ነው የገዥው ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ቅጅ ነው ሀገሪቷ በጠመንጃ አፈሙዝ በሚተማመን አገዛዝ እንደወደቀች ነው የሚሉ እና የመሣሰሉትን በማኒፌስቶው ማንበብ ይቻላል በተራ ቁጥር 11 የተጠቀሰው ሰነድ 40ኛ ተከሣሽ እንዳርጋቸው ጽጌ ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ የሚለው መጽሀፍን 131ኛ ተከሣሽ ቀስተዳመና ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እና ማህበራዊ ፍትህ ንቅናቄ እዲያሣትም እንዲያከፋፈል እንዲሸጥ ከሽያጭ የሚገኘውንም ጥቅም በጥሬ ገንዘብም ሆነ በቼክ እንዲቀበል በማለት ውክልና መስጠቱን የሚያሣይ ሰነድ በተራ



Scanned by CamScanner

ቁጥር 12 የተጠቀሰው ሰነድ ቅንጅት በ5/3/97 ዓ.ም. ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ምርጫን ለመካፈል እንዲያስችለው መሟላት አለባቸው ያላቸውን ነጥቦች የያዘ ሰነድ ነው በሰነድ ማስረጃው ቁጥር 14 እስከ 18 ያሉ ሰነዶች 1ኛ 2ኛ ክሶችን 14ኛው ሰነድ ደግሞ 5ኛውንም ክስ ጭምር እንደሚያስረዳ የተገለፀ ሲሆን ከግንቦት 12-18 ባሉት ቀናት በወጡት መግለጫዎች ምርጫው በቆጠራ ግዜ ስላጋጠሙ ችግሮች በሰፊው የተዘረዘረ ሲሆን ይዘታቸውም ቆጠራ በተጠናቀቀበት ቦታዎች እና ቅንጅት አሸናፊ በሆነባቸው ቦታዎች ኢህአዴግ አሸነፍኩ በማለት ህገወጥ መግለጫ እያወጣ ነው በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች ቆጠራው በገዥው ፓርቲ እንዲቋረጥ ተደርጉአል ቆጠራው በቀጠለበት ጥቂት ቦታዎች ገዥው ፓርቲ በአፈና በማስገደድ እና በማጭበርበር ስልት በህገወጥ መንገድ የህዝብን ድምጽ በመቀማት ላይ ነው ገዥው ፓርቲ የገጠሩን ህዝብ ድምጽ በመቀማት የአምስት አመታቱን መንግስታዊ ስልጣኑን በህገወጥ መንገድ እያራዘመ ነው ገዥው ፓርቲም ሆነ ምርጫ ቦርድ የተከሰቱ ችግሮች እንዲታረሙ የሚያስችል የተግባር እንቅስቃሴ ላይ አይደሉም ይኸንን ሁኔታ ቅንጅቱም ሆነ ህዝቡ ከዚህ በላይ ታግሶ መቆየት እንደማይችሉ የኢትዮጵያ ህዝብ የተናጥል እርምጃ ከመውሰድ በመቆጠብ ቅንጅት ለሚሰጠው ህጋዊ እና ሰላማዊ እንቅስቃሴ አመራሩን እንዲጠብቅ ህዝቡ ማንኛውም ስለ ሰላማዊ ትግል ማዕቀብ ውስጥ የሚገኝ የትግል ስልት ተጠቅሞ መብት እና ጥቅሙን ለማስጠበቅ ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ እና ከቅንጅት የሚሰጠውን ተከታታይ መመሪያ በንቃት እንዲጠባበቅ የፖሊስ እና የደህንነት አባላትም ከህዝቡ ጐን እንዲቆሙ ጥሪ ማቅረቡን ከሰነዶቹም ለመረዳት ይቻላል በሰነድ ማስረጃው ቁጥር 19 የቀረበው ጋዜጣዊ መግለጫ በችሎቱ በ8ኛ ቪዲዮ ካሴት የታየው ሲሆን ይዘቱ እዛ ላይ የቀረበ በመሆኑ መድገሙ አላስፈለገም በሰነድ ማስረጃ ቁጥር 20 የቀረበው ግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ከቅንጅት እና ከህብረት በጋራ የተሰጠ መግለጫ ሲሆን አቃቤ ህግ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዳለት ገልጾአል ይዘቱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከግንቦት 28 ሌሊት የተጀመረው እንቅስቃሴ ግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ተባብሶ በቀጠለው ረብሻ የኢህአዴግ መንግስት የወሰዳቸውን የኃይል እርምጃዎች በመግለጽ ለዚህ መፍትሄ ይሆናል ያላቸውንም በመዘርዘር ከገለፀ በኋላ ይኸ ካልሆነ ግን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተጀመረው እንቅስቃሴ ሀገር አቀፍ ሽፋን በመያዝ በኢህአዴግ እና በህዝቡ መካከል አላስፈላጊ ሂደቶችን በመፍጠር ማንንም የማይጠቅም ሁሉንም ሊጐዳ የሚችል ደዘት እና አቀጣጫ



Scanned by CamScanner

ሊወስድ እንደሚችል በመግለጽ የተሰጠ መግለጫ ነው በሰነድ ማስረጃ ቁጥር 21 በቀረበው የሰነድ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት ቅንጅት እና ኢህአዴግ መካከል ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ቅሬታ ስለሚሰማበት እና ስለሚያጣራበት ሂደት የተደረገ የጋራ ስምምነት በሚል ሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. በ3ቱ ድርጅቶች የተደረሰውን ስምምነት የሚያሣይ ሲሆን የስምምነቱ መንፈስም በምርጫ አፈፃፀም ላይ የታዩ ጉድለቶችን በማስመለከት በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ የሚሰጠው በምርጫ ህጉ መሠረት በተበጁ ውሣኔ አሰጣጥ ስርአቶች አማካይነት እንደሆነ እና ስልጣን ያላቸው አካላት በአገሪቱ ህጐች በተሰጣቸው ሙሉ ስልጣን መሠረት በሚወስኑዋቸው ውሣኔዎች ለመገዛት እና ውሣኔዎቹን ተፈፃሚነት ለማደናቀፍ ከመሞከር መቆጠብ እንዳለባቸው ምርጫ ቦርድ የምርጫ ችግሮች ናቸው ተብለው የ299 አቤቱታዎች ለመመርመር መወሰኑን መቀበላቸውን የተስማሙበት ሰነድ ነው 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን ለማስረዳት የቀረበው በተራ ቁጥር 22 የቀረበው ሰነድ ሰኔ 4 ቀን 1997 ዓ.ም. ከቅንጅት የተሰጠ መግለጫ ሲሆን በዚህ መግለጫ ቅንጅቱ ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቃውሞ ጀምሮ የታክሲ ሹፌሮች የግል ንግድ ባለቤቶች በስርአቱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በሚያስደንቅ ሁኔታ እየገለፁ እንደሚገኙ ቅንጅቱ ይኸንን ሁኔታ በከፍተኛ አድናቆት እንደሚመለከተው ይህ እንቅስቃሴ የአገራችን የሰላማዊ ትግል እርምጃ ወደ ከፍተኛ እና ወደ ኋላ የማይመለስ የትግል ደረጃ መሸጋገሩን እንደሚያሣይ ገልጾ በአሁኑ ወቅት ወቅታዊው ሁኔታ ወደ አጠቃላይ አገርን እና ህዝብን ወደሚጐዳ አደጋ እንዳይሸጋገር ህዝቡ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ከሰኞ ሰኔ 6 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ህዝቡ ወደ እለት ከእለት ስራ እንቅስቃሴው እንዲመለስ እንጠይቃለን የሚል ነው በሰነድ ማስረጃው ቁጥር 23 የቀረበው ማስረጃ ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም. ከቅንጅት ድራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሀል በማለት ያወጣው መግለጫ ሲሆን በመግለጫው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የረሀብ እና የትምህርት ማቆም አድማ እንዲሁም ሹፌሮች እና ነጋዴዎች ስራ በማቆም እና መደብሮቻቸውን በመዝጋት በሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ መንገድ ተቃውሞአቸውን መግለፃቸውን ይኸንን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህገ ወጥ በማለታቸው ከተጠያቂነት መሸሽ እንደማይችሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምርጫ ቦርድን እና የፍ/ቤቱን ውሣኔ ተቀብለን አርፈን እንድንቀመጥ በእሣት ሊያስፈራሩን ሞክረዋል ሆኖም ተደናግጠን በአምባገነን አገዛዝ ስር አንበረከክም በህይወት በንብረት እና በአካል ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂዎች ህግ ፊት እንዲቀርቡ ያለ ጥፋት የታሰሩም እንዲለቀቁ በምርጫ መጭበርበር ምክንያት የቀረበው አቤቱታዎች ትክክለኛ ማጣራት ይደረግ ይኸ ካልሆነ ቀርቶ ኢህአዴግ ችግሮችን በጠመንጃ ለመፍታት



Scanned by CamScanner

የሚያደርገው ሙከራ በሰነድ ማስረጃ ቁጥር 24 እና 25 የቀረበት 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዱለት አቃቢ ህግ የገለፀ ሲሆን እነዚህ ሰነዶች ሀምሌ 12 እና 20/1997 ዓ.ም. ከቅንጅት እና ህብረት የወጡ መግለጫዎች ሲሆኑ ይዘታቸውም የድምጽ ማጣራቱ ሂደት ችግር ውስጥ መግባቱን እና በስመ ማጣራት ተግባር የድምጽ መንጠቅ እንቅስቃሴ መሆኑ የምርጫ ቦርድም ሆነ የመንግስት እንቅስቃሴዎች ተመሣሣይ እንደሆነ በመግለጽ በዚህ አይነት ሂደት መቀጠል አግባብ አለመሆኑን እና የሚገኘው ውጤትም የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽ እንደማያስከብር ምርጫ ቦርድ የኢህአዴግ አፈቀላጤ እና ሌላው የኢህአዴግ ክንፍ ወይም 5ኛው የግንባሩ አባል ድርጅት እንጂ የተለያዩ አካላት አይደሉም ይኸ በመሆኑም የህዝብ ድምጽ ተነጥቆ ውጤቱም ከቶውንም በፀጋ አንቀበልም ስለዚህም ትክክለኛ የህዝብ ድምጽ ተከብሮ የህዝብ መረጋጋት እንዲፈጠር እና ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ ገለልተኛ በሆነ ወገን በማንም በኩል ቅሬታ የቀረበባቸውን ምርጫ ክልሎች ሁሉ ከአፈና ከግድያ እና ከወገንተኝነት በፀዳ ሁኔታ ምርጫው ሊደገም ይገባል በመጨረሻም የኢትዮጵያ ህዝብ በተከታታይ ለምንወስዳቸው እርምጃዎች በትዕግስት እና በንቃት እንዲጠባበቅ እናሳስባለን የሚል ይዘት ያለው መግለጫዎች ናቸው በሰነድ ማስረጃ ቁጥር 26 የቀረበው ማስረጃ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዱለት የገለፀ ሲሆን ይኸ ሰነድ መኢአድ ነሀሴ 4 ቀን 1997 ዓ.ም. ያደረገው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን በዚህ ሰነድ ላይ የተገኙ የፕሬዝዲየም አባላት መካከል 1ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል 2ኛ ተከሣሽ አቶ አባይነህ ብርሀኑ 3ኛ ተከሣሽ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ 4ኛ ተከሣሽ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው እና 26ኛ ተከሣሽ መቶ አለቃ አለማየሁ የኔነህ ስም የሚታይ ሲሆን በዚህ ሰነድ መረዳት የሚቻለው መኢአድ ጠቅላላ ጉባኤ ለአመራሩ ውክልና መስጠቱን እና ለመፍትሄ መነሻ እንዲሆን በሚልም ከአንድ አመት ለማይበልጥ ግዜ የሚሰራ ተግባሩ ነፃ የሆነ ማለትም እንደ ምርጫ ቦርድ የፍትህ አካላትን እና ለምርጫው በሰላም እና በተረጋጋ ሁኔታ መጠናቀቅ የሚያገለግሉ ሌሎች ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን አቋቁሞ ምርጫ ሲጠናቀቅ ስልጣኑ የሚያበቃ በምርጫው የተወዳደሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተ ግዜያዊ መንግስት እንደ አማራጭ መቅረብ ይኖርበታል በማለት መገለፁን ከሰነዱ ለመመልከት ተችሏል በተራ ቁጥር 27 የቀረበው የሰነድ ማስረጃ 1ኛ 2ኛ 5ኛ እና 7ኛ ክሶችን እንደሚያስረዱ የተገለፀ ሲሆን ይኸ ሰነድ በቪዲዮ ካሴት በ7ኛነት የታየ ሲሆን የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች ለመግባት የቀረቡ

Scanned by CamScanner

ቅድመ ሁኔታዎች በማለት በቅንጅት መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተጻፈ ነው በዚህ ሰነድ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጡ ምርጫ ቦርድ ነፃ እና ገለልተኛ መሆኑን በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንደገና መቋቋም ያለበት መሆኑን ፍትሀዊ የሆነ መንግስት ሚዲያ አጠቃቀም እና የግል ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መቋቋም እንዳለበት ፍርድ ቤቶችን ነፃነት ማረጋገጥ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. በዜጐች ላይ የደረሰውን ግድያ የሚያጣራ ነፃ አካል እንዲቋቋም የፖሊስ የመከላከያ እና የደህንነት ተቋማት ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና በተወካዮች ምክር ቤት አሰራር እና አዲስ አበባ መስተዳደርን በመለከተ አዲስ ህጐችን መቀየር እና እነዚህን ጉዳዮች ተፈጻሚ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አንድ ነፃ የሆነ አካል መቋቋም ያለበት መሆኑን በመግለጽ እንዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ወደ ፓርላማ እንደማይገቡ የተገለፀበት ሰነድ ነው በቁጥር 28 የቀረበው ሰነድ ማስረጃ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን እንደሚያስረዱ በአቃቢ ህግ የተገለፀ ሲሆን ይኸ ሰነድ ቅንጅት ጥቅምት 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ሁሉም ኢትዮጵያዊ ህገመንግስት የማስከበር ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሆን በዚህ መግለጫ ወቅት ጊዜው የሙስሊሙ የረመዳን ጾም ወቅት በመሆኑ ጠንከር ያለ የትግል ጥሪ ለማድረግ ያለመቻሉን ሆኖም ሊወሰዱ የሚችሉ ሌሎች እርምጃዎች በጥቂት ቀናት እንደሚያሣውቁ እና ህዝቡ በየመንደሩ በዜጐች ላይ በኢህአዴግ መንግስት የሚወሰደውን እርምጃ ሁሉ በመተባበር እንዲከላከል ትግሉን ከህዝቡ ጋር በመሆን እንደሚያፋፍም የገለፀበት ሰነድ ነው በቁጥር 29 የቀረበው ሰነድ 1ኛ 2ኛ እና 5ኛ ክሶችን እንደሚያስረዳ የተገለፀ ሲሆን ይኸ ሰነድ ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም. ከቅንጅት ለኢትዮጵያ ህዝብ የተደረገ ሰላማዊ ትግል ጥሪ የሚል ሲሆን በርካታ ጉዳዮችን በመዳሰስ ምርጫው መጭበርበሩንም በመግለጽ የትግል ጥሪው የአጭር ጊዜ ኢላማ ቅንጅት ያስቀመጣቸው 8 ቅድመ ሁኔታዎች ኢህአዴግ እንዲቀበል ለማድረግ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሙሰሶዎች የሆኑ ተቋማት ህገ መንግስት በሚያዘው መሠረት በነጻነት እንዲዋቀሩ ለማድረግ ግፊት መፍጠር መሆኑን በመግለጽ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግም ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን የኢትዮጵያ ሬድዮ ሬድዮ ፋና እና ድምጽ ወያኔ ኤፍ ኤም 97.1 እና የመሣሰሉትን አለመስማት የማህበራዊ ማግለል እርምጃዎች የጉልበት ትብብርን በመንፈግ ቤት መዋል ህገወጥነትን በትብብር መከላከል ከጥቅምት 21 እስከ 23 በመዲናው የሚገኙ የአፍሪካ መሪዎች ለኢህአዴግ መንግስት እውቅና ከመስጠት እንዲገቱ ለማድረግ የሠላማዊ ሰልፍ መንግስት አመጽ ነው ይላቸዋል በሚል ማስማት ህዝባዊ ስብሰባ እና ሰላማዊ ሰልፍ መንግስት አመጽ ነው ይላቸዋል በሚል



Scanned by CamScanner

ሆኖም ሁኔታው እየከረረ እና ለመፍትሔ
ፍርሀት የሚተው አለመሆኑን ከሌሎች አርምጃዎች ጋር አብሮ የሚወሰድ መሆኑን በመግለጽ
እያስቸገረ ሲመጣ ከሌሎች አርምጃዎች ጋር አብሮ የሚወሰድ ማስረጃ ከላይ በቁጥር 29
ጥሪ ያቀረበበት ሰነድ ነው በቁጥር 30 የቀረበው የሰነድ ማስረጃ 1ኛ እና
ለታየው ጭማቂው ወይም ሰመረ ሲሆን በቁጥር 31 የጠቀሰው ማስረጃ 1ኛ እና
2ኛ ክሶችን ለማስረዳት የቀረበ ነው ይኸ ሰነድ ቅንጅት ጥቅምት 22 ቀን 1998
ዓ.ም. ያወጣው መግለጫ ነው በዚህ መግለጫ በአዲስ አበባ ከተማ በመርካቶ
ጉለሌ ፒያሳ አራት ኪሎ እና ልደታ አካባቢዎች በመንግስት እየተገፋ የሚቀሰቀስ
አመጽ መቀስቀሱን በመግለጽ መንግስት ትንኮሳውን እንዲያቆም በሌላ በኩል
ደግሞ ህዝቡ የመንግስትን አሸባሪነት አፈና እና ህገወጥ ተግባር እስከ አሁን
ካደረገው በላቀ ሁኔታ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ ማቅረቡን በተለይም ማንኛውም
ዜጋ ከመኖሪያው ሳይወጣ ከጥቅምት 22 ቀን 98 ዓ.ም. ከምሽት 3:30 እስከ
4:00 ሰዓት ድረስ የተለያዩ ድምጾችን ፊሽካ የእጅ ጡሩንባ ፉጨት ወዘተ
በማሰማት ተቃውሞውን እንዲያሰማ ጥሪ ማቅረቡን ከሰነዱ ለማየት ተችሎአል
በቁጥር 32-36 በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ የተጠቀሱት ሰላም እና
ስርአት ለውጥ የሚያመጣ የዲሞክራሲያዊ ምርጫ የህዝባችን ነው የሚል
የኢመማ መግለጫ የህዝብ ድምጽ ይከበር የሚል ከአዲስ አበባ መምህራን
ማህበር የወጣ መግለጫ ህገባዊ አንድነት በዘረኛ እና ጉጠኞች ሴራ አይፈታም
በሚል ከኢትዮጵያ ሲቪክ ማህበራት የጋራ መድረክ የተሰጠ መግለጫ
በተማሪዎቹ እና ሰብአዊ መብት እንዲከበር በጠየቁ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ
መንግስታዊ ሽብር ሰላም ወዳድ ሀይሎች ሁሉ ድርሻቸውን መወጣት
ይኖርባቸዋል በሚል ከኢትዮጵያ መምራን ማህበር ማዕከላዊ ጽ/ቤት የተሰጠ
መግለጫ እና የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር አጠቃላይ ስብሰባ በሚል በእጅ
የተጻፈ ቃለ ጉባኤ የሚሉት ሰነዶች በማስረጃ መግለጫ ላይ የሚታዩ ቢሆኑም
ሰነዶቹ ግን ማስረጃዎቹ ከፍ/ቤቱ ማስረጃዎቹ ዝርዝር ጋር ስላልተያያዙ መተቸት
አልተቻለም በቁጥር 37 የተጠቀሰው ሰነድ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን በማስረዳት የቀረበ
ሲሆን በዚህ ሰነድ 2ኛ ተከሳሽ አባይነህ ብርሀኑ የኔ ጽሁፍ ነው በማለት ከጽሁፉ
በስተመጨረሻ ፊርማውን ያኖረበት ሲሆን ይዘቱም ተማሪዎች እስኪበተኑ
የተወጠነ ሴራ በገዥው ፓርቲ ስላለ የትምህርት ማቆም አድማ ሰኞ ይደረጋል
በኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች በሙሉ የሚል ይዘት ያለው ነው በቁጥር 38
የተጠቀሰው ሰነድ 1ኛ እና 7ኛ ክሶችን ለማስረዳት እንደቀረበ የተገለፀ ሲሆን
በዚህ ሰነድ ሚስጥር በሚል መመሪያት ያለባቸው የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናት

Scanned by CamScanner

ስም ዝርዝር ለውይይት የቀረበ በማለት 1- የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ 2- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አዲሱ 3- ጄኔራል ሣሞራ ዩኑስ 4- ገነት ዘውዴ 5- በረከት ስምኦን 6- ተፈራ ዋልዋ ስም ዝርዝርን የያዘ ሰነድ ነው በቁጥር 39 የተጠቀሰው ሰነድ ሁሉንም ክሶች እንደሚያስረዱለት የገለፀ ሲሆን በዚህ ሰነድ አጀንዳ በሚል 1- አባሎቻችን እና ደጋፊዎቻችን ገጀራ ሽጉጥ ቦንብ እና የመሣሰሉት መሣሪያዎች ባገኙት መንገድ እንዲያሰባስቡ እና ለተከታታይ እርምጃ ተዘጋጅተው ባሉበት እንዲጠባበቁ በከፍተኛ ሚስጥር ለታማኝ አባሎቻችን መመሪያ ስለመስጠት 2- በከፍተኛ ሚስጥር ከኤርትራ መንግስት ግንኙነት በማድረግ ድጋፍ ማግኘት እና በወያኔ ባለስልጣናት እና የንግድ ድርጅቶች አስተማማኝ ጥቃት ስለሚፈፀምበት ሁኔታ 3- የከፍተኛ ባለስልጣን ጠባቂዎችን በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች የሚመለመሉበት ሁኔታ ማመቻቸት 4- በምስራቅ ጐጃም እና ሰሜን ሸዋ ያሉት ታጣቂ ቡድኖቻችን በሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ እና በማሙሸት አማረ ብቻ እንዲመሩ ማድረግ የሚል ይዘት ያለው ሰነድ ነው 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን ለማስረዳት የቀረበው በቁጥር 40 የተጠቀሰው ሰነድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር በ4/9/97 ዓ.ም. ለቅንጅት የጻፈው ደብዳቤ ነው በማለት የቀረበ ሲሆን ምርጫው በኢህአዴግ ህውሀት ቢጭበረበር ቅንጅት በሚወስደው ማንኛውም የትግል ስልት የግንባሩአባላት በሙሉ ከጐናችሁ ነን በማለት የተጻፉ ሲሆን በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ አቶ ገ/ክርስቶስ ለሚቀጥለው ስብሰባ ይነበብ እና ምስጋና መልስ ይጻፍ የሚል ጽሁፍ እና የማይነበብ ፊርማ ያለው ነው በቁጥር 41 የተጠቀሰው ማስረጃ 1ኛ 2ኛ እና 3ኛ ክሶችን ያስረዳል በማለት የቀረበ ሲሆን የደህንነት መረጃ ዴስክ የሚል ነው በቁጥር 42 የተጠቀሰው ሰነድ ለኦሮሞ ነጻነት ግንባር በማለት የተጻፈ ደብዳቤ የቅንጅት ክብ ማህተም እና የራስጌ ማህተም የያዘ ሲሆን በመጨረሻም ሀይሉ ሻወል ኢንጅነር የሚል ስም እና ፊርማ ይዞአል የጽሁፉ ይዘትም ጥቅምት 22 ቀን 1998 በአገሪቱ በሙሉ በሚደረገው ምድር አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመጽ የእናንተ አባላት እና ታጣቂዎች እዲሳተፉ ተገቢው ዝግጅት እንዲደረግ እናሳስባለን የሚል ነው በቁጥር 43 የቀረበው የሰነድ ማስረጃ በዶ/ር ነገደ ጎበዜ ሕገ መንግስት ምርጫና ዲሞክራሲ በሚል የተጻፈ መጽሀፍ ሲሆን በዚህ መጽሐፍ በርካታ የተለያዩ ርዕሶች የተንፀባረቁ ሲሆን ከክሱ ጋር አግባብነት ያለው ብቻ ተመልክተናል፡፡ በዚህ መጽሐፍ መቅድም ላይ የኢህአዲግ ስርዓት ውስጥ ምርጫ ሃደት ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ ያለው ሚና እና ተልዕኮ የሌሎች ህዝባዊና ሰላማዊ ትግሎች ተልዕኮ ዛሬ በአገራችን የተተከለውን እስታሊናዊ ህገ መንግስት ቀይረን ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርዓት ለማምጣት ነው ይህንን ካልን ለምን እና እንዴት ምርጫ በምርጫ እንደምንሳተፍ፡ ወይም በይኩት እንደምናደርግ ግልጽ

እና ሕዝባዊ አስተራረቢዎች ያገረሸል የዚህ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት መቀየር ጉዳይ አገራዊ የጋራ አጀንዳ ነው በሚል የሰፈረ ሲሆን የመፍትሔ ዝርዝር ውስጥም ሕገ መንግስቱ የኢህአዴግ ድርጅታዊ ፕሮግራም እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሊያከብሩት እና ሊገዙለት የሚገባቸው ሰነድ ባለመሆኑ በአገሪችን ለሰምና ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማምጣት የሚቻለው ይህንን ሕገ መንግስት አስወግዶ በሙሉ ሕዝባችን ፍቃድ አዲስ ሕገ መንግስት ማጽደቅ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው ለዚህ እውን መሆን አገር ወዳድ ሀይሎች ሁሉ የጋራ ትግል ማካሄድ አለባቸው የምርጫ ሂደት ይህን ህገ መንግስታዊ ስርዓት በሰላምና ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርዓት ለመተካት ለሚደረገው ሕዝባዊ ትግል የምንጠቀምበት ነው ተሳትፎአችን ከምርጫ ምርጫ የተሻለ ውጤት እያገኘን አንድ ቀን ወደፊት ዝናብ ዘንቦ ተባርቆ በ5ኛው ወይም በ6ኛው የምርጫ ዙር ቀንቶን ማሸነፍ አምጥተን በቀጥታ በወያኔ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ስር አገር የምናስተዳድርበት መንግስት እናቋቁማለን በሚል ተስፋ መሆን የለበትም ይህ አጉል እና ለሕዝባችን ትግል አደገኛ የሆነ ሕልም ነው። ዲሞክራቶች የሚያራምዱት በጣም ግልጽ የሆነ ሲሆን ይህውም በመጪውም ሆነ በማንኛውም በኢህአዴግ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ስር የሚካሄድ ምርጫ መሰረታዊ ተልዕኮ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት የሚደረገውን ትግል ለማገዝ ስለሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀናጀ ታአማኒነትና ቀጣይነት ያለው ሕዝባዊ ማዕበል ለመቀስቀስ እንጠቀምበት የሚል ሀይሎች እንዲሆኑና እነዚህ ሀይሎች የእነዚህ ሀይሎች አቋም የኢህአዴግን አገዛዝ በሰላማዊ ሕዝባዊ ተጋድሎ በማስወገድ የዲሞክራሲያዊ የሽግግር ዘመን እንከፍታለን የሚሉ እንዲሆኑ ሁለት አመት ተኩል ሲጠናቀቅ በሚችል የሽግግር ዘመን የምርጫ ህግ የፓርቲዎች ደንብ የምርጫው ስርዓት ዲሞክራሲያዊ ተደርጎ በተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት የሕገ መንግስት ጉባኤ እናስመርጣለን በሚል የሚንቀሳቀሱ ዲሞክራቶች ናቸው በማለት የተገለጸ ሲሆን ሕገ መንግስቱም ማለትም ጊሐሬው የኢህአዴግ ሕግ መንግስት የሚለውን ለማሻሻል ሳይሆን ጨርሶ ለመቀየር መታገል እንደሚያስፈልግ ይህንንም ለማድረግ በምርጫ እንቅስቃሴ ሰበያ ሕዝባዊ ማዕበል በማስነሳት ኢህአዴግን ከስልጣን ለማስወገድ መስራት እንዳለበት አልያም ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ በሮች በመዘጋታቸው ለዚህ አላማችን በስራ ማቆም አድማ፣ በመሬት እንቅጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፎች፣ በተለያዩ የሲቪል ዲሲ. ኦቢዲየንስ ታክቲኮች የታገዘ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ የሚያመጣ ኢህአዴግ እራሱንም ቢሆን ከላዩ የሚያደክም ሕዝባዊ ማዕበል የመቀስቀስ

እስትራቴጂ መከተል እንደሚያስፈልግ፣ በምርጫ ስንሳተፍ በዋነኛነት ትኩረታችን መሆን ያለበት በሂደቱ መሆን እንደሚገባው ይህም ማለት ወያኔ ኢህአዴግ ከዚህ ምርጫ በአሸናፊነት ወጣሁ ለማለት ከፈለገ ካለፉት ምርጫዎች ሁሉ ይበልጥ አይን ባወጣ ሁኔታ በገፍና በኢንዱስትሪ ደረጃ አጭበርብሮ በፖለቲካ ክስረት በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአለም አቀፍ ኮሚኒቲው ፊት ሙሉ በሙሉ መጋለጥን መርጦ ብቻ እንደሆነ መስራት እንደሚያስፈልግ ወያኔ ኢህአዲግ እዚህ ክስረት ደረጃ ባደረስነው ማግስት ምርጫው ተጭበርብሯል ውጤቱን አንቀበልም በሚል ተቃውሞአችንን አስመዝግበን ይህንን ምዕራፍ እስከሚቀጥለው 2002 ዓ.ም. ምርጫ ላለመዘጋት እና በሰርቢያ በጆርጂያ እና በሌሎች አገሮች እንደታየው ሕዝባዊ ትግሉ እርቃኑን ለቀረው የኢህአዲግ ምንም ፋታ ሳይሰጥ ስለሚቀጥልበት ሁኔታ ህዝባችንን ከወዲሁ በግልጽ ማዘጋጀት ይኖርብናል በማለት ከመጽሐፉ መገለፁን ለማየት ይቻላል ሌሎች በርካታ ኢ-ሕገመንግስታዊ ቅስቀሳዎች ከመጽሐፉ የሚታዩ ቢሆንም ባጭሩ በጣም በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን አይነት ይዘት ያላቸው ናቸው በተ.ቁ 44 የተጠቀሰው ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጪ የሚለው የአንዳርጋቸው ጽጌ መጽሐፍ ሲሆን በተ.ቁ 45 የተጠቀሰው የግንቦት 7ቱ ምርጫ መጭበርበር ያስነሳቸው ጥያቄዎች በሚል በዚሁ ፀሐፊ ማለትም አንዳርጋቸው ጽጌ መስከረም 1998 ዓ.ም. የተጻፈ 19 ገጽ ያለው ጽሁፍ ነው በዚህ ጽሁፍ ስለምርጫ 97 እና ስለመጭበርበሩ እና የመሳሰሉትን በሰፊው ከተጠቀሰ በኋላ ፓርላማ በመግባትና ባለመግባትም የተለያዩ አሳቦችን አንፀባርቋል በጽሁፉ ከተንፀባረቁት አሳቦች የአገራችን ህዝቦች ያገኙትን የዲሞክራሲ ምርት ከወያኔ ዘረፋ መከላከልና ወደተሻለ የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ የሚቻለው ወያኔን በሰላማዊ ሕዝባዊ እንቢተኝነት ትግል ማንበርከክ ሲቻል ብቻ እንደሆነ ፓርላማ አለመግባት ወያኔን ለማስገደድ መደረግ ላለበት የሰላማዊና ህዝባዊ እንቢተኝነት ትግሉ አንድ አካል ተደርጎ መታየት እንዳለበት፣ ፓርላማ አለመግባት በኩርፊያ ዙርያ ብቻ ታጥሮ ይቀራል የሚል እምነት እንደሌለው፣ ፓርላማ አለመግባት በወያኔ አምባገነን ባህሪ ላይ የተያዘ ግልጽነት ያለው አቋም መገለጫ ነው ብሎ እንደሚያምን በእንዲህ አይነት አምባገነን ሐይል ጋር የሚደረገው ትግል በዋነኛነት የህዝባዊ ኢንቢተኝነትና የአልገዛም ባይነት ትግል በማቀጣጠል እንደሆነ በማያሻማ ቋንቋ ያስቀምጣል ብሎ እንደሚያምን ወያኔ አንባገነን እስከሆነ ድረስ በእርሱ ፍርድ ቤት እና የምርጫ አስፈጻሚ አካላት በኩል ተሂዶ የተጭበረበረን ድምጽ ማስመለስ እንደማይቻል ፓርላማ አንገባም ማለት ብቻ ሳይሆን ከፓርላማ አለመግባት ውሳኔ ጋር በምናደርጋቸው ህዝባዊ ትግሎች አምባገነኑን የወያኔ መንግስት የህዝብን ድምጽ የሚያከብርበትን አስገዳጅ ሁኔታዎች



Scanned by CamScanner

መፍጠር ይቻላል። ፓርላማ አለመግባት በሰላማዊ ትግሉ የማይደገፍ ከሆነ ትርጉሙ ለዜሮ የቀረበ ይሆናል ሰላማዊ ህጋዊ በሆነ ህዝባዊ እምቢተኝነት ዲሞክራሲያዊና ህገ መንግስታዊ መብቶች መጠቀም ወያኔን የመሰሉ አምባገነን ቢቻል የህዝብን ፍላጎት እንዲያከብር ይህንን ለማድረግ ፍቃደኛ ካልሆነ በሀገራችንና በሌሎች ሀገሮች ህዝቦች ታሪክ እንዲታዩት አምባገነኖች በሙሉ ከምድራችን ላይ ጠራርጎ ማስወድ የሚቻልባቸው አብዛኛዎቹ ቁልፍ ሁኔታዎች የተሟሉ ናቸው የሚሉና የመሳሰሉት ይገኙበታል እንግዲህ የሰነድ ማስረጃው ይሄንን ይመስላል ቀጥሎ ያለው ጋዜጦች ናቸው ጋዜጦቹን በዛሬው እለት አንጀምርም ስለዚህ ጋዜጦች ምን እንደሚሉ ሌሎች ማስረጃዎች ምን እንደሚሉ ሰኞ ነው የምናነበው ይሄም ከሰዓት ልንቀጥል ነበር ግን ጠዋት እንዳልኩት በህመም ላይ ያሉ ዳኛ አሉ ስለዚህ ከሰዓት መቀጠል አንችልም ሰኞ ነው የምናነበው ሌሎቹን ስለዚህ ቀጠሮ ለሰኞ ሰጥተናል።

2ኛ ወንጀል ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 43246

መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አዲል አህመድ

ልዑል ገ/ማሪያም

መሐመድ አሚን ሳኒ

ከሣሽ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ ሽመልስ ከማል፣ ሚካኤል ተክሉ፣ አብርሃም ተጠምቀ ቀርበዋል፡፡

ተከሣሾች፡- እነ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል ባለፈው ችሎት የቀረቡት ሁሉም ተከሣሾች ቀርበዋል፡፡ ባለፈው ችሎት የቀረቡት ጠበቆችም ቀርበዋል፡፡

* መዝገቡ ያደረው የተጀመረውን ብይን ለመቀጠል ነው በዚሁ መሠረት ካቆምንበት እንቀጥላለን ማለት ነው፡፡
* በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ከተራ ቁጥር 46-70 ድረስ የተዘረዘሩት የተለያዩ ጋዜጦች ርዕስ አንቀጾቻቸው ሲሆኑ እነዚህም በማስረጃነት ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ እስከ 49ኛ ድረስ የተዘረዘሩት የአዲስ ዜና ጋዜጦች ማለትም ሦስተኛ ዓመት ቁጥር 149 ሐምሌ 12/97 ቁጥር 150 ሐምሌ 19/97 ቁጥር 151 ሐምሌ 26/97 ቁጥር 153 ነሐሴ 10/97 የወጡትን የሚመለከት ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ እነዚህን ማስረጃዎች አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዱልኛል በማለት ያቀረበ ሲሆን የጋዜጦቹ ዋና አዘጋጅ ወስንሰገድ ገ/ኪዳን ምክትል ዋና አዘጋጅ ስምረት ገ/ማሪያም አሳታሚ ደግሞ ፋሲል የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ነው የጋዜጦችም ይዘትም፤ "መረጃዎቹ በአፋጣኝ ለህዝቡ ይገለጽ" በሚል እርእስ አንቀጽ ሥር፤ የምርጫ ማጣራቱ ሂደቱ አደጋ ላይ መውደቁን፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ ድምፁን መዘረፉን፤ ቦርዱም የዚህ የዘረፋ ዋነኛ ተባባሪ እና አቀነባባሪ መሆኑን፤ የሕዝብ ተቀባይነትም ሊያጣ እንደሚገባ፤ ገዢው ፓርቲ አሁን ባለው የተዘረፈ ምርጫ ተማምኖ ስልጣን ለመያዝ ከደፈረ ሌባ መንግሥት መባሉ የማይቀር መሆኑን ፅዋል፡፡ በሌላ በኩል "ህፃኑ መንግሥት ሊቆነጠጥ ይገባል" በሚል እርእስ አንቀጽ ሥር፤ ባለፉት 14 ዓመታት እንደህፃን ሲያበላሽ የነበረው መንግሥት አሁን ዐሐይ ስትጠልቅበት ጥያቄያችሁን መልሰን ማለፍ፣ አለብን በሚል ምክንያት እየሰራ ያለው



Scanned by CamScanner

እኩይ ስራ በእስቸኳይ ካልተገታ የሚያደርሰው ጥፋት ወደር ላይኖረው እንደሚችል፤ የአዲስ አበባም ሆነ የሌሎች ክልሎች ህዝቦች ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ እየሰራ ያለውን አገር የማፍረስ እና ህዝብን የማበጣበጥ ስራ በንቃት ሊከታተሉት እንደሚገባ ገልፆ በሌላ እርእስ አንቀጽ ደግሞ ፓርቲዎች የመረጣቸውን ህዝብ ድምጽ አሰርቀው ወደፓርላማ ቢገቡ የሕዝብ አመኔታ ሙሉ በሙሉ እንደሚያጡ እና ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መቀለጃ ከመሆን እንደማያልፉ አሳስበዋል፡፡ "ለአንዳንድ የሚዲያ ሰዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ አባላት" በሚል እርእስ አንቀጽ ደግሞ የሲቪል ማሕበረሰቡ እና አንዳንድ የሚዲያ ሰዎች ምርጫው መጭበርበሩን እና ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ድምጽ ሰርቆ መንግሥት ለመመስረት መዘጋጀቱን እንደሚያውቁ፤ ምናልባት ተቃዋሚዎች ምርጫውን ማሸነፋቸውን እንደሚያውቁ፤ ይሄን እያወቁ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ግን ከመቶች ተቃዋሚዎችን መቶች እና ጫና አሳድረው የመንግሥት አጃቢ ሆነው ፓርላማ እንዲገቡ መወትወታቸውን፤ ህገ-ወጥ መንግሥት መደገፍ ህገ-ወጥ መሆኑን መርሳታቸውን፤ ገና አገር ልትበታተን ነው ደም ሊፈስ ነው በሚሉ ምክንያቶች መንግሥትን ከህዝብ በላይ አድርጎ የሚመለከት ሥርዓት እንዲፈጠር መተባበር ማንም መንግሥት ከእንግዲህ እንደፈለገ እየተነሳ በምርጫ ስም እያጭበረበረ በዲሞክራሲ ስም አምባገነን ሆኖ እንዲቀጥል መንገድ የሚከፍት መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ነው፡፡ በሌላ በኩል በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ከተራ ቁጥር 50-54 ድረስ የተዘረዘሩት የኢትኦጵ ጋዜጦቹ ርእሰ አንቀፆች ሲሆኑ በተለይ ቁጥር 501 ግንቦት 17/97፤ ቁጥር 509 ሐምሌ 13/97፤ ቁጥር 511 ሐምሌ 27/97፤ ቁጥር 513 ነሐሴ 11/97፤ ቁጥር 519 መስከረም 18/97 የወጡትን ጋዜጦች የሚመለከት ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ ማስረጃዎቹ አንደኛን ክስ ያስረዱልኛል በማለት ያቀረበው ሲሆን የጋዜጦቹ ዋና አዘጋጅ አንዱአለም አየለ፤ ምክትል ዋና አዘጋጅ ተስፋ ተገኝ፤ የጋዜጦቹ አሳታሚ ደግሞ ሲሳይ የሕትመትና ማስታወቂያ ድርጅት ነው፡፡ የጋዜጦቹ ይዘትም፤ "ተስፋ የራቀው ህዝብ ተስፋውን በነጠቁት አይገዛም" በሚል ርዕሰ አንቀጽ ሥር፤ በከተሞች በአጠቃላይ በዜሮ የተሸኘ ቡድን ዋና ባለሥልጣናት ጭምር በህዝብ ድምጽ ያጣ ሀይል የምርጫ ታዛቢዎች በሌሉበት ያሉትም በታሰሩበት ሁኔታ ውስጥ አሸናፊነት ቢያውጅ በፍፁም



Scanned by CamScanner

ተቀባይነት እንደማይኖረው፤ ፍርሀትን አሸቀንጥሮ የጣለው እና ድፍረትን የተላበሰ ህዝብ ድምጽ ሲሰረቅበት ሐቅ ሲዛባበት በቸልታ እንደማይመለከት፤ ተስፋ የማይታየው ህዝብ ተስፋውን ጭምር በነጠቁት በፍፁም እንደማይገዛ እና ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ በተለይ አቶ መለስ በመጨረሻው ሰዓት እራሳቸውን ከውርደት አገራቱንም ከአደጋ እንዲታደጉዋት ጥሪ ማቅረቡን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ "ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ተጨማሪ የጥፋት ጊዜ ሊሰጠው አይገባም" በሚል አርዕስ አንቀጽ ሥር የፌዴራሉ መንግሥት ስልጣን ካጣሁ አገሪቱ መፍረስ ይገባታል ብሎ በመደምደም ለአንዳንድ ክልሎች የመገንጠል ረቂቅ እያዘጋጀ ያለ ሀይል ተጨማሪ አምስት አመት ቢሰጠው ተጨማሪ የጥፋት አጀንዳዎችን የሚቀርጽበት እንጂ ስለዚች አገር ልማት እና ብልጽግና የሚጨነቅበት እንዳልሆነ ለመገመት ነብይ መሆን እንደማይጠይቅ፤ የዛሬው እኩይ ተግባር መርምሮ መጪውን መናገር እንደሚቻል፤ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ በህዝብ ድምጽ ከተሸኘ ደግሞ ያለማመንታት ቤተ-መንግሥቱ ለተረኛው እንዲለቅ ማስገደድ እንደሚገባ ተሸንፎ በስልጣን እቀጥላለሁ ካለ ሕዝብ መነሳቱ፤ ሰላም መታወኩ እንደማይቀር የተገለፀበት ነው፡፡ ሐምሌ 27/97 በወጣው ጋዜጣ "ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ለዲሞክራሲ ለአንድነትና ለህዝብ ሲል የህዝብን ድምጽ ያክብር" በሚል እርእስ አንቀጽ ሥር የተቃውሞ ሀይላት ምርጫውን ተጭበርብሮ ከቀጠለ የዩክሬን እና የጆርጂያ ህዝባዊ መዓበል የሚቀሰቅሱ ስለመሆናቸው መናገራቸውን፤ አቶ መለስ ከቤተ-መንግሥት ሆነው ህገ-ወጥ ነው ማለታቸውን፤ እውነታው የዩክሬንም ሆነ የጆርጂያ ህዝብ የአለም ድጋፍ ያገኘው ሆ ብሎ በመነሳቱ እና የተባበረ ድምፁን በአደባባይ በማሰማቱ እንጂ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ጎች እንደሚሉት በሌላ ምክንያት አለመሆኑን፤ ከእንግዲህ የኦሮሞ ሕዝብ በእነ ጃነዲን ሳዶ የአማራው ህዝብ በእነ ዮሴፍ ረታ የደቡብ ህዝብ በእነ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ወዘተ... ይገዛል የሚል መደምደሚያ ላይ መደረስ ህዝቡ ባርነት ይፈልጋል ብሎ መሳደብ እንደሆነ በመግለጽ ያትታል፡፡ ነሐሴ 11/97 በወጣው እርእስ አንቀስ ስር የህዝብ ድምጽ ተሰርቆ፤ ውሣኔው በጉልበት ተሽሮ፤ የጠመንጃ አገዛዝ በግልጽ በህዝቡ ላይ ተጭኖ፤ የቀድሞ ኢ.ህአዴጎች ስለየትኛው ሰላም እንደሚናገሩም ግልጽ አለመሆኑ፤ በሰላም እና መረጋጋት ስም ለአመታት በጉልበተኞች አገዛዝ ሥር ከመማቀቅ የሰላም እና የመረጋጋት [illegible] በጉድን ለህዝብ ድምጽ [illegible] ስልጣኑን እን[illegible] ማስገደድ [illegible] እና

031157 /016 Library Jimma University

Scanned by CamScanner

አቋራጭ መንገድ መሆኑን፤ የኢ..ሕ..አ.ዴ.ግ ተላላኪ የሆነው ምርጫ ቦርድ ሳይፈርስ ነፃ ምርጫ እንደማይኖር፤ የኢ..ሕ..አ.ዴ.ግ ካድሬዎች የበላይነት የተቋቋመው እና በዝርፊያ የከበሩ ሰዎች በአብዛኛው በተሰበሰቡበት ፍርድ ቤት ፍትህ እንደማይኖር በብሔራዊ የአንድነት መንግሥት እነዚህን ጠራርጎ እና አጽድቶ መንቀሳቀስ በእርግጥም ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት ያመጣል በማለት እርዕሰ-አንቀጹን ይደመድማል:: መስከረም 18/98 በወጣው ጋዜጣ "የደም ካሳውን ለመመለስ ስንት አመት መገዛት ይቀረናል" በሚል እርእሰ-አንቀጽ ሥር ኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ ምስክርነት ይዞ በአሸናፊ አለው ባይነት የሚለቀው ጩኸት ያንንም ተከትሎ የሚያሰማው ቀረርቶ ሰሚ እንደማይኖረው፤ የአለም አቀፍ ታዛቢዎች ምስክርነትም ሆነ በአካባቢው የተገኙ መረጃዎች የሚያረጋግጡት ኢ..ሕ.አ.ዴ.ግ የአደባባይ ሌብነት በመሆኑ በተሰረቀ ድምጽ ህዝብን መግዛት እንደማይቻል፤ በምርጫው ያሸነፉት የቅንጅት እና የህብረት በምርጫው ለተሸነፈው ኢ..ሕ..አ.ዴ.ግ ያቀረቡለት የብሔራዊ አንድነት መንግሥት አገሪቱን ከገባችበት ቀውስ የሚያወጣት በመሆኑ የተለያዩ አካላትን በመጥቀስ በብሔራዊ አንድነት መንግሥት ዘብ በመቆም አገራቸውን መታደግ እንደሚኖርባቸው ገልፀዋል:: በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 55 በማስረጃነት የቀረበው ሐምሌ 26 ቀን 1997 ዓ.ም የወጣው የአስኳል ጋዜጣ ርእስ-አንቀጽ ሲሆን ይሄ ማስረጃ ዐቃቤ ህግ አንደኛ የወንጀል ክስ እንደሚያስረዳለት ገልፀዋል:: የዚህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ወናክሰገድ ዘለቀ ምክትል ዋና አዘጋጅ ሰርካለም ፋሲል፤ የጋዜጣው አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ነው የጋዜጣው ይዘትም፤ "የተቃዋሚዎች ዋነኛ እና ብቸኛ አማራጭ" በሚል እርእሰ-አንቀጽ ሥር ድምጼን አላስነጥቅም እያለ ያለው ህዝቡ እንጂ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ብቻ አለመሆናቸውን፤ ከዚህ በፊት በፓርላማ የነበራቸውን መቀመጫ አስር ብቻ ነበረ አሁን ሁለት መቶ አግኝታችኋል ስለዚህ ይሄንን እያጣጣማችሁ አምስት አመት ጠብቁ የሚለው ምክር ፊር የሳተ ሆኖ ማግኘታቸውን፤ ስለዚህ አሁኑኑ ጥርስ ነክሶ የህዝብ ድምጽ እንዲከበር መታገል አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል:: በቀጣይነት የተዘረዘሩት የሚኒሊክ ጋዜጦች እርእስ - አንቀጾች ሲሆኑ ይሄውም ቁጥር 365 ሐምሌ 22/97፤ ቁጥር 358 ነሐሴ

6/97፣ ቁጥር 364 መስከረም 13/98 ዓ.ም በሚኒሊክ ጋዜጣ የወጡ እርእስ አንቀፆች ናቸው፡፡ ዐቃቤ ህግ ሐምሌ 22/97 እና መስከረም 13/98 ዓ.ም በወጡ ርእስ-አንቀጾች ላይ መግለጫ ያልሰጠበት ቢሆንም ነሐሴ 6/97 ዓ.ም በወጣው እርዕስ አንቀጽ ላይ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ ዐቃቤ ህግ ማስረጃው አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዳልኛል በማለት አስመዝግቧል፡፡ የሚኒሊክ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ዘላለም ገብሬ ምክትል ዋና አዘጋጅ ሰርካለም ፋሲል ስትሆን አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ነው፡፡ የጋዜጦቹ ርዕስ-አንቀሶች ይዘት አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው መዝግበነዋል፤ ሐምሌ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የወጣው ርዕስ-አንቀጽ ምናልባት ተቃዋሚዎች እንደሚሉት የምርጫ ቦርድ ውጤትን ባለመቀበል ወደ ቀጣይ ዲሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ ትግል ሲሄዱ እንደሚችሉ፤ ይሄ መብታቸው መሆኑን፤ የምርጫ ቦርድ ውጤትን ያለመቀበል የመብት ጉዳይ እንጂ የሥርዓት አልበኝነት ምግባር አለመሆኑን፤ ሲገልጽ ነሐሴ 6/97 ዓ.ም በወጣው ርእስ-አንቀጽ ደግሞ የምርጫ ቦርድ ውጤት የማያመጣው መሠረታዊ ለውጥ አለመኖሩን ህዝቡ በሰላማዊ እና ህጋዊ መንገድም መብቱን ለማስከበር ወደኋላ የሚል ህዝብ አለመሆኑን የምርጫ ቦርድ ይሄንን ሁኔታ መለወጥ የማይችል መሆኑን፤ ለጊዜው ግን ለኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አጉል ተስፋ ማስጨበጡን፤ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ የትም የማይደርስ መሆኑን ከገለፀ በኋላ መስከረም 13/98 በወጣው እርእስ-አንቀጽ ደግሞ የህዝብ ድምጽ ተቀምቶ በተስፋ መቁረጥ ስሜት ባለበት በዚህ ወቅት ቅንጅት እና ህብረት በጋራ ለማድረግ ያሰቡት ሰላማዊ ትግል የህዝቡን ስሜት እንደአዲስ ማነቃቃቱን፤ ይህ ጊዜ ህዝብ መብቱን ለማስከበር ወደኋላ የሚልበት ጊዜ አለመሆኑን ያስገነዘበ ጽሁፍ ነው፡፡ በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 59 እስከ 64 ድረስ ያሉት ማስረጃዎች የነፃነት ጋዜጣ ርእስ አንቀፆች የሚመለከት ሲሆን በተለይ ነፃነት ቁጥር 10 ሐምሌ 14/97 ዓ.ም፤ ቁጥር 11 ሐምሌ 21/97፣ ቁጥር 15 ነሐሴ 19/97፣ ቁጥር 17 ጳጉሜ 3/97፣ ቁጥር 18 መስከረም 5/98፣ ቁጥር 20 መስከረም 19/98 ዓ.ም የወጡትን እርዕስ አንቀፆች ይመለከታል፡፡ ዐቃቤ ህግ በእነዚህ የሰነዶች ማስረጃ ላይ መግለጫ ያቀረበ ሲሆን ማስረጃዎችም አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዱልኛል በማለት አስመዝግቧል፡፡ ከእነዚህ ጋዜጦች መረዳት እንደሚቻለው የጋዜጦቹ ዋና አዘጋጅ አብይ ግዛው ምክትል ዋና አዘጋጅ ደረጀ ሐብተወልድ አሳታሚው ደግሞ ዘካርያስ የህትመትና ማስታወቂያ ድርጅት ነው፡፡ የእርእስ



Scanned by CamScanner

እንቀፆቹም ይዘትም "ህዝቡ መብቱን ሊያስከብር ቢነሳ ተጠያቂው መንግሥት ይሆናል" በሚል እርስ አንቀጽ ሥር በአለም የታዩ አምባገነን መሪዎች ዋነኛ መጠንጀያ እና እራሳቸውን ከአደጋ የመጠበቅ አይነተኛ መሳሪያቸው ህገ መንግሥቱ እና አገራዊ ሉአላዊነት ሽፋን በማድረግ መሆኑን ህገ መንግሥትን የቀረፀው መንግሥት ሊያከብረውና ሊያስከብረው ካልቻለ ህዝቦችም ህገ-መንግሥት ይበጀናል ብለው ሊያስከብሩት ቆርጠው እስካልተነሱ ድረስ ህገ-መንግሥቱ መታፈርና መከበሩ ቀርቶ የመማሪያ ደብተር ላይ የተፃፈ ህገ-መንግሥታዊ ወይም የህግ ትምህርት ማስታወሻ ሆኖ እንደሚቀር ህዝቡን ሀሳቡን ያለገደብ በነፃ እንዲገልጽ ጥያቄውን እንደሚያቀርብ ጥያቄው መመለስ ያለበት ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ መሆኑን ይሄ ሳይሆን ቀርቶ ለሚነሳው ቀጣይ ጥያቄ ሁከት እና ብጥብጥን ተጠያቂው መልስ መስጠት ያልቻለው ክፍል መሆኑን ህዝብ ለጠየቀው መብቱ ምላሽ ሲያጣ መብቱን ለማስከበር ይነሳል ያኔም ተጠያቂው መንግሥት እንጂ ህዝብ ያለመሆኑን ህዝብ መብቱን ሊያስከብር ሲንቀሳቀስ ቀላል የማይባሉ ችግሮች እንደሚከሰቱ ያኔም ቢሆን ህዝቡ ተጠያቂ አለመሆኑን ገልፆ ሐምሌ 21/97 ዓ.ም ደግሞ "የምርጫ ውጤት ቀድሞ የተበላ እቁብ ነው" በሚል እርእስ አንቀጽ ሥር እኩይም እንበለው ሰይጣናዊ ገዢው ፓርቲ የራሱን አላማ አንግቦ እሱ በማስፈፀም ላይ እንደሚገኝ ምርጫው የተበላ እቁብ ያደረጉት በዋነኛነት ምርጫውን እንዲያስተባብሩ እድል የተሰጣቸው የቦርዱ ሰብሳቢ እና ኃላፊዎች መሆናቸውን፤ ስለዚህ የሕዝብ ድምጽ ለማስከበር በቁርጠኝነት መነሳት ማስፈለጉን ይሄንን ለነገ የማይባል አፋጣኝ እርምጃ ከሁሉም የፓርቲ አመራሮች እንደሚጠበቅ አስታውቋል በማስከተልም ነሐሴ 19/97 ዓ.ም በወጣው እርእሰ-አንቀጽ ህዝቦች በተጠናከረ ትግል የገዢውን ፓርቲ ከወንበሩ ለማንሳት እስካሁን ከከፈሉት የባሰ መስዋትነት መክፈል እንደሚጠበቅባቸው አገርን ከውድቀት ለመታደግ መንገዱ አልጋ በአልጋ አለመሆኑን እና ብዙ መስዋትነት የሚጠይቅ መሆኑን ህዝቦች ለዚህ መስዋትነት እራሳቸውን ማዘጋጀት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበው ጳጉሜ 3/97 ዓ.ም በወጣው እርዕስ አንቀጽ ደግሞ በአዲሱ አመት ህዝቦች በተሰናባቹ "አመት የተረከቡትን ከአንባገነኖች ጋር የመፋለም ትግል

Scanned by CamScanner

የሚገፉበትን እንጂ ተረጋግተው የነፃነት ፍሬ የሚያጣጥሙበት ሊሆን አለመታደላቸውን ገልፀዋል:: በተጨማሪ መስከረም 5/98 ዓ.ም በጠጣው እርእስ አንቀጽ ሥር የኢትዮጵያ ህዝብ በአቶ መለስ እና አስተዳደራቸው አምስት አመት ቀርቶ አምስት ወራት ለመኖር ትዕግሥት እና ፍላጎት የሌለው መሆኑን በአዲሱ አመት የኢትዮጵያ ህዝቦች የተባበረ ቅንጅ አንባገነኖች በአንባገነንነታቸው እንዳይኖሩ የሚደረግበት መላ የሚፈለግበት እንደሚሆን ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ በጠመንጃው ቢመካ ተቃዋሚዎች ደግሞ በህዝባቸው ሊመኩ እንደሚገባቸው ገልፆ መስከረም 19/98 ዓ.ም በወጣው እርእስ አንቀጽ ደግሞ ቦርዱ ሀላፊዎች ከገለልተኝነት ይልቅ ወገንተኝነታቸውን አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ እንደሚያራምዱ ገልፀዋል:: በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 65-69 ድረስ ያሉት የአባይ ጋዜጣን የሚመለከቱ ሲሆን በተለይ አባይ አንደኛ ዓመት ቁጥር 17 ግንቦት 13/97 ቁጥር 27 ሐምሌ 23/97 ቁጥር 31 ነሐሴ 1/97 ቁጥር 33 ጳጉሜ 5/97 ቁጥር 34 መስከረም 7/98 የወጡትን እርእስ አንቀፆች ይመለከታል ዐቃቤ ህግ ከአቀረበው የሰነድ ማስረጃ መግለጫ አንፃር ሲታይ ሐምሌ 23/97 የወጣው እርእሰ አንቀጽ 7ኛውን የወንጀል ክስ ጳጉሜ 5/97 የወጣውን እርእሰ አንቀጽ አንደኛውን እና አምስተኛውን የወንጀል ክስ እንደሚያስረዳለት ገልጾ ሌሎቹ እርእሰ አንቀፆች ደግሞ አንደኛውን የወንጀል ክስ እንደሚያስረዱለት ገልፀዋል:: ከጋዜጦቹ መረዳት የሚቻለው የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ መስፍን ተስፋዬ፣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ፍቃዱ እንድሪስ ሲሆን አሳታሚው ደግሞ አባይ አሳታሚ ነው የእርእስ አንቀፆችንም ይዘት አጠር ባለ መልክ እንደሚከተለው ቀርቧል:: ይሄውም ግንቦት 13/97 በወጣው እርእስ አንቀጽ ሥር በህዝብ ድምጽ የተፈተነው እና አደጋው ላይ የወደቀው ወንበር በጉልበት እና በመሳሪያ ጋጋታ ጠግኖ ለማቆየት የሚደረገው ሙከራ ውጤቱ የከፋ እንደሚሆን የህዝብ ድምጽ ተቆጥሮ ባላለቀበት ተቆጥሮ ያለቀውን የተቃዋሚዎቹን አሸናፊነት እያረጋገጠ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት ሩቅ በሆኑ የገጠር ወረዳዎች ፍፁም አፈናንን በማስፈን እና ህገ-ወጥነት በማንገስ ኮሮጆ እየሰረቁ እና እየገለበጡ አሸናፊነት ማወጅ እንደማይቻል የኢህአዴግ መንግሥት በከፍተኛ ድምጽ የሚመነጨውን ሥልጣን በአፈሙዝ መቀልበስ እንደሌለበት ገልፆ ሐምሌ 23/97 በወጣው እርእስ አንቀጽ ደግሞ ሁለቱ ዋነኛ የተቃውሞ ኃይላት ቅንጅት እና ሕብረት የምርጫውን ውጤት እንደማይቀበሉት የገለፁት ተጨባጭ ነጥቦችን ዘርዝረው የምርጫ ቦርድ ወገናዊነት



Scanned by CamScanner

የሚያረጋግጡ መረጃዎችን ተንተርሰው በመሆኑ ለጥያቄያቸው ምላሽ መስጠቱ ለዚህች አገር ዘላቂነት ያለው ሰላም ለማረጋገጥ ዋስትና መሆኑን የምርጫ ቦርድ ሀሳብ ተቃዋሚዎች ካልተስማማቸው ወደፍርድ ቤት እንዲሄዱ የሚለው ሀሳብ የዚህች አገር ችግር ለመፍታት መፍትሄ ሳይሆን ይበልጥ ችግሩን የሚያወሳስብ መሆኑን፤ በአገሪቱ የሚገኙት ሁለቱ ታላላቅ ብሔረሰቦች ማለትም ኦሮሞ እና አማራ ተገፍተው ሌሎች ከ80 የሚልቁ ብሔረሰቦች ተዘንግተው፤ የህዝብ ድምጽ ተረግጦ ነገሮች ባሉበት እንዲቀጥሉ ማራገብ ኃላፊነት የጎደለው እና ተጨባጩን የአገሪቱን ሁኔታ ያላገናዘበ ዘረኛ ቅስቀሳ መሆኑን በዚህች አገር የሁሉም ነገር አድራጊ ፈጣሪዎች የሕውሃት ሰዎች በሆኑበት የኦሮምያ በአማራ በደቡብ ወዘተ ... አሽከርነትን የፈቀዱ ህሊና ቢሶች ባለሥልጣን ተብለው እንዲቀጥሉ እንደማይፈቅድ ህዝቡ በምርጫ ድምፁን ማረጋጡን፤ በራሱ ቅሬታ በቀረበበት ምርጫ ቦርድ እና የኢሕአዴግ ሰዎች በበላይነት በሚመሩት የፍትህ ሥርዓት የህዝቡ ጥያቄ ምላሽ ስለማያገኝ ሁሉም ወገን የሚስማማበት ገለልተኛ አካል ጉዳዩን እንዲመረምር ለዚህች አገር የሚያስቡ እና ለህዝቧ የሚጨነቁ ሁሉ ሊገፉበት የሚገባ ተግባር መሆኑን ያሳስባል። "ነሐሴ 21/97 ዓ.ም ሰራዊቱ ለህገ-መንግሥቱ እንጂ ለገዢዎች ዘብ መቆም አይኖርበትም" በሚል እርእሰ-አንቀጽ ሥር አለማቀፍ ታዛቢዎች ጭምር የምርጫው ሂደት በችግር የተሞላ መሆኑን እንደገለፁ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆኑን እንዳረጋገጡ የምርጫ ቦርድ ውሣኔን መቀበል ከዚህ በኋላ ጨርሶ የሚታሰብ አለመሆኑን አለም አቀፍ ማህበረሰብ ጭምር ምርጫው ስለመጭበርበሩ ማረጋገጫ የሰጠበት የምርጫው ውጤት መቀበል በአገሪቱ ያለው የዲሞክራሲ ጅማሮ እንዲቀለበስ መተባበር እና በዚህች አገር የአፈና አገዛዝ እንዲነግስ መፍቀድ መሆኑን የድምጽ ቀበኞቹ ሰላማዊውን እና ህጋዊውን የስልጣን ሽግግር መንገድ ዘግተው አገሪቱን ወደሌላ ዙር የትርምስ እና የምስቅልቅል ሁኔታ እየገፏት በመሆኑ ሰራዊቱ አገሪቱን መታደግ እንደሚኖርበት ህገ-መንግሥቱን የማስከበር ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት ህገ-መንግሥቱን ለማስከበር ባይችል እንኳን ህገ-መንግሥቱ እንዲጠበቅ የህዝብ ድምጽ እንዲከበር በሰላማዊ እና በህጋዊ መንገድ በሚጠይቁ ዜጎች ላይ ብረቱን ባለማንሳት



Scanned by CamScanner

ለህግ የበላይነት አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅበት አስታውቆ ጳጉሜ 5/97 ዓ.ም በወጣው ጋዜጣ "ከቃሊቲ ኑሮ ይሻላል የብሔራዊ አንድነት መንግሥት" በሚል እርእስ አንቀጽ ሥር ደግሞ ድምፁን የተነጠቀው ህዝብ በብረት የማይቆም ይልቁንም ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ቁጥጥር ውጪ የመሄድ እድሉም የሰፋ መሆኑ በግልጽ እየታየ መምጣቱን ኢሕአዴግ ወደደም ጠላም አመነም አላመነም ቤተመንግሥት ያሉ ተጨምረው የአብዛኛው ሁራዊት ልብ ጭምር መሸፈቱን በብረት መመከት ብረቱ በወሳኝ ሰዓት ወደእነማን እንደሚዞር አለማስተዋል መሆኑን ህብረት እና ቅንጅት ማጥቃት የህዝብን ቁጣ የሚያበረታታ እና የሚፈሩትን የጆርጂያና የዩክሬን ህዝባዊ አመጽ እንደሚያፋጥን የኢህአዴግ ቡድን በተለይ አቶ መለስ እና አቶ በረከት ሁሉም እንደ ክ/ል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም እንደማይቀናው አምነው ከቃሊቲ ኑሮ ይሻላል የብሔራዊ አንድነት መንግሥት መባሉን ጋዜጣው ያስረዳል። በመጨረሻም መስከረም 7/98 ዓ.ም በወጣው ጋዜጣ "ኢህአዴግ ሁሉም ፈርዶበታል አባላቱ በቃ ሊሉት ይገባል" በሚል እርስ-አንቀጽ ሥር ከድምጽ መስጠት በኋላ ያለው ሂደት ግደፈቶች የበዙበት ማጭበርበር በስፋት የተስተዋለበት መሆኑ በአደባባይ መረጋገጡን የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች የሆኑ የካርተር ማዕከል ይሄንኑ በማረጋገጥ ሪፖርታቸውን ይፋ ማድረጋቸውን የተሸነፈ ቡድን ከአሸናፊዎች የቀረበለትን የአንድነት መንግሥት እንዲቀበል ግፊት ከውስጥም ማስፈለጉን በመግለጽ እርእሰ አንቀጹን ያጠቃልላል። በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 70 ላይ የተገለፀው ጋዜጣ ሀዳር ቅጽ 1 ቁጥር 26 ጳጉሜ 3/97 የወጣው እርእስ አንቀጽ ሲሆን ዐቃቤ ህግ በዚህ ማስረጃ ላይ በሰጠው መግለጫ ማስረጃ አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበው መረጃ ነው። ከጋዜጣውም መረዳት እንደሚቻለው የሀዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደ ሲሆን ምክትል ዋና አዘጋጅ ደግሞ ፊለቀ ጥበቡ ነው አሳታሚው ደግሞ አረጋዊ የህትመት እና ማስታወቂያ የሚባል ድርጅት ነው በዚህ ጋዜጣ "ህገ-መንግሥቱን በኃይል እየናደ ያለው ማን ነውን?" በሚል እርእስ አንቀጽ ሥር የህዝቡ ዲሞክራሲያዊ መብት መረገጡን ምርጫ ቢካሄድም ውጤቱ መጭበርበሩን ህዝቡም በየእለቱ የመንግሥት ፍርፋሪ በሚጣልላቸው ሚዲያዎች ክብሩን የሚያዋርድ መብቱን የሚጋፋ ዘለፋዎች እየወረደበት መሆኑን በአዲሱ ዓመት አንዱ ለነፃነት ታጋይ ሌላው አፋኝ መሆን እንደሌለበት መቀራረብ እና መደማመጥ ማስፈለጉን ህዝቡ እርስ በርሱ ይበጣበጣል



Scanned by CamScanner

የሚለው እርካሽ አጀንዳ ጠደግን አድርጎ የዘመናት ትስስር እውነታን ማስናገድ ግድ እንደሚል የተገለፀበት እርስ-አንቀጽ ነው:: ከዚህ በመቀጠል በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ከተራ ቁጥር 71/85 ድረስ የተዘረዘሩት ማስረጃዎች በተለያዩ ጋዜጦች የተደረጉ ቃለ-ምልልሶች ሲሆን በቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው መዝግበነዋል:: በሰነድ ማስረጃ ተራ ቁጥር 71 ላይ የተገለፀው ግንቦት 18/97 ዓ.ም አንደኛው ተከሣሽ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ለነፃነት ጋዜጣ የሰጠው ቃለ-ምልልስ ሲሆን ዐቃቤ ህግ በመግለጫው ላይ እንደገለፀው ይሄ ቃለ-ምልልስ 1ኛውን እና 2ኛውን የወንጀል ክሶች ያስዳልናል በማለት ገልፀዋል ጋዜጣውንም ስንመረምረው የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ አብይ ግዛው ሲሆን ምክትል ዋና አዘጋጅ ደግሞ ደረጀ ሐብተወልድ ነው አሳታሚ ደግሞ ዘካርያስ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት መሆኑን መረዳት ይቻላል:: የቃለ-ምልልሱ ይዘትም አንደኛ ተከሣሽ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል ከሌሎች ባልደረቦች ጋር ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠበት ወቅት በአጃንስ ፍራንስ ፐሬስ ለቀረበለት ጥያቄ እንጠቅሰዋለን "በመግለጫችሁ ላይ ምርጫ ቦርድ ላቀረበላችሁ አቤቱታ ምላሽ ካልሰጣችሁ እርምጃ እንደምትወስዱ እና ለዚህ እርምጃ ህዝብ በተጠንቀቅ እንደሚጠብቅ ጥሪ አቅርባችኋል:: እርምጃውም ደግሞ ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል ነው ብላችኋል ይሄንን ያህል በመንግሥት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ ምን አይነት ሰላማዊ እርምጃ ለመውሰድ ነው ያሰባችሁት" በማለት ለቀረበው ጥያቄ 1ኛ ተከሣሽ ሲመልስ እሱ እንግዲህ የስራ ማቆምም አድማም ሊሆን እንደሚችል ህዝብ ከቤቱ እንዳይወጣ ጥሪ በማቅረብ ሊሆን እንደሚችል ሌላም መሰል እርምጃዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ እርምጃዎቹ የሚወሰዱት ለምርጫ ቦርድ በተፃፈ አቤቱታ መሠረት ተገቢውን ምላሽ ካላገኙ የሚታዩ መሆኑን የሚገልጽ ነው በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 72 ላይ የሚገኘው ግንቦት 19/97 ዓ.ም አቶ አባይነህ ብርሃኑ በሚኒሊክ ጋዜጣ የሰጠው ቃለ-ምልልስ ሲሆን ዐቃቤ ህግ ይሄንን ማስረጃ ያቀረበው 1ኛው፣ 2ኛው እና 3ኛው የወንጀል ክሶች መፈፀማቸውን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበው መረጃ ነው ጋዜጣው ሲመረመር ዋና አዘጋጅ ዘላለም ገብሬ ምክትል ዋና አዘጋጅ ሰርካለም ፋሲል ስትሆን አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት መሆኑን ከጋዜጣው

መረዳት ይቻላል። የቃለ ምልልሱም ይዘትም አጠር ባለመልኩ እንደሚከተለው መዘግበነዋል። ቅንጅቱ በምሥራቅ ጐጃም ብቻ በ17 የምርጫ ጣቢያዎች ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ለቦርዱ ጥያቄ አቅርቦ መልስ ባልተገኘበት ሁኔታ ኢህአዴግ እንዴት አሸንፌአለሁ ነው የሚለው በማለት ለቀረበለት ጥያቄ አቶ አባይነህ ሲመልስ እኛ አሸንፈናል ብንል ነው የሚያምርብን ኢህአዴግ ግን ዘረፋ ነው ያካሄደው ማለቱን እንግዲህ እንዲህ አይነቱ ተግባር ሲፈፀም የምርጫ ቦርድ ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ አልነበረም ወይ ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ አቶ አባይነህ ሲመልስ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ምርጫ ለማጭበርበር ይረዳው ዘንድ በቂ የድምጽ መስጫ ኮሮጆ እንደነበረው የድምጽ መስጫ ወረቀትም እንደነበረው እነዚህን ያለ ምርጫ ቦርድ ትብብር ከየትም ሊያመጣ እንደማይችልና ምርጫ ቦርድም የገዢው ፓርቲ ወገን መሆኑን ገልጿል ከእዚሁ ጋር ተያይዞ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም እያላችሁ በሌላ በኩል ደግሞ አቤቱታችሁን ለምርጫ ቦርድ እያቀረባችሁ ምርጫ ቦርድ የሚሰጠውን ውሣኔ ለመቀበል አይቸግራችሁም ወይ ተብሎ ለተጠየቀው አቶ አባይነህ ሲመልስ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉን በእነዚህ እውነተኛ ማስረጃዎች ከወሰነ ሰላማዊ ስልጣን ሽግግር እንደሚደረግ የማይወስን ከሆነ ግን የሕዝብን ተቃውሞ የሚያስነሳና የግድ በሰላማዊ ትግል ግፊት ይህ ስልጣን መደምደም እንደማይቀር በሌላ በኩል ኢህአዴግ አሸንፌያለሁ እያለ ነው ስልጣን ለቅንጅቱ ካልሰጠ ሰላም ሊያደፈርስ የሚችል ነገር ይከሰታል ብለው ያስባሉ ወይ ተብሎ ለተጠየቀው ሲመልስ የሕዝብ ድምጽ የማይከበር ከሆነ የሚያስፈልገውን የሰላማዊ ትግል አሚጠን ጨርሰን የሕዝብ ጫና ያስፈልጋል በምንልቧት ጊዜ አብረን የምንነሳበት ሁኔታ አመራር እንደሚሰጥና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ምን ተስፋ ወደፊት ይኖራል ለተባለው ጥያቄ አቶ አባይነህ ሲመልስ ይህ መንግሥት ወይ በሰላም ወይም በህዝብ ግፊት ስልጣኑን እንደሚለቅ ገልፀዋል ሌላው በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 73 ላይ የተገለፀው ግንቦት 20/97 ዓ.ም ዶክተር በፍቃዱ ደግፌ በአባይ ጋዜጣ የሰጠው ቃለምልልስ ሲሆን ዐቃቤ ህግ ባቀረበው መግለጫ 86ኛ እና 87ተኛ ተከሣሾች በመተባበር ታትሞ እንዲሰራጭ ባደረጉት ጽሁፍ አንደኛውንና ሁለተኛው የወንጀል ክሶችን የተመለከቱትን የወል የወንጀል ድርጊት አላማውን ተቀብለው በመተግበር በክሱ ላይ የተመለከቱትን ተከሣሾች ፈጽመውታል ያለውን በዝርዝር አቅርቧል። ጋዜጣውን እንደመረመርነው መስፍን ተስፋዬ



Scanned by CamScanner

የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ሲሆን ፍቃዱ እንድሪስ ደግሞ ምክትል ዋና አዘጋጅ አሳታሚ ደግሞ አባይ አሳታሚ በመባል ተመዝግቧል። በዚህ ጋዜጣ በተደረገው ቃለምልልስ የምርጫ ቦርድ ውሣኔ ትክክል ካልሆነ ወደሕዝብ እንደምትሄዱ ገልፃችኋል ህዝቡ ምን እንዲያደርግ ነው የምትፈልጉት ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ዶ/ር በፍቃዱ በሰጠው ምላሽ ህዝቡ የመረጠውን እንደሚያውቅ ችግሩ የሚመጣው እሱ ያልመረጠውን መርጠሀል ሲባል መሆኑን ህዝቡ መብቱን ለማስከበር በመረጣቸው ሰዎች ብቻ ለመመራት እንደሚፈልግ ከእዚህ ውጪ የሚጫኑትን እንደማይቀበል ከዚህም በፊት መናገሩና አሁንም እየተናገረ መሆኑን እዚህ ሀገር ምርጫውን አስመልክቶ ችግር ብጥብጥ ቢነሳ ደም ቢፈስ ኃላፊነቱን የሚወስደው ምርጫ ቦርድ መሆኑን ከዚህም ጋር ተያይዞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተቃዋሚዎች ብጥብጥ ሊያስነሱ ነው ብለው ይከሷቸዋል ይህንን እንዴት ያዩታል ተብሎ ለተጠየቁት ጥያቄ ዶክተር በፍቃዱ ሲመልስ ብጥብጥ የማስነሳት ፍላጐትም ሆነ አቅም እንደሌላቸው ተፋላሚዎች ተቃዋሚዎች ሳይሆኑ ህዝብ እንደሆነ ብጥብጥ ሊመጣ የሚችለው አንደኛ ህዝብ ያልመረጠውን ምርጫ ቦርድ መርጣችኋል ብሎ ህጋዊ ሽፋን ከሰጠው ህዝቡ እኔ አልመረጥኩም ብሎ ከሚነሳ አምባጓሮ መሆኑን ሁለተኛው ደግሞ ኢህአዴግ ይህንን የተሳሳተ ውሣኔ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞክር መሆኑንና ኢህአዴግ እዚህ አገር ውስጥ ብጥብጥ እንዳይነሳ ከፈለገ ለህዝቡ ፍላጐት ተገዢ መሆን እንዳለበት ይህ ሳይሆን ቀርቶ በጉልበት ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያደርገው ጥረት ተከትሎ ብጥብጥ ቢነሳ ኃላፊነቱን በሌሎች ለማላከክ ምክንያት መደርደር እንደማያዋጣው ያስገነዘበበት ይገኝበታል። በማስከተልም በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 74 ሥር የተዘረዘረው ሲሆን ይኸውም ግንቦት 26/97 ዓ.ም ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ከሚኒሊክ ጋዜጣ ጋር ያደረገው ቃለ-ምልልስ ነው ይህንን መረጃ በተመለከተ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው መግለጫ 1ኛ እና 2ኛ የወንጀል ክሶች ለማስረዳት የቀረበው ሲሆን የ77ተኛ ተከሣሽ ንብረት በሆነው በ76ተኛ ተከሣሽ ሰርካለም ጋዜጣ አሳታሚ ሥር የሚወጣውና በ79ኛ እና በ80ኛ ተከሣሽ አዘጋጅነት የ4ኛው ተከሣሽ ቃለ-ምልልስ ሲሆን የወንጀል ድርጊት አላማን ተቀብለው አትመው ማውጣታቸውን ያስረዳልኛል

Scanned by CamScanner

በማለት ያቀረበው መረጃ ነው። የዚህ የሚኒሊክ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ምክትል ዋና አዘጋጅና አሳታሚ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው በመሆኑ ደግሞ መሣፍ አስፈላጊ ባለመሆኑ አልፈነዋል። የቃለ ምልልሱን አጭር ይዘት ስንመረምረው ገዢው ፓርቲ በምርጫው አሸነፈ የሚል ነገር ከቀጠለ ምን ታደርጋላችሁ ተብሎ ለተጠየቀው ኢንጂነር ግዛቸው በሰጠው ምላሽ ገዢው ፓርቲ አሸንፏል የሚባል ውጤት ሊኖር እንደማይችል የህዝብ ድምጽ ካልተቀማ በስተቀር በምንም አይነት ገዢው ፓርቲ የሚያሸንፍበት ሁኔታ አለመኖሩን የሕዝብ ተቀምቶ ምርጫ በርድም ተስማምቶ የሚገልጽ ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ድምፁን የሚያስከብርበት የተለያዩ ሰላማዊና ህጋዊ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ሰላማዊና ህጋዊ እርምጃ የሚባለውም እንደ ሰላማዊ ሰልፍ ስራ ማቆም ሰዎች ቤታቸው ተቀምጠው ተቃውሟቸውን የሚገልፁበት ማለት እንደሆነ የሕዝብ ድምጽ የሚከበርበትን ማንኛውም ሰላማዊ ህጋዊ ትግል ቅንጅት እንደሚያካሄድ ለህዝቡም አመራር እንደሚሰጥ የተገለፀበት ነው። በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 75 ሥር ሰኔ 1/97 አቶ አባይነህ ብርሃኑ በጦማር ጋዜጣ የሰጠው ቃለ-ምልልስ ሲሆን ዐቃቤ ህግ በአቀረበው መግለጫ ይህ ማስረጃ አንደኛውን እና ሁለተኛውን የወንጀል ክሶች ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበው ሲሆን በጋዜጣው ውስጥ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር እንዲደረግ እንፈልጋለን በሚል እርእስ ሥር በተደረገው ቃለ-ምልልስ መንግሥት ባወጣው መግለጫ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አነሳስተሀል ተብሏል ምን አድርገህ ነው ለተባለው ጥያቄ ተከሣሹ ምላሽ ሲሰጥ በመኢአድ ጽ/ቤት ውስጥ የድርጅቱ አባል ወጣቶች ለስብሰባ እንደነበሩና ቁጥራቸውም ከ500 መቶ በላይ መሆናቸውን ስብሰባው በሚካሄድበት ወቅት መጨረሻው አካባቢ ከዩኒቨርስቲ በርከት ያሉ ወጣቶች መምጣታቸውንና ከማግስቱ ጀምሮ ትምህርት ለማቆም ወስነናል ማለታቸውን ተከሣሹ የትምህርት ማቆም አድማ ውሣኔያቸው መቀበል እንደማይችልና አካሄዱ ሰላማዊ ትግል እስከሆነ ድረስ ማንም ግጭት ውስጥ የማያስገባ ስለሆነ ከጊዜው ጋር ታይቶ ምን መደረግ እንዳለበት ተወስኖ ይደርሳችኋል ማለቱን ከዚህ በተጨማሪ ምርጫ ቦርድ የመንግሥት አገልጋይ እንጂ ነፃ አለመሆኑን ገልጿል። በሌላ በኩል ተከሣሽ በድሩ አደም ሐምሌ 14/97 በሀዳር ጋዜጣ የሰጠው ጋዜጣ በማስረጃነት የቀረበ ሲሆን በዚህ ጋዜጣና በቀጣይነት የሚቀርቡት የሀዳር ጋዜጦች ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደ ምክትል ዋና አዘጋጅ ፈለቀ ጥበቡ አሳታሚ ደግሞ አረጋዊ የህትመትና ማስታወቂያ



Scanned by CamScanner

ድርጅት ነው። የሐምሌ 14/97 ቃለ-ምልልስ በተመለከተ ዐቃቤ ህግ መግለጫ ያልሰጠበት በሆንም ለተከሣሽ በድሩ አደም ሚያዚያ 30/97 በመስቀል አደባባይ ተገኝቶ ያሰማው መፈክር በተመለከተ ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት ምን እንደነበር ተጠይቶ በሰጠው ምላሽ ኢህአዴግ ንግግሩን በተንኮል ሽርቦ እርስ-በርስ ለማጋጨት ለማከፋፈል የሚጠቀምበት እንዳልመሰለውና ቃል-በቃል ያለውም የዛሬ ሳምንት አንድ በፈጣሪ ሁለት በእናንተ ጡንቻ ኢሕአዴግ ወደነበረበት ይመለሳል በማለቱን ይህም ማለት ከጉዳና የመጣ ወደጉዳና ከሕዝብ የመጣ ወደሕዝብ ማለት ነው ብሎ መልስ የሰጠበት ይገኝበታል ሌላው በሀዳር ጋዜጣ ነሐሴ 12/97 የወጣው የሻለቃ መላኩ አድማሱ ቃለ-ምልልስ ሲሆን ዐቃቤ ህግ በዚህ መረጃ ላይ መግለጫ አላቀረበበትም ለሻለቃ መላኩ ኢህአዴግ በትክክል አሸንፏል የሚል እምነት አላችሁ ወይ ተብሎ ለተጠየቀው ሲመልስ ኢህአዴግ በሥልጣን የመቆየት ተስፋ እንደሌለው ይህ ፍፁም የማይታሰብ እንደሆነ ህዝቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንደመረጠ ስለሚያውቅና ያለተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሳትፎ ብቻውን የመሰረተው መንግሥት ሕዝቡ በፍፁም እንደማይቀበለው ህዝቡ አንድ ጊዜ ቆርጦ መጓዝ ከጀመረ ወደኋላ ሊመለስ እንደማይችል ገልፀዋል ሰኔ 23/97 የዶክተር ታዬ ወ/ሰማያት ቃለ-ምልልስ የሀዳር ጋዜጣ ይዞ የወጣ ሲሆን የዐቃቤ ህግ ይህ ማስረጃ አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዳልኛል በማለት አስመዝግቧል። ቃለ-ምልልሱም ይዘትም የሲቪል ማህበረሰብ ወቅታዊ ጥያቄ የህዝብ ድምጽ ይከበር መሆኑን የምርጫው ሂደት ከጅንሱ ጀምሮ ስህተት ያለበት መሆኑን በሁለቱም ወገኖች በኩል በንፁህ ልብ ላይ የተመሰረተ ፍላጎት አለመኖሩን በውሸት ላይ የተመሰረተ አስመሳይ ፓርላማ ለመፍጠር አስመሳይ ተወካዮችም ለመምረጥ የተደረገ ስለሆነ ውድቀቱ ከዚህ ሂደት ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልፀዋል በሰነድ ማስረጃ ተራ ቁጥር 79 ሥር የተጠቀሰው ነሐሴ 10 ቀን 1997 ዓ.ም የወጣው የአስኳል ጋዜጣ ሲሆን ዐቃቤ ህግ ማስረጃ አንደኛ ክስ ያስረዳልኛል በማለት መዝግቧል የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ወናስሰገድ ዘለቀ ምክትል ዋና አዘጋጅ ሰርካለም ፋሲል አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ነው በዚህ ጋዜጣ አንደኛው ተከሣሽ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ወደፊት የምታዩት ነገር



Scanned by CamScanner

ምንድን ነው? ተብሎ በተጠየቀው በሰጠው ምላሽ የሚታየኝ አንድ መንገድ ብቻ ነው ይኸውም ህዝብና መሣሪያ የሚፋጠጥበት ቀን ቀርቧል ይሄ ምርጫ እንደገና እንዲካሄድ ጊዜያዊ መንግሥት ተመስርቶ አብረን እንስራ ብለናል መስራት አለብን የሚል ነው:: በማስተከተልም ዐቃቤ ህግ ሐምሌ 22 ቀን እና ጳጉሜ 4 ቀን 1997 ዓ.ም በወጡት የሚኒሊክ ጋዜጦች አንደኛው ተከሣሽ ያደረገው ቃለ-ምልልስ በማስረጃነት ያቀረበ ሲሆን የእነዚህ ጋዜጦች ዋና አዘጋጅ ዘላለም ገብሬ ምክትል ዋና አዘጋጅ ሰርካለም ፋሲል አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ነው የሐምሌ 22/97 ጋዜጣን በተመለከተ ዐቃቤ ህግ መግለጫ አልሰጠበትም የጋዜጣው ይዘትም ከአንደኛው ተከሣሽ በተደረገው ቃለ-ምልልስ መጨረሻ ላይ የምታስተላልፈው መልዕክት አለ ወይ ተብሎ በተጠየቀው በሰጠው ምላሽ ህዝቡ መንግሥት ስልችቶናል ፈጠን በሉ እንዳላቸው በትዕግሥት ሁሉን ካስጨረሱ በኋላ ከህዝቡ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንደሚሰሩና የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ እንደማያስነጥቁ ሁሉም እንዲያውቀው እንደሚፈልጉ የተገለፀበት ማስረጃ ነው ጳጉሜ 4 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው ጋዜጣ አንደኛው ተከሣሽ ስለህዝብ ትግል አካሄድ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ ትግሉ መካሄድ ያለበት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ ለአዲስ አበባ ሕዝብ ብቻ አለመሆኑን የአዲስ አበባ ነዋሪ የክልሎች ድምጽ ይከበር ብሎ መጠየቁንና ኢትዮጵያ በሙሉ ነፃ መውጣት አለበት ማለቱን ከዚሁ ጋር ቡተያያዘ መልኩ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ግጭት ቢነሳ የሰኔ አንድ እልቂት ሊደገም ይችላል ብለህ ትገምታለህ ወይ ተብሎ ለተጠየቀው ሲመልስ ሊኖር እንደሚችል ያለመስዋትነት ነፃነት እንደማይገኝ ዘላለም ሥልጣን ላይ እንቀመጣለን ብለው የመጡ ሰዎች ቀውጢ ቀን ሲመጣ ያላቸው መሣሪያ ብቻ ስለሆነ መተኮሳቸው እንደማይቀር በጥይት ሲያስፈራሩ በየጉሬው እየገባ የሚደበቅ ሕዝብ አለመኖሩን ያ ጊዜ ማለፉን በመግለጽ ቃለ-ምልልሱን ሰጥተዋል:: ዶክተር ያቆብ አለመኖሩን ያ ጊዜ ማለፉን በመግለጽ ቃለ-ምልልሱን ሰጥተዋል:: ዶክተር ያቆብ መስከረም 19/98 ዓ.ም በወጣው ጦቢያ ጋዜጣ ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጓል በማለት ዐቃቤ ህግ በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር የገለፀ ቢሆንም የጋዜጣው ይዘት ስንመረምረው ቃለ-ምልልሱን ያካሄደው ዶክተር ያቆብ ሳይሆን አንተነህ ሙሉጌታ ነው:: አንተነህ ሙሉጌታ በሰጠው ቃለ-ምልልስ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እንጂ ፍቃድ እንደማያስፈልግ በአሁኑ ሰዓት ነፃ ፍርድ ቤት አለመኖሩን የደስሙላ ፓርላማ ፓርላማው በጠቅላይ ሚኒስተሩ ትዕዛዝ ውጪ የማይወጣ

መሆኑን ገልፀዋል:: ሐምሌ 17/97 በወጣው ዘሾይስ በተባለው ጋዜጣ ተከሣሽ ዶክተር ታዬ ወ/ሰማያት ባደረገው ቃለ-ምልልስ በትጥቅ ትግልና በሰላማዊ ትግል ጉራህ የተሰለፉ የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ መረጋጋት ምን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ? ተብሎ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ ስልጣን ላይ ያለውንና ተቃዋሚዎችን ጨምሮ በሰላማዊ መንገድ የማይንቀሳቀሱትን ስንመለከት በሰላማዊ መንገድ ከሄዱ በሰላማዊ መንገድ ድምጽ ሰጥቶ የተፈለገውን መምረጥ ይቻላል ተብሎ ህዝቡ ድምፁን ሰጥቶ የተሰጠው ምላሽ በወኪሉ በኩል ችግሩን መፍታት ሳይሆን ጥፋት መሆኑን ይህ መንግሥት ሌላ ቋንቋ ስለማይገባው ታግሎ ማሸነፍ ነው የሚሉ እንዳሉም አሁን እንደሚታየው ይህ አባባል በሚደነቅ ሁኔታ እየታየ መሆኑን ገልፀዋል:: ይኸው ተከሣሽ ነሐሴ አንድ ቀን 1999 ዓ.ም በወጣው ዘሾይስ ጋዜጣ በመጨረሻ ምን መልዕክት አለህ? ተብሎ ሲጠየቅ ተከሣሹ የሰጠው ምላሽ ምርጫው ወያኔ ለራሱ ብሎ የፈጠረው አጀንዳ መሆኑን እውነተኛ ምርጫ በወያኔ እንደማይሰራ ህዝቡ እንደሚያውቀው ህዝቡ በዚህ ሁኔታ ዘላለም መዝለቅ እንደሌለበትና ተስፋ ሳይቆርጥ ትግሉን መቀጠል እንዳለበት በተጨማሪ ህዝቡ በአለበት የፍትህ ተቋማትን ነፃ ማድረግ እንዳለበት ኢ-ፍትሀዊ ነገሮች ሲሰሩ ማቆም እንዳለበት፣ ህዝቡ አልመረጥኩህም አታስተዳድረኝም ብሎ ማለት መቻል እንዳለበት፣ ማለትም መጀመሩን ህዝቡ ያለውን አስከፊ ሥርዓት ለውጦ ለተሻለ ህይወት ለመገንባት ትግሉን በተቻለ ሁኔታ መቀጠል እንዳለበት ገልጿል:: ነሐሴ 21/97 በወጣው ሞገድ ጋዜጣ ደግሞ ዶ/ር ታዬ ባደረገው ቃለ-ምልልስ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተበላሸ መሆኑን ሕዝቡ የመረጣቸው ፓርላማ እንዲገቡ እንጂ ገዢው ፓርቲ የመረጣቸው ፓርላማ ለማስገባት አስመሳይ ግለሰቦች አምስት ዓመት እንደቀመጡ አይደለም በማለት ሀሳቡን የገለፀበት ጋዜጣ በማስረጃነት ቀርቧል:: በመጨረሻል እላይ ከተገለፁት በተጨማሪ ዐቃቤ ህግ በማስረጃነት ያቀረበው በቁጥር 2365/ጠ/50/59 በቀን 13/03/98 በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ የቀረበ ማስረጃ ሲሆን ይኸውም ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ከግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ህዳር 13/98 ዓ.ም ድረስ በቀሰቀሰው ረብሻና ሁከት በሰውና በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማጣራት



Scanned by CamScanner

እንዲቻል የቀረበ ማስረጃ ሲሆን ማስረጃው የተጎዱትን የሠራዊቱን አባላት ስም ዝርዝርና የጉዳታቸውን መጠን ጭምር የሚገልጽ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ችለናል።

በዐ/ህግ በኩል ጋዜጦችን በማመለከት በመጀመሪያ የቀረበው ሰነድ ይህንን ሲሆን ዐ/ህግ እነዚህን ሰነዶች ካቀረበ በኋላ ተጨማሪ ሰነድ በማቅረብ ለችሎቱ ተጨማሪ ሰነዶቹን አቅርቧል። ተጨማሪ ሰነዶች ምን እንደሚመስሉ እናያለን። ዐ/ህግ በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ቁጥር አንድ ያቀረበው ግንቦት 6/1997፣ ግንቦት 20/1997 እና ሰኔ 4/1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የአዲስ አበባ መምህራን አባላት ስብሰባ የሚል ሲሆን አንደኛው ክስ እንደሚያስረዳለት ገልፀዋል ሰነዱ ላይ ካሣሁን ከበደ ቢሮ የተገኘ የሚል የሚነበብ ሲሆን የሰነዶቹ ይዘት የሥርአቱን አስከፊነትና መጥፎነት በመግለጽ የታክሲ ሹፌሮችን ያሳዩትን አቋም የበለጠ ለማሳደግ የመምህሩ ሚና ምን መሆን እንዳለበት ከጠቀሰ በኋላ ሥርዓቱን ገርስሶ ለመጣል ትግላችንን ከህዝቡ ጋር በመሆን ማፋፋም አለብን ፓርቲዎች አንድነት ፈጥረው አስከፊውን ሥርዓት ማስወገድ አለባቸው። ከሰኔ 4 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የሥራ ማቆም አድማ ሊደረግ ስለሆነ መዘጋጀት እንደሚጠበቅባቸው ለስራ ማቆም አድማ የሚሆን የመቀስቀሻ ጽሁፍም መሰራጨት እንዳለበት መሞት ካለም የክብር ሞት ለመሞት መፍራት የለብንም መምህራን የሥርዓቱን እድሜ ለማሳጠር መሥራት እንዳለባቸው ውይይት መደረጉን ከሰነዱ ለመረዳት ይቻላል። በሁለተኛው ተራ ቁጥር የቀረበው ሰነድ ማስረጃ የግንቦቱ ምርጫ ሂደትና አገራችን የምትገኝበትን አጣብቂኝ በሚል የተፃፈ ስምንት ገጽ ሰነድ ሲሆን በዚህ ሰነድ ገጽ አንድ ላይ ቢሮ ውስጥ የተገኘ ዳንኤል በቀለ የሚል ጽሁፍ የሚታይ ሲሆን ሰነዱ ከምርጫ በፊት የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታና ከምርጫ በኋላ ስለገጠሙ ችግሮች በመዘርዘር ከገለፀ በኋላ ቅንጅት ጉዳዩ ያገባናል የሚሉ ዜጎችን ምክራችሁን ስጡን በሚል የሚደመድም ሰነድ ነው በሦስተኛ የቀረበው ሰነድ ነሐሴ 2 ቀን 1997 ዓ.ም የሲቪል ማህበረሰብ ግማሽ ቀን ስብሰባ ሪፖርት የሚል ሲሆን ይህ ሰነድ አራት ገጽ ያለው ሆኖ ገጽ አንድ አራስጌ ላይ ቢሮ ውስጥ የተገኘ ከዳንኤል በቀለ የሚል ጽሁፍ ይነበባል። የጽሁፍ ይዘትም ከግቦት 7 ምርጫ በኋላ በተከሰቱ ችግሮች ዙሪያ ሆኖ የተለያዩ አቋሞች የሚታዩበት ሰነድ ነው። አራተኛ የቀረበው ሰነድም ከዳንኤል በቀለ ቤት የተገኘ በሚል አንድ ገጽ ያለው ለውይይት የቀረበ የመንደርደሪያ ሀሳቦች



Scanned by CamScanner

የሚል ዕርእስ ያለው ሲሆን ከዚሁ ጋር በሁለተኛ ገጽ የሚታየው በእንግሊዘኛ የሚታየው የሰፈረ ቃላት ያሉበት ሲሆን እንዲተረጉም ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ሳይተረጉም በመቅረቱ በማስረጃነት የሚያያዝ አይደለም በአምስተኛ የቀረበው ማስረጃ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበት 16ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔና የአቋም መግለጫ ሲሆን የአቋም መግለጫ በሚል የተለያዩ ይዘት ያላቸውና የግንቦት 7/1997ቱን ምርጫን የሚያካትቱ መግለጫዎችን የያዘ ሲሆን በዚህ ሰነድ ከግራ ጉን ካሣሁን ከበደ ከቢሮ የተገኘ ሁለት ገጽ የሚል ስምና የማይነበብ ፊርማ ይታያል። በስድስተኛ ቁጥር የሚታየው ሰነድ ዶክተር በፍቃዱ ደግፌ ለሰለሞን በቀለ መጋቢት 28/97 የፃፈው ደብዳቤ ሲሆን ለምርጫ ቅስቀሳ በሚል የተላከላቸው 89000 ሺ 994 ዶላር የደረሳቸው መሆኑን በመግለጽ የምስጋና መልዕክት ያስተላለፈበት ሲሆን ደብዳቤው የቅንጅት የራስጌ አርማ እና ክስ ማህተም የያዘ ነው። በሰባተኛ ቁጥር የሚታየው ሰነድም በተመሳሳይ ሁኔታ ብር 29994 ዶላር የደረሳቸው መሆኑ የተገለፀበት ሰነድ ነው በስምንተኛው ቁጥር.የተመዘገበው ሰነድ ሊሻን ግዛው የቀስተ ዳመና ድርጅት የጀርመን ተወካይ መሆኑን የሚያሳይና በ9/2/2005 በዶክተር ብርሀኑ ነጋ የተፃፈ ደብዳቤ ሲሆን በቁጥር ዘጠኝና አሥር የተመለከቱት ሰነዶች በድጋሚ የቀረቡ በመሆናቸው ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም። በቁጥር አሥራ አንድ የተጠቀሰው ሰነድ ጥር 27 ቀን 1997 ዓ.ም ከኢንጂነር ሀይሉ ሻውል ለብርሃነ መዋ እና ለሌሉች ሁለት ግለሰቦች ለሜን አሜሪካ የቅንጅቱ የገንዘብ አሰባሳቢና የፖለቲካ ሥራ አስተባባሪ በመሆን እንዲሰሩ የተመደቡ መሆኑን የሚያሳይ እና የሥራ መመሪያ ሲሆን ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የሚል የራስጌ አርማና ክብ ማህተም ያለበት ነው በቁጥር አሥራ ሁለት የተጠቀሰው ሰነድ ከኢንጂነር ሀይሉ ሻውል ለአንዳርጋቸው ጽጌ የተፃፈ ደብዳቤ ሲሆን ይዘቱም ከላይ በአሥራ አንደኛ የተገፀለው ይዘት ያለው ሆኖ በእንግሊዝ ሀገር የተወከለ መሆኑ የሚያሳይ ነው። በቁጥር አሥራ ሦስት የተጠቀሰው ሰነድ የካቲት 2 ቀን 1997 ዓ.ም ከኢንጂነር ሀይሉ ሻውል ለጌታቸው ጋረደው የተፃፈ ደብዳቤ ሲሆን ይዘቱም ግለሰቡ ለቅንጅት የላከው ብር 10000 የደረሳቸው መሆኑ የገለፀበት የብዳቤ ነው። ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የሚል የራስጌ

Scanned by CamScanner

እርማ እና ክብ ማህተም እንዲሁም የኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የያዘ ሰነድ ነው፡፡ በቁጥር አሥራ አራት የቀረበው ሰነድ የቅንጅት አርማና ክብ ማህተም የያዘ ሲሆን የቅንጅቱን የባንክ ሂሳብ ቁጥር በመጥቀስ ለአቶ ሰለሞን በቀለ ለተከሳሽ ሰለሞን በቀለ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል አድማሱ ገበየሁ ብርሃኑ ነጋና ቸከሉ ጌታሁን ወጪ ባደረጉት ደብዳቤ በመፈረም የገለፁበት ሰነድ ነው፡፡ በቁጥር አሥራ ስድስት የተገለፀው ሰነድ ማንነቱ ባልተገለፀ ግለሰብ ለአቶ ሀይሉ ሻውል የተለያዩ ኮሚቴዎችን እንዲያዋቅሩ በመግለጽ የተፃፈ ጽሁፍ ሲሆን በቁጥር አሥራ ሰባት በተጠቀሰው ሰነድ መስከረም 21 ቀን 1998 ዓ.ም ከቅንጅትና ህብረት ሰላማዊና ህጋዊ የህዝብ ትግል ጥሪ በሚል የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ ነው፡፡ ይዘቱም በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ዙሪያ ያጋጠሙ ትግሮችን በማንሳት ለመፍትሄ ይሆናል ያሉትን የብሔራዊ አንድነት መንግሥት እንዲመሰረት ሀሳብ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ገልፀው ከመስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ለሦስት ቀናት በተከታታይ በቤት በመቆየት ሰላማዊ ቅሬታና ቁጭታቸውን ለገዢው ፓርቲ እና መንግሥት እንድትገልፁ በማለት ጥሪ ማቅረቡን ከሰነዱ ለመረዳት ይቻላል፡፡ እሺ በቁጥር አሥራ ስምንት የተጠቀሰው ሰነድ ለመላው ሀገር ወዳድ በሚል የተበተነ ወረቀት ሲሆን በቁጥር 19 የተጠቀሰው ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በሙሉ በሚል የተበተነ በራሪ ወረቀት ነው በራሪ ወረቀት የተለያዩ ጉዳዮችን በማካተት ህዝቡ አልመረጥኩህም እያለው ተመርጫለሁ የሚለውን ልንታገሰው አይገባም መምህራንም ከተማሪዎች ጐን እንድትሰለፍ ጥሪያችንን እናቀርባለን የሚል ይዘት ያለው ነው በቁጥር 20 እና 21 የቀረበው ማስረጃ የአስኳል፣ ሚኒሊክ፣ ሳተናውና፣ ኢትዮጵ ጋዜጣ ባለቤት አሳታሚና ዋና አዘጋጆቹን የሚገልጽ ከንግድ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲሁም ከማስታወቂያ ሚኒስቴር የተሰጡት ማረጋገጫዎች ሲሆኑ በዚሁ ማረጋገጫዎች መሠረት የሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ባለቤት ወ/ሮ ሰርካለም ፋሲል የአስኳል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ደረጀ በጋሻው የሚኒሊክ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ዘላለም ገብሬ የሳተናው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ናርዶስ ማእዛ የፓሬሱ ባለቤት ወ/ሮ ሰርካለም ፋሲል የሲሳይ አሳታሚ ድርጅት ባለቤት አቶ ሲሳይ ያጌና መሆናቸውን ቀንና ቁጥር በጨበጠ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤዎች የተገለፀበት ሰነድ ነው፡፡ በቁጥር 22 የጠቀሰው ሰነድ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ፎረራል



Scanned by CamScanner

ሆስፒታል የዘጠኝ ፖሊስ አባላት የአስክሬን ምርመራ ውጤት የተገለፀበት ሲሆን ለሞት ያበቃቸው ምክንያትም በዚሁ ሰነድ ተገልጿል። በዚሁም መሠረት ኮንስታብል ኮንግቴውል ሞቲያን የተባለው የሞተው ከሚበር መኪና ላይ ተስቦ በመውደቅ በደረሰበት የደም መፍሰስ አደጋ መሆኑን፣ ኮንስታብል አሸናፊ ደሳለኝ በደረሰበት የቦንብ ፍንዳታ አደጋ በመላው አካላቱ ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት፣ ኮንስታብል ፈይሳ ገ/መንፈስ በቦንብ ፍንዳታ አደጋ መላ ሰውነቱ በመጐዳቱ፣ ኮንስታብል ሽዋታጠቅ ወርቁ በደረሰበት የጥይት አደጋ በደረቱ ላይ በመመታቱ፣ ኮንስታብል ዮሐንስ ሰለሞን በደረሰበት ጥይት አደጋ፣ ኮንስታብል ሙሉጌታ ጎርኪ በደረሰበት የጥይት ምት፣ ኮንስታብል ነጋ ገብሬ በደረሰበት የጥይት ምት፣ ኮንስታብል ጀበና ደሳለኝ በደረሰበት የጥይት ምት፣ ኮንስትብል ገልገሉ ጀቤሳ በደረሰበት የጥይት ምት ለሞት የበቁ መሆኑን የገለፀበት ደብዳቤ ሲሆን 136 የቆሰሉ የፖሊስ አባላትን ስም ዝርዝርም ይዟል። በቁጥር 23 የጠቀሰው ሰነድ የተወሰኑ ተከሣሾች ፊርማ በፌዴራል ፖሊስ ፍረንሲክ መምሪያ አማካኝነት ተመርምሮ ውጤቱ የተገለፀበት ሲሆን በቁጥር 24 የተጠቀሰው በተከሣሾች መኖሪያ ቤቶች በብርበራ ተይዘዋል የተባሉ ንብረቶች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደሆነ የሚገልጽ ሰነድ ነው። በቁጥር 25 የጠቀሰው ሰነድ 30ኛ ተከሣሽ ከሆነው ኮ/ል ታምሩ ጉልላት ቤት በብርበራ ተገኝተዋል የተባሉትን ንብረቶች ዝርዝር የያዘ ሰነድ ነው በማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 26-44 ከ49-51 እንዲሁም በቁጥር 53 እና 56 የተጠቀሱት ማስረጃዎች በየማስረጃዎቹ ላይ የሚታየው ጊዜ ክሱ ከቀረበ በኋላ ከመሆንም በላይ በዚህ ክስ ጋር አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም በሰነዶቹ ላይ የሚታይ ይዘቱ የወንጀል ፍሬ ነገር ቢኖረው እንኳን ከእዚህ ክስ በተለየ መልኩ ለብቻው በሚመለከታቸው ሰዎች ላይ በማስረጃነት ከሚያገለግል በቀር በዚህ በተያያዘው ጉዳየ ላይ አግባብነት ስለሌለው መተቸት ሳያስፈልግ እና ማስፈረም ሳያስፈልግ ታልፏል። በቁጥር 45 እና 46 የተገለፀው ሰነድም ቢሆን ሰነዱ በትክክል በጽሁፉ በስተመጨረሻ በሚታዩ ሰዎች የተፃፈ መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚቻል ባለመሆኑ አልፈነዋል። በቁጥር 47 የተጠቀሰው ሰነድ ሰለሞን በቀለ ለኢንጂነር ሀይሉ ሻውል 1997 ዓ.ም ምርጫውን በማስመልከት ትንታኔና ግንዘቤ

Scanned by CamScanner

እንደሰጣቸው ቀሽንግተን አንድ ሰው እንዲመጣ በሚል ግብግ የተላከበትን የሚያሳይ ሰነድ ነው። በቁጥር 48 የተጠቀሰው ከዚህ ቀደም መጀመሪያ ቀርበው ከነበሩ ሰነዶች በቁጥር 45 ላይ የተመዘገበና የታየ በመሆኑ ታልፏል። በቁጥር 52 የተጠቀሰው ሰነድ ኤልያስ ክፍሌ 51ኛ ተከሣሽ ማለት ነው ለፍሬዘር ነጋሽ እንንዲሁም ለብርሃኔ ሀይሉ ነሐሴ 19/1997 ዓ.ም በሁለት የተለያዩ ጽሁፎች የላከው ደብዳቤ ሲሆን በዚህ ደብዳቤ መጨረሻ ፓራግራፍ ላይ ዳንኤል በቀለና ነፃነት ደምሴ የቅንጅት አገናኝ መኮንን እንደሆኑ በኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የተገለፀለት መሆኑን በመግለጽ ተባብረው እንዲሰሩ የገለፀበት ደብዳቤ ነው። በቁጥር 57፣ 58፣ 60፣ 61፣ 63፣ 64፣ 67 የተጠቀሱ ሰነዶች ይዘታቸውም ምንም ይሁን ምን እነዚህ ጽሁፎች በትክክል ስማቸው በጽሁፍ ከሚታዩ ሰዎች ስለመፃፉ የተረጋገጠ ነገር የለም በመሆኑም እነዚህንም መተቸት ሳያስፈልግ ታልፏል። በቁጥር 59 የተጠቀሰው ሰነድ ከፍትህ ሚኒስቴር የአክሽን ኤድ ማንዴት ምን እንደሆነ የተገለፀበት ሰነድ ነው ከዳንኤል በቀለ ቤት ተገኝቷል ተብሎ በቁጥር 62 የቀረበው ሰነድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቅም የሀገር ጥቅም ይቅደም በሚል የተጻፈ ጽሁፍ ሲሆን በዚህ ጽሁፍ ላይ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ያጋጠሙ ችግሮችን በመጥቀስ የተለያዩ ሀሳቦችን የያዘ ጽሁፍ ነው ከእነዚህም ሁሉም ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድ በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት ወደፓርላማው እንዲገቡ ቅሬታ ካላቸው ወደፍርድ ቤት እንዲሄዱ ፍርድ ቤቶችም የተከሰተው ችግር ተአማኒነት ባለው መንገድ እንዲጠናቀቅ ህጋዊና ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚል ይዘት ያለው ነው። በቁጥር 65 የተጠቀሰው ሰነድ 95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ለወጣቶች እንዲያሰራጩው በማለት ሰጥቷል የተባለው ሦስት ገጽ ሰነድ ሲሆን የካርዳችን ድምጽ ይሰማ በሚል ኢህአዴግ ድምጽ ማጭበርበሩን መጪውን አምስት አመት የባርነት ቀንበር በመጫን ሀገራችንን በማትወጣው አዘቅት ለመክተት እየተሯሯጠ እንደሚገኝ ገልፆ ከቅንጅት ጐን በመሆን ቅንጅት በሚጠራው ማንኛውም ሰላማዊ ተቃውሞ አመጽ የሥራ ማቆም አድማ ሁሉም በመተባበር ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ይገልፃል በማለት የተፃፈ ሲሆን ከሰነዱ በስተመጨረሻ ነፃነት ደምሴ ለሌሎች አባዝቱ የሰጠኝ ወረቀት ነው አዳነ በቀለ የሚል ስምና የማይነበብ ፊርማ ያለበት ነው። በቁጥር 66 የጠቀሰው ሰነድ የቅንጅት ታዛቢዎች ዝርዝር በሚል ከ1-56 ስም ዝርዝር የያዘ ሲሆን 94ኛ ተከሣሽ

ዳንኤል በቀለ በተራ ቁጥር ሰላሳ ሰባት 95ኛ ተከሣሽ ነፃነት ደምሴ ስም ደግሞ በ6ኛ ተራ ቁጥር ላይ ሰፍሮ ይታያል። ከዚህ በመቀጠል ዐቃቤ ህግ በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረባቸው ጋዜጦች የሚገኙ ሲሆን የጋዜጦቹም ይዘት እንደሚከተለው ይነበባል። በዐ/ህግ በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች ዝርዝር ከተራ ቁጥር 69 እስከ 86 ድረስ ያቀረባቸው ማስረጃዎች የተለያዩ ጋዜጦች ላይ የተፃፉ ጽሁፎች ሲሆኑ እንደሚከተለው መዝግበናቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ የተመዘገበው ሀዳር ቁጥር 19 ሐምሌ 14/97 የወጣው ጋዜጣ ሲሆን በዚህ ማስረጃ ላይ ዐቃቤ ህግ መግለጫ አልሰጠበትም ሆኖም በቀረበው ማስረጃ መረዳት የሚቻለው በ1998 ዓ.ም በ1998 በጀት አመት ለአዲስ አበባ የተመደበው በጀት 0% መሆኑን ተከሣሽ በድሩ አደም መግለፁንና ተከሣሽ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ደግሞ የሰስትዮሹን ስምምነት መጣሱን የገለፀበት ይገኝበታል። በሌላ በኩል በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቀጥር 70፣ 71፣ 72፣ 73፣ 84 እና 86 ሥር የተዘረዘሩት ማስረጃዎች የአባይ ጋዜጦችን የሚመለከት ነው የእነዚህ ጋዜጦች ዋና አዘጋጅ መስፍን ተስፋዬ ምክትል ዋና አዘጋጅ ፍቃዱ እንድሪስ ሲሆን አሳታሚ ደግሞ አባይ አሳታሚ ነው። ዐቃቤ ህግ እነዚህን ማስረጃዎች በተመለከተ በሰጠው መግለጫ በማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 73 የተገለፀው ማስረጃ በወቅቱ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የጦርነት ስጋት የነበረ መሆኑን ያስረዳል በማለት የቀረበ ሲሆን ሌሎቹ ማስረጃዎች ደግሞ አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዳሉ በማለት የቀረበ ሲሆን ሌሎቹ ማስረጃዎች ደግሞ አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዳሉ በማለት የቀረበ ነው። በጋዜጦቹ የተፃፉት ጽሁፎች ይዘትም አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ተመዝግቧል ይኸውም አባይ አንደኛ አመት ቁጥር 003 ጥር 28 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው ጋዜጣ በነፃ ምርጫ ያልተገኘ ሥልጣን በህዝባዊ አመጽ ይረጋገጣል የሚል አርእስ አንቀጽ ሥር የግንቦት 7ቱ ምርጫ ከተጭበረበረና ኢህአዴግ አሸናፊነቱን ካወጀ በዩክሬን የታየው ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ እንደሚከተል በጆርጂያ በኤድዋርድ ሸበርናዘ ላይ የደረሰው ቅሌት በሀገራችን እንዲደገም ከምርጫው ቅስቀሳ ጎን ለጎን ህዝቡን በዚህ ረገድም መዘጋጀት እንደሚጠበቅበት የኢትዮጵያ ሰራዊት ነፃ ምርጫ ተካሄዶ የኢትዮጵያ ህዝብ



Scanned by CamScanner

ነፃነቱን ካልተቀዳጀ በህዝባዊ አመጽ ባለ አጋርነቱን እንደሚያውጅ ዘንድሮ ወደምርጫ ሲገባ ኢህአዴግ ምርጫውን አያጭበረብርም በሚል ሙሉ እምነት ሳይሆን በተጭበረበረ ምርጫ አሸነፍን በማለ ስልጣን ላለመገዛትና ወደህዝባዊ አመጽ ለመሸጋገር የህዝብ መነሳሳት ትልቅ ትርጉም ስለሚኖረው ጥምር መሆኑን በዚሁ መልስ በሙሉ ልብ ተነሳስተን ኢሕአዴግ አጭበርብሮ በሥልጣን ላይ የሚቀጥል ከሆነ ህዝባዊ ሥልጣን የሚመነጨው በህዝብ አመጽ እንደሆነና የየአምስት አመቱ ቲያትርም እንደሚያከትም ገልጿል፡፡ ይኸው ማስረጃም በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 86 ላይ በድጋሚ የቀረበ ስለሆነ እና ይሄንኑ ማስረጃ ደግሞ መዓፍ አስፈላጊነት የሌለው ስለሆነ አልፈነዋል፡፡ የካቲት 26 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው ጋዜጣ ደግሞ በአቶ አረጋዊ በርሄ የሚመራው የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር /ቲዲት/ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ በሚመለከት መግለጫ አውጥቷል በማለት በጋዜጣው የቀረበው ጽሁፍ በማስረጃነት የቀረበ ሲሆን ይሄውም አገራችን ባለችበት ዘግናኝ እና አሳፋሪ ሁኔታ የምትገላገለው ኢህአዴግ ተወግዶ ሕዝብ የሚቆጣጠረው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲመሰረት ብቻ መሆኑን ህዝቡ ኢሕአዴግን መልሶ ወደሥልጣን የሚያወጣ የምርጫ ሂደት መሳተፉን አቁሞ ይሄ አፋኝ አገዛዝ የሚወገድበት ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ እንዲያነሳ መቀስቀስ ማደራጀት እና ማምራት የሁሉም አገር ወዳድ ዲሞክራት ተቀዳሚ ሥራ መሆን እንዳለበት ያሳሰበበት ይገኝበታል፡፡ ሚያዚያ 8 ቀን 1997 በወጣው ጋዜጣ ሠራዊቱ በዓላማ ከኢህአዴግ ይልቅ ለተቃዋሚዎች ይቀርባል በሚል አርዕ እንቁጽ ሥር ምርጫው የተጭበረበረ እና ህዝባዊ አመጽም ከተሰናከለ ያቆጠቆጡት የትልቅ ትግሎች ተፋፍመው የሚቀጥሉ በመሆናቸው ሠራዊቱ ተረጋግቶ ኑሮውን መምራት እንደሚሳነው በመጨረሻም ሽንፈት ይከተል እና በ1983 የታየው መባቱን እንደሚከተል በአርእሰ አንቀጹ ካብራራ በኋላ ግንቦት 20 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው ጋዜጣ ደግሞ የኤርትራው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ግንቦት 16/97 [illegible] በዓልን ምክንያት በማድረግ ንግግር ሲያደርግ [illegible] ጠርነት [illegible] መሆኑን አረጋግጧል በማለት የዘገበ [illegible] 28 ቀን 1998 ዓ.ም የወጣው ጋዜጣ ደግሞ [illegible] ሲሆን [illegible] በሚል ህዝባዊ [illegible] በሚል [illegible] ሥር [illegible] አራት [illegible] የተቋቋመ [illegible]



Scanned by CamScanner

ስለሆነ እዚያ ውስጥ ተገብቶ ምንም የሚፈየድ ነገር አለመኖሩን የአገራችን ዲሞክራቶች ያለማወላወል በህዝባዊ ትግል ብቻ የሚተማመን ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል ጎዳና መያዝ እንደሚኖርባቸው በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፓርላመንታዊ የትግል ዘርፍ እና ከፓርላመንት ውጪ የሚደረጉ የትግል ዘርፎች ተጋግዘው የሚራመዱበት መንገድ እጅግ ጠባብ መሆኑን ድርድር እና ህዝባዊ ትግል ግን በአንድ ላይ ሊካሄዱ የሚችሉ ብቻ ሳይሆኑ ሳይነጣጠሉ መካሄድ እንደሚኖርባቸው ኢሕአዴግ መደራደር ከፈለጋችሁ ትግሉን አቁሙ ትግል እንቀጥላለን ካላችሁ ደግሞ አልደራደርም የሚል አቋም እንዳለው ግልጽ መሆኑን፤ በህዝብ ትግል ሳይታጀብ የሚካሄደው ውይይት በኢህአዴግ የበላይነት የሚካሄድ ስለሆነ የሕዝብን ትጥቅ ከማስፈታት ሌላ የሚያመጣው ፍሬ እንደማይኖር በዝርዝር በጋዜጣው ላይ መቅረቡን መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል ሐምሌ 4 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው አንድነት ጋዜጣ ውስጥ ይድረስ ለአገሬ ሕዝብ ሁሉ በሚል እርስ አንቀጽ የተፃፈ ጽሁፍ በመረጃነት የቀረበ ሲሆን ዐቃቤ ህግም ይሄንን ማስረጃ በተመለከተ በሰጠው መግለጫ ማስረጃው አንደኛውን የወንጀል ክስ የሚያስረዳለት መሆኑን እና ጋዜጣ ላይ ታትሞ የተሰራጨው ጽሁፍም 52ኛ ተከሣሽ ዳዊት ከበደ ከአትላንታ የፃፈው ጽሁፍ መሆኑንም ገልጸዋል። ከጽሁፍም መረዳት የሚቻለው ጽሁፍ የዳዊት ከበደ መሆኑን በሰላማዊ መንገድ ህዝባዊ ለልፍ ለማድረግ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው የወጡት ታዳጊ ወጣቶች በወያኔ ኢሕአዴግ አረመናዊ ግፍ መሸማቀቃቸውን በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የለውጥ መዓበል ዳግም ወደኋላ በማይመለስበት ደረጃ ላይ መድረሱን ከእንግዲህ ወያኔ በአገራችን ያመሽ እንደሆን እንጂ እንደማያድር የገለፀበት ይገኝበታል ቀጣዮቹ ማስረጃዎች ደግሞ በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 75 እና 76 ላይ የተገለፁት ሲሆኑ እነዚህም ሳተናው ጋዜጣ ነሐሴ 8/97 እና ሐምሌ 10/97 ታትመው የወጡት ጋዜጦችን ይ... ...ል። ዐቃቤ ህግ ለችሎቱ ባቀረበው መግለጫም በ76ኛ ተከሣሽ አሳታሚነት በ81ኛ እና በ82ኛ ተከሣሾች አዘጋጅነት በ77ተኛ ተከሣሽ ባለቤትነት እየታተሙ የሚወጡ ጋዜጦች መሆናቸውን ገልጾ ማስረጃዎችም አንደኛውን የወንጀል ክስ እንደሚያስረዱለት አመልክቷል። በተለይ ነሐሴ



Scanned by CamScanner

8/97 የወጣው ጋዜጣ በተመለከተ 45ኛ ተከሣሽ ማሞ ሙጬ ከሌሎች ሁለት የኢትዮጵያ ምሁራን ኔትወርክ ማሕበር አባላት ጋር በመሆኑ በስሙ ጽፎ ያሰራጨውን ጽሑፍ፡ እትሞ በማውጣት በአንደኛው ክስ የተመለከተውን የወንጀል አድማ ተፈፃሚ ለማድረግ ማነሳሳታቸውን ያስረዳልኛል በማለት ነው ያቀረበው ነሐሴ 8/97 በወጣው ጋዜጣ እንደተገለፀው የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ደረጀ በጋሻው ምክትል ዋና አዘጋጅ ዳዊት ፋሲል አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ነው ሆኖም ሐምሌ 10/97 በወጣው ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጁ ዳዊት ፋሲል ዋና አዘጋጁ ደግሞ ታምራት ሰርቤሳ መሆኑን ከጋዜጣው በግልጽ መረዳት ይቻላል። የማስረጃዎችም ይዘት አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው መዝግበነዋል። ነሐሴ 8/97 በወጣው ጋዜጣ የኢህአዴግ መስዋትነት የቀድማል ወይስ የህዝብ ድምጽ በሚል አርእስት ሥር ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬ የኢትዮጵያ ምሁራን ኔትወርክ እስካንዲቪያ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር ብርሃኑ ባልቻ ምክትል ሊቀመንበር ተኮላ ወርቁ ዋና ፀሐፊ መሆናቸውን ከገለፀ በኋላ በኢትዮጵያ ምሁራን ኔትወርክ አባላት ስም የወጣውን መግለጫ በዝርዝር አቅርቧል። ከዚህም ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫው ሳቢያ ለተነከረበት ችግር ተጠያቂው የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መሆኑንን ድምፁን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የሰጠው ህዝብ የአገዛዙን እና የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አካሄድን በሰላማዊ መንገድ የመቃወም መብት እንዳለው ይሄንን ተከትሎ አገሪቱ ውስጥ ሊፈጠር የሚችለው ህዝባዊ ቀውስ ተጠያቂዎቹ የገዢው ፓርቲ እና ቦርዱ መሆናቸውን እና አገሪቱም አሁን ካለችበት ችግር ወደባሰ ቀውስ እንዳታመራ የብሔራዊ እርቅ መንግሥት መመስረት አስፈላጊ መሆኑን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ገዢው ፓርቲ ምርጫው እንዲካሄድ ከፈቀዱ በኋላ የድምጽ ቆጠራው በአግባቡ ባለመካሄዱና ቅሬታውም በተገቢው መልኩ ባለመጣራቱ የተፈጠሩትን ችግሮች ብሔራዊ እርቅ ወደሚመሰረትበት እድል መቀየር አለባችሁ የሚል እምነት እንዳላቸው ይህንኑ በተደጋጋሚ ለመጠቆም እንደሞከሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠንካራ የህዝብ ድጋፍ እንዳላቸው የአሁኑ ምርጫ ያመላከተ በመሆኑ ለብሔራዊ የእርቅ መንግሥት ምስረታ አስፈላጊ ነገር ሁሉ ለመፍጠር አመቺ ነው ብለው እንደሚያምኑ በአገሪቱ ውስጥ ያሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች በበርካታ ጉዳዮች ዙሪያ የሚቃረኑ አቋሞች ሊኖሯቸው ቢችልም በአሁኑ ወቅት የብሔራዊ እርቅ እንደ እስትራቴጂ መውሰድ እንደሚኖርባቸው ይሄው ብሔራዊ እርቅ አገሪቷ ወደ



Scanned by CamScanner

ዲሞክራሲ የምታደርገው ጉዞ ያፋጥንላታል የሚል እምነት እንዳላቸው የገለፁበት ይገኝበታል። ሐምሌ 10 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው ሳተናው ጋዜጣ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ፡ ኢህአፓ ወቅታዊ መግለጫ ነው በማለት በቀረበው ጽሁፍ፡ የህዝብ ድል እንዳይነጠቅ በጋራ እንከላከል በሚል አርእስ ሥር የኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድ እና የጭቆናውንም ሰንሰለት በጠሶ ለመወርወር ዳር እስከዳር አምርሮ በመነሳት በቅርቡ በተካሄደው እና ገና ውጤቱ በመጠቃለል ላይ ባለው ምርጫ ድምፁን ለተቃዋሚ ድርጅቶች በመስጠት አገዛዙን ሽንፈት ማከናነቡን እስካሁን በተደረጉት ቆጠራዎች መሠረት መንግሥት በከተማዎችም ሆነ በገጠር ተሸንፎ እያለ በተለመደው የማጭበርበር ሥራው አሸንፈናል ማለቱ የህዝብን ድምጽ ለመንጠቅ ማሰቡን እንደሚያመላክት ይሄ በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር ሊደርስ የሚችል ሂደት ስለሆነ በሰከነ እና በተራቀቀ ስልት አቅጣጫ ማስያዝ የወቅቱ ተቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን እንደሚገባ ይሄንን ለውጥ ያረገዘ ሁኔታ ለማጨናገፍ የመለስ ዜናዊ ቡድን በመወራጨት ላይ እንደሚገኝ የህዝቡ የምርጫ ድምጽ በትክክል ተቆጥሮ ወደተፈለገው የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ከመሄድ እንዳይጨናገፍ ሁሉም የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከህዝቡ ጎን መቆም የሚጠበቅባቸው መሆኑን ገልፀዋል። በተጨማሪ አገዛዙ በሥልጣን ላይ ሊቀጥል የሚችለው በህዝብ ምርጫ ሳይሆን የህዝብ ውሣኔ ረግጦ እና አጭበርብሮ እንዲሁም በሀይል አፍኖ እና ከቻለም ጨፍልቆ ሊገዛ ከቻለ ብቻ መሆኑን የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊት እና የፀጥታ ሠራተኛ አባላት በሙሉ ተልዕኮዋቸውን እና ግዴታቸውን ለህዝብ እና ለአገር መቆም እንደሆነ ገልፀዋል። በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 79 የተገለፀው ግንቦት 10/1997 የወጣው የኢትኦጵ ጋዜጣ ሲሆን የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ እንዱአለም አየለ ምክትል ዋና አዘጋጅ ተስፋ ተገኝ አሳታሚ ደግሞ ሲሳይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ነው ዐቃቤ ህግ ይሄ ማስረጃ አንደኛውን የወንጀል ክስ ያስረዳልኛል በማለት አስመዝግቧል። በጋዜጣው ገጽ 10 ላይ ህዝባዊ አመጽ ወይም ሰላማዊ አመጽ በሚል ሐረግ ሥር የኢህአፓ መልዕክት መሆኑን ተገልጾ የተፃፈ ሲሆን ይሄው ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ



Scanned by CamScanner

ሲባል ህዝቡ ለመብት ሲል ማመጽ እንዳለበት ሕዝብ ለመብቱ መከበር የመለስ አገዛዝ ይወገድ ብሎ መሰለፍ ማደም መታገል እንደሚገባው አገዛዙን አትቀስቁሱት የሚሉ ክፍሎች የመለስ ዜናዊ ፀረ-ትግል አሳት አደጋዎች አሳት አጥፊዎች መሆናቸውን ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ አገዛዙን ማናደድ ብቻ ሳይሆን ብርክ አስይዞ ከሥልጣን ለማስወገድ የተቃኘ መሆን እንዳለበት ስለዚህም የማያቋርጥ የሕዝብ አመጽ ትግል ማደራጀት የግድ እንደሆነ የተቃውሞ ሰልፍ ተፈቀደም አልተፈቀደም ለፀረ-ህዝብ ህግ አንገዛም ማለት የሥራ ማቆም አድማ በአገዛዙ የንግድ ተቋማት ላይ ማዕቀብ ማድረግ፣ የረሐብ አድማ፣ ሰልፍ ሰልፍ ሰልፍ የአምቢኝ አልገዛም አድማ አድማ አድማ አድማ ይሄ ነው ፍትሁን መንገድ አገዛዙን አስጨንቆ ለመጣል እና አገርን ለማዳን በማለት ጽሁፍ በዝርዝር አቅርቧል። በመቀጠልም ግንቦት 10/1997 ዓ.ም የወጣው የአዲስ ዜና ጋዜጣ 1ኛ፣ 5ኛ እና 7ኛ የወንጀል ክሶችን ያስረዳል በማለት ዐቃቤ ህግ ያቀረበው ነው። ጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ፋሲል የኔአለም ምክትል ዋና አዘጋጅ ስምረት ገ/ማሪያም ስትሆን ዐቃቤ ህግ ባቀረበው መግለጫ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን በማለት አስመዝግቧል። የጋዜጣውም ይዘት የቅንጅት መሪዎች በሞት ጥላ ሥር ናቸው በሚል እርእስ ሥር መንግሥት የቅንጅት አመራሮች ለመግደል ሦስት ኤርትራዊ ነብሰ-ገዳዮችን ማስመጣቱ ግድያውም የሚፈፀመው የቅንጅት አመራሮች አሉበት በተባለው ስፍራ ከኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለሥልጣን መ/ቤት ጋር በመመሳጠር መብራት አስጠፍተው ግድያውን እንደሚያካሄዱ ይሄም ካልተሳካ 11 የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ሴቶች በሆቴል ሙያ ሠልጥነው እንዲመረቁ ተደርገው የቅንጅት መሪዎች የሚጠቀሙባቸው ሆቴሎች መርዝ በመበተን እንዲገድሉዋቸው ታቅዷል የሚል ይዘት ያለው ነው። ከዚህ በመቀጠል በማስረጃነት የተዘረዘሩት ጳጉሜ 4 ነሐሴ 6 እና ሚያዝያ 7 ቀን 1997 የወጡትን የሚኒሊክ ጋዜጦችን የሚመለከት ነው የጋዜጦችም ይዘትም ጳገሜ 4/97 የወጣው ኢትዮጵያ እና ኤርትራ ውይይት እንዲጀምሩ የተባበሩ መንግሥታት ድርጅት አሳሰበ በሚል እርእስ ሥር በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ፍጥጫ የአካባቢውን ሰላም እና ፀጥታ ሊያናጋ እንደሚችል መግለፃቸውን ነሐሴ 6 በወጣው ደግሞ ዐቃቤ ህግ በማስረጃነት ያቀረበው የጋዜጣው ርዕስ እንቀጽ እና የመኢአድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ያወጣው የአቋም መግለጫ ነው እርእሰ አንቀፁም በሰነድ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 57 ሥር ከዚህ በፊት



Scanned by CamScanner

በማስረጃነት የቀረበ ስለሆነ ዳግም ማስረጃውን መሻሻ አስፈላጊ አይደለም የመኢአድ የአቋም መግለጫ ደግሞ ከምርጫው በኋላ የተከሰቱት ችግሮችን ከገለፀ በኋላ ለአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ የሚሰራ ጊዜያዊ መንግሥት መመስረት እንደአማራጭ መቅረብ እንደሚኖርበት የተሰጠ መግለጫ ነው ሚያዝያ 7 ቀን 1997 ዓ.ም የወጣው ጋዜጣ ደግሞ ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት እና ከፍሌ ሙላት ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት እና ለቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ቅንጅት ያስተላለፉት ጥሪን የሚመለከት ነው ይዘቱም ላለፉት 14 ዓመታት በአንባገነንነት ኢትዮጵያን ሲያሥቃዩአት የቆየው የኢህአዴግ አገዛዝ በዲሞክራሲ ምርጫ ለመተካት የሚካሄደው ታላቅ ተግባር በአንክሮ እንደሚከታተሉት እንዲሁም ከልብ እንደሚደግፉት ለነፃ እና ፍትሀዊ ምርጫ መካሄድ የሲቪክ ማህበራት የጋራ መድረክ በአስቸኳይ እንዲመሰረት ጥሪ ያቀረቡ መሆኑን የሚገልጽ ነው በመጨረሻም የካቲት 15 ቀን 1997 በወጣው የአስኳል ጋዜጣ የሻቢያ ሦስት መቶ ሺ የኢትዮጵያ ሥልሳ ሺ ጦር ተፋጠዋል በማለት ኢትዮጵያ በኤርትራ አምስት ለአንድ እየተመራች መሆኑን በመግለጽ ዘግቧል፡፡

ዐቃቤ ህግ በሰነድ ማስረጃነት ያቀረባቸው ከላይ የመሰሉ ሲሆኑ ሰነድ ማስረጃ በኋላ ደግሞ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ምስክሮች ቃል በአጭሩ ደግሞ እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ቀርበው የተሰሙ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል፡- ዐቃቤ ህግ ጉዳዩን ያስረዱልኛል ብሎ የቆጠራቸው ምስክሮች 367 ሲሆኑ ከእነዚህም መከከል 19 ያህሉ በሌሎች ከተሰሙ የምስክርነት ቃል የተለየ የምስክርነት ቃል አይሰጡም በማለት ከሁለት መቶ ያህል ደግሞ የሚሰጡትን የምስክርነት ቃል ድግግሞሽ ነው በመባሉ ታልፈዋል፡፡ ከተቆጠሩት ምስክሮች ከ69 በላይ ምስክሮች ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዋና ምስክርነት ከተቆጠሩት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ሌላ 15 ተጨማሪ ምስክሮች እንዲሰሙበት ዐቃቤ ህግ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ከቆጠራቸው ተጨማሪ ምስክሮች መካከልም አሥራ ሦስት



Scanned by CamScanner

ተሰምተዋል። የምስክሮቹ የምስክርነት ቃል አሰጣጥን በሚመለከት ምስክሮቹ በየትኛው ተከሣሽ እና በየትኛው የወንጀል ክስ ላይ መመስከር እንደሚችሉ ዐቃቤ ህግ አስቀድሞ ባስያዘው ጭብጥ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ተደርገዋል። በዚሁ መሠረት ሀ. በዐቃቤ ህግ የምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥር 200፣ 223፣ 307፣ 314 እና 277 ስማቸው የተመለከተው ምስክሮች ዐቃቤ ህግ በተለይ በ3ኛ፣ በ4ኛ፣ በ5ኛ፣ በ91ኛ እና በ15ኛ ተከሣሾች መኖሪያ ቤትና ቢሮዎች ውስጥ ተገኙተው ክሱን ለማስረዳት የቀረቡ ሰነዶች በህጋዊ መንገድ ስለመያዛቸው ያስዱልኛል ብለው የቆጠራቸው ምስክሮች ሲሆኑ በተራ ቁጥር 107፣ 108 እና 109 ስማቸው የተጠቀሰው ምስክሮች ደግሞ በ2ኛ፣ በ18ኛ እና በ24ኛ ተከሣሾች ሰብሳቢነት አዲስ አበባ በሚገኘው የመኢአድ ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ግንቦት 28 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገውን የአመጽ ቅስቀሳ እና የማነሳሳት ስራ እንዲሁም ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ዋዜማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተነሳው ረብሻ እና ብጥብጥ ውስጥ የተከሣሾችን ሚና ያስረዱልኛል ተብለው የተቆጠሩ ናቸው። ከበደ ደስታ የተባለው 200ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በሦስተኛው ተከሣሽ መኖሪያ ቤት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ብርበራ ሲደረግ በታዛቢነት መገኘቱን ገልጾ፣ ብርበራው ሲደረግ ተከሣሽ እንደነበረ በተከሣሽ ፍቃድ ብርበራው ተከናውኖ በብርበራው በተገኙ እና ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ለስብሰባ እና ለአንዳንድ አጀንዳዎች የሚጠቀምባቸው 295 ገጽ ሰነዶች ካሴቶች እና ኮምፒውተር መገኘቱን እንደተመለከተና በሰነዶቹ ላይም ተከሣሹ በፍቃደኝነት መፈረሙን፣ እሱ እና ሌሎች ታዛቢዎችም ስለተገኙ ሰነዶች በቬርባል መፈረማቸውን በማስረዳት መስክረዋል በተራ ቁጥር 223 የተጠቀሰው ምስጉን ገ/ሊባኖስ የአራተኛው ተከሣሽ መኖሪያ ቤት ውስጥ ብረበራ በተደረገ ጊዜ በታዛቢነት መገኘቱን ገልጾ ስለ ብርበራው አፈፃፀም የሚከተለውን ብለዋል። ብርበራው ሲካሄድ ሦስት ታዛቢዎች እንደነበሩ እና ብርበራው የተካሄደውም የፍርድ ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ በያዙ ፖሊሶች መሪነት ሆኖ በብርበራው በተከሣሹ መኖሪያ ቤት ሳሎን እና መኝታ ቤት ውስጥ ብዛት ያላቸው ሰነዶች እና ካሴቶች እንዲሁም ኮምፒውተር መገኘታቸውን በማስረዳት በሰነዶቹ ላይ ተከሣሹ መፈረሙን እና ነገር ግን በመፈረም ላይ እያለ የጎዳም ህዝብ ቦንብ ገጀራ ይታጠቅ የተወሰኑ አባላት ይመልመሉ የሚል እና



Scanned by CamScanner

የሚገደሉ ባለሥልጣኖች ስም ዝርዝር ማለትም የአገ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አዲሱ ለገሰ፣ ወ/ሮ ገነት ዘውዴ እና በጠቅላላ ስድስት የሚሆኑ ባለሥልጣኖች ስም ዝርዝር ያለበት ሰነድ ሲደርስ አልፈርምም ማለቱም ገልጾ ሰነዶቹን አይቶ እንዲያረጋግጥ ዐቃቤ ህግ በጠየቀው መሠረት አይቶ ያረጋገጠ ሲሆን ሰነዶቹም በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር በተራ ቁጥር 32፣ 38፣ እና 39 የተመለከቱት መሆናቸውን ተረጋግጠዋል። በሰነደቹም ላይም እሱ እና ሌሎች ታዛቢዎች እንደፈረሙባቸው አስረድቷል። በቀለ ጉዲሳ የተባለው 277ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ላንቻ አካባቢ የሚገኘው የኢዴፓ ጽ/ቤት ሲበረበር በታዛቢነት መገኘቱን ብርበራው የተከናወነው አምስተኛው ተከሳሽ በተገኘበት እና የፍርድ ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ በያዙ ፖሊሶች አማካኝነት መሆኑን ገልጾ ስለ ብርበራው አካሄድ የሚከተለውን ብሏል። በብርበራው ሂደት ከእርሱ በተጨማሪ ሌሎች ታዛቢዎች እንደነበሩ ተከሣሹ ባለበት ሰነዶቹ መታየታቸውን ሰነዶቹ የተቀመጡባቸው ክፍሎች እና ኮመዲኖዎች የተቆለፉ እንደነበሩ እና ቁልፎቻቸው ተሰብሮ ሲከፈቱ ማየቱን እና ከሰነዶቹም መካከል የትግል ጥሪ የሚል አርእስ እና በኑሮ ውድነት መነሳት እና የማግለል ሁኔታ የሚገለፁ ሰነዶች እንደነበሩ የሚያስታውሰውን ገልጾ ተከሣሽ ሌሎች ወረቀቶች ተጨምረው ሊሆን ይችላል ሲል እንደነበረ መስማቱም ጭምር መስክረዋል። አለም ገ/መድህን የተባለው 307ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር በ91ኛ እና በ92ኛ ተከሣሾች ላይ ለመመስከር፣ የፍርድ ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ በያዙት ፖሊሶች በታዛቢነት እንዲገኝ ተጠይቆ ብርበራው ሲካሄድ መገኘቱን በመግለጽ ብርበራው የተካሄደውም የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ መ/ቤት አጠገብ ባለው የመምህራን ማህበር ጽ/ቤት ውስጥ ባለው 91ኛው ተከሣሽ ቢሮ ሲሆን በቢሮ ውስጥ ልዩ ልዩ በርካታ ሰነዶች መገኘታቸውን እና በተለይም ምስክሩ በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ በተራ ቁጥር 57 እና 61 በተጠቀሱት ሰነዶች ላይ መፈረሙን በማስረዳት ብርበራው ሲካሄድ ተከሣሽ እንዳልነበረ መስክሯል። 314ኛ ምስክር አሸብር ሀይሉ በግምት ጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም በመኢአድ ጽ/ቤት በተደረገው ብርበራ በታዛቢነት መገኘቱን ገልጾ

Scanned by CamScanner

ብረበራው የተካሄደውም የፍርድ ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ በያዙ ፖሊሶች አማካኝነት መሆኑን ብርበራው ሲከናወን አንደኛው ተከሣሽ እና የድርጅቱ አስተዳዳሪ ነው ያለው 15ኛው ተከሣሽ እንደነበሩ በብርበራው ሰነዶች እና ካሴቶች መገኘታቸውን እና በካሴቶቹ ላይ አንደኛው ተከሣሽ እንደፈረመባቸው እንዲሁም በሰነዶቹ ላይ ታዛቢዎች ጭምር መፈረማቸውን መስክረዋል። ግርማ ጫኔ የተባለው 107ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ግንቦት 28 ቀን 1997 ዓ.ም በመኢአድ በተጠራው ስብሰባ እንደነበረ በመግለጽ ስለ ስብሰባው ዓላማ ሁለተኛው ተከሣሽ ተናገረው እንዳለው ኢሕአዴግ በፌዴራል ደረጃ መንግሥት ለመመስረት የሚያበቃኝ ደምጽ አግኝቻለሁ በማለት በማስሚዲያ በማስነገር መንግሥትን የመመስረት ሀሳቡን ይፋ በማድረጉ ነገር ግን በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በክልሎች መንግሥትን ለማቋቋም የሚያበቃ ድምጽ ያላገኘ በመሆኑ ይሄንን ለመቃወም እና የህዝባችን በድምጽ ለማስከበር በኢህአዴግ ላይ አለማቀፋዊ ጫና ለማሳደር እና ህዝቡንም የማደራጀት ሥራ ድርጅታችን በሚሰጠው አመራር መስራት ይኖርበታል የሚል እንደነበረ አስረድተዋል። በስብሰባው ወቅት ስለተሰብሳቢዎች ሲያስረዳ አብዛኛው ተሰብሳቢዎች የድርጅቱ ደጋፊ ወጣቶች እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንደነበሩ በተለይም ከተሰብሳቢዎች መካከል አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጥሪ የሚል በራሪ ጽሁፍ አባዝቶ ለታዛቢዎቹ እንዲበትን በጠየቀው መሠረት ለተሰብሳቢዎቹ እንዲበትን በጠየቀው መሠረት በስብሰባው ሰብሳቢ በ2ኛው ተከሣሽ ፈቃደኝነት ከጽ/ቤቱ ብር አንድ መቶ ብር ወጥቶ ጽሁፉ መባዛቱን እና ለተሰብሳቢዎቹ እንዲዳረስ መደረጉን በማስረዳት ሰነዱም በዐቃቤ ህግ የጽሁፍ ማስረጃ በተራ ቁጥር 19 የተመለከተው መሆኑን ለይቶ አረጋግጧል። በወቅቱም ስብሰባውንም ይመሩ ነበሩ ያላቸውንም ሰዎች 2ኛ እና 24ኛ ተከሣሽ መሆናቸውን በችሎት በመለየት አመልክቷል። ስለ 24ኛው ተከሣሽ ሚና ሲገልጽ በወቅቱ የመድረክ አስተባባሪ እንደነበረ እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከዚህ በፊት የረሀብ አድማ አድርገው ታፍነውባቸዋል በጣም እንግልት ደርሶባቸዋል ከጎናቸው በመቆም እስከመጨረሻው ድረስ አብረናቸው በመሆን ጽ/ቤት በኩል እገዛ ይደረግላቸዋል ሲል መስማቱን ከመመስከሩም በተጨማሪ ከስብሰባው በኋላ ግንቦት 29 ቀን እስከ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በአዲስ



Scanned by CamScanner

አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ረብሻ መደረጉ እና ይሄውም ረብሻ ከተደረገ ስብሰባ ጋር ተያያዥነት የነበረው መሆኑን አስረድተዋል። እየሩሳሌም ሀይሌ የተባለችው 108ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር በበኩሏ ግንቦት 28 ቀን 1997 ዓ.ም በመኢአድ ጽ/ቤት በተደረገው ስብሰባ መገኘቷን ገልፃ በወቅቱ ኢሕአዴግ ምርጫውን ድምጽ በማጭበርበሩ የተጭበረበረውን ድምጽ ለማስመለስ የሥራ ማቆም አድማ እንዲደረግ የታክሲ ሹፌሮች ሥራ እንዲያቆሙ ጥሪ መደረጉን እና በመድረክ መሪው በምርጫ ቦርድ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ በምርጫ ማጭበርበር ክስ የተመሰረተ መሆኑን ሲናገር እንደሰማች ገልፃለች። በ107ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ከተነገረው የምስክርነት ቃል ተቀራራቢ ስለሆነ ዝርዝሩ አላስፈለገም። 109ኛው የዐቃቤ ህግ ምስክር ዳኛቸው ተካ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥበቃ ክፍል ኃላፊ መሆኑን ከገለፀ በኋላ በዩኒቨርስቲው መማር ማስተማር ሂደት ላይ በተማሪዎች መካከል በተነሱ ሁከቶች ህገ-ወጥ ወረቀቶች ይበተኑ እንደነበረ በተለይም ግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ተኩል አካባቢ በስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ቁጥራቸው ከ700 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ያሰሙት ነበረ ስላለው ጩኸት እና የፀጥታ ማደፍረስ ህገ-ወጥ ተግባር የሚከተለውን መስክሯል። ተማሪዎቹ በወቅቱ በትነዋቸዋል የተባሉት ወረቀቶች በዐቃቤ ህግ የጽሁፍ ማስረጃ ዝርዝር ተራ ቁጥር 19 የተመለከቱትን በማየት ምስክሩ ያረጋገጠ ሲሆን በተማሪዎቹ ይሰሙ ነበሩ ካላቸው ምስክሮች መካከልም መለስ ከሥልጣን ይውረድ የቅንጅት አመራሮች ምሁራን ናቸው የኢሕአዴግ አመራሮች መሀይሞች ናቸው የሚሉ እንደሚገኙበት ገልጿል። ከተበተኑት ወረቀቶች መካከልም ከመኢአድ ቅንጅት ፍትህ ፈላጊ ሕያው ድምጽ የሚሉ በራሪ ጽሁፎች በመላው ኢትዮጵያ ተማሪዎች ለመላው ሠራተኛ ማህበር ለመላው ታክሲ ሹፌሮች ማህበር ለመላው አውቶቡስ ሹፌሮች ማህበር ለመላው ኢትዮጵያ ባንክ ሠራተኞች በውጪ ድርጅት ውስጥ ለምትሰሩ ሠራተኞች እንዲሁም ለመላው ኢትዮጵያውያን በሙሉ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም የሥራ ማቆም አድማ የሚደረግ ስለሆነ አገሩን የሚወድ ኢትዮጵያ በሙሉ ይነሳ ተነሱ እንነሳ የሚል ጥሪ የያዙ እንደሚገኙባቸው እና ከዚህም ሌላ ከሦስተኛ



Scanned by CamScanner

አገራዊ ምርጫ ተከትሎ በማን እንደተዘጋጀ የማይለያቸው ከመኢአድ ቅንጅት በሚል በራሪ ጽሁፎች በየጊዜው በዩኒቨርስቲ ውስጥ ይበተኑ እንደነበሩ መስክረዋል:: ለዐቃቤ ህግ በ1ኛ፣ በ2ኛ፣ በ24ኛ እና በ122ኛ እስከ 127ኛ ተከሣሾች ላይ በ1ኛ፣ በ2ኛ እና በ3ኛ ክሶች ባስያዘው ጭብጥ ተመስርቶ ተከሣሾቹ ቅድመ ምርጫ እና ድህረ ምርጫ ምርጫው ከተካሄደ በኋላ በህገ-መንግሥቱ በተቋቋመ አካላት ላይ በሕቡእ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ የሽፍታ ቡድን ሲያደራጁ መቆየታቸውን እንዲሁም በአገሪቱ የገጠር ክፍል ገጀራ መጥረቢያ ሌሎች የጦር መሣሪያዎችን በማስታጠቅ ህዝቡ ለአመጽ እንዲነሳሳ ሲቀሰቅሱ መቆየታቸውን ያስረድልኛል ብሎ ባስያዘው ጭብጥ የቆጠራቸው በተራ ቁጥር 45 እና ከ101 እስከ 106 ስማቸው የተመለከቱ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል:: 45ኛው ምስክር ሻለቃ ግዛው ደንቢ በ1993 ዓ.ም የመኢአድ አባል ሆኖ እንደነበር በመግለጽ 1996 ዓ.ም በ24ኛው ተከሣሽ መልማይነት የመኢአድ አባል ሆኖ መደራጀቱን ኢህአዴግ በምርጫ ካሸነፈ በቅንጅት ጠንካራ አመራሮች ላይ እርምጃ ሊወስድ ስለሚችል በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አመራሮች ላይ የአፀፋ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል ወይም ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ በምርጫው ከተሸነፈ ትግራይን በማስገንጠል የትግራይን ግዛት በመመስረት ወደ ትግራይ የሚሄዱ መሠረተ-ልማቶችን መብራት እና መኪኖችን የመሳሰሉትን ለማቋረጥ የሚችሉ ጠንካራ ሰዎችን በሚስጢር ለመመልመል በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሣሾች መመሪያ እንደተሰጠው እና በዚሁ መሠረት በሚያዚያ ወር 1997 ዓ.ም ከ1ኛው ተከሣሽ ጋር ተገናኝቶ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በተለይም በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሣሾች አመራር ሥር ህዝቡን ሰላማዊ ላልሆነ አደረጃጀት በመመልመል የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲያከናውን የተመለመለ ስለመሆኑ በአንደኛው ተከሣሽ በተፈረመ ደብዳቤ እንዲደርሰው መደረጉ በዚሁ ተከሣሽ እንደተገለፀለት አስረድቷል:: በዚሁ መሠረት በደብረብርሃን ማረሚያ ቤት አዛዥ ሆኖ ሲሰራ በማረሚያ ቤቱ ታስረው ከነበሩት እና ከሚያውቃቸው የቀድሞ መንግሥት ወታደሮች እንዲሁም ሽፍቶች መካከል ጠንካራ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን 13 ሰዎች መመልመሉ እና ይሄም ለተጠቀሱ ተከሣሾች አሳውቆ በርታ ቀጥልበት መባሉን ለዚሁ ተግባሩም የቀን አበል ከቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ የተከፈለው መሆኑን ከተመለመሉትም ሰዎች መካከልም የተወሰኑት በግላቸው



Scanned by CamScanner

የጦር መሣሪያ የታጠቁ መሆናቸውን በመግለጽ መስክረዋል። 101ኛው የዐቃቤ ህግ ምስክር አለባቸው አያሌው 123ኛ እና 124ኛ ተከሣሾች ላይ የዐቃቤ ህግ ምስክር አለባቸው አያሌው 123ኛ እና 124ኛ ተከሣሾች እርሱ በሚኖርበት አካባቢ ለመመስከር መምጣቱን ተናግሮ ተከሣሾቹ እርሱ በሚኖርበት አካባቢ ነዋሪዎች እና የሚያውቋቸው መሆናቸውን በመግለጽ ተከሣሾች ሚያዚያ 16 ቀን 1997 ዓ.ም በጠሩት ስብሰባ ላይ ጨረጨር በሚባል የአባባቢው መሰብሰቢያ አዳራሽ በተገኘው ህዝብ ግንቦት በሚደረገው ምርጫ ሁለት ጣት እንደሚያሸንፍ የአለቀለት ጉዳይ ነው። እኛ አለንላችሁ ከአሁን ጀምሮ አሸናፊነታችን ተረጋግጧል። ማንም ታጣቂም ሆነ ፖሊስ ቢመጣ በመጥረቢያ እጨዱት እያሉ ህዝብን ሲቀሰቅሱ መስማታቸውን በማስረዳት ከእዚህም በተጨማሪ ተከሣሾቹ ይሄንን ስብሰባ ለመምራት እና ቅስቀሳውን ለማካሄድ በአካባቢው ቢሮ ከፍቶ ይሰራ የነበረው የቅንጅት አባላት ናቸው ሲባሉ መስማቱን መስክረዋል፣ ዘለቀ ዋሰልኝ የተባለው 102ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር 123ኛ እና 124ኛ ተከሣሾች ላይ እንደሚመሰክር በመግለጽ ተከሣሾች ሚያዝያ 16 ቀን 1997 ዓ.ም እሱ በሚኖርበት አካባቢ፣ ምስራቅ ጎጃም ደጀን ወረዳ ዝለገል ቀበሌ ጨረጨር በሚባል የመሰብሰቢያ ቦታ ለተገኘው ተሰብሳቢ ለኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ አትገዙ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ያለቀለት መንግሥት ነው ከግቦት በኋላ በውድም ሆነ በግድ ገዢዎች እኛ ነን ወታደርም ሆነ ታጣቂ ቢመጣ በመጥረቢያ ቁረጡት እያለ ሁለቱ ተከሣሾች በመፈራረቅ ሕዝቡን ይቀሰቅሱ እንደነበረ በመዘርዘር መስክሯል። 103ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ለማይ ጫኔ 1222ኛ እና 123ኛ ተከሣሾች ላይ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥቷል። ተከሣሾቹ በቅንጅት አደረጃጀት ምስክሩ በሚኖርበት ምሥራቅ ጎጃም ደጀን ወረዳ አካባቢ ሲሰሩ ከጥር ወር 1997 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚያውቃቸውና 122ኛው ተከሣሽ ኀሐሴ ወር 1997 ዓ.ም ተለይቶ ባልተጠቀሰ ቀን የአካባቢ ህዝብ በመንግሥት ላይ የተነጠቀ እጃችን ለማስመለስ የሰልፍ እና የትጥቅ ትግል ማካሄድ እንዳለበት እና ከአምስት እስከ ስድስት ሰው እየሆነ ማጥቃት እና መከላከል እንዳለበት ለዚሁም የጦር መሣሪያ እንደሚሰጥ እና ማንኛውንም ሰው ቤቱ መተኛት እንደሌለበት ሲያስተምር ውሏል በማለት ከማስረዳቱም በተጨማሪ 123ኛው ተከሣሽ መስከረም 8 ቀን 1998 ዓ.ም



Scanned by CamScanner

በተደረገው ስብሰባ የተነጠቁ እጆቻችን ለማስመለስ መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ.ም እጅ ለእጅ ተያይዘን ሰልፍ መውጣት እንደሚገባን ሲያስተምሩ ውለዋል በማለት መስክረዋል። ከዚህ በማያያዝ የውጪ መንግሥታት ይረዱናል እነሱ ያልቃሉ እንጂ እኛ እናልቅም ብሉ ሲናገር መስማቱን አስረድቷል። ደምሰው ያራ የተባለው 104ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር 122ኛውን ተከሣሽ በቅንጅት አደረጃጀት ሲሰራ እንደሚያውቀው በመግለጽ ከምርጫ በኋላ ነሐሴ 12 ቀን 1997 ዓ.ም እሱን (ምስክሩን) እና ጋሻው አየለ የተባለ ሌላ ግለሰብ ጠርቶ ተከሣሽ ምርጫችን ተጭበርብሯል በአፈሙዝ ካልሆነ በምርጫ አልሆነም ለዚህም ሲባል ከደጀን ወረዳ ሰዎች ተመልምለው ጫካ ገብተዋል። እንዳላቸው እነሱም አሥራ አምስት አሥራ አምስት ሰዎችን መልምለው እንዲልኩ እና በረሃ እንዲቀመጡ በአለቃ በአለቃ ተደራጅተው አለቃው የሚያዛቸውን እንዲፈጽሙ እንደነገራቸው በማስረዳት ለዚህም ማስፈፀሚያ የሚሆን ከአገር ውስጥ እና ከወጪ አገር የሚገኝ ገንዘብ አለ ብሎ እንደነገራቸው መስክሯል። በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር ተራ ቁጥር 105 እና 106 የተመለከቱት ሀጂ መሐመድ እስማኤል እና ኮንስታብል ጋሻው ጥበቡ ዐቃቤ ህግ ከላይ በተሰጠው የምስክርነት ቃል የተለየ የምስክርነት ቃል እንደማይሰጡ በመግለጽ አልፈልጋቸውም በማለቱ በምስክርነት ሳይሰሙ ተሰናብተዋል።

ብይኑን ማስማት እዚሁ ለዛሬው አብቅተናል። ከሰዓት አንሰየምም በአዳሪ ነው የምንሰየመው። ምክንያቱም አርብ እለት በሰጠነው ምክንያት ማለት ነው። ስለዚህ ነገ ጠዋት እንቀጥላለን ብይኑን ማሰማት።

Scanned by CamScanner

2ኛ ወ/ችሎት

የመ/ቁ. 43246

መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች:- አዲል አህመድ

ልዑል ገ/ማርያም

መሀመድ አሚንሳኒ

ከሳሽ፡ የፌዴራል አቃቤ ህግ ሽመልስ ከማል ሚካኤል ተክሉ አብርሃ ተጠምቀ

ቀርበናል

ተከሳሾች:- እንጂነር ኃይሉ ሻወል በተከሰሱበት ሁሉም ተከሳሾች ቀርበዋል

- መዝገቡ ያደረው የተጀመረውን ብይን ንባብ ማሰማት ነው በዚሁ መሠረት የጀመርነውን ንባብ ማሰማት እንቀጥላለን ማለት ነው።
- በትናንትናው እለት ከቆምንበት ቀጥለን የምስክሮቹን ቃል እንደሚከተለው እናሰማለን /ሐ/ በዚህ ክፍል ከተመለከቱት የአቃቤ ህግ ምስክሮች ከሚመሰክሩባቸው ተከሳሾች እና በሚመሰክሩትበት የወንጀል ክስ አቅጣጫ ከፋፍሉ ማየቱ ለአቀራረብ አመቺነት ይኖረዋል በሚል እምነት ምስክሮቹ የምስክርነት ቃል ይሰጡበታል ከተባለው ጉዳይ አኳያ እንደሚከተለው ቀርበዋል። 1/ 49ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር የምስክርነት ቃል አቀራረብ ሲሳይ ምትኩ የተባለው ይህ የአቃቤ ህግ ምስክር በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ እና 7ኛ ክሶች በተመለከተው አኳኋን የወንጀል ተሳታፊ ናቸው በማለት ክስ የተመሰረተባቸው 1ኛ 6ኛ እና 12ኛ ተከሳሾች በሚመሩበት ድርጅት ስም አቃቤ ህግ በተራ ቁጥር 29 በተጠቀሰው የሰነድ ማስረጃ ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም አባሎቻቸውን በመሰብሰብ ይዘቱን በማስረዳት እና ስለአፈፃፀሙም መመሪያ በመስጠት ፁሁፎን ለአባሎቻቸው ማሰራጨታቸውን፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 20ኛ እና 23ኛ ተከሳሾች በወንጀሉ ክሶች የተመለከተውን አላማ ለማሳካት በአመፅ እና በትጥቅ ትግል ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለማፍረስ ስለመወሰናቸው፣ እንዲሁም 35ኛ፣ 37ኛ፣ እና 38ኛ፣ ተከሳሾች በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ልዩ ክፍለ ከተማዎች



Scanned by CamScanner

ያደረጉትን የአመፅ ቅስቀሳ ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ካስያዙው ጭብጥ አኳያ የሚከተለውን መስክረዋል ምስክሩ በቅንጅት የሰሜን ቀጠና የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪ እንደነበረ የምርጫው ውጤት ተጭበርብሯል፣ መንግስት ወደ አምባገነንነት እየተቀየረ በመሆኑ ከሰላማዊ ትግል ይልቅ በጦርነት ለማታገል የጎሬላ ሲስተም ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን በተለይም የምስራቅ ጎጃምን ህዝብ ማነሳሳት እንደሚቻል ከ2ኛው ተከሳሽ እንደተነገረው እና 3ኛው ተከሳሽም የአመፅን መነሳሳት በመደገፍ ተባባሪ እንደነበረ እንዲሁም 20ኛው ተከሳሽ በምርጫው ከወደቀ በኋላ የአመፅ ተግባር ለማነሳሳት ይፈልግ እንደነበረ፣ ከዚህም በተጨማሪ 2ኛው፣ 20ኛው እና 23ኛ ተከሳሾች ዋናው የቅንጅት አመራር ከታሰረ በኋላ በተተኪ አመራር ስራውን ያስተባብሩ እንደነበርና በተለይም በምርጫው ያለፉ የቅንጅት ተመራጮች ወደ ፓርላማ እንዳይገቡ የመከላከል ስራ ያከናውኑ እንደነበረ፣ በጠቅላላው እኚህ ተከሳሾች የስራ አስፈፃሚው ስብሰባ በተደረገ ግዜ ሁሉ የአመፅ ባህርይ ያሳዩ እንደነበረ ከምርጫም በኋላም ይሄንን መንግስት መጣል የሚቻለው በጦርነት ነው ይሉ እንደነበረ መስክሯዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተሰብስቦ 8 የአመፅ ቅስቀሳ ነጥቦችን ያካተተ 13 ገፅ ሰነድ ተዘጋጅቶ 1ኛው፣ 12ኛ፣ 23ኛው፣ 6ኛው፣ ተከሳሾች ባሉበት ገለፃ መደረጉንና፣ የሰነዱ ይዘትም የአመፅ ጥሪ እና ማነሳሳት ማለትም ከኢህአዴግ ድርጅቶች ግዢ አለ ለመፈፀም፣ ጡሩምባ መንፋት፣ ቤት መዋል፣ የሚሉ ነጥቦች እንደነበረበት መስክረዋል፡፡ 2ኛ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥር 155ኛ፣ 157ኛ፣ 166ኛ፣ 169ኛ፣ እና 176ኛ የተጠቀሱት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል፡፡

➢ በ1ኛ እና በ2ኛ ክስ የተመለከተው ወንጀል ለመፈፀም፣ 5ኛ፣ እና 16ኛው ተከሳሾች በወረዳ 10፣ 33ኛ፣ ተከሳሽ በወረዳ 20፣ 9ኛው ተከሳሽ በኮልፌ ቀበሌ 05 አዳራሽ እድር አዳራሽ 8ኛ፣ 9ኛው እና 22ኛው ተከሳሽ በኮልፌ በስሊጢ እድር አዳራሽ 4ኛ ተከሳሽ በኮተቤ ወረዳ ነሀሴ 19 ቀን 1997 ዓ.ም አባሎቻቸውን እና ደጋፊዎቻቸውን ሰብስበው ምርጫው ተጭበርብሯል የተቀማነውን ድምፅ ማስመለስ አለብን በማለት ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ ያደረጉባቸውን ቅስቀሳዎች ያስረዱልኛል ብሉ አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ምስክሮቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ሽልመጡ ደረሰ የተባለው 155ኛ ምስክር ነሐሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀጨኔ



Scanned by CamScanner

አካባቢ የሁለገብ ሸማኔዎች የህብረት ስራ ማህበር አዳራሽ በተደረገው ስብሰባ ተካፋይ እንደነበረ ገልፀው በወቅቱ የስብሰባው መወያያ አርዕስ በመድረኩ መሪው በ5ኛ ተከሳሽ ተነገረ እንዳለው ፖርላማ እንግባ እንግባ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተናል የሚል እንደነበረ በማውሳት በወቅቱ በተሳታፊዎቹ ውይይት እንደተደረገበት ፖርላማ አትግቡ ጫካ መግባት ወያኔ ብቻ ሳይሆን እኛም ጫካ መግባት እናውቅበታለን የሚሉ አስተያየቶች ይሰጡ እንደነበረ እና በሰኔ 1 ቀን የሞቱትን ማስታወስ አስፈላጊ መሆኑን ጭምር እያነሱ ተሳታፊዎች አሳባቸውን ይገልፁ እንደነበረ ከማስረዳትም በተጨማሪ ስብሰባው ሲጠናቀቅ 16ኛ ተከሳሽ በተደረገ የመዝጊያ ንግግር ትግሉ መቀጠል እንዳለበት እና ለቀጣዩ ጥሪ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን መግለፁን መስክሯል፡፡ 157ኛው የአቃቤ ምስክር ቴዎድሮስ ቦጋለ ነሀሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም በወረዳው 20 ቀበሌ 42 የመሰብሰቢያ አዳራሽ ቅንጅት በጠራው ስብሰባ መገኘቱን ገለፀው የሚከተለውን መስክረዋል 33 ተከሳሽ ከፍሌ ጥሩነህ ከተባለው ግለሰብ ጋር በመሆን የመድረኩ መሪ እንደነበረ ስብሰባው ሲጀመር በሰኔ 1 ወያኔ ኢህአዴግ ወገኖቻችን ስለጨረሰብን የህሊና ፀሎት እናድርግ ተብሎ በዚሁ መሠረት መከናወኑን እና የወቅቱ አጀንዳ ፖርላማ እንግባ አንግባ የሚል ሆኖ ተከሳሽ እና ከእሱ ጋር የነበረው ስሙ ከላይ የጠቀሰው ግለሰብ መሆናቸውን በስብሰባው ሂደት አብዛኛው ተሳታፊ ፖርላማ አትግቡ ፖርላማው በደም ተጨማልቀዋል እየተባለ ሲቀሰቀስ የነበረ ቢሆንም ምስክሩ ስሙ ያልጠቀው ተሳታፊ ፖርላማ ገብታችሁ የሚባለው ነገሩን ብሎ ሲናገር ወዲያውኑ እንዳስቆሙት በመጨረሻም በቀጣይ አመፅ ጥሪ ተዘጋጅ ብሉ ስብሰባውን መጠናቀቁን ገልፀዋል፡፡ ተስፋዬ አይፎክሩ የተባለው 169ኛ ምስክር ነሀሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም በወረዳ 24 ስልጤ እድር አዳራሽ ቅንጅት በጠራው ስብሰባ ተሳታፊ እንደነበረ በመግለፅ በወቅቱ የመድረክ መሪዎች የነበሩት 8ኛ 9ኛ እና 22ኛ ተከሳሾች መሆናቸውን የስብሰባው አጀንዳም ስለ ፖርላማ መግባት አለመግባት እንደነበረ በማስረዳት በተደረገው የመክፈቻ ንግግር ውስጥ 9ኛው ተከሳሽ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ በዶማ እና በዶንጋይ የታጠቀውን ሠራዊት እንዳባረረው አሁንም በዚህ መልኩ መብታችን እናስከብራለን ሲል መናገሩን በመቀጠልም

ሕዝቡ አስተያየት እንዲሰጥ ተደርጎ በህዝብ ከዝቡ ፖርላማ አትግቡ የሚል እና የህይወት መስዋዕትነት እንታገላለን ወደ ጌላ አንልም ወደ ቤተመንግስት እንገባለን የሚል አስተያየት ይሰጥ እንደነበረ በመጨረሻም አድማ በመምታት ብዙ ነገር የማድረግ መብቶች ስላሉን ለማደረግላቸው ጥሪ ዝግጁ ሆናችሁ ጠብቁን በማለት ከመድረክ በተደረገው የመዝጊያ ንግግር ስብሰባው መጠናቀቁን መስክረዋል 176ኛ ምስክር መኮንን ታዬ የተባለው ነሀሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም በወረዳ 28 የብረታ ብረት አዳራሽ ተብሎ የሚታወቀው የስብሰባ አዳራሽ በተጠራው የቅንጅት ስብሰባ የተገኘ መሆኑን ገልፀው ስብሰባው የተመራውም በ4ኛ ተከሳሽ እና አብሮት ከነበረው ረዳት ፕሮፌሰር ቶማስ ከተባለው ሰው ጋር መሆኑን ተከሳሹ የመክፈቻ ንግግሩን በ3 ምእራፎች በመከፋፈል ከምርጫ በፊት በምርጫ ወቅት እና ከምርጫ በኋላ በሚል የምርጫ ግምገማ ዙሪያ እንደነበረ ለንግግሩ መሀል በምርጫው አሸናፊ የሆነው ቅንጅት እንደሆነ እና ኢህአዴግ ምርጫውን እንዲጭበረበረ የሚያብራራ የሚገኝበት እንደነበረ ከዚህም በማያያዝ ህዝቡ አስተያየት እንዲሰጥ ተደርጉ በምንም አይነት ፓርላማ መግባት የለብቸውም የሚል እና እኛንተ እንደ ክብሪት ሁኑ እኛ ማገዶ እንሆናለን የሚል አስተያየት እንደተሰጠ በመጨረሻም ተከሳሹ ተከሳሾች ሀሳባችሁ ገብቶናል በአጭር ግዜ ውስጥ የህዝባዊ ማእበል ጥሪ እናደርጋለን ተዘጋጅታችሁ ጠብቁን ብሎ ስብሰባው እንዲቋጭ ማድረጉን መስክረዋል።

3/ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥሮች 46ኛ፣ 47ኛ 48ኛ 53ኛ የተመለከቱትን ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል በ1ኛ በ2ኛ እና 7ኛ ክሶች የተመለከቱትን የወንጀል ተግባር ለማሳካት ጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በተለይም 6ኛ 8ኛ 12ኛዋ 16ኛ 33ኛ ተከሳሾች በሰነድ ማስረጃ ተራ ቁጥር 29 የተጠቀሰውን ባለ 12 ገፅ ሰነድ የአመፅ ጥሪ ማብራሪያ መስጠታቸውን እና ማሰራጨታቸውን የሚከተለውን መስክረዋል። 46ኛ ያስረዱልኛል ብሉ ካስያዘው ጭብጥ አንፃር የአቃቤ ህግ ምስክር ሳሳሆልህ ከበደ በአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ 8 የቅንጅት ጽ/ቤት በተደረገው ተመራጭ መሆኑ ገለጸ ጥቅምት 20 ቀን 1998 ዓ.ም በቅንጅት ጽ/ቤት በተደረገው ስብሰባ እንደተገኘ እና በአቃቤ ህግ የሁሁፍ ማስረጃ በተራ ቁጥር 29 የተጠቀሰው ከቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ፖርቲ ለኢትዮጵያ ህዝብ የደረገ የለላማጨ ትግል ጥሪ በተባለው ሰነድ ዙሪያ በ8ኛ እና 12ተኛዋ ተከሳሾች 89 ለሚሆኑ

ተሰብሳቢዎች ማብራሪያ መስጠቱን ከማስረዳቱም ሌላ በሰነዱ ከተካተቱት ነጥቦች አብዛኛዎቹን ነጥቦች የጠቀሰ ሲሆን ከአፈፃፀም አኳያ የመኪና ጡርምባ እንዲነፋ በአንዳንድ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊዎች ላይ የማግለል እርምጃ እንዲወሰድ ቅስቀሳ መደረጉን እና ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም አንስቶ በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ሁከቶች መካሄዳቸውም ከመግለፁም በተጨማሪ በተለይም 12ኛዋ ተከሳሽ የጥሪው ይዘት በህግ የማያስጠይቅ መሆኑን ለተሰብሳቢዎቹ ስትናገር መስማቱን መስክረዋል፡፡ ተሾመ አለሙ የተባለው 48ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 20 ቀን 1998 ዓ.ም በቅንጅት ጽ/ቤት ተደርጉ በነበረው ስብሰባ መገኙቱን እና በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 3 የቅንጅት ተመራጭ መሆኑን በመግለፅ የመድረኩ መሪዎች የነበሩት 8ኛው 12ኛ 14ኛው እና 33 ተከሳሾች ሲሆኑ በ8ኛ ተከሳሽ ሰብሳቢነት ስብሰባውን ማካሄዱን ይሄ የስብሰባው ሂደት በአቃቤ ህግ የፁሁፍ ማስረጃ በቁጥር 29 የተመለከተው ሰነድ የሚያብራራ እና ለተግባራዊነቱም እያንዳንዱ ተሰብሳቢ በ3 ኮፒ እያባዛ ለህብረተሰቡ እንዲያሰራጭ እና ቅስቀሳ እንዲደረግ የሚል እንደነበረ በማስረዳት በ46ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ከተነገረው ጋር ተመሳሳይነት ያለው የምስክርነት ቃል ተሰጠ ሲሆን ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው አመፅ በወቅቱ ይደረግ ከነበረው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ጋር በተያያዘ መልኩ እንዲከናወን የተፈለገበት ዋና ምክንያት አለማቀፋዊ ድጋፍ ለማግኘት እና በመንግስት ላይም ጫና ለማሳደር ታስቦ እንደነበረ አብራርተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አቃቤ ህግ በተራ ቁጥር 47 እና 53 ቅደም ተከተል የተጠቀሱትን አስናቀ ሽምገማ፣ ታዬ በቀለ በ46ኛ እና በ48ተኛ ምስክሮች ከተሰጠው የምስክርነት ቃል የተለየ የምስክርነት አይሰጡም በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሳይሰጡ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ /መ/ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥሮች 92 እና 91 በ1ኛ ክስ እንደተመለከተው 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች የግንቦት 7ን ምርጫ ለመታዘብ በሚል የሲቪል ማህበራትን የወንጀል ለአድማው አላማ ማስፈፀሚያ ለማድረግ ባዘጋጇዋቸው ስብሰባዎች እና ስልጠናዎች ላይ የፈፀሟቸውን ተግባራት ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል መሠረት ወርቁ የተባለችው

Scanned by CamScanner

ተሰብሳቢዎች ማብራሪያ መስጠቱን ከማስረዳቱም ሌላ በሰነዱ ከተካተቱት ነጥቦች አብዛኛዎቹን ነጥቦች የጠቀሰ ሲሆን ከአፈፃፀም አኳያ የመኪና ጡርምባ እንዲነፋ በአንዳንድ የኢ.ሀ.አ.ዴ.ግ ደጋፊዎች ላይ የማግለል እርምጃ እንዲወሰድ ቅስቀሳ መደረጉን እና ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም እንስቶ በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ሁከቶች መካሄዳቸውም ከመግለፁም በተጨማሪ በተለይም 12ኛዋ ተከሳሽ የጥሪው ይዘት በህግ የማያስጠይቅ መሆኑን ለተሰብሳቢዎቹ ስትናገር መስማቱን መስክረዋል፡፡ ተሾመ አለሙ የተባለው 48ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 20 ቀን 1998 ዓ.ም በቅንጅት ጽ/ቤት ተደርጐ በነበረው ስብሰባ መገኙቱን እና በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 3 የቅንጅት ተመራጭ መሆኑን በመግለፅ የመድረኩ መሪዎች የነበሩት 8ኛው 12ኛ 14ኛው እና 33 ተከሳሾች ሲሆኑ በ8ኛ ተከሳሽ ሰብሳቢነት ስብሰባውን ማካሄዱን ይሄ የስብሰባው ሂደት በአቃቤ ህግ የፁሁፍ ማስረጃ በቁጥር 29 የተመለከተው ሰነድ የሚያብራራ እና ለተግባራዊነቱም እያንዳንዱ ተሰብሳቢ በ3 ኮፒ እያባዛ ለህብረተሰቡ እንዲያሰራጭ እና ቅስቀሳ እንዲደረግ የሚል እንደነበረ በማስረዳት በ46ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ከተነገረው ጋር ተመሳሳይነት ያለው የምስክርነት ቃል ተሰጠ ሲሆን ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው አመፅ በወቅቱ ይደረግ ከነበረው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ጋር በተያያዘ መልኩ እንዲከናወን የተፈለገበት ዋና ምክንያት አለማቀፋዊ ድጋፍ ለማግኘት እና በመንግስት ላይም ጫና ለማሳደር ታስቦ እንደነበረ አብራርተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አቃቤ ህግ በተራ ቁጥር 47 እና 53 ቅደም ተከተል የተጠቀሱትን አስናቀ ሽምገማ፣ ታዬ በቀለ በ46ኛ እና በ48ተኛ ምስክሮች ከተሰጠው የምስክርነት ቃል የተለየ የምስክርነት አይሰጡም በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሳይሰጡ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ /መ/ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥሮች 92 እና 91 በ1ኛ ክስ እንደተመለከተው 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች የግንቦት 7ን ምርጫ ለመታዘብ በሚል የሲቪል ማህበራትን የወንጀል ለአድማው አላማ ማስፈፀሚያ ለማድረግ ባዘጋጅዋቸው ስብሰባዎች እና ስልጠናዎች ላይ የፈፀሟቸውን ተግባራት ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል መሠረት ወርቁ የተባለችው



Scanned by CamScanner

92ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር [illegible]
መምህራን ገለፃ የሚከታተሉትን [illegible]
ግንቦት 2 እና 3 97 ዓ.ም [illegible] የምርጫ [illegible]
ስልጠናው የመድረክ መሪ እና [illegible]
እንደነበረ በወቅቱ ከተከሳሾቹ [illegible] ኢህአዴግ [illegible]
እያጭበረበረ ምርጫውን ለማሸነፍ ጥረት ያደርጋል ኢህአዴግ [illegible] ነው፡ መስራት
ለሚያጠፉ ተጠንቀቃችሁ ጠብቁ፤ ባትረም ያስጠቻገል የሚል እና ምርጫውን
እንዴት መታዘብ እንዳለባቸው የሚያስረዳ እንደነበር ከተከሳሾቹ አንዱ የሌላውን
ሀሳብ በመደገፍ እና አንዱ የተናገረውን ሌላውን በመድገም ኢህአዴግ ገዢው
ፓርቲ ያጭበረብራል፤ ተግታችሁ ጠብቁ እያሉ ከመናገራቸው በቀር ቅንጅት
ወይንም ህብረት ያጭበረብራል ብለው ሲናገሩ ባለመስማቷ እንደ አንድ የሲቪል
ሶሳይቲ ሳይሆን ወደ አንድ ያዘነበለ የተቃውሞ ፓርቲ ስለመሰላት የተዘጋጀው
ስልጠና አካሄድ እንዲስተካከል ሀሳብ ለመስጠት ብትሞክርም ተቀባይነት ባለማግኘቷ
ጉዳዩን በወቅቱ ወክላው ለመጣችበት ማህበር ማሳወቋን በስልጠናው ቀን በጠዋት
ክፍለ ግዜ ስልጠናውን ከተከፈተ በኋላ የተከሳሾቹ በውል ማስታወስ ያልቻለችው
አንዱ ለፍርድ ቤት ቀጠሮ አለብኝ በሚል በመሀል ስልጠናውን አቋርጦ የሄደ
ቢሆንም ከሰዓት በኋላ መመለሱን በማስረዳት ከዚህም በተጨማሪ ግሎባል ሆቴል
ከተሰጠው የምርጫ ታዛቢነት ስልጠና በኋላ ግንቦት 6 ቀን 1997 ዓ.ም በሲአርዲኤ
ገለፃ ሲሰጥ መካፈሏን እና ለእየቡድኑ መብራት ቢጠፋ መገልገያ ይሆናል በሚል
አንዳንድ ባትሪ መሰጠቱንም ጭምር መስክራለች። ንግስት መኳንንት የተባለችው
91ኛዋ የአቃቤ ህግ ምስክር በበኩሏ የሚከተለውን መስክራለች ስለ ምርጫ 97
በነበረው የሲቪል ሶሳይቲ የምክክር መድረክ በተነሱ ነጥቦች ዙሪያ በተለይም እሷ
በወከለችው የአዲስ አበባ ከተማ ሴቶች ማህበር ሊቀመንበር የስብሰባ ተካፋይ
እንድትሆን ተነግሯት ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም በቀይ መስቀል አዳራሽ
በተደረገው የግማሽ ቀን ስብሰባ ተካፋይ እንደነበረች ተናግራ ስብሰባውን የጠራው
የሲቪል ሶሳይቲ ኔትወርክ መሆኑን ስብሰባውን ይመሩ እና ያስተባብሩ የነበሩት
94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች አቶ ዳንኤል በቀለ እና ከተባሉት ሰው ጋር በመሆኑን
እንደነበር የስብሰባው አላማ በምርጫው ዙሪያ በተቃዋሚዎች እና በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ
መካከል በነበረው አለመግባባት ምክክር ለማድረግ መሆኑን በዚህ ጉዳይ የሲቪል



Scanned by CamScanner

ለሰቋሊው ድርሻ ምን መሆን አለበት ከሚል ክ... ከተሳታፊዎች መካከል መንግስት አፋኝ ነው ምርጫው ተጭበርብሯል በወቅቱ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ምርጫ ጣቢያዎች እንደገና ምርጫው መካሄድ አለበት ሚዲያው መዘገብ አለበት የሚል ሀሳብ ይሰጥ እንደነበር እና ተከሳሾችም መንግስት አፋኝ ነው ምርጫው ተጭበርብሯል በሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ምርጫ ጣቢያዎች ምርጫው ይደገም በማለት 94ኛው ተከሳሽ ሊናገር መስማቷን እና 95ኛውም በተጨማሪ ይህንን ደግሞ መናገሩ ከዚህም በተጨማሪ 94ኛ ተከሳሽ ተቃዋሚዎች ተጨንቀዋል አማክሩን መፍትሄ ስጡን፣ ብለውናል ስለዚህ የሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ የምርጫ ጣቢያ ድምፅ ተጭበርብሮ የምርጫ ቦርድ መግለጫ ከመስጠቱ በፊት አንድ ነገር ማድረግ አለብን ሲል መስማቷን በሌላ በኩል ግዜያዊ መንግስት መቋቋም አለበት ምርጫው ቦርድ ገለልተኛ አይደለም የመንግስት አካል ነው መቀየር አለበት፣ በምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤት መነገር የለበትም መግለጫው ቢወጣ መንግስትን ደግፎ ነው ሲባል ከተከሳሾቹ መስማቷን በአጠቃላይ በስብሰባው ቅንጅት ተቃዋሚዎች ወደ ፓርላማ ይግቡ አይግቡ የሚሉ ሀሳቦች ይራመዱ እንደነበረ ገለፃ ስምምነት ላይ ባለመድረሱ በጉዳዩ ላይ የሚደረግ ቀጣይ ስብሰባ የአቋም መግለጫ ለማውጣት 5 አባላት ያሉበት አዘጋጅ መመረጡን እና ይደረጋል በተባለው ስብሰባ ግን አለመገኘቷን በስብሰባው ግዜ ተከሳሾች ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር የማነሳሳት ስራና መንግስትን ለመቀየር የሚያደርግ እንቅስቃሴ ያሳዩ ነበር ከዚህ አንፃር አላማውን ስቶ ነበረ በማለት መስክራለች።

- /ሠ/ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥር 89 ስሙ የተመለከተው 26ኛ፣ 94ኛ 95ኛ ተከሳሾች በ1ኛው የወንጀል ክስ የተመለከተው የወንጀል አላማ ለማሳካት ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም እና ጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በተነሱት አመፆች ስለነበራቸው ተሳትፎ ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ላስያዘው ጭብጥ የሰጠው የምስክርነት ቃል በዚሁ ጭብጥ ላይ በተለይ በ94ተኛው ተከሳሽ 111ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር የሰጠው የምስክርነት ቃል እንደሚከተለው ነው አዲስ በቀለ የተባለው ይሄው 89ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር

Scanned by CamScanner

ከማንበብ ~~97 ምርጫ~~ ጋር በተያያዘ ከ95ኛው ተከሳሽ ጋር የነበረውን ግንኙነት በተመለከተ ለመመስከር መቅረቡን ገለጾ ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ከአካባቢው ህብረተሰብ ቅንጅትን እንዲመርጥ ወጣትን ማስተባበር፣ ወጣት በዘኔ እንዲሁን እና የተለያየ ህብረተሰብ ክፍሎች ከስራ እንዲፈናቀሉ ያደረገው ለአንድ ብሄር የትግራይ ብሔር የሚያደላው የገዢ ፓርቲ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሆኑን 95ኛው ተከሳሽ ይነግረው እንደነበር ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያመጣው ለውጥ የለም ጥቂት የትግራይ ተወላጆች ተጠቃሚ ከመሆናቸው በቀር ስለዚህ በዚህ መሠረት ቅስቀሳ አድርገህ ቅንጅት እንዲመረጥ ህዝቡን በተለይ ወጣቱን አስተባብር እንዳለው ከምርጫ በኋላ ኢ.ህ አ.ዴ.ግ አጭብርብሯል በማለት አመፅ እና ሁከት እንዲነሳ ከአካባቢ ያሉትን ኑዋሪዎች መቀስቀስ እና ማስተባበር በራሪ ወረቀቶችን መበተን አንዱ ወረቀት ተባዝቶ ለ5 ሰዎች እንዲሰጥ ለተከሳሽ እንደተሰጠው መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ.ም ቅንጅት እና ህብረት በጠሩት ሰልፍ ፖሊስን ሳይፈሩ ፊለፊት ተጋፍጠው ሰልፍ መውጣት እንደሚገባቸው ለተከሳሹ እንደተነገረው ሰልፍ የሚወጡ ወጣቶችን ማስተባበር የአንበሳ አውቶብሶችን የመንግስት ተቋውሞዎችን ማውደም የእሳት ቃጠሎ ማንሳት እንደሚገባ ተከሳሽ የነገረ መሆኑን ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢዎች ረብሻ ተነስቶ ነበረ ቢሆንም በአዲሱ ገበያ ይህ አይነቱ ረብሻ ስላልነበር እናንተ እያላችሁ እንዴት ዝም ትላላችሁ ከማን ታንሳላችሁ በማለት ለረብሻው እንዲዘጋጁ የነገረ መሆኑን ከዚህም በመነሳት በአዲሱ ገበያ አካባቢ ኢንሺስተሮች ያጠሩትን አጥር እሱ እና ሌሎች ወጣቶች ማፈራረሳቸውን ጎማ ማቃጠላቸውን አውቶቢሶች እና ታክሲዎች ስራ እንዳይሰሩ ማድረጋቸውን ለዚህም ጉዳይ በተለያዩ ግዜያት ከ30 እስከ 60 ብር ይከፈለው እንደነበረ ቅንጅት ሲያሸንፍ ስራ እንደሚሰጠው ቃል እንደተገባለን 26ኛ እና 94ኛ ተከሳሾቹም በተመሳሳይ ሁኔታ የቅስቀሳ እና የማስተባበር ተግባር እንዲያከናውን እና ወረቀት እንዲበትን ይነግሩት እንደነበረ ሲበትነው የነበረውን ወረቀት በአቃቤ ህግ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃነት የተያያዘው አይቶ መለየቱን ማለትም የካርዳችን ድምፅ የካርዳችን ድምፅ ይሰማ ጥሪ ለአዲስ አበባ ወጣቶች የሚሉ እና ለባለስልጣኖች በውጪ አገር ባንኮች የተቀመጠ ገንዘብ ልክ እና ለባለስልጣኖቹ ስም የተመለከተበት እንደነበር ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የምርጫ ምልክት ያለበትን ካኒተራ ለብሰው



Scanned by CamScanner

ቅንጅት እንዲመረጥ እንዲቀሰቅስ እና መረጃ እንዲያሰባስብ በተነገረው መሠረት ይሄንን መፈፀሙን በዚሁ ተግባሩ ተፀፅቶ ለአንድ ወር ያህል ከተሰወረበት በመውጣት በትክክል በማያስታውሰው ቀን እጁን ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ሰጥቶ እንደነበር እና ስለሁኔታው ለፖሊስ ቃሉን በመስጠት ስትፈለግ ትጠራለህ ተብሎ መሰናበቱን እና ከተወሰነ ግዜ በኋላ ቀኑን የማያስታውሰው በተለምዶ ማእከላዊ ፖሊስ ተብሎ ወደ ሚታወቀው ተጠርቶ በመሄድ ስለሁኔታው ካስረዳ በኋላ ያነጋገረው ፖሊስ ሲበትናቸው ከነበሩት ወረቀቶች ቀሪ እንዳለው እንዲያወጣ በጠየቀው መሠረት በሰነዶቹ ግርጌ ከ95ኛ ተከሳሽ የተሰጠ መሆኑን በፖሊስ ማፃፎን እና መፈረሙን በመግለፅ በወረቀት ግርጌ በ5 ተባዝቶ እንዲሰጥ የሚለው የእጅ ፁሁፍ ግን ተዘጋጅቶ እንደተሰጠው አመልክተዋል፡፡ ከዚህ ሌላ 94ኛ ተከሳሽ ግዜያዊ የሽግግር መንግስት መቋቋም እንዳለበት ይሄ ካልተሳካ ለቀጣይ ሁከት ለመፍጠር ቅንቅስቃሴ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይሆን በብዙ የአገሪቱ ክፍሎች የሚካሄድ ስለሆነ የኢ.ህ.አ.ዲ.ግ መንግስት ከስልጣን እናወርዳለን ብሎ እንደነገረው የገለፀ ሲሆን በዚህ ጉዳይ እነማንን እንዳስተባበረ እና እንደቀሰቀሰ ተሰጠኝ ያለው ወረቀት ለእነ ማን እንደሰጠ በስም እንዲጠቅስ ተጠይቆ ተግባሩን ያከናወነው በታክሲ ውስጥ በእየአደባባይ እና በእየመጠጥ ቤቶቹ አካባቢ ነው በማለት ማንነታቸው ለመለየት እንደማይችል መስክረዋል፡፡ ወንድወሰን ስዩም የተባለው 111ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር በተለይ በ94ኛው ተከሳሽ ተከታዩን የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፡፡ ቀኑን ለይተው ባለወቀው በሰኔ ወር 1997 ዓ.ም ከተከሳሹ ጋር ኢዴአፖ መድን ቢሮ በምስክሩ አገላለፅ በወቅቱ ቅንጅት በሚባለው ድርጅት እሱ በሚሰራበት ቢሮ አካባቢ ከሚገኝ ሻይ ቤት ጎሹ ከተባለ ሌላ ግለሰብ ስለ ቅንጅት ጉዳይ በአሰራር ዙሪያ እየተወያዩ በነበረበት አጋጣሚ ከተከሳሹ ጋራ ለመጀመሪያ ግዜ መገናኘታቸው እና ተከሳሹ ውይይታቸውን ካዳመጠ በኋላ በስራው እንዲቀጥልበት በርታ እንዳለው ከ15 ቀን በኋላ ባደረጉት ግንኙነት ስለፖርቲው ቀጣይ እንቅስቃሴ ምን መምሰል እንዳለበት ቻይና ሬስቶራንስ አካባቢ መንግድ ላይ ቆሞ መወያየታቸው እና በተለይም ወጣቶችን እንዴት ማደራጀት እንደሚገባ



Scanned by CamScanner

ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በአፈሙዝ በመግዛት ላይ ያለ ፓርቲ መውደቅ እንዳለበት መነጋገራቸውን ለዚህ ተግባሩ መሳካት ደግሞ ወጣቶችን ለአድማ ማሰባሰብ ፖምፕሌቶችን መበተን እንደሚያስፈልግ ተነጋግረው ለዚሁ አላማ ማስፈፀሚያ እና በወቅቱ ለተፈጠረው እንቅስቃሴ ህዝቡን ለማስተባበር የወረቀት ማባዣ እና ለፎቶ ኮፒ ብር /200/ /ሁለት መቶ/ ከተከሳሽ እንደተሰጠው በዚህም ወጣቶች እና በየመንገዱ የሚያገኛቸውን ሌሎች ሰዎች ሁሉ ስለምርጫው ውጤት ይቀሰቅስ እንደነበረ በመጀመሪያ የተከሳሽ እና የምስክሩ ግንኙነት ተከሳሹ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ለመጣል መበርታት አለብን ህዝቡ የተወሰደበትን ድምፅ ለማስመለስ በሚያደርገው እንቅስቃሴ መንግስት አፈሙዝ የሚጠቁም ከሆነ እየተንቀሰቀሱ አድማው እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚገባ ተከሳሹ የነገረን መሆኑን እና ከዚህም በኋላ ሁከት ተፈጥሮ በየአካባቢ የእሳት ቃጠሎ መነሳቱን ከዚያም መንግስት ይፈልገኛል በሚል ስጋት እራሱን ሰውሮ ቆይቶ ህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም ለወረዳ 21 ፖሊስ እጁን መስጠቱን እና ወደ ማእከላዊ ፖሊስ ምርመራ ተወስዶ ስለፈፀመው ተግባር ቃሉን በመስጠቱ ስትፈለግ ትጠራለህ ተብሎ መለቀቁን ጭምር ገልፀዋል። ከዚህ ጋር በማያያዝ ስለቀሰቀሷቸው ሰዎች ማንነት በስም እንደማያስታውስ እና የቅስቀሳውን ስራውን ያከናውን የነበረው በእየመንገዱ ከሚያገኛቸውን ሰዎች ስለጉዳዩ በመነጋገር እንጂ በመሰብሰብ እንዳልነበር እና ለዚህ ማስፈፀሚያ ቢሮ እንዳልነበረው እንዲሁም እራሱን ሰውሮ በነበረበት ውቅት የተደበቀባቸው ሰዎች ገዢው ፖርቲው ኢ.ህ.አ.ዴግ እንደሚፈልገው ስለነገራቸው እንደደበቁት እንጂ ማንነታቸው እንደማያውቅ አስረድተዋል ከዚህ በኋላ አቃቤ ህግ 88ኛ 10ኛ እና 158ኛ ምስክሮች በ89ኛ 111ኛ ምስክሮች ከተነገረው የተለየ አያስረዱልኝም በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሳይሰጡ ተሰናብተዋል /ረ/ በአቃቤ ህግ ስም ዝርዝር በተራ ቁጥር 97 እና 108 የተመለከቱት ምስክሮች በ1ኛ 2ኛ እና 7ኛ ክሶች በተመለከተው የወንጀል ተግባር 29ኛ 113ኛ 114ኛ 116ኛ 117ኛ እና 118ኛ ተከሳሾች ወረዳ 7 ቀበሌ 32 ወይንም ቀበሌ 13 15 ጽ/ቤት አካባቢ በመሩት እና በአስነሱት አመፅ ጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ለደረሰው ጉዳት ስለነበራቸው ተሳትፎ ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ የሰጡት የምስክርነት ቃል። 97ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ተስፋዬ ሹምዬ በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 15 ጽ/ቤት አካባቢ



Scanned by CamScanner

ጥቅምት 22 እና 23 1998 ዓ.ም ስለነበረው ረብሻ የቀበሌው ጽ/ቤት እና አዳራሽ ጉዳት እንደደረሰባቸው በተለይም የእሳት ቃጠሎ ተነስቶ በህዝብ ንብረት እና የእሳት አደጋ መከላከያ ሰራተኞች በህዝብ እርዳታ እና የእሳት አደጋ ቃጠሎ ሰራተኞች የቀበሌ ጽ/ቤት እና አዳራሽ ጉዳት እንደደረሰባቸው በተለይ የእሳት ቃጠሎ ተነስቶ በህዝብ ጥሬት እና የእሳት አደጋ መከላከያ ሰራተኞች መጥፋቱን በረብሻው ጽ/ቤት እና የአዳራሹ መስታወቶች በድንጋይ መሰባበራቸውን ግድግዳዎቻቸውም በእሳት መለብለባቸውን እንዲሁም ወንበሮች መቃጠላቸውን በማስረዳት ሁሉቱን ያነሱት 29ኛው 113ኛ 114ኛ 115ኛ 116ኛ 117ኛ እና 118ኛው ተከሳሾች መሆናቸው በመዘርዘር ምክንያታቸውም ምርጫው ተጭበርብሯል የሚል እንደነበረ ገልፀው በድርጊቱም 7ቱ ተከሳሾች እንደተሳተፉበት እና በተለይም 29 ተከሳሽ ይሄንን የወያኔ መንግስት ወደ መጣበት ጫካ እንዲመለስ እናደርገዋለን አይሏቹ በርቱ ድሉ የኛ ነው እያለ ሲያስተባብር እንደነበረ በሁለቱም ቀናቶች ውስጥ የቀበሌው ንብረት እንዲወድም መደረጉን ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም ሲዘረዝር ተከሳሾች በቡድን በቡድን ድንጋይ በመወርወር ለቃጠሎም የሚሆን ጎማ ላይ ጋዝ በማርከፍከፍ፣ እና ክብሪት በመጫር በተለይም 118ኛዋ ተከሳሽ ጋዝ በማቅረብ መሆኑን ገልፀው በአዲስ አበባ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካባቢ እና ጩሄው በረንዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በድንጋይ በሚቀጣጠሉ ጎማዎች መንገዶች ተዘግተው እንደነበር ተከሳሾቹም አትነሳም ወይ እያሉ መንገደኞችን ጭምር ወደ ረብሻው እንዲቀላቀሉ ያስተባብር እንደነበረ በማስረዳት ተከሳሾቹን ማንነት እንዲለይ ተደርጎ ሌሎችን በትክክል ሲያመለክት ነገር ግን 114ኛ ተከሳሽ ምንአለ ገብርኤ 116ኛ ተከሳሽ ገዛኸኝ ተሰፋዬ ነው በማለት እንዲሁም 116ኛ ተከሳሽ ገዛኸኝ ተስፋዬን ነው በማለት እንዲሁም 116ኛ ተከሳሽ ገዛኸኝ ተስፋዬን 114ኛ ተከሳሽ ምንአለ ገብሬ ነው በማለት በትክክል ሲያመለክት አልቻለም አፀደ ወ/ገብርኤል የተባለችው 100ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 21 ቀን 1998 በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 15 ጽ/ቤት አጠገብ 113ኛ 114ኛ 116ኛ 117ኛ 118ኛ ተከሳሾች የትርፍር /ነገድ

Scanned by CamScanner

የምትሰራበትን መደብ እንዳፈረሱበባት ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም እና ድንጋይ በመወርወር የቀበሌውን ጽ/ቤት እና ወደ አዳራሹ በመወርወር የእሳት ቃጠሉ እንዲነሳ ማድረጋቸውን እና በህዝብ ትብብር በእሳት አደጋ ሰራተኞች ቃጠሉው እንዲጠፋ መደረጉን በእሷም ላይ በተለይ ተከሳሾቹ አደጋ ሲያደርሱባት በላት እያሉ ይቺን አቃጣሪ ትግሬ እናቃጥላታለን ብለው ወደ መኖሪያ ቤቷ እንደሄዱ እና በፌደራል ፖሊስ እርዳታ እንደዳነች እና ጩኸት ብታሰማም እንኳን ሌላ እረዳት እንዳላገኘች በማስረዳት መስክራለች:: ስለ ተከሳሾች የወንጀል ተሳትፎ በተለይ 113ኛው ተከሳሽ ድንጋይ ሲወረውር የቀበሌውን ጽ/ቤት መስታዎቶች ሲሰባበር በእሱ ምክንያት ሁከቱ እንደተነሳሳ እንዲሁም 118ኛው ተከሳሽ ከአካባቢው ከሚገኘው ሱቅ ጋዝ አምጥታ ለሌሎች ተከሳሾች ስታቀብል እና ተከሳሾቹም ጋዙን ጎማ ላይ በማርከፍከፍ እና በማቀጣጠል ሲወረውሩ ማየቷን ገልፃ ከዚህም በተጨማሪ ተከሳሾቹ በእየትግሬው ቤት እንሄድ ብለው በግልፅ ይጨፍሩ እንደነበረ በማብራራት ስለእያንዳንዱ ተከሳሽ ማንነት በመለየት ያመለከተች ቢሆንም 114ኛውን ተከሳሽ ምንአለ ገብሬ 116ኛ ተከሳሽ ገዛኸኝ ተስፋዬ ነው በማለት በትክክል መጠቆም አልቻለችም::

ሠ/ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ስም ዝርዝር በተራ ቁጥር 55 56 59 61 62 63 64 66 እና 78 በ1ኛ 2ኛ 7ኛ ወንጀል ክሶች በተመለከቱት የወንጀል ተግባራት ተከሳሾች ስለነበራቸው ተሳትፎ እና በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በተከሳሾች አማካኝነት ጉዳት ደርሶባቸው የጉዳቱ ሰለባ ከነበሩት ሰዎች መካከልም ምስክሮቹ ይገኙበታል በማለት አቃቤ ህግ በአጭሩ በአስያዘው ጭብጥ የሰጡትን የምስክርነት ቃል እንደሚከተለው ነው አፈወርቅ አሰፋ የተባለው 55ተኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ስለተፈጠረው ሁከት በተለይ አዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በተለምዶው 7ኛ በሚባለው አካባቢ በቀበሌ 11 የህዝብ ክበብ ጉዳት መድረሱን በመግለፅ ~~ስለ~~ ጉዳዩ መነሻ ምክንያት እና ስለደረሰው ጉዳት ሲያስረዳ በምርጫው ~~ምክንያት~~ ግርግር መነሳቱን ቁጥሩ በ100ዎቹ የሚቆጠር ህዝብ ድንጋይ እና ገጀራ ~~ይዞ~~ ሲንቀሳቀስ ማየቱ የድንጋይ ውርወራ እና ጋዝ ያለው ጠርሙስ እንዲሁ እየተወረወረ ስለነበረ የእሳት ቃጠሎ ተነስቶ ማየቱን በሚወረወረው ድንጋይ



Scanned by CamScanner

በአካባቢው በነበሩት ሱቆች እና መስታወቶች እና የከበብ መስታወቶች

በአካባቢው በነበሩት ሱቆች እና መስታወቶች እና የከበብ መስታወቶች በፌዴራል ፖሊስ እርዳታ መሰባበራቸውን በከበቡ ላይ ቃጠሎ ተነስቶ በፌዴራል ፖሊስ እርዳታ መሰባበራቸውን በከበቡ ላይ ቃጠሎ ተነስቶ በፌዴራል ፖሊስ ኮንትሮል መኪና እና በህዝብ እንዲጠፋ መደረጉን በአካባቢ በነበረ አንድ የግል ፖትሮል መኪና እና በህዝብ አውቶብሶች ላይ ጉዳት ሲደርስ መመልከቱን በተለይም በአብነት ወደ መርካቶ ይሄድ የነበረው አንድ አውቶብስ ላይ የቃጠሎ ሙከራ ተደርጎ በፖሊሶች እርዳታ መጥፋቱን ከማስረዳቱም በተጨማሪ በወቅቱ በፖሊሶች ላይ ስለደረሰው ጉዳት ሲያስረዳ ከ8 ያለነሱ የፌዴራል ፖሊስ አባላት በድንጋይ ውርወራ እና በገጀራ ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታል መውሰዱን በተለይ ከተጎጂዎቹ አንዱ የፖሊስ አባል ሆስፒታል እንደደረሰ ህይወቱ ማለፉን እና በሁለት በኩል ስለት ባለው መሳሪያ መመታቱን በማየት መስከረዋል በሁከቱ የነበሩትም የቅንጅት አርማ ያለበትን ይዘው እንደነበር እና የወያኔ መንግስት ወደ መጣበት ይመለሳል የተማረ ይግዛን ሲሉ መስማቱን አክለው ገልፀዋል 59ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጌታቸው ብርሃኔ ጥቅምት 23 እና 24 1998 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ አካባቢ በተለይ በቀበሌ 16 እና 17 ግንቦት 20 ትምህርት ቤት አካባቢ ተፈጥሮ ስለነበረው ረብሻ እና ግርግር ሲያስረዳ የትምህርት ቤትን በር እና አጥር ተሰብሮ ተማሪዎች እንዲወጡ መደረጋቸውን ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር በቡድን በቡድን እየሆነ ከረብሻው ሲቀላቀል ማየቱን እና ኢህአዴግ ሌባ መለስ ሌባ ቀበሌ ሌባ እያሉ እረብሾኞቹ ሲጮሁ መስማቱን ጥቅምት 24 ማታ በቀበሌ ጽ/ቤት የእሳት ቃጠሎ ሙከራ መደረጉን እና ቃጠሎውም ጋዝ በመርጭት መካሄዱን ነገር ግን ቃጠሎውን እንደተቆጣጠረው ብዛት ያለው ድንጋይ ውርጅብኝ እንደነበረ በማስረዳት ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓ.ም በምሽቱ 2 ሰዓት አካባቢ ብዛት ያላቸው ሰዎች በመኖሪያ ቤቱ ላይ ከፍተኛ የድንጋይ ናዳ በመወርወር እና አጥሩን በማቃጠል ጥቃት እንዳደረሱበት ከዚህም የተነሳ በቤተሰቡ ላይ የአይምሮ ጭንቀት እና የጤና መታወክ መድረሱን በተለይም በህፃን ልጁ ላይ በደረሰው የአይምሮ መታወክ ሳቢያ ባለቤቱ ከስራ መሰናከሏን በዝርዝር የገለፀ ሲሆን ለዚህ ሁሉ ጉዳት ያጋለጠው የቀበሌው የሲቪል እና ማህበራዊ ጉዳይ ሀላፊ በመሆኑ እና በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባልነቱ ምክንያት በምርጫው ባደረገት

Scanned by CamScanner

እንቅስቃሴ ነው የሚል ግምት እንዳለው አክሎ አስረድቷል አበባ እሸቱ የተባለችውን 62ኛዋ ምስክር ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በአካባቢዋ በተለይ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 17 ክልል ገነመ ትምህርት አካባቢ ሁከት ተፈጥሮ እንደነበረ እና እርሷ በምትሰራበት ቀበሌ ጽ/ቤት አቅራቢያ ከፍተኛ የህዝብ ጩኸት ይሰማና ጎማ እና ጎማም እየተቀጣጠለ እንደነበረ በደረሳት መረጃ መሠረት ለበላይ አለቃዋ ማሳወቋን በአካባቢ ይሰማ የነበረው ያለችው ጩኸትም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሌባ ነው የሚል እንደሆነ በመግለፅ ሁኔታው በሁኔታዋ በመረበሽዋ ወደ ቤተሰቦቿ ስልክ በመደወል ለእርሷ ከቤተሰቦቿ ጋር የምትኖሪበት የግል መኖሪያ ቤት በእሳት መያያዙን መስማቷን በተጨማሪም የወያኔ ቅጥረኛ ነኝ ነች እያሉ እየጮሁ ስለነበረ አደጋ እንዳይደርስባት በመፍራት ወደ ቤት እንዳትመጣ እንዳትሄድ እንዳትመጪ ስለተባለች በአካባቢው የነበረው ሁኔታ እንዲመለከቱላት የላከቻቸው ሰዎች በመኖሪያ ቤቷ በእሳት መያያዙን እና በቤት ውስጥ የነበሩትንም መገልገያ ንብረቶቿ የግል አልባሶቿን ጨምሮ ግምታቸው እስከ /አስራ ሰባት ሺህ ብር/ የሚደርስ ንብረት ሜዳ ላይ እያወጡ ሲያቃጥሉ ማየታቸውን እንደነገሯት እና የተረፈውንም መዝረፋቸውን በመመስከር በዚህ ጉዳይ ያጋለጣትም በቀበሌው በልዩ ልዩ ደረጃ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ተወካይ እና ሹመኛ ሆና ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ መስራቷን ሊሆን ይችላል የሚል ግምት እንዳላት በመግለፅ ሁኔታው በቤተሰቦቿ ላይ በተለይም በወላጅ እናቷ ላይ ከኑሮ የመፈናቀል እና የመንገላታታት ጉዳት ያስከተለባቸው መሆኑን አስረድታለች 63ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር እድሉ መሀመድ ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም ጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ስለተፈጠረው እረብሻ እና እርሱ በሚሰራበት የአነስተኛ ጥቃቅን ንግድ ተለጣፊ ሱቅ ስለደረሰው ጉዳይ ሲያስረዳ በወቅቱ በተፈጠረው እረብሻ ሱቁ እንደተቃጠለበት እና ግምቱ ብር አራት ሺህ የሚሆን ንብረት እንደወደመበት ከዚያም ወዲህ የጤና መታወክ እና በኑሮ ላይ ችግር እንዳጋጠመው በመግለፅ አሁንም የመገለል ሁኔታ እየደረሰበት እንዳለ ጥቃቱ ሊደርስበት የቻለውም የምርጫ ሂደት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊ ሆኖ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እንዲመረጥ ይቀሰቅስ ስለነበር ሊሆን እንደሚችል ግምቱን አክሎ አብራርቷል መብራት ተስፋዬ የተባለችው 64ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 22 እና 23፥29 1998 ዓ.ም በእየቀናቱ ከምሽቱ 1 ሰዓት በኋላ ቤቷ በድንጋይ ኡርምታ መደብደቡን

እና ደሄ አይነቱ ጥፋት በአካባቢው ካሉ ጉረቤቶቿ ላይ ሳይደርስ በእሷ ብቻ ያነጣጠረ እንደነበር እና ሁኔታውን በወቅቱ በአካባቢው ፖሊስ በማሳወቅ እርዳታ እየተደረገላት በአደጋ መትረፏን ገልፃ በጥፋቱ ምክንያት ስለ ህፃን ልጅዋ እና ስለእራስዋ ደህንነት ከፍተኛ ጭንቀት ላይ እንደነበረች በማብራራት የዚህ አይነት ጥቃት በእርሷ ላይ ሊደርስ የቻለውም በትግራይ ብሔረሰብ ተወላጅነቷ እና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሰራዊት የቀድሞው አባል መሆኗን ምክንያት በማድረግ ሊሆን እንደሚችል ገልፃለች 50 አለቃ ጌቱ ረዳይ የተባለው 66ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር እርሱ በሚኖርበት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በቡድን በተደራጁ ሰዎች ድንጋይ በመወርወር እና አካባቢውን በጭኸት በመረበሽ ላይ እንደነበሩ የትግራይ መንግስት እናጠፋለን ትግሬዎች ወየውላቹ እያሉ ሲጮሁ መስማቱን በአካባቢው ኮነሬል አርአያ ነው ያለው ግለሰብ መኖሪያ ቤት ሲቃጠል ማየቱን በመቀጠልም አንድ የሚቃጠል ቤት ይቀረናል ብለው ወደ እሱ ቤት ሲያመሩ የፀጥታ ሀይሎች በመምጣታቸው መበተናቸውን የረብሸኞቹ ብዛት ከሁለት መቶ ሃምሳ እስከ ሶስት መቶ ሊደርሱ እንደሚችሉ በመግለፅ በወቅቱ ረብሻውን ይመሩ የነበሩት 96ኛ እና 97ኛ ተከሳሾችን በማመልከት በተለይ 96ኛ ተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ስልክ በመጠቀም ሁከቱ ቡልጋሪያ ተብሎ ወደ ሚጠራው እና 09 ቀበሌ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ድረስ እንዲስፋፋ መመሪያ በመስጠት እንዲሁም 97ኛ ተከሳሽ ወጣቶቹን ሰብስቦ ቅንጅት ያሸንፋል የትግሬ መንግስት አልቆለታል እያለ ሲፎክር መስማቱን ሁከት ፈጣሪዎቹ ግማሹ ድንጋይ ግማሹ ጋዝ በጋዝ የተሞሉ የለስላሳ ጠርሙሶች ይዘው እንደነበረ መስክረዋል 77ተኛውን የአቃቤ ህግ ምስክር አይዳያ ኮንሳ ጥቅምት 23 1998 በጉለሌ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 18 ጽ/ቤት ላይ ስለደረሰው ጉዳት እና በቤተሰቡ እንዲሁም በራሱ ላይ ስለደረሰበት መንገላታት ሲያስረዳ በወቅቱ የቀበሌው ዋና ስራ አስፈፃሚ እንደነበረ የቅንጅት ደጋፊ የሆኑ ሰዎች እየጨፈሩ ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ ሌባ መንግስት አልቆለታል ዘንድሮ እያለ ወደ ቀበሌው ጽ/ቤት አጥሩን ደርምሰው በመግባት እና ድንጋይ በመወርወር ጽ/ቤቱን መስኮቶች መሰባበራቸውን በጽ/ቤት ተሰቅሎ የነበረው



Scanned by CamScanner

ባንዲራ በማውረድ እና በተለይም በባንዲራ መሀል ላይ የሚገኘውን ልዩ ምልክት ቀደው ይዘው ሲሄዱ ማየቱን ከዚያም ረዘም ላለ ግዜ እሱ እና ሌሎች ሰራተኞች በጽ/ቤት ተጠልለው ከቆዩ በኋላ ፖሊሶች ለራሳቸው ደህንነት ሲባል ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዷቸው እና በተለይም እሱ ለ8 ቀናት ያህል በዚያው ተጠልሎ መቆየቱን ከዚህም በተጨማሪ ከአደጋው ለመዳን ሲባል ቤተሰቦቹ መኖሪያ ቤታቸውን ለቀው በእየዘመድ ቤት መጠለላቸውን ቤቱ መዘረፉን እንዲሁም ከዚህ ግዜ በኋላ በራሱ እና በህፃናት ልጆቹ ሳይቀር እንገላችኋለን የሚል ዛቻ እና የማግለል ሁኔታ እንደገጠመው በመግለፅ አስረድተዋል 56ኛ 61ኛ 78ኛ ምስክሮች የተለየ አያስረዱልኝም በማለት አቃቤ ህግ እንዲሰናበቱ በጠየቀው መሠረት የምስክርነት ቃላቸውን ሳይሰጡ ተሰናብተዋል።

ሸ/ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥር 70 73 81 361 362 365 367 80 364 እና 366 ስር የተመለከቱት ምስክሮች በ1ኛ በ2ኛ እና 7ኛ የወንጀል ክሶች በተጠቀሰው የወንጀል ተግባር ተሳታፊ ናቸው የተባሉት ተከሳሾቹ በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በአነሳሱት በመሩት እና በቀጥታም ሳይቀር በተሳተፉበት ድርጊት የጉዳቱ ሰለባ እና ከፍተኛ የአካል እና የህሊና ጉዳት የደረሰባቸው በተለይም 36ኛው ተከሳሽ ስለነበረው ተሳትፎ የሚያስረዱ እና እንዲሁም ተከሳሾቹ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊ እና አባላት በተመሳሳይ ሁኔታ የትግራይ ብሔር ተወላጆች ላይ በጅምላ እንዲፈፀም መርተዋል በተባሉበት የዘር ማጥፋት ወንጀል ሙከራ ሳቢያ ጉዳት መድረሱ የሚያስረዱ በተለይም ከዚሁ ጋ ተያይዞ በክስ ማመልከቻው ላይ በ107 እስከ 112 የጠቀሱት ተከሳሾች ስለነበራቸው ተሳትፎ ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ የሰጡት የምስክርነት ቃል ማሙዬ መኩሪያ የተባለው 70ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በጉለሌ ክፍለ ከተማ አዲሱ ገበያ አካባቢ ተፈጥሮ ስለነበረው ረብሻ እና በረብሻው ምክንያት ስለደረሰበት አካላዊ እና ህሊናዊ ጉዳት ሲያስረዳ በወቅቱ የኢህአዴግ አባል እንደነበረ እና በቅንጅት አመራር ከኢህአዴግ አባላት ጋር ህብረተሰቡ እንዳይገናኝ ኢህአዴግ አባላትን እዲያገል መግለጫ ከተሰጠ በኋላ ጉዳቱ እንደደረሰበት በተለይ በተጠቀሰው ቀን ለፖሊስ ጠቁመህ ታስደዘናለህ በሚል ምክንያት ከ50 ያላነሱ ሰዎች ከበው በዱላ በጠርሙስ እና በእርግጫ በመደብደብ ጭንቅላቱ ላይ እና በሌላ



Scanned by CamScanner

የሰጡንቱ ክፍሎቹ ላይ ጉዳት አድርሰውበት ገድለነዋል ብለው ጥለውት እንደሄዱ በመግለፅ ከዚሁም ጉዳት የተነሳ የመተንፈስ ችግር እንደደረሰበት እና እራሱን እና ኩላሊቱን እንደሚያመው ስራም እንደ ልቡ መስራት እንደማይችል በማብራራት ከደረሰበት ከፍተኛ አካላዊ እና የሀሊና ጉዳት የተነሳ ከኢህአዴግ አባልነቱ እራሱን ማግለሉን እንዲሁም ቤተሰቦቹ ላይ ኢህአዴግ አባል ቤተሰብ ናችሁ በሚል የማሸማቀቅ ተግባር እንደተፈፀመባቸው መስክሯል 73ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር አጌና አካለጎንታ ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በሚኖሩበት ቦሌ ክፍለ ከተማ 13/14 በወቅቱ ተፈጥሮ ከነበረው እረብሻ የተነሳ ይሰራበት የነበረው ሱቅ እንደወደመበት እና ሱቅ ወስጥ የነበረው እቃ ወደ አስፖልት እየተወረወረ እንዲቃጠል መደረጉን እና የወደመውን ንብረት በጠቅላላ እስከ ብር አራት ሺህ ሊገመት እንደሚችል በመግለፅ በአካባቢው ከነበሩት ሱቆች መካከል የእሱ እና እራቅ ብሎ የሚገኝ የአንድ ኢህአዴግ አባላት የሆነ ግለሰብ ሱቅ ብቻ መቃጠሉን ለደረሰው የንብረት ውድመት ምክንያት እሱ ቀበሌው ኢህአዴግ አባል ሆኖ የ8 አመታት ያህል መስራቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት እንዳለው ጭምር አስረድተዋል። ይርጋአለም ወ/ማርያም የተባለው የ81ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር በ36ተኛ ተከሳሽ ላይ የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ ተከሳሽን በቅስቀሳ ወቅት እንዳየሁ እና ነሀሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አካባቢ በቀበሌ 42 አዳራሽ ቅንጅት በጠራው ስብሰባ ላይ ለሁለተኛ ግዜ እንዳገኘው ገልጾ በስብሰባው ላይ ተከሳሽ ፖርላማ መግባት የለብንም ፖርላማ ከገባን የኢህአዲግ አሻጉሊት እና የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን አንድንም እያለ ሲናገር እንደነበረ እና ከስብሰባው በኋላም በርከት ያሉ ወጣቶች ጋር ሆኖ እንደ ጆርጂያና ዩክሬን ብርቱካናማ አብዮት በእኛም አገር የአደይ አበባ ሰላማዊ አቢዮት ማድርግ አለብን ለአለምአቀፍ ህብረተሰብ ድምፃችንን ማሰማት ይኖርብናል እያለ ለወጣቶቹ ሲናገር እንደሰማው ከዚህም በኋላ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በአራተኛ ክፍለ ጦር አካባቢ በርካታ ወጣቶች ድንጋይ በመወርወር ከፖሊስ ጋር ግጭት ፈጥረው ነበር ባሉ ግዜ ተከሳሽ ከወጣቶቹ ጋር ሲነጋገር እንደነበረ ነገር ግን ከቦታው እርቀት የተነሳ



Scanned by CamScanner

የነገግሩን ይዘት ለመስማት ያልቻለ በመሆኑም ጥምር በማብራራት መስክረዋል ቅድመስለም በሀይሉ የተባለው 361ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በግምት ከረፋዱ 4 ሰዓት ሲሆን ሽሮሜዳ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ ኑር ሁሴን በተባለው ግለሰብ ስለደረሰው ጉዳት ሲገልፅ በወቅቱ በአካባቢ ታክሲዎች አገልግሎት እንዳይሰጡ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እንደነበረ እና በተለይም 112ተኛው ተከሳሽ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ታክሲዎች ስራቸውን እንዳይሰሩ ለማገድ ሲራሯጥ ስለነበረ ይሄንን በመቃወም ተጉጂው ለአካባቢ ፖሊሶች በማሳወቁ ታክሲዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ፖሊሶች ሲያስገድዱ ነበር ወዲያውኑ ፋጨት ተጀመረ እሱም የኢህአዴግ አባል በመሆኑ ክትትል ያደርጉበት ስለነበረ በጥንቃቄ በመሄድ ፖሊሶች ይዞ ወደ አካባቢው ሲደርስ ኑር ሁሴን ሞተ ሲባል ሰምቶ ወደ ተጉጂው ተጠግቶ እንዳረጋገጠው ግን በወቅቱ ተጉጂው በድንጋይ እና በገጀራ መላ ሰውነቱ ተደብድቦ በደም ተጨማልቆ እንደነበር እና ጥቂት በጥቂት ይናገር እንደነበረ ጉዳቱም ያደረሱበትም 112ኛ ተከሳሽ እና ፍቃዱ ቻይና ያላቸው ሌሎች ሰዎች መሆናቸው እንደነገረው እና ወዲያውኑ አምቡላስ ተጠርቶ ለህክምና መላኩን አስረድተዋል በተጨማሪም በግለሰቡ ላይ ደረሰው ጉዳት መነሻ ምክንያት የሆነው ተጉጂው የኢህአዴግ ደጋፊ እና የትግራይ ብሔር ተወላጅ ነው በሚል ምክንያት ይሆናል ብሎ እንደሚያምን እና ተጉጂው እራሱ ጉዳቱ ሳይደርስበት አስቀድሞ ትግሬ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደጋፊ ነው እያሉ ተከሳሽ እና ሌሎች ስማቸውን የሚያስታውሷቸው ሰዎች ይዝቱብኛል ብሎ እንደነገረው እንዲሁም ተጉጂው ጉዳቱ በደረሰበት ግዜ ተከሳሽ ሽጉጡን እንደወሰደበት ነግሮት ስለነበረ ይሄንኑ ለፖሊስ አሳውቆ ተከሳሽ መርቶ ካስቀመጠበት ሽጉጡን ለፖሊስ ሊያስረክብ በታዛቢነት ተገኝቶ ማየቱንና ተከሳሹ ይሄንን ለመፈፀም የቻለው በቅንጅት በተደረገው ጥሪ ምክንያት መሆኑን ቃሉን ለፖሊስ ሲሰጥ መስማቱን ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በነበረው ረብሻ ተሳታፊ የነበሩትን ድንጋይ በመወርወር በአካባቢው የነበሩት ቤቶች እና የፖሊስ መኪኖች ሲሰባበሩ ማየቱን እንዲሁም በወቅቱ ከነበረው ከፍተኛ እረብሻ የተነሳ የሰላማዊ ሰዎች እንቅስቃሴ ተገትቶ እንደነበረ የረብሻው ተሳታፊ የነበሩት ሰዎች በወያኔ አንገዛም አልመረጥናችሁም ልቀቁን እያሉ ሲጮሁ መስማቱንም መስክረዋል ያለው እውነቱ የተባለው 365ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 22 ቀን



Scanned by CamScanner

1998 ዓ.ም በተፈጠረው አረብሻ ኑር ሁሴን የተባለው ተጉዳ 112ኛ ተከሳሽን ጨምር ሌሎች ታምራት ቾምቤ ታደሰ በንቱ ደጉ አዩብ የተባለ የአባታቸው ስም ያልገለጿቸው ግለሰቦች እንገልሃለን አንተ ጠያኔ አንድ ነገር ሲጀመር ከአንተ ነው የምንጀምረው እያሉ ይዝቱብኛል ያስፈራሩኛል በማለት እንደነገረው እና ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በተለይ ሽሮሜዳ አካባቢ ከፍተኛ አረብሻ ደርሶ ነበረ ባለበት ቀን ከጠዋቱ 3:30 አካባቢ ተጉጂው አግኝቶት የተጠቀሱት ሰዎች አሁን እየዛቱበት እንደሆነ ከነገረው ከትንሽ ደቂቃ በኂላ ኑር ሁሴንን ገደሉት ሲባል ሰምቶ በወቅቱ በአካባቢው ከነበሩት የፀጥታ ሀይሎች እና 361ኛ ምስክር ጋር በመሆን ኑር ሁሴን ወድቆ ከፍተኛ ደም እየፈሰሰበት እያጣጣረ እንዳየው እና ጉዳቱ ያደረሱበትንም እነ መላኩ መሆናቸውን እንደነገረው በማስረዳት በወቅቱ ከፍተኛ ረብሻ እንደነበረ ድንጋይ በእየመንገዱ ተደርድሮ መንገድ ተዘግቶ እንደነበር መኖሪያ ቤቱም በድንጋይ እንደተደበደበበት ገልጾ ቤተሰቦቹም በፖሊስ እርዳታ ወደ መጠለያ ተወስደው ሊተርፍ እንደቻሉ ገልፀው አሁንም ጭምር ከመኖሪያ ቤቱ ተፈናቅሎ በመጠለያ እንደሚገኝ አስረድተዋል 362ኛ የአቃቤ ምስክር በራብ በሉማ ጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም 112ኛ ተከሳሽ መታሰሩን ሰምቶ ቤተሰቡን ለመጠየቅ ወደ ተከሳሹ መኖሪያ ቤት ሄዶ እንደነበረ ገልጾ በዚሁ እለት ተከሳሹ ፖሊስ ወደ መኖሪያ ቤቱ ይዘውት በመምጣት እፎቴ ስር አንድ ሽጉጥ አንስቶ ለፖሊስ ሲያሳይ ማየቱን እና ሽጉጡን ከማን እንደወሰደው ሲጠይቁት ምስክሩ ስሙን ማስታወስ ያልቻለው ሰው ስም ጠርቶ እገሌ ሰጥቶኝ ብሎ ሲናገር መስማቱን መስክረዋል 377ኛ ምስክር 112ኛ ተከሳሽ ላይ እና በሌሎች ምስክሮች ከተነገረው የተለየ አያስረዱም በማለት 367ኛ ምስክር እንዲታለፍ 364ኛ 366ኛ በዚሁ ጭብጥ የተለየ አያስረዱም በማለት እንዲሁም 80ኛው ምስክር በ81ኛ ከተነገረው የተለየ አያስረዳም በማለት እነዚህ ምስክሮች እንዲታለፍ አቃቤ ህግ በጠየቀው መሠረት የምስክርነት ቃላቸው ሳይሰጡት ታልፈዋል /ቀ/ በአቃቤ ህግ የምስክሮች ዝርዝር በተራ ቁጥር 7 10 11 15 18 20 21 22 31 እና 36 ስማቸው የተመለከቱት ምስክሮች በ1ኛ በ2ኛ በ5ኛ እና 7ኛ ክሶች



Scanned by CamScanner

የተመለከቱትን የወንጀል ተግባሮች ስመፈፀም ሁሉም ተከሳሾች በአዲስ አበባ ከተማ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም እና ጥቅምት 22 እና 23 1998 ዓ.ም በአነሷቸው በመሯቸውን እና በተሳተፎባቸው አመጾች በህይወት እና በንብረት ላይ ስለደረሰው ጉዳት ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ የሰጡት የምስክርነት ቃል 10ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ኢንስፔክተር ውለታው ደሴ ግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም ከአንድ ሺህ አምስት መቶ እስከ ሁለት ሺህ የሚሆኑ ወጣቶች ስድስት ኪሎ ገንዘብ ሚኒስቴር አካባቢ ተሰባስበው ድንጋይ እና አጠና በመያዝ ሁከት በመፍጠር ሲንቀሳቀሱ ከሌሎች አባሎች ጋር በመሆን የማረጋጋት ስራ ሲሰራ ሁከት ፈጣሪዎቹ ሌቦች መጡ በማለት ድንጋይ በመወርወር ጭንቅላቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት እንደነበር ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በጠዋቱ 3:30 ሲሆን ቀበና አራት መንታ መንገድ ላይ ቁጥጥር ሲያደርግ ብዛት ያላቸው ወጣቶች መንገዶቹን በድንጋይ እና በጎማ እንደዘጓቸው እና ነዳጅ ማደያውን እናቃጥላለን እያሉ ሲዝቱ መስማቱን በጋዝ የተሞሉ ለስላሣ ጠርሙሶች ይዘው እንደነበረ እና እንዳስጣሏቸው እናንተ ሌቦች እያሉ ይሰድቧቸው እንደነበር እና የታሰሩ የቅንጅት መሪዎች ካልተፈቱ አንላቀቅም እያሉ መዛታቸውን ከዚህም ሌላ የፀጥታ ስራ አገልግሎት ተሰማርቶ በነበሩት መኪኖች ላይ የእሳት ማቃጠል ሙከራ ማድረጋቸውን እንዲሁም የሴኖዶሱን ጽ/ቤት እና የፓትሪያሪኩን መኖሪያ ቤት የአገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት እና ጉድሸበር የተባለው ድርጅት ለማቀጣጠል እንቅስቃሴ ያደርጉ እንደነበረ እና በቀድሞ የወረዳ 14 ፖሊስ ጣቢያ የነበሩትንም እስረኞች ለማስፈታት ሙከራ ማድረጋቸውን በመዘርዘር በወቅቱ በተወረወረ ድንጋይ በሁለት የፖሊስ አባላት ላይ ጉዳት መድረሱን ጭምር መስክረዋል ዋናው ሳጂን ዘውዴ አስማረ የተባለው 7ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ተመድቦ ይሰራበት ከነበረው ባልቻ አባነፍሶ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በቀለወያ እና ተስፋ ኮከብ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አካባቢ የፀጥታ ቁጥጥር ስራ ላይ እንዳለ ከጠዋቱ 5 ሰዓት አካባቢ ከአብነት ወደ መርካቶ እንዲሁም ጦር ሀይሎች ወደ ተክለ ሃይማኖት የሚያመሩ መንገዶች በድንጋይ በመዘጋት እና ጎማ በማቃጠል ብዛት ያላቸው ወጣቶች ሁከት በመፍጠር ላይ እንደነበሩ ሁከት ፈጣሪዎቹ ወያኔ ሌባ ይሉ እንደነበረ እና አልፎ አልፎ የምርጫ 97 ቅንጅት



Scanned by CamScanner

የተጠቀመበትን የጣት ምልክት ያሳዩ እንደነበረ በሁከቱ ስራ ላይ የነበሩትን የፖሊስ አባላት እና ኢህአዴግ ቅጥረኞች በማለት ይሰድቧቸው እንደነበረ ድንጋይ ይወረውሩባቸውን እንደነበረ እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥሩ 0065 የሆነ ላንድ ክሩ ዘር የፖሊስ መኪና በድንጋይ መሰባበራቸውን በእለቱ 9 ሰዓት አካባቢ መርካቶ ጭላሎ ሆቴል አጠገብ ባለው የነዳጅ ማደያ ላይ ድንጋይ በመወርወር ጉዳት በማድረሳቸው እና ተቀጣጣይ ጎማ በመጠቀም ቃጠሎ ለማስነሳት ተሞክሮ በፀጥታ ሀይሉ አባላት ቁጥጥር ስር መዋሉን በመግለፅ የራሱን ጨምሮ ምክትል ኢንስፔክቴር ሲሳይ ተፈራ እና ዋና ሳጂን ዘውዱ አስማረ ሳጅን ሳመሶንም አድማሱ ምክትል ኢንስፔክቴር ሲሳይ ዲሳሳ እና አንድ ሌላ ስሙን የሚያስታውሰው አባል መጉዳታቸውን መስክረዋል 11ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ዋና ሳጂን ሀይሌ ዘነበ ጥቅምት 22 እና 23 ቀን 1998 ዓ.ም ተፈጥሮ በነበረው አረብሻ ጉለሌ ክፍለ ከተማ አዲሱ ሚካኤል አካባቢ ከነበረው የፀጥታ አመራር ጥሪ ተደርጎላቸው ሄደው በአካባቢው የነበሩ መንገዶች በጎማ በድንጋይ እና በሌሎች ቁሳቁሶች ተዘግተው እንደነበር በእነሱም ላይ ድንጋይ እንደተወረወረባቸው እና በርበሬ ጭምር በማቃጠል ሰው እንዳይተላለፍ መደረጉን አመፀኞቹ ፖሊስ ሌባ ነው የመንግስት ቅጥረኛ ነው እያሉ እና ቅንጅት በምርጫ የተጠቀመበት የጣት ምልክት እያሳዩ ይጮሁ እንደነበረ በወቅቱ ሲወረወር በነበረው ድንጋይ የፖሊስ መኪና መሰባበሩን እና ሚካኤል ቤተክርስቲያን ፊለፊት የነበረው ፎቅ መስታወቶቹ መሰባበራቸውን እንዲሁም ስሙን ባልጠቀሰው ምክትል ኢንስፔክተር ላይ ጉዳት መድረሱን ገልጾ መስክረዋል። ሳጂን አራጌ አሸኔ 15ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ኮልፌ ቀራኒዮ ፖሊስ መምሪያ አካባቢ በተወርዋሪ ፖሊስ ምድብ ሲሰራ ከጠዋቱ በግምት 4 ሰዓት በድንገት በአካባቢ በተፈጠረው አረብሻ እና በጎማ መንገዶች መዘጋታቸውን ለማስከፈት ጥረት ሲደረግም የአካባቢው ህብረተሰብ በተለይም ወጣቶች ፖሊሶች ላይ ጉዳት ለማድረስ ድንጋይ ይወረውር እንደነበረ በወቅቱ የቅንጅት የምርጫ አርማ የሆነው የጣት ምልክት ያሳዩ እንደነበረ የወያኔ ቅጥረኞች ይሲዛል ዘንድሮ የወያኔ ነገር የእናቶቻችን ድምፅ ተሰርቆ አይቀርም እያሉ ይጮሁ እንደነበረ

Scanned by CamScanner

እና ይወረወር በነበረው ድንጋይም ግጭቱ ደምሴ የተባለው የፖሊስ ባልደረባ መጎዳቱን ገልፀዋል እንዲሁም ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በተጠቀሰው አካባቢ ስራ ላይ እንዳለ አዲስ ከተማ አካባቢ ችግር ተፈጥሮ እንደነበረ መስማቱን በተመሳሳይ አካኂን በምድር ስራው አካባቢ ድንጋይ በመወርወር እንደተጀመረ መንገዶች መዘጋታቸውን በአንድ ቪታራ የግለሰብ መኪና ላይ ዘረፋ መፈፀማቸውን የመኪናዋን አሽከርካሪ በማስወረድ መኪናዋን ይዘው ለመሄድ ሲሞክሩ በተደረገው ክትትል መኪናዋ ለባለቤቷ እንድመለስ መደረጓን ከመግለፅም በተጨማሪ በአካባቢ በሚገኘው በቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም ጥቃት ለማድረስ በእሳት በተያያዘ ቆሻሻ ይወረወር እንደነበረ እና በአካባቢ ባለው እፎይታ ገበያ ማእከል ይሰሩ በነበሩ ባለ ሱቆች ስራቸውን እንዳያከናውኑ ድንጋይ ይወረወርባቸው እንደነበረ ገልፀዋል፡፡ አያና ትርፌሳ የተባለው 18ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር አዲስ ከተማ አካባቢ የወንጀል መከላከል ስራ ላይ እንዳለ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በግምት ከ2፡30 እስከ 3 ሰዓት ባለው ግዜ ውስጥ አዲስ ከተማ ባለው ትምህርት ቤት የተፈጠረው ግርግር እስከ መርካቶ ተዳርሶ ቅንጅት አሸንፎል ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ወድቋል እያሉ በመጮህ በሁለቱ ተሳታፊዎች በምርጫው ወቅት የቅንጅት አርማ የነበረውን የጣት ምልክት ያሳዩ እንደነበረ በትምህርት ቤቶች በፖሊስ እና በተለያዩ ተቋማት ላይ ድንጋይ ሲወረወር እንደነበር እና ሁለት አውቶብሶች እና አንድ የፖሊስ መኪና መሰባበራቸውን በተክለሀይማኖት ነዳጅ ማደያ ላይ አደጋ ለማድረስ ጋዝ የተሞላ ጠርሙስ ተወርውሮ በፖሊስ ጥረት ቃጠሎው ሳይደርስ መቅረቱን መንገዶች በድንጋይ በተቀጣጣይ ጎማዎች መዘጋታቸውን ሁከት ፈጣሪዎቹ ድንጋይ ዱላ ገጀራ ይዘው እንደነበረ እና በጋዝ የተሞሉ ጠርሙሶች ወደ ፖሊስ ሲወረውሩ ማየቱን ገልጿል፡፡ ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበር እና በሁከቱ ተሳታፊ የነበረው ሰው ቁጥር እና የደረሰው ጉዳት ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ከነበረው የባሰ መሆን ገልጾ በአካባቢው በነበሩት ተቋማት ሼል ነዳጅ ማደያም ጭምር ለማጥቃት ተሞክሮ እንደነበረ ለፖሊሶች ላይም ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት መድረሱን በተለይም መሀሪት ሰናድር አለማየሁ በተባሉ ሌሎች በስም ባልጠቀሳቸው ፖሊሶች ላይ ጉዳት መድረሱን መስክረዋል 20ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ሙሉ ከበደ ጥቅምት 22



Scanned by CamScanner

ቀን 1998 ዓ.ም መርካቶ አካባቢ ከሌሎች የፀጥታ ሀይል አባላት ጋር መሆን ሲሰራ ቅንጅት አሸንፎአል ምርጫ ተጭበርብሯል እያሉ እና የቅንጅትን ምርጫ አርማ ምልክት እያሳዩ ቁጥራቸው ከ1000 እስከ 1500 መቶ የሚሆኑ ሰዎች ድንጋይ ጩቤ ገጀራ ይዘው ድንጋይ እየወረወሩ ወደ እሱ መጠጋታቸውን እና በሁኔታው ለማ ኪዳኔ እና ከበደ የተባሉት የፖሊስ አባላት ጭንቅላታቸውን እና እግሮቻቸው በድንጋይ እና በዱላ ተመተው መጎዳታቸውን ቤንዚን በተሞላ አሮጌ ቆርቆሮ ውስጥ እሳት ጨምረው በአካባቢው ወደ አለው ሞቢል የነዳጅ ማደያ ላይ በመወርወር አደጋ ለማድረስ ሙከራ ተደርጎ በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋሉን መስክረዋል ሳጂን ደባስ ፈይሳ የተባለው 21ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም የካ ክፍለ ከተማ አካባቢ በወንጀል መከላከል ስራ ላይ እንደነበረ ገልጾ በእለቱ በግምት ከቀኑ 6 ሰዓት ሲሆን የአካባቢ ወጣቶች ወደ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በመሄድ አትነሳም ወይ እያሉ ይጮሁ ከነበሩ ተማሪዎች ጋር መቀላቀላቸውን እና ድንጋይ መወርወር መጀመራቸውን በጎማ በግንዲላ እንጨት እና በድንጋይ መንገዶች መዘጋታቸውን በአካባቢ ይንቀሳቀሱ የነበሩት የመከላከያ ሬንጀር ቴዎታ ፒካፕ መኪና ቤንዚል አርከፍክፈው ማቃጠላቸውን እና እሳቱን ለማጥፋት የተደረገው ሙከራ በድንጋይ ውርወራ ምክንያት እንዳይሳካ ማድረጋቸውን ሁከት ፈጣሪዎቹ ቤንዚል የተሞሉ ጠርሙሶች ድንጋይ እና ገጀራ ይዘው እንደነበረ ወደ ፖሊሶች በተወረወረው ድንጋይ እሱ እራሱ ዋና ኢንስፔክተር ባየልኝ እና ኮንስታብል ቶሎሳ አደራ የተባሉ የፖሊስ አባላት መጎዳታቸውን እና በወቅቱ ተሳታፊዎቹ ቅንጅት አሸንፏል ኢህአዴግ ሌባ ነው እያሉ ይጮሁ እንደነበረ መስክረዋል ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም ቡተመሳሳይ ሁኔታ ድንጋይ በመወርወር እና መንገድ በመዝጋት በአካባቢው ረብሻ እንደነበር ገልጾ ሁከት ፈጣሪዎቹ ወያኔ አይገዛንም እያሉ ሲጮሁ እንደነበረ እንዲሁም ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓ.ም በ33 10 እና 40 ቁጥር የከተማ አውቶብሶች ላይ ድንጋይ ተወርውሮ መስታዎታቸውን መሰባበሩን እንዲሁም ጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም በመንግስት አውቶብሶች ሁከቶኞችን በቁጥጥር ስር ለማዋል በተደረው ሙከራ አንዱ የፖሊስ አባል በገጀራ



Scanned by CamScanner

ተመትቶ ጉዳት እንደደረሰበት እና አንድ ሌላ ፖሊስ ደግሞ ታጥቆት የነበረውን ከሳሽኮኘ ጠመንጃ መቀማቱን መስክረዋል።

ሳጂን ክንፌ መርሳ የተባለው 22ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም ቀጨኔ ችሎት ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ አድማ በታኝ ሆኖ ስራ ላይ ከነበሩት አባላት ጋር ተመድቦ ይሰራ እንደነበረ በመግለፅ በወቅቱ በአካባቢ በነበሩት ወጣቶች አማካኝነት ረብሻው እንደተነሳ በአካባቢው የነበረው የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር በተወረወረ ጋዝ የተሞላ ጠርሙስ ፈንድቶ ፍንዳታ ተከትሎ ኢትዮጵያ ትቅደም ትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩ ተማሪዎች በሙሉ ወጥተው ወደ ረብሻ መቀላቀላቸውን እና ጎማ በማቀጣጠል መንገዶችን በመዝጋት ድንጋይ በመወርወር የአካባቢው ፀጥታ ማደፍረሳቸውን በፖሊሶች ላይ ድንጋይ በጋዝ የተሞሉ ጠርሙሶች ከመወርወራቸው በተጨማሪ ለሆዳችሁ ያደራችሁ ውሾች እያሉ በመሳደብ እና አትነሳም ወይ ይሄ ባንዲራ የአንተ አይደለም ወይ እያሉ በመጮህ እና የቅንጅት ምርጫ አርማ የሆነው የጣት ምልክት በማሳየት ሌላው ህብረተሰብ ከሁከቱ እንዲቀላቀል ያደርጉ እንደነበረ እንዲሁም ወረሠ አርአያ በተባለው የፖሊስ አባል በስም በማያስታውሷቸው ሌሎች አባላት ላይ ጉዳት መድረሱን እና በከተማ አውቶብሶች ማለትም በቁጥር 6 31 እና 45 የመሰባበር ጉዳት መድረሱን መስክረዋል። 31ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ኢንስፔክተር ታፈረ ተጠምቀ ጥቅምት 22 እና 23 1998 ዓ.ም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ሲሰራ በወቅቱ ከምርጫ ጋር በተያያዘ አካባቢውን ያደረሰ ረብሻ እንደነበረ በተለይም ጳውሎስ ባንክ ሻወልደማ ትምህርት ቤት በርበሬ በረንዳ እስከአብነት ዙሪያ የተስፋፋ እና ከፖሊስ አቅም በላይ የሆነ ሁከት እንደነበር እና በረብሻው ተሳታፊ የነበረው ሰው ቁጥር እስከ ስድስት ሺህ ሊገመት የሚችል መሆኑን በረብሻው ወቅት ድንጋይ እና በጋዝ የተሞሉ ጠርሙሶች ሲወረውሩ እንደነበረ እና ጎማ በማቀጣጠል ድንጋይ በመደርደር መንገዶች ተዘግተው እንደነበረ በረብሻው ከነበሩት መሀል ጩቤ፣ መጥረቢያ ገጀራ የያዙ እንደነበሩበት እና ጥይት የሚተኩስም እንደነበሩበት በመግለፅ በሁኔታው በስም ያልጠቀሳቸው 5 ፖሊሶች መጎዳታቸውን እና በከተማ አውቶብስ መናኸሪያ ቆመው የነበሩት 6 አውቶብሶች መስታወታቸው ረግፈው እና የሰሌዳ ቁጥሩ 1880 የሆነ አንድ የፖሊስ መኪና መስታወታቸው ረግፈው ማየቱን እንዲሁም አመፀኞቹ ምርጫው ምልክት ጣት እያሳዩ አካባቢውን ሲያውኩ እንደነበረ መስክረዋል። 36 የአቃቤ ህግ ምስክር ኢንስፔክተር ኪዳኔ አያና ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 ክልል ተመድቦ ሲሰራ



Scanned by CamScanner

በወቅቱ የግንቦት 20 ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በማነሳሳት የተጀመረው ረብሻ ወደ ሌሎቹ አካባቢዎች ተስፋፍቶ ድንጋይ መወርወር መጀመሩን እና በሁኔታውም በሰሌዳ ቁጥር 0038 የፖሊስ መኪና መሰበሩን በፖሊሶች ላይ ድንጋይ ይወረወር እንደነበረ እና መንገዶች ተዘግተው እንደነበረ ፖሊስ ሌባ ወያኔ ሌባ እያሉ በመሳደብ እና የቅንጅት የምርጫ ምልክት የሆነው ጣት በማሳየት ረበሸኞቹ ይጮሁ እንደነበረ ሰኔ 2 ቀን 1997 ዓ.ም በቀጠለው እረብሻ ኮንስታብል ተዘራ አብሽሬ የተባለው ፖሊስ እና ሌሎች አባላት መጉዳታቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም በተመሳሳይ ሁኔታ የግንቦት 20 ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በማነሳሳት ድንጋይ በመወርወር የተጀመረው እረብሻ የአካባቢው የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ጉዳት ለማድረስ ተሞክሮ በፖሊስ ሀይል መክሸፉን ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰዓት ሲሆን የቀበሌው ስራ አስፈፃሚ አቶ ጌታቸው ብርሃኔ መኖሪያ ቤት ለማቃጠል በተደረገው ሙከራ የቤቱ አጥር እና በግቢ ውስጥ የነበሩ ፅዶች መቃጠላቸውን የቤቱ መስታወቶች መርገፋቸውን እና ቤቱ በሙሉ ሳይቃጠል በፖሊስ ጥረት መትረፉን እንዲሁም ረብሸኞቹ ቃጠሎ ለማስነሳት በጋዝ የተሞሉ ጠርሙሶችን ሲወረውሩ እንደነበረ እና ጩቤ ገጀራ የብረት ዱላ ይዘው እንደነበረ መስክረዋል በአቃቤ ህግ ምስክሮች ስም ዝርዝር በተራ ቁጥር 68 69 75 ስር የተመለከቱት ምስክሮች በአቃቤ ህግ 1ኛ ክስ በአምስተኛ ድርጊት እንደተመለከተው ከ1 እስከ 39 የተዘረዘሩት ተከሳሾች በ1ኛ 2ኛ እና 7ኛ የተመለከቱት የወንጀል ተግባራት ለመፈፀም በማሰብ ከጥቅምት 22 እስከ 24 1998 ዓ.ም በመሩት እና በአነሳሱት አመፅ ምክንያት ስለተፈፀመው ወንጀል እና ስለደረሰው ጉዳት ያስረዱልኛል ብሎ አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ የሰጡት የምስክርነት ቃል እንዲሁም 51ኛ ምስክር 1ኛ 2ኛ 3ኛ እና 24ኛ ተከሳሾቹ ከምርጫ 97 በኋላ በሰሜን ሸዋ ዞን አካባቢ በመንግስት ላይ የትጥቅ ትግል ለማራመድ ሽፍቶችን እና የተበታተኑ የቀድሞ መንግስት ወታደሮች አባላት ስለማደራጀታቸው ያስረዱልኛል ብሎ አቃቤ ህግ ባስያዘው ጭብጥ የሰጡት የምስክርነት ቃል ተክለሃይማኖት ዘካሪያስ የተባለው 68ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በነበረው እረብሻ ተጎጂ መሆኑን ገልጾ ከ150 እስከ 200 መቶ በሚገመት ሰዎች መኖሪያ ቤቱ ለግማሽ ሰዓት ያህል በድንጋይ ናዳ ተደብድቦ ቆርቆሮው ተበሳስቶ ጣሪያው

እና መዝጊያው መሰባበሩን ይሄ ጉዳት የደረሰበት 96ኛው ተከሳሽ የተክላይ ቤት ይሄ ነው በሉት ብሎ በሰጠው ጥቆማ እና አስተባባሪነት መሆኑን ይሄ ጉዳት ሊደርስበት የቻለበት ዋና ምክንያትም የትግራይ ብሔረሰብ ተወላጅ ከመሆኑ እና በምርጫው በወቅት ኢ.ህ.ዲ.ግን ደግፉ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረጉ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ጥፋት እንደሌለበት በማብራራት ይሄ ጉዳት ወይም በደል የደረሰው የጉረቤቶቹ ቤቶች ተነጥሎ በእርሱ መኖሪያ ቤት ብቻ እና እራቅ ብሎ የሚገኘው ሌላ የትግራይ ብሔር ተወላጅ ኮነሬል አርአያ ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓ.ም የደረሰው የቤት ቃጠሎ ብቻ እንደሆነ የእርሱ መኖሪያ ቤት በድንጋይ ሲደበደብ በቤቱ ውስጥ እሱ እና ቤተሰቦቹ እንደነበሩ እና ከዚህም የተነሳ በእርሱም ሆነ በቤተሰቦቹ ላይ ለአይምሮ ጭንቀት መዳረጋቸውን በተለይም ከዚህ ጥቃት በኂላ መታመሙን መስክረዋል፡፡ 75ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ኮኔሬል አርአያ ገ/ዩሀንስ ከምርጫው ውጤት ጋር በተያያዘ ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በነበረው እረብሻ ብዛታቸው እስከ 300 የሚገመቱ የረብሻ ተካፋዩች መኖሪያ ቤት ድረስ መመምጣት ድንጋይ በመወርወር መኖሪያ ቤቱን እንደበደቡት እንዲሁም በጋዝ የተሞሉ እና በእሳት የተቀጣጠሉ ጀሪካኖች እና ጎማዎች ወደ ተጠቀሰው መኖሪያ ቤቱ በመወርወር ቤቱ ከነንብረቱ እንዲወድሙበት ይህ ሁሉ ሲሆን ህፃናት ልጆቹ እና ሌሎች የቤተሰቦች አባላት እቤት ውስጥ እንደነበሩ እና በሰዎች እርዳታ ከቃጠሎ መትረፋቸውን 97ኛ ተከሳሽ በመቀጣጠል ላይ በነበረው መኖሪያ ቤቱ ላይ ቦምብ ሲወረውር ማየቱ እና ቦምብ በወቅቱ ሳይፈነዳ በአግዚቢት መያዙን ጥይትም ወደ መኖሪያ ቤቱ አቅጣጫ ሲተኩስ እንደነበረ እና 16 ጥቅም ላይ ያልዋሉ የሬሽ ጠመንጃ ጥይቶች በመኖሪያ ቤቱ በር ላይ ተገኝቶ በኢግዚቢት መያዛቸውን በመቀጣጠል ወደነበረው መኖሪያ ቤቱ ሲወረወሩ የነበሩትን ተቀጣጣይ ጎማዎች እና ጀራካኖች ለመመለስ ሲሞክር በነበረበት ግዜ ማን እንደወረወረው ባላወቀው ሰው በጦር ጀርባው ላይ ተወግቶ መውደቁን እና በግዜው 96ኛ ተከሳሽ በቦታው ሆኖ ቤቱ ተቀጣጥለዋል እሱም ከእነ 5 ልጆቹ ተቃጥለዋል እያለ ሲናገር መስማቱን ይሄው ተከሳሽ ለደረሰው ጉዳት ለመመሪያ ሰጪነት እና በአስተባባሪነት ከፍተኛ ሚና እንደነበረው እንዲሁም 97ኛ ተከሳሽ ትግሬ ወያኔ ይጠፉል እያለ ከሌሎች ጋር ሲጮህ መስማቱን እንዲሁም 98ኛ ተከሳሽም እሳት በመወርወር እቤቱ ጣራ ላይ ወጥቶ እሳቱ እንዲያያዝ ማድረጉን መስክረዋል 69ኛ ተከሳሽ የትግሬ ቤት ይሄ ነው በሉት ብሎ ሲጠቁም መስማቱን ከዚያም ረብሸኞቹ የትግራይ ብሔር ወደ ሆነችው ወ/ሮ ሮማን ቤት በማምራት በተመሳሳይ ሁኔታ መኖሪያ ቤቷን በድንጋይ መደብደባቸውን ከዚህም



Scanned by CamScanner

የ75ኛ ምስክር መኖሪያ ቤት በድንጋይ በመደብደብ እና ተቀጣጣይ ነገሮችን በእሳት እያያዘው በመወርወር ቤቱ እንዲቃጠል ማድረጋቸውን በዚሁ ግዜ ረብሸኞቹ በጋዝ የተሞሉ የፕላስቲክ ጠርሙሶችን ሲወረውሩ ማየቱን እና 96ኛ ተከሳሽ በሌት እያለ አመፅ ሲመራ እንዲሁም 98ኛ ተከሳሽ ግቡ ብሎ ረብሸኞቹን ወደ ተጐጂው ቤት እንዲያመሩ እና ጉዳት እንዲያደርሱ ማድረጉ በምስክሩ ቤት ላይ ተመሳሳይ የድንጋይ ድብደባ እንደተደረገበት እና ተከሳሾቹ እሱን እና ቤተሰቦቹን ለማጥፋት ይሯሯጡ እንደነበረ መስክረዋል:: 51ኛ የአቃቤ ህግ ምስክር ካሣሁን ማሜጫ 1986 ዓ.ም ጀምሮ የመአሕድ አባል እንደነበረ ገልጾ በምርጫው 97ኛ በሰሜን ሸዋ የምርጫ ቅስቀሳ ተሳታፊ እንደነበረ መጋቢት 18 ቀን 1997 ዓ.ም 122ኛ እና 24ኛ ተከሳሾች ሸዋሮቢት ባደረጉት ስብሰባ ለብቻው በመጥራት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በምርጫው ቢሸነፍ ስልጣኑን ስለማይለቅ ይሄንን ለማቋቋም የሚችሉ ጠንካራ የሆኑ እና ትጥቅ ያላቸው የደርግ ወታደሮች እንዲያዘጋጅ መመሪያ በመስጠትና በአየወረዳውም እንዲህ አይነቱ መመሪያ በሚሰጢር በመስጠት ላይ መሆኑን እንደነገሩት ከዚያም በኋላ 10 ሰዎቹን መልምሎ እንደነበር እና አላማውም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በምርጫው ተሸንፎ ስልጣን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባይሆን ውጊያ ለመክፈት እና በእየወረዳው በተመሳሳይ ሁኔታ የተደራጁ ሰዎች ስላሉ ስልጣን ለመያዝ መሆኑን ለተመልማዩቹ እንደነገራቸው ከምርጫው በኋላ በቅንጅት እና በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መካከል ውዝግብ ከተፈጠረ በኋላ 24ኛ ተከሳሽ ደውሎለት ሰዎቹን አዘጋጅተሃል ወይ ብሎ 8ቱን ሰዎች አዘጋጅቶ ማነጋገሩን እና እሺ እንዘጋጃለን እንዳሉ ሰኔ 14 ወይንም 15 በውል ለይቶ በማያስታውሰው ቀን አዲስ አበባ ወደሚገኘው የመኢአድ ጽ/ቤት መጥቶ 24ኛው 3ኛው 1ኛው ተከሳሾች በአካል ማግኘቱን እና አንደኛውና 3ኛው ተከሳሽ ተከሳሾቹ በተነገረህ መሠረት ሰዎች እንዲዘጋጁ አድርግ እንዳሉት እና በተለይም 24ኛ ተከሳሽ እና 3ኛ ተከሳሾች አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ይሟላል ሰዎቹን አደራጃቸው ይሉት እንደነበረ መስክረዋል በመቀጠልም በሰው ማስረጃ ዝርዝር በርካታ ምስክሮች የተቆጠሩ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ሊሰጡት የሚችሉት የምስክርነት ቃል ድግግሞሽ እና ከተሰሙት ምስክሮች የምስክርነት ቃል ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ከተቆጠሩት የአቃቤ ህግ ምስክሮች መካከል ብዛታቸው ከ219 ያህል እንዲታለፉ አቃቤ ህግ በጠየቀው መሠረት ምስክሮቹ ሳይሰሙ ታልፈዋል በአንፃሩ ግን ሌሎች 15 ምስክሮች በተጨማሪነት እንዲሰሙ



Scanned by CamScanner

አቃቤ ህግ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ደሄው ተፈቅዶለት የእነዚህ ተጨማሪነት እንዲሰሙለት የቀረቡላቸው ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል 1ኛ 12ኛ 15ኛ ምስክሮች በ1ኛ 2ኛ 5ኛ 7ኛ ክሶች ላይ በተመለከቱት የአድማ ተሳታፊ የሆኑ ተከሳሾች በመሪነታቸውን በአነሷቸው የወንጀል ስራ ሙከራዎች ስለደረሰው ጥፋት እና ጥፋቶች እና ጉዳቶች 8ኛ 9ኛ 10ኛ እና 11ኛ ምስክሮች በአንደኛ እና ሁለተኛ የወንጀል ክሶች በተመለከተ የወንጀል ተግባር ተሳታፊ ናቸው የተባሉት 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ያላቸውን የአድማ ተሳትፎ ለማሳየት በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 የተመለከቱት ሰነዶች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተደረገ ብርበራ በሌላ መዝገብ ተከሳሽ ከሆነች ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃኔ ሀይሌ የተገኘ መሆናቸውን ከ2ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር የተመሰከሩት ምስክሮች በስድስተኛ የወንጀል ክስ እንደተመለከተው የክህደት ወንጀል ስራ ለመስራት ከኤርትራ መንግስት ድጋፍ እና እርዳታ በኢትዮጵያ ጦርነት ለመክፈት ከተደራጀ ከወንበዴ ቡድን ጋር በተመሳጣባበር በቅንጅት ስም ወደ ኤርትራ በመሄድ ከጠላት መንግስት ጋር በመተጋገዝ ቡድኑን በትጥቅ እና በስንቅ በማደራጀት 40ኛ እና 44ኛ ተከሳሾች እንዲሁም ሌሎች የቅንጅት አመራሮች ተሳተፎ እና 114ኛ 115ኛ ተራ ቁጥር የተመለከቱት ምስክሮች ጥቅምት 22 እና 23 1998 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ልዩ ቦታዎች የተነሱትን አመጾች ለማሳየት በሰነድ ማስረጃነት ለፍርድ ቤቱ የቀረቡት ቻርቶች ያስረዱልኛል በማለት አቃቤ ህግ ባስያዛቸው ጭብጦች የሚከተለው የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል 111ኛው ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክር ኑር ሁሴን ኢንዲሪስ ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም ሽሮሜዳ በሚባለው አካባቢ በተፈጠረው እረብሻ የቅንጅት ደጋፊ ናቸው ባላቸው ሰዎች በተለይም 111ኛ 112ኛ 110ኛ ተከሳሾች እና ታዬ ቶምቤ ታደሰ በንቲ አለማየሁ በማለት የጠቀሳቸው ሰዎች ሽሮሜዳ አፍሪካ ሆቴል ፊትለፊት በመከትከቻ ብረት በመተባበር ደብድበው ጭንቅላቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሱበት እና ገድለነዋል እያሉ ሲናገሩ በወደቀበት ሁነው መስማቱን ከደረሰበት ጉዳት ከፍተኛነት የተነሳ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተኝቶ ለ4 ወራት ያክል ህክምና ቢደረግለትም እራሱን መቆጣጠር እና ምንም አይነት ስራ መስራት እንደማይችል አይኑም እንደማያይለት የዚሁ አይነቱ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስበት የቻለውም ተከሳሾች ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ደህንነት በማል እና የትግራይ ብሔር ተወላጅ በመሆኑ ካልሆነ በስተቀር ሌላ የፈፀመው ጥፋት እንደሌለ እና የማንም የፖለቲካ ድርጅት አባል አለመሆኑን ተከሳሾች እና የማንም የፖለቲካ ድርጅት አባል አለመሆኑን ተከሳሾች እና ሌሎች የጠቀሳቸው ሰዎች ደብድበው



Scanned by CamScanner

ጥለውት እንደሄዱ ታናሽ ወንድሜ ነው ያለው ማእሩፍ የተባለው፣ አለማየሁ ከተባለው ሰው ጋር በመሆን ከወደቀበት አንስተው ተከሳሹን ወደ ሆስፒታል የወሰዱት መሆኑን ተከሳሾች እና ሌሎች የጠቀሷቸው ሰዎች ለመተባበር ሲደበድቡት በተለይ 112ኛ ተከሳሽ ተጉዟው የገሉ ነው ያለውን ሽጉጥ እንደወሰደበት በማብራራት ከመሰከረ በኋላ ተከሳሾች ላቀረቡለት መስቀለኛ ጥያቄ በወቅቱ ከደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት የተነሳ አይምሮውን ስቶ ስለነበረ ለመጀመሪያ ግዜ የመታውን 112ኛ ተከሳሽ ሽጉጡንም ሲወስድበት ማየቱን በትክክል ከማስታወስ በቀር ጉዳት አድርሶብኛል ያላቸውን ሰዎች ሌሎች ማለትም 108ኛ 109ኛ 110ኛ እና 111ኛ ተከሳሾች በትክክል ለይቶ ስላደረሱበት ጉዳት መግለፅ አልቻለም 112ኛ ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክር ተሻለ ገብሬ ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓ.ም በጦር ሀይሎች ሆስፒታል ጥበቃ ላይ ተመድቦ ሲሰራ በወቅቱ ከረፋዱ 4 ሰዓት አካባቢ በአካባቢ አረብሻ ወይንም ግርግር መከሰቱን በረብሻው ተሳታፊ የነበሩት በእለቱ ይከበር የነበረው የሙስሊም በአል አክብረው እስታዲዮም አደባባይ በመመለስ ላይ የነበሩ ሲሆን ድንበጋይ ሲወረውር እና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሌባ፣ መሀይም፣ የታሰሩት ይፈቱ እያሉ ሲጮሁ እንደነበረ አረብሾቹ 3 ቡድኖች የተከፋፈሉ ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን እስከ 1000 /አንድ ሺ.ህ/ የሚገመት ሰው እንደነበረበት ከረብሸኞች መካከል አጥር ዘለው እና ሾልከው ወደ ካምፕ ከገቡት ውስጥ ከ30 እስከ 40 የሚገመቱ በቁጥጥር ስር መዋላቸውን በወቅቱ በተወረወረው ድንጋይ ማማ ላይ ተመድቦ ይሰራ የነበረው ሙሉጌታ አዲስ የተባለ አባል እና ሌላ በምድር ሀይል ተመድቦ ጥበቃ ላይ የነበረና ስሙን ያልጠቀሰው አባል እና ሌላ በምድር ሀይል ተመድቦ ጥበቃ ላይ የነበረና ስሙን ያልጠቀሰው አባል ላይ ጉዳት መድረሱን በወቅቱ በቁጥጥር ስር ከዋሉት ረብሸኞች ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ አብዛኞዎቹ ክርስቲያን እንደነበሩ በማስረዳት መስክረዋል። የሚቀጥለውን የመጨረሻውን ክፍል በአዳራ።

Scanned by CamScanner

የወ/መ/ቁ. 43246
መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አዲል አህመድ

ልዑል ገብረማርያም

መሐመድ አሚን ሳኒ

ከሣሽ፡- የፌደራል አቃቤ ሕግ ሽመልስ ከማል ሚካኤል ተክሉ አብረሃ ተጠምቀ ቀርበዋል

ተከሣሾች፡- እነ ኢንጂነር ሃይሉ ሻወል በተከሰሱበት መዝገብ ሁሉም ተከሣሾች ቀርበዋል የዳንኤል እና የነፃነት ጠበቃ ኮለኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ቀርበዋል፡፡

- ይህ መዝገብ በአዳሪ የተቀጠረው የተጀመረውን ብይን ለማጠናቀቅ ነው በዚሁ መሰረት ካቆምንበት እንቀጥላለን፡፡
- የምስክሮቹን ቃል ከቆመበት እንደሚከተለው እንቀጥላለን ምክትል መቶ አለቃ ታደሰ ፍቃዱ 13ኛ ተጨማሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓመተ ምህረት በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተረኛ መኮንን ሆኖ ሲሰራ እንደነበረ ገልጾ በወቅቱ ስለነበረው ሁከት በ12ኛው ተጨማሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር እንደተናገረው በተመሳሳይ ሁኔታ መስክሯል ካሣሁን በላይ የተባለው ሁለተኛ የአቃቤ ሕግ ተጨማሪ ምስክር የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር እና በቅንጅት መካከል ስለነበረው አንድነት እና ግንኙነት ለመመስከር መቅረቡን ገልጸው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በኤርትራ ውስጥ የተደራጀ እና በኤርትራ መንግስት ሙሉ ድጋፍ የሚንቀሳቀስ የኢትዮጵያን መንግስት በትጥቅ ለማስወገድ የተደራጀ መሆኑን ገልጾ ምስክሩ እራሱ የኤርትራ መንግስት ከታሰረ በኋላ ወደ ሳዋ ማሰልጠኛ ማዕከል ገብቶ ወታደራዊ ስልጠና ተሰጥቶት ወደ ድርጅቱ እንዲቀላቀል መደረጉን በኋላም በድርጅቱ ተልዕኮ መሠረት በቡድን በቡድን ተመድበው ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ጦርነት ሲያካሂዱ ከነበሩ የግንባሩ ሰራዊት አንዱ መሆኑን በዚህም ተልኮ ወታደራዊ ካምፖችን እና ድልድዮችን በፈንጂ ማውደማቸውን ገልጸዋል በግምባሩ እና በቅንጅት መካከል ነበረ ስላለው ግንኙነትም ሲገልጽ ከ1997 አመተ ምህረት ጀምሮ ቅንጅት አላማውን በሚዲያ ከተገለጸ ወዲህ

የቅንጅት አላማ ግንባሩ ከሚያራምደው ጋር አንድነት ስላለው እንደራሳቸው እንዲቆጥሩት በምርጫ ቢያሸንፍ ስልጣን እንደሚጋሩ የቅንጅት ሽንፈት የግንባሩም ሽንፈት ሊሆን ስለሚችል አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ማድረግ እንደሚገባ በግንባሩ መሪዎች እንደተነገራቸው ስለሆነም ስለ ቅንጅቱ እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙሃን እንዲከታተሉ ይደረግ እንደነበር እና ጋዜጣና ልዩ ልዩ ጽሑፎች እየተላኩላቸው ሲያነቡ እንደነበረ ከምርጫ በኋላ በተፈጠረው አረብሻ ተገደሉ ስለተባሉ ሴቶች እና ህፃናት የሚያሳዩ ፊልሞችን በማሣየት ሠራዊቱ ለትግል እንዲነሳሳ ይቀሰቀስ እንደነበረ በተለይም አባ ዮሐንስ ዘለቀ የተባለ መሪያቸው ወደ ኢትዮጵያ አንድ ቡድን በመምራት ሲንቀሳቀስ ቆይቶ መስከረም 14 ቀን 1998 አመተ ምህረት ወደ ኤርትራ ከተመለሰ በኋላ ጥቅምት 8 ቀን 1998 አመተ ምህረት በተከበረው የድርጅቱ ምስረታ በዓል ባደረገው ንግግር ከቅንጅት ጋር የነበረው ግንኙነት በበለጠ እንዲጠናከር ስርተን ተመልሰናል ቅንጅት ያሸነፈባቸው አካባቢዎች ለጦርነት አላማቸው ማስፈጸሚያ እንደሚጠቀምባቸው ከቅንጅት መሪዎች ጋር ተነጋግረናል ብሎ መግለጹን ከዚያም ከጥቅምት 10/1998 አመተ ምህረት በተደረገው የግንባሩ ስብሰባ በኤርትራ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች በበላይነት እንደሚመራ የገለጸው ኮለኔል ፍጹም ይስሃቅ የአርበኞች ግንባር ከፍተኛ አመራር ነው ያለው መስከረም አታላይ ጀርመን ሐምቡርግ ከቅንጅት ከፍተኛ አመራር ጋር ስብሰባ ላይ መሆኑን በመግለጽ ይህ ደግሞ ለግንባሩ ከፍተኛ ድል ነው ብሎ ለቀጣይ ትግል እንዲዘጋጁ እንደነገራቸው በመዘርዘር መስከረዋል መሐመድ ሐሰን አህመድ አራተኛ ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክር በሁለተኛው፣ በሶስተኛው፣ በአምስተኛውና በስድስተኛው ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክሮች እንደተገለጸው በተመሳሳይ ከመመስከሩም በተጨማሪ የምርጫው ውጤት ከተነገረ በኋላ ኢህአዴግ ምርጫውን የምርጫውን ውጤት አጭበርብሯል የምርጫው ኮሮጆዎች ተሰርቀዋል የቅንጅት መሪዎች በመታሰር ላይ ናቸው ደጋፊዎቻቸውም እየተገደሉ ነው ተማሪዎች በባዶ እጃቸው እየታገሉ እኛ ብረት ይዘን እንዴት ዝም እንላለን የሚል ቅስቀሳ በድርጅቱ ውስጥ እንደተሰጠ ታህሳስ ወር 1998 አመተ

ምህረት መጨረሻ ላይ እንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃኑ መዋ እና አንዱ በስም የማያውቀው ሶስተኛ ሰው ኤርትራ መጥተው እስከ አሁን ድረስ የሚያታግላችሁ እና የሚያሰለጥናችሁን የኤርትራ መንግስት እና ህዝብ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን ከእንግዲህ በኋላ ቅንጅት በምርጫ ወዳሸነፈባቸው አካባቢዎች በመሄድ ትግል ማድረግ ይገባል በማለት መግለጫ መስጠታቸውን እንዲሁም ለሰራዊቱ ወታደራዊ ልብስ እና መገናኛ አሬድዮ እና ገንዘብ በመስጠት ድጋፍ ማድረጋቸውን መስክረዋል አሾቱ ብርሃኑ የተባለው ሰባተኛ ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክር በበኩሉ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የሚባለውና በኤርትራ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ተቃዋሚ ድርጅት አባል እንደነበረ እና የድርጅቱ አባል የሆነበት ምክንያትም ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከድቶ ለኤርትራ መንግስት እጁን በመስጠት በዚያው አካባቢ ወታደራዊ ስልጠና ከወሰደ በኋላ መስከረም 25 ቀን 1997 አመተ ምህረት ወደ ድርጅቱ መቀላቀሉን ገልጾ ኮለኔል ፍጹም ይስሐቅ የኤርትራ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንን የተቃዋሚ ድርጅቶችን ሲያስተባብር እንደነበረ ኮነሬሉ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ በተለይ በአማራ ክልላዊ መንግስት አካባቢ የፈንጅ አደጋ እንዲያደርስ በሃገር ውስጥም ሆነ በኤርትራ መንግስት ድጋፍ እንደሚደረግለት የቅንጅት አመራሮች እና አባላት ለዚሁ ተግባር እንደሚተባበሩት የስልክ አድራሻቸውንም እንደሚሰጠው ነግሮት እንደነበረ ለዚህ ጉዳይ አፈጻጸምም የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ከፍተኛ አመራር የሆነ መስከረም አታላይ ጀርመን ሃገር በሚገኘው የኤርትራ ኤምባሲ በኩል ከቅንጅት አመራሮች ጋር እንደተነጋገረበት የነገረ መሆኑን ከዚህም በተጨማሪ ታህሳስ 8 ቀን 1998 አመተ ምህረት ሶስት የቅንጅት አመራሮች ማለትም አርባኛ እና አርባ አራተኛ ተከሳሾች እና አንድ በስም ያላወቀው ሶስተኛ ሰው ጋር በመሆን ወደ ኤርትራ ሄደው ድርጅቱን በእውቀታቸው እና በገንዘባቸው በሰው ሃይል ለማጠናከር በኬንያ በሱዳን በሌሎች ሃገሮች ያሉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደ ትግሉ እንዲቀላቀሉ እንደሚንቀሳቀሱ እና የቅንጅቱ አላማ እና ፕሮግራም ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አንድነት ያለው ስለመሆኑ በየትኛውም የአለም ክፍል ለሚገኙ ኢትዮጵያዊ እንደሚያሳውቁ መናገራቸውን በመግለጽ ቅንጅት በምርጫ ያሸነፈባቸው አካባቢዎች ለወጊያ ሊጠቀምባቸው እንደሚችሉ እና ህዝቡም እንደሚተባበርቸው እንደገለጹላቸው መስክረዋል ተስፋዬ

እማሪ ኢብራሂም ከድር እና ወርቁ ገነት የተባሉት ሶስተኛ፣ አምስተኛ እና ስድስተኛ የአቃቤ ህግ ተጨማሪ ምስክሮች በሁለተኛው ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክር ካሣሁን በላይ እንደተነገረው በተመሳሳይ በመመስከር በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እና በቅንጅት መካከል የአላማ አንድነት መኖሩን የቅንጅቱ መሸነፍ እንደራሳቸው አድርገው እንዲቆጥሩት በድርጅታቸው አመራር አካላት ይነገራቸው እንደነበረ እንዲሁም ከምርጫ ውጤት በኋላ የድርጅታቸው አመራሮች ወደ ሃገር ውስጥ ገብተው ሲመለሱ ከቅንጅት አመራሮች ጋር ተገናኝተው መመለሳቸውን እና ለበለጠ ትግል እንዲዘጋጁ ቅንጅት ያሸነፈባቸው የሰሜን ጉንደር እና ምእራብ ጎጃም አካባቢዎች ለውግያ መጠቀሚያነት እንደሚገለገሉባቸው ህዝቡ ትግሉን በመደገፍ ወታደራዊ እርዳታ እንደሚያደርግና ይኸውም ስንቅ በማቀበል ቁስለኞችን በማገልገል በማከም እንደሚረዳ በቅንጅት ከፍተኛ አመራሮች ቃል እንደተገባላቸው መናገራቸውን በማብራራት የቅንጅት አመራሮች ከታሰሩ በኋላም ለቅንጅት ያልሞተ ኢትዮጵያዊ አይደለም አመራሮቹ እየታሰሩ ስለሆነ እንድረስላቸው በማለት በድርጅቱ ቅስቀሳ ይደረግ እንደነበረ በየበኩላቸው መስክረዋል ተፈሪ ኃይለማርያም የተባለው ስምንተኛ የአቃቤ ህግ ተጨማሪ ምስክር ብርሃን ኃይሌ የተባለው ግለሰብ በማረፊያነት እጠቀምበታለሁ ሲል ለምቻለሁ ባለው ቤት ጥር 20 ቀን 1998 አመተ ምህረት በተደረገው ብርበራ በታዛቢነት መገኘቱን ገልጸው ፖሊስ የፍርድ ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ በወቅቱ ቤቱን ለከፈተችው በስም ያልጠቀሟት ሴት አሳይቶ ወደ ተባለው ቤት ፖሊሶች ብርሃነ ሃይሌን በመያዝ መግባታቸውን በቤቱ ውስጥ ከነበረው ሼልፍ ላይ ከተደረደሩት ሰነዶች እያነሣ ለፖሊስ ሲሰጥ ማየቱን ከሰነዶቹም መካከል ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሕብረት የቀጣይ ትግል ጥሪ የሚል እንዲሁም ከቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ሕገ መንግስታዊ መብቶችን በማስፈን ህዝብን ማረጋጋት አይቻልም በሚል ርእስ ማህተም ያለበት ሰነድ እና ለብርሃነ ሃይሌ ከኤልያስ ክፍሌ የሚል ወረቀት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ሰነዶች ማየቱን በመግለጽ በሰነዶቹ ላይ ብርሃነ ሃይሌ እና ታዛቢዎች መፈረማቸውን መስክረዋል አየኋቸው ያላቸውንም

ሰነዶች ለይቶ ለፍርድ ቤቱ አሳይቷል አዳሙ ለገሰ የተባለው ዘጠነኛ ተጨማሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር መኖሪያ ቤት ፖሊሶች ሲፈተሹ መገኘቱን ገልጾ ፖሊሶች ቤት እንፈትሻለን የምንፈልገው ማስረጃ ስላለ ታዛቢ እንድትሆኑን ነው ብለውት በዚህ መሠረት ፖሊሶች ቤት ውስጥ ገብተው ፍተሻውን ሲያካሂዱ ከኮሞዲኖዎች እና ከጠረጴዛ ስር የሚፈልጓቸውን ዶክሜንቶች እያወጡ ሲይዙ እንደነበረ በተገኙት ዶክሜንቶች ላይ እሱና ሌሎች ታዛቢዎች መፈረማቸውን ፍተሻውን ያካሄዱት ፖሊሶች የመመርመሪያ ትዕዛዝ መያዛቸውን እንደማያስታውስ በፍተሻው ሃደት ፍሬዘር ፈቃደኛ ሆና ማስፈተሸዋን በመግለጽ ለፍሬዘር ነጋሽ አዲስ አበባ ከኤልያስ ክፍሌ ሰሜን አሜሪካ በሚል የተጻፈ ደብዳቤ ማየቱንና በመጀመሪያው ገጽ ላይ መፈረሙን አስታውሶ በአቃቤ ሕግ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ በቁጥር 52 የተመለከተውን ለይቶ አሳይተዋል በተጨማሪም ፍሬዘር ነጋሽ ተገኘበት በተባለው ሰነድ አለመፈረሟን ገልጿል ወ/ሪት መርሻ ተሾመ አስረኛ ተጨማሪ የአቃቤ ሕግ ምስክር ጥር 19 ቀን 98 አመተ ምህረት የፍሬዘር ነጋሽ ቤት ሲፈተሽ ታዛቢ ሁና መገኘቷን በወቅቱ ፍተሻውን ያከናወኑ የነበሩ ፖሊሶች እና እርሷና ሌሎች ታዛቢዎች ፍሬዘርን ተከትለው ቤት ውስጥ መግባታቸውን ቤቱ ውስጥ ኮምፒዩተር የተለያዩ ሰነዶች እንደነበሩና ፈታሾቹ ከኮመዲኖዎች እና ከጠረጴዛ ስር ሰነዶቹን ሲያነሱ ማየቷን በመጨረሻም ፖሊሶቹ ለይተው ባሳዩዋቸው ሰነዶች ላይ ፍሬዘር እና ሌሎች ታዛቢዎች እሷም ጭምር መፈረማቸውን ነገር ግን ከተገኙት ሰነዶች መካከል በአንዱ ላይ ለእይታ በማስታውሰው ሰነድ ላይ ፍሬዘር የኔ አይደለም በማለት አለመፈረሟን ፍተሻው በተደረገው ጊዜ ፖሊሶች የፍርድ ቤት የመመርመሪያ ትዕዛዝ መያዝ አለመያዛቸውን እንደማስታውስ ገልጻ ፈረምኩባቸው ካለቻቸው ሰነዶች መካከል ለፍሬዘር ነጋሽ አዲስ አበባ ከኤልያስ ክፍሌ ሰሜን አሜሪካ የሚለውን ተጨማሪ የአቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ለይታ ለፍርድ ቤቱ አሳይታለች ኮማንደር ግርማይ ካህሳይ የተባለው ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክር ሰኔ 19/97 አመተ ምህረት እና ጥቅምት 19/98 አመተ ምህረት በአዲስ አበባ ከተማ የነበረውን ፀጥታ ሁኔታ አስመልክቶ አረብሻ የተከሰተባቸውን ቦታዎች ለማሳየት የተዘጋጀውን ካርታ ለማስረዳት መምጣቱን ከገለጹ በኋላ በወቅቱ የማእከላዊ ዶስክ መረጃ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ እንደነበረና እያንዳንዱ መረጃ በማየት ምልክት



Scanned by CamScanner

ሲያደርግባቸው እንደነበረ መረጃዎችም አዲስ አበባ ካሉት የማዘገር ጣቢያዎች እና ኮማንዶ ኮስቶች ያገኝ እንደነበረና ከእነዚህ በአቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ቁጥር 68 የተመለከቱ ቻርተሮች በጠቅቱ የተሰበሰበና አረብሻው የተነሳባቸው ነጥብ ቦታዎች የሚያሳዩ መሆናቸውን በመመስከር በተጠቀሱት ጊዜያት ሁከቱ የተነሳባቸውና በረብሻው የደረሰውን ጉዳት የሚጠቁሙ በካርታው ላይ ያሉ ልዩ ምልክቶችን በመጥቀስ አዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በየካ ከተማ ክፍለ ከተማ እንዲሁም ከኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ እና በአራዳ ክፍለ ከተማ ስር የሚካለሉትን ኮማንድ ፖስቶች በመተንተን እና ደረሰ ከተባው ጉዳቶች ጋር በማነጻጸር አስረድተዋል የምስክሮች ቃል እዚህ ላይ ያበቃል።

⇨ በዓቃቤ ህጉ በኩል በቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ላይ የተወሰኑ ተከሣሾች ማስተባበያቸውን ያቀረቡ ሲሆን 92ኛ ተከሣሽ ካሣሁን ከበደ ባቀረበው ማስተባበያ በአጭሩ ሲታይ አቃቤ ህግ ባቀረባቸው ሰነዶች እኔ የኢትዮጵያ መምህራን አመራር አካልና አባል መሆኔን ቀርቶ ተራ አባል መሆኔንም የሚያሳዩ አይደሉም በማስረጃነት የቀረቡት ሰነዶች በሙሉ የኔ አይደ [141] ስለመገኘታቸውም የቀረበ ማስረጃ የለም የኢመማ የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር አባላት ስብሰባ ናቸው በማለት የቀረቡትና ሰኔ 4/1997 ግንቦት 6/1997 እና ግንቦት 20/1997 አመተ ምህረት ተደርገዋል በተባሉ ስብሰባዎች ላይ ባለው ቃለ ጉባኤ የማህበሩ ማህተምም ሆነ የተሰብሳቢዎች ስም ዝርዝር እና ፊርማም የለም ቃለ ጉባኤዎቹ የማህበሩ ናቸው ቢባሉ እንኳን የኔን ተሳትፎ የሚያሳዩ አይደሉም ሰነዶቹ በኔ ቤት ስለመገኘታቸው ማስረጃ አልቀረበም የሚሉ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል 80ኛ ተከሣሽ ደረጀ ሃብተወልድ ባቀረበው ማስተባበያ አቃቤ ህግ በማስረጃነት ባቀረባቸው ጋዜጦች እኔ የሚኒሊክ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አለመሆኔን የሚያሳይ በመሆናቸው እና የተከለከሉትም ሰርቼበት በማላቀው ጋዜጣ ስለሆነ ከክሱ በነፃ እንድሰናበት የሚል ነው። 94ኛ እና 95ኛ ተከሣሾች የቀረበው ማስተባበያ ነሐሴ 2 ቀን 1997 አመተ ምህረት የተዘጋጀው የሲቪል

ማህበረሰብ የግማሽ ቀን ስብሰባ ላይ በተቋቋመው የስራ ቡድን ውስጥ 95ኛ ተከሣሽ ጎም አለመኖሩ እየታወቀ ስሙ እንዳለ መጠቀሱ አግባብ አይደለም ውይይቱም ቢሆን በወቅቱ የዜግነት ኃላፊነታቸውን በህገ መንግስት መሠረት ሃሳባቸውን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብታቸውን ተግባራዊ ከማድረግ ውጪ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ አንድም ሁኔታ መኖሩን አያመላክቱም በስብሰባው የተገኙ ከስባ በላይ የሚሆኑ ሰዎች እንደነበሩና የተንጸባረቀውም ሃሳብ የበርካታ ሰዎች በመሆኑ ማን ምን እንደተናገረ እንኳን ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የተከሣሾች ብቻ ተደርጎ መወሰዱ ተገቢ አይደለም በሰነድ ማስረጃ ቁጥር 52 የቀረበውን በሚመለከት በደብዳቤዎች ሁለተኛ ገጽ ላይ ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ የቅንጅት አገናኝ መኮንኖች ናቸው የሚለውን በሚመለከትም ተከሣሾች ደብዳቤው የተጻፈላቸውንም ሆነ የደብዳቤውን ጸሐፊ አያቋቸውም በዚህ ሁለተኛ ገጽ ላይ አንደኛው ምስክር ፊርማቸው የሌለ መሆኑንም መስክረዋል እነዚህ ተገኙተዋል የተባሉ ሰነዶች ኦርጂናል ያለመሆናቸውንም የሰነዶቹን ተአማኒነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም የሰነድ ማስረጃ ቁጥር 65ን በሚመለከት ይሄንን ሰነድ በሚመለከት ቃላቸውን ስለሰጡት ምስክር የሚተች በመሆኑ ማስፈር አስፈላጊ ሳይሆን ቀልፏል በቁጥር 62 እና 66 ስር የተመዘገቡ ሰነዶች ተከሣሾች ከምርጫው በፊትና በኋላ ሲያደርጉት የነበረውን ጠቃሚ ስራ የሚያስረዱ እንጂ ሌላ ይዘት ያላቸው አይደሉም የሚሉ ናቸው ሌሎችም በርካታ ተቃውሞ በሚል ክሱን በሚመለከትና የክሱን ፍሬ ነገር በሚመለከት ያቀረቡ ቢሆንም ከተቃውሞ አንጻርም ከቀረበው ክተቃውሞ አንጻር ይሄንን ከላይ ያሰፈርነውን ብቻ ማስፈሩ በቂ ሆኖ አግኝተነዋል። 72ኛ ተከሣሽ ጠሰን ሰገድ ገብረኪዳን የተባለውም ባቀረበው ማስተባበያ እኔ የአዲስ ዜና ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኜ መስራት የጀመርኩት ከሐምሌ ወር 1997 ጀምሮ ነው በአቃቤ ህግ በኩል በተጨማሪ ማስረጃነት በቀረበው ከግንቦት 10/1997 አመት ምህረት እኔ አልተሳተፍኩም በጋዜጠኝነት ሙያም አልሠራሁም በወቅቱ የነበሩ አዘጋጆች በጋዜጣው ላይ የሚታዩ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይሄንን የተሳላተ የአቃቤ ህግ ማስረጃ

ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት አቅርቧል ተከሣሽ በድሩ አደም ያቀረበው ማስተባበያ የሰነድ ማስረጃዎችን በማመለከት ያልሆነ በተለይም በሸዲዩ የቀረበውን የሚመለከት ስለሆነ ጊዜውን ያልጠበቀ በመሆኑ ማስረፈ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበው ማስረጃና በአንዳንድ ተከሣሾች የሰነድ ማስረጃን በማመለከት የቀረበው ማስተባበያ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ክስ ከማስረጃው ጋር በማገናዘብ መርምሮታል አቃቤ ህግ በሁሉም ተከሣሾች ላይ ባቀረበው አንደኛ ክስ ላይ ተከሣሾች ተሳልፈዋል በማለት ያቀረበው ክስ አባሪ ተባባሪ በመሆንና በማደም የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ለ 38 34 27/1 እና 238/2,258 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ህገ መንግስቱና በህገ መንግስታዊ ስርዓት ላይ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ሲሆን በሙከራ ደረጃ ተጥሷል የተባለው የወንጀል ህግ ቁጥር 238 በመሆኑ ይህ አንቀጽ ምን አይነት ይዘት እንዳለው ማየቱ ተገቢ ይሆናል በዚህ አንቀጽ መሰረት ማንም ሰው በሃይል በዛቻ በአድማ ወይም ህገ ወጥ በሆነ በማናቸውም መንገድ እስቦ የፌደራሉን ወይም የክልሉን ህገ መንግሥት ወይም በህገ መንግስት የተቋቋመውን ስርዓት ያፈረሰ የለወጠ ወይም ያገደ እንደሆነ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትልበት ሲሆን አቃቤ ህግ በክስ ማመልከቻው እንደጠቀሰው ይህ የወንጀል ድርጊት ተሞክሯል የተሞከረበት ጊዜም ሃገሪቷ የጉረቤት ሃገር ከሆነው የኤርትራ መንግስት ጋር የጦርነት ስጋት ባለበት ጊዜ ስለሆነ ይህ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግ ቁጥር 258 የተጠቀሰውን ከባድ ሁኔታ የሚለውንም የሚሸፍን ስለሆነ ይህንኑ አንቀጽም ጠቅሷል የወንጀል ህግ ቁጥር 238 ከላይ የመሰለው ይዘት ያለው ሲሆን ተከሣሾች ይህንን የወንጀል ድርጊት በእርግጥ በሙከራ ደረጃ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል አልፈጸሙም የሚለውን ሁኔታ ለማየት የሚከተሉትን ጭብጦች ይዘናል አንደኛ በቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ድርጅት ስር በመሰባሰብ ከግንቦት 7/1997 አመተ ምህረት ምርጫ በፊት ሲደረግ በነበሩ ቅስቀሳዎች መግለጫዎች ቃለ መጠይቆች እና

ከምርጫው በኋላ ውጤት እስኪገለጽ ውጤት ከተገለጸም በኋላ በዚህ በተጠቀሰው ድርጅት ስር ሲንቀሳቀሱ በነበሩ ግለሰቦችና አመራሮች ምርጫውን በማስመልከት ሲደረጉ በነበሩና በየጠረጴዛም፣ ሲካሄዱ በነበሩ ውይይቶች ጋዜጣዊ መግለጫዎች በየጋዜጣው እርስ እንቀጽና ለተለያዩ ግለሰቦች ሲደረጉ በነበሩት ቃለ መጠይቆችና ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት እንዲሁም ከጥቅምት 21 ቀን 1998 አመተ ምህረት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በተቀሰቀሰው የአመጽ እንቅስቅሴ መካከል የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖር አለመኖር አንደኛው መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ከላይ በአንደኛው ለተነሳው ጥያቄ ምላሹ አዎንታዊ ከሆነ ይህ ከላይ በተጠቀሱት ቀናት የተፈጸመው ድርጊት የወንጀል ድርጊት መሆን አለመሆኑና ወንጀል ከሆነ በወንጀል ህግ ቁጥር 238 ስር የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን የምንመለከት ሲሆን በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ክስ የቀረበባቸው ተከሣሾች በዚህ ረገድ ተሳትፎ ነበራቸው ወይስ አልነበራቸውም ማለትም የእያንዳንዱ ተከሣሽ ተሣትፎ ምን እንደነበር ማየት የሚሉትን በቅደም ተከተል እናያለን በአቃቤ ህግ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ሁሉም ለማለት በሚቻልበት መልኩ አንደኛውን ክስ እንደሚያስረዱለት በአቃቤ ህግ በኩል የተገለጸ በመሆኑ ሁሉንም እንደአግባብነታቸው አይተናቸዋል ከግንቦት 7 ቀን 1997 አመተ ምህረት ከተደረገው ምርጫ በፊት ታህሳስ 24 ቀን 1997 አመተ ምህረት የኢትዮጵያና የኤርትራ ድንበር ጉዳይን በማስመልከት በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ አንደኛው ተከሣሽ ሃይሉ ሻወል ለተሰብሳቢዎች ባደረገው ንግግር የህዝብን ሃይል ማንም ሊመልሰው እንደማይችል ይህንንም በብዙ ሃገራት ለምኑን የታየው ሊያስተምራቸው እንደሚገባ በመግለጽ ለተሰብሳቢው በአሁኑ ጊዜ ስልጣናችሁ በሃገር አስተዳደር ተወስዶባችኋልና ይህንን መንግስት ከስልጣን ለማውረድ መጀመር አለባችሁ ዛሬውኑ ህዝቡ በአንድነት በመተባበር ዛሬውኑ ከታች እስከ ላይ ያለውን ባለስልጣን እናወርደዋለን ትልቁን ባለስልጣን ለማስወገድ መጀመሪያ ትንሹን እንበል ማለት እንደሚያስፈልግ ለምኑን በተለያዩ ሃገራት የታየው እዚህም የማይደረግበት ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ ንግግር መደረጉን በግልጽ



Scanned by CamScanner

ተመልክተናል መጋቢት 3 ቀን 1997 አመተ ምህረት በደጀንና በደብረ ማርቆስ በተደረጉ ምርጫ ቅስቀሳዎች በቅስቀሳው ወቅት ዘጠነኛው ተከሳሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ ለተሰብሳቢው ባደረገው ንግግር ገዢው ፓርቲ ምርጫውን ካጭበረበረ ህዝቡ እንደማይለቀው በዩክሬንና ጆርጂያ እንዲሁም በሊባኖስ እንደተደረገው ህዝቡ በማመጽ የማይፈልገውን ስርዓት እንዳባረረ እዚህም ይሄ ከመሆኑ በፊት በሰላም ልቀቁ ጽምጹን አክብሩለት በማለት የተናገረው ይገኛል ከምርጫ በፊት የነበረውን ሁኔታ ለማስረዳት በቀረበው ሌላ ማስረጃ የካቲት 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት በሰሜን ሆቴል በቅንጅት ስም የተሰጠ መግለጫ ሲሆን በዚህ ህዝብን በማሸማቀቅና በማጭበርበር ለመመረጥ መሞከር ወንጀል ነው በሚል መግለጫ በምርጫ ምዝገባና ቅስቀሳ ወቅት እያጋጠሙ ያሉ የተለያዩ ችግሮችንና መንግስት እየፈጸመው ያለው ግፍን በመጥቀስ ምርጫ ቦርድም ከኢህአዴግ ሙስናዊ አሰራር ውጪ ስላልሆነ መፍትሄ ለመስጠት የሚችል አካል አይደለም በመሆኑም ህዝቡ ምርጫው ፍትሃዊ እንዲሆን የተዛባውን ምርጫም ለማስቀልበስ እንዲነሳ ከወዲሁ ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ ጥሪ ማቅረቡን መረዳት የሚቻል ሲሆን ከመግለጫው በኋላም አንደኛው ተከሳሽ ኢንጂነር ኃይሉ ሻወል ኢህአዴግ በዚህ ምርጫ ኢያሸንፍም ከህዝቡ ጋር ተጣልቶ ሌላ ችግር ይመጣል ኢህአዴግን ስልጣን እናስለቅቀዋለን ማለቱን አራተኛ ተከሳሽ ኢንጂነር ግዛቸውም የፍትህ ስርዓቱና ምርጫ ቦርድ መፍትሄ መስጠት የማይችሉ የገዢው ፓርቲ መሣሪያዎች ስለሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱን ትግል ያካሂዳል ማለቱንና ዘጠነኛ ተከሳሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ፈቅዶ ስልጣን አይለቅምና ህዝብ ስልጣኑን ለማስከበር መንቀሳቀስ አለበት በማለት ሲናገር አስረኛ ተከሳሽ ፕሮፌሰር መስፍንም በትግል ሊያጋጥም የሚችል ችግሮችን ከገለጸ በኋላ በቅርቡ በጆርጂያና ዩክሬን የተደረጉት ለእኛም ለወያኔም ምሳሌ ይሆናሉ ማለቱን ሃያኛ ተከሳሽ እንዲሁም አራተኛም እንዲህ አይነት አንባገነናዊ መንግስት የሚወገደው ህዝባዊ



Scanned by CamScanner

ሰላማዊ አመጽ ስለሆነ ለምን ከዚህ አቅጣጫ እንደማይሰራና ህዝቡን ለምን ለዚህ አናዘጋጀውም በማለት መናገሩን ከቀረበት ቪዲዮዎች ተመልክተናል ከግንቦት 7/1997 አመተ ምህረት በፊት በጋዜጦች የወጡትን ጽሁፎችም አጠር ባለ መልኩ ያየናቸው ሲሆን ይኸውም በነፃ ምርጫ ያልተገኘ ስልጣን በህዝባዊ አመጽ ይረጋገጣል በሚል ርዕስ አንቀጽ ስር በሰፈረው ጽሁፍ የግንቦት 7ቱ ምርጫ ከተጭበረበረና ኢህአዴግ አሸናፊነቱን ካወጀ በዩክሬን የታየው ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ እንደሚከተል በጆርጂያ በኢድዋርድ ከቨርናዜ ላይ የደረሰው ቅሌት በሃገራችን እንዲደገም ከምርጫው ጎን ለጎን ህዝቡን በዚህ ረገድም ማዘጋዘጀት እንደሚጠበቅበት ነፃ ምርጫ ተካሂዶ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን ካልተቀዳጀ የኢትዮጵያ ሰራዊት በህዝባዊ አመጽ ባለሃገርነቱን እንደሚያውጅ ወደ ምርጫ ሲገባ ኢህአዴግ ምርጫውን አያጭበረብርም በሚል ሙሉ እምነት ሳይሆን በተጭበረበረ ምርጫ አሸነፍን በሚሉ ሰዎች ላለመገዛት ወደ ህዝባዊ አመጽ ለመሸጋገር የህዝቡ መነሳሳት ትልቅ ትርጉም ስለሚኖረው ጭምር መሆኑን ኢህአዴግ ምርጫውን አጭበርብሮ ስልጣን ላይ እቀጥላለሁ ካለ ህዝባዊ ስልጣን የሚመነጨው በህዝብ አመጽ ብቻ መሆኑን መግለጹን በሌላ በኩል ሰራዊቱ በአላማም ከኢህአዴግ ይልቅ ለተቃዋሚዎች ይቀርባል በሚል ርእስ አንቀጽ ስር በወጣው ጽሁፍ ምርጫው ተጭበርብሮ ህዝባዊ አመጽም ከተሰናከለ የትጥቅ ትግል ቀጥሎ በመጨረሻ ኢህአዴግ ተሸንፎ በሰራዊት ላይ 1983 አመተ ምህረት የታየው መበተን እንደሚከተል የካቲት 26/97 በወጣው ጋዜጣም የወጣው መግለጫ ደግሞ የኢህአዴግ አገዛዝ የሚወገድበት ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ እንዲነሳ መቀስቀስ ማደራጀትና መምራት የሁሉም ሃገር ወዳድ ዲሞክራት ተቀዳሚ ስራ መሆን እንዳለበት የገለጸ ማስረጃ አቃቤ ህግ ካቀረባቸው ማስረጃዎች ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች ምርጫው ከመደረጉ በፊት የኢትዮ ኤርትራን ድንበር ጉዳይ በማስመልከት በተጠራው ሰብሰባ የደጀንና የደብረ ማርቆስ የምርጫ ቅስቀሳ እና በምርጫ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን የደጀንና የደብረ ማርቆስ የምርጫ ቅስቀሳ እና በምርጫ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በማስመልከት በተሰጡ መግለጫዎችና ከግል ጋዜጦች በግልጽ የተደረገው ቅስቀሳ



Scanned by CamScanner

በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የህዝብ ይሉኝታ የሌለውና በመሳሪያ በመተማመን ህዝቡን ስልጣን የነጠቀ እንደሆነ ህዝቡ ይህንን ማስወገድ እንዳለበት በመግለጽ የፍትህ አካላቱንና የምርጫ ቦርድን በከፍተኛ ሁኔታ በማጥላላት በተለይ እነዚህ ሁለቱ አካላት የገዢው ፓርቲ መሣሪያ እንጂ ሌላ ምንም እንዳልሆኑ በእነዚህ አካላት ምንም አይነት ፍትህ ይገኛል ተብሎ እንደማይጠበቅ ለህዝቡ በመግለጽ ነገ ወደ ፊት ግንቦት ላይ የሚደረገው ምርጫም ስለሚጭበረበር ህዝቡ በከፍተኛ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ይህንን ሁኔታ መቀልበስ እንደሚገባው በዩክሬንና ጆርጂያ የተደረጉትንም በመደጋገም እንደ ምሣሌ በማቅረብ ህዝቡን በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በተመሳሳይ ሁኔታ ከስልጣኑ ያስወግደዋል በማለት መዛቱንና መቀስቀሱን ለመረዳት ይቻላል አንደኛው ተከሣሽ የኢትዮ ኤርትራን ጉዳይ በማስመልከት በተደረገው ስልፍ ዩክሬንና ጆርጂያን በግልጽ ባይጠቅስም ለምኑን ህዝብ በየቦታው ያደረገውን ማስታወሱና እኛስ ከማን እናንሳለን ማለቱ ከዚህ በኋላ በቅንጅት ቅስቀሳና መግለጫ ወቅት ይህ ሁኔታ በግልፅ በሌሎች ተከሣሾች መገለፁ አንደኛ ተከሣሽም ይህንን ማለትም ዩክሬንና ጆርጂያን ማለቱን እንደሆነ ግልፅ ያደርገዋል በግል ጋዜጠኞም በተመሣሣይ ሁኔታ መቀስቀሱን ለመመልከት ተችሏል ይህ ሁኔታ ማለትም ከምርጫ በፊት የተደረጉ ቅስቀሳዎችና መግለጫዎች መታየት ያለባቸው ከምርጫ በኋላ ከሆነውም ጋር በማጣመር ስለሆነ ከምርጫ በኋላ የነበረውን ሁኔታ ቀጥሎ እናያለን

ግንቦት 7 ቀን 1997 አመተ ምህረት በሃገር አቀፍ ደረጃ ምርጫ ከተደረገ በኋላ እስከ ግንቦት 29 ቀን 1997 አመተ ምህረት በነበሩት ጊዜያት በቅንጅት ሲወጡ የነበሩ ጋዜጣዊ መግለጫዎች በሚታዩበት ጊዜ በግንቦት 9 11 እና 12 መግለጫዎች ገዢው ፓርቲ ወቅቱን ሳይጠብቅ አሸነፍኩ ብሏል በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ቆጠራው በገዢው ፓርቲ እንዲቋረጥ ተደርጓል ገዢው ፓርቲ በማስገደድ በአፈናና በማጭበርበር ድምጽን እየቀማና ተቃዋሚዎች ያሸነፉንበትንም በመቀልበስ ላይ እንደሆነ ገዢው ፓርቲ



Scanned by CamScanner

ለሚቀጠሉት አምስት አመታት በስልጣን ሊያቆየው የሚችለውን ድምጽ በህገ ወጥ መልክ ከህዝብ እየነጠቀ ስልጣኑን ለማራዘም ጥረት እያደረገ መሆኑን ምርጫ ቦርድም ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል ምንም አይነት እርምጃ ያለመውሰዱንና የመሳሰሉትን በመጥቀስ ህዝቡ የተናጥል እርምጃ እንዳይወስድ ቅንጅቱ የሚሰጠውን ሰላማዊ ጥሪ እንዲጠባበቅ ጥሪ ማቅረቡን የሚያሳዩ ናቸው ግንቦት 15 እና 18 ባወጣቸው መግለጫዎችም ከላይ የተሰነዘሩትንና ከድምጽ ቆጠራው ጋ ተከስተዋል የተባሉ ችግሮችን በማጠናከር ቅንጅት ከአሁን በኋላ የህዝብ ድምጽ እየተነጠቀ ከዚህ በላይ ታግሶ መቆየት እንደማይችል በመግለጽ በሰላማዊ ትግል ማእቀፍ ውስጥ ያሉትን ማንኛውንም ስልት በመጠቀም ድምጹን ለማስመለስ ዝግጁ እንዲሆን ጥሪ ማቅረባቸው የሚታይ ሲሆን ግንቦት 23 ባወጣው መግለጫም ከላይ የተጠቀሱት ችግሮችን በድጋሚ በመግለጽ ህዝቡ የተቀማውን ድምጹን በሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴ ለማስመለስ እንደሚገደድ ቅንጅት የሰከነ አመራር ለመስጠትም አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሆነ ገልጸ ሊወሰዱ የታሰቡት እርምጃዎችንም ማለትም በሃገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች በርካታና ተከታታይ ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፎች የትምህርት የትራንስፖርት የንግድና የማምረት ስራ ከማቆም ጀምሮ እስከ ሃገር አቀፍ የስራ ማቆም እርምጃ ለመውሰድ ህዝቡ ዝግጁ ሆኖ የቅንጅትን ጥሪ በንቃት እንዲጠባበቅ በማለት የቀረበ መግለጫ ሲሆን ከመግለጫ በኋላ በቪድዮ ማስረጃ ተራ ቁጥር 8 እንደታየው በመድረኩ ላይ በነበሩ ግለሰቦች በተሰጠው ማብራሪያም የዚህ አይነት ፖለቲካዊ ጉዳይ በፍርድ ቤት ያከትማል ማለት እንደማይቻል የተገለፀ ሲሆን 8ኛው ተከሳሽ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋም ዩክሬንና ጆርጂያ ጉዳይን በማንሳት በረከት በራሱ ላይ የሚደርስበት ስላልመሰለው ህጋዊ ነው በማለት መግለጫ ሰጥቶ የነበረ በመሆኑ አሁን ህገ ወጥ ነው ሊል አይችልም በማለት መናገሩንና መግለጫ መስጠቱን ተመልክተናል ግንቦት 29/1997 አመተ ምህረት ከቅንጅትና ከህብረት በጋራ በተሰጠ መግለጫ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡ የተጀመረው እንቅስቃሴ ሃገር አቀፍ፡ ሽፋን በመያዝ በኢህአዴግና በህዝብ መካከል አላስፈላጊ ግጭት ይፈጠራል በማለት የሰጡት መግለጫ ሲሆን በተራ ቁጥር 37



Scanned by CamScanner

በቀረበው ሰነድ ሁለተኛው ተከሣሽ አባይነህ ብርሃኑ የኒ ጽሑፍ ነው በማለት በገለጸበት ጽሑፍ ላይ ተማሪዎች እስኪበተኑ በገዢው ፓርቲ የተወሰነ ሲሆን ሶላሰ ሰዎ የትምህርት ማቆም አድማ በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች በሙሉ ይደረጋል የሚል ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘም አቃቤ ህግ ምስክሮችን አቅርቦ አስምቷል ቀርበው የተሰሙት ምስክሮች ቃልን ከማየታችን በፊት በእነዚህ ጊዜያት ማለትም ከግንቦት 7 በኋላ በተለያዩ ጋዜጦች ሲወጡ የነበሩ ዘገባዎችን በአጭሩ ተመልክተናል ከምርጫው በኋላ እስከ ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት በተለያዩ ጋዜጦች ጽሑፎች ጥቂቶችን ለአብነት እንደሚከተለው አይተናቸዋል ይኸውም ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ ሲባል ህዝብ ለመብቱ ሲል ማመጽ እንዳለበት የመለስ አገዛዝ ይወገድ ብሎ መሰለፍ ማደም መታገል እንደሚገባው በሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ አገዛዙን ማናደድ ብቻ ሳይሆን ብርክ አስይዞ ከስልጣን ለማስወገድ የተቃኘ መሆን እንዳለበት የማያቋርጥ የህዝብ አመጽ ትግል ማደራጀት የግድ እንደሆነ የተቃውሞ ሰልፍ ተፈቀደም አልፈፈቀደም ለፀረ ህዝብ ትግል አንገዛም ማለት የስራ ማቆም አድማ ማካሄድ የረሃብ አድማ ሰልፍ ሰልፍ ሰልፍ እንቢ አልገዛም አድማ አድማ አድማ ይህ ነው ፍቱን መንገድ አገዛዙን አስጨንቆ ለመጣልና ሃገርን ለማዳን በማለት በዝርዝር በጋዜጣ ቀርቧል በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 13/97 በወጣው ጋዜጣ በህዝብ ድምጽ አደጋ ላይ የወደቀውን ወንበር በጉልበት በመሣሪያ ጋጋታ ጠግኖ ለማቆየት የሚደረገው ሙከራ ውጤቱ የከፋ እንደሚሆን ኮሮጆ እየሰረቁና እየገለበጡ አሸናፊነትን ማወጅ እንደማይቻል የኢህአዴግ መንግስት በከፍተኛ ድምጽ የሚመነጨውን ስልጣን በአፈ ሙዝ መቀልበስ እንደሌለበት ይገልጻል በመቀጠልም ግንቦት 17/97 አመተ ምህረት በወጣው ጋዜጣ ኢህአዴግ አሸናፊነቱን ቢያውጅ በፍጹም ተቀባይነት እንደማይኖረው ፍርሃትን አሽቀንጥሮ የጣለና ድፍረትን የተላበሰ ህዝብ ድምጽ ሲሰረቅበት በቸልታ እንደማይመለከት ተስፋ የማይታየው ህዝብ ተስፋውን ጭምር በነጠቁት በፍጹም እንደማይገዛና ኢህአዴግ በተለይ አቶ

Scanned by CamScanner

ሙሉን በመጨረሻው ሰዓት እራሳቸውን ከውድድሩ ዝግጅቱንም ከአደጋ እንዲታደጉት
ኖሪ ማትረቡን ግንቦት 19/97 በወጣው ጋዜጣም ኢህአዴግ ምርጫውን
ማጭበርበሩን ምርጫ ቦርድ የኢህአዴግ ወገን መሆኑን ቦርዱ በእውነተኛ ማስረጃ
ከሆነ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንደማይደረግ የማይወስን ከሆነ ግን የህዝብን
ተቃውሞ የሚያስነሳና የግድ በሰላማዊ ትግልና ግፊት ይህ ስልጣን መደምደሙ
እንደማይቀር ይህ መንግስት ወይ በሰላም ወይ በህዝብ ግፊት ስልጣኑን እንደሚለቅ
የሚያስረዳ ነው ግንቦት 26/97 በወጣው ጋዜጣ ምርጫ ቦርድ ገዢው ፓርቲ
አገናኙነትን የሚገልጽ ከሆነ ቅንጅቱ ለህዝብ ጥሪ የሚያቀርብ መሆኑን ከዚህ
ዙፋ ግንቦት 20/97 የወጣው ጋዜጣ ደግሞ ኢህአዴግ በጉልበት ስልጣን ላይ
ለመቆየት በማያደርገው ጥረት ተከትሎ ብጥብጥ ሲነሳ ኢህአዴግ ኃላፊነቱን ወደ
ሌሎች ለማላከክ ምክንያት መደርደር እንደማያዋጣው የገለጸበት ይገኛል በየጋዜጦቹ
ሊዘገቡ የነበሩት ከላይ የመሰለው ሲሆን ቀጥሎ ምስክሮች ቃል እናያለን አቶ ግርማ
ግንቦት 28 ቀን አቶ ግርማ የተባለው ምስክር ግንቦት 28 ቀን 1997 አመተ
ምህረት በመኢአድ ጽ/ቤት በተደረገው ስብሰባ ላይ ምስክርነቱን ለመስጠት
እንደመጣ ገልጾ በስብሰባው ወደ አምስት መቶ ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ
ወጣቶችና ደጋፊዎች እንደነበሩ ስብሰባውንም ሲመሩ የነበሩት አባይነህ ብርሃኑ
ማሙሸት አማረና መስፍን አማን የተባሉት እንደነበሩ ገልጾ በእለቱ ለተሰብሳቢው
ምርጫው በመጭበርበር ምርጫውን በማጭበርበር ኢህአዴግ አሸነፍኩኝ እያለ ነውና
ድርጅቱ ለሚወስደውና በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት ሁሉንም ነገር እያደረጋችሁ
ትከተሉናላችሁ በማለት አባይነህ ብርሃኑ ለተሰብሳቢው ሲናገር እንደነበር
ከተሰብሳቢዎች መካከልም አንድ ወጣት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እድል ይሰጠኝ
በማለት የያዘው ወረቀት እንዲባዛለት ጥያቄ ሲያቀርብ ብር ወጪ ተደርጎ ወረቀቱ
ኮፒ ተደርጎ እዚያው ለተሰብሳቢው እንዲበተን የተደረገ መሆኑን ይህ እንዲበተን
የተደረገው ወረቀትም በሰነድ ማስረጃነት ለፍርድ ቤቱ የቀረበ እንደሆነ ምስክሩ
በማረጋገጥ የመሰከረ ሲሆን የሰነዱን ይዘትም ጥሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ተማሪዎች የሚል ርእስ ያለው ሆኖ ዝርዝሩ ላይም ምርጫው መጭበርበሩንና

ከምርጫ ጋር የተፈጠረ ችግርችን በመግለጽ የዩኒቨርስቲው ተማሪ እዳን አጣጥፎ እንደማይቀመጥ ሌሎች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ከጐናቸው እንዲቆሙ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ከዘመናት አዘቅት ከገባችበት ሊያወጣት የሚችል ኃይል በምትሻበት ሰዓት ትገኛለችና ይህንን ኃላፊነታችንን እንድንወጣ ጥሪ እናደርጋለን የሚል ይዘት ያለው ነው ማሙሽት የተባለው ተከሣሽም በዩኒቨርስቲው ለሚደረገው የረሃብ አድማ ከጐናችሁ እስከ መጨረሻው እንቆማለን በማለት መናገሩንም ተመስክሯል ይህ ከሆነ በኋላ ግንቦት 29 እና 30 ረብሻ ከዩኒቨርስቲው መጀመሩን አውቃለሁ በማለት ቃሉን አጠናቋል ወ/ሪት እየሩሣሌም የተባለችውም ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ቃልዋን የሰጠች ሲሆን አቶ ዳኛቸው ተካ የተባሉት ምስክርም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥበቃ ኃላፊ እንደሆኑ ገልጸው ግንቦት 29 ቀን 1997 አመተ ምህረት ሰባት መቶ የሚሆኑ ተማሪዎች ሌሊት ላይ በመነሳት መለስ ከስልጣን ይውረድ የኢህአዴግ አመራሮች መሃይሞች ናቸው እና የመሳሰሉትን ሲያስተጋቡ እንደነበር ከዚህ ቀን በፊትም የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች ከመኢአድ ቅንጅት በሚል ለመላው ኢትዮጵያ የሚልና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ሲበተኑ እንደነበር ገለጸ በግቢ ውስጥ ግንቦት 29 ቀን ለ30 አጥቢያ ሌሊት የተጀመረው በዚሁ ሁኔታ አድሮ በሁለተኛው ቀንም ተመሳሳይ ሁኔታ የነበረ ሲሆን እረብሻው ከግቢው ቁጥጥር ውጪ በመሆኑ የፌደራል ፖሊስ በመምጣት ጸጥታውን ተቆጣጥሯል ሲል መስክሯል ከግንቦት 29 30 እስከ ሰኔ 1 እና 2 የነበሩ የአመጽ እንቅስቃሴዎችን ለማስረዳት ከቀረቡት ምስክሮችም ሳጅን አራጌ እሹቴ የተባለው በሰጠው ቃል ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አካባቢ እንደነበር በግምት አራት ሰዓት አካባቢ መንገዱ በድንጋይና በመሳሰሉት ተዘግቶ እንደነበር በአካባቢው የነበሩ ወጣቶችም እኛ ላይ ማለትም ፖሊስ ላይ ድንጋይ ሲወራወሩና ቅንጅትን የጣት ምልክት እያሳዩ የእናቶቻችን ድምጽ ተሰርቆ አይቀርም ይሉ የል ዘንድሮ

የወያኔ ጉሮና ተመሳሳይ መፈክሮችን ሲያሰሙ እንደነበርና አንድ አባል በድንጋይ መምታቱንም እንደሚያቅ ገልጿል አያና ተርፌሳ የተባለው የፖሊስ አባልም በሰጠው ቃል ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በወንጀል መከላከል ስራ ላይ እንደነበር ገልጾ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ በአዲስ ከተማ ት/ቤት አካባቢ እና መሳው መርካቶ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ አመጽ እንደነበር በከተማ አውቶቢሶች ላይ ጉዳት ላይ ጉዳት እንደደረሰ በጊዜውም አመጹን ሲሳተፉ በነበሩ ሰዎች ቅንጅት አሸንፏል ኢህአዴግ ወድቋል በማለትና የቅንጅትን የጣት ምልክት እያሳዩ በፖሊስና በተለያዩ ተቋማት ድንጋይ ሲወራወሩ ነበር በጊዜውም ገጀራ ሳንጃ እና ዱላም ተይዞ የነበረ ሲሆን ነዳጅ በያዘ ጠርሙስ እሳት በመለኮስ ወደ ፖሊስና ወደ ማደያ ሲወረወር እንደነበር በጊዜው በአካባቢው የነበረውን የነዳጅ ማደያ እንደምንም በማለት የተከላከሉ መሆኑን በሰጠው ቃል ገልጿል ሳጆን ደቤሳ ፈይሳ የተባለው የፖሊስ አባልም ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት የካ ክፍለ ከተማ ኮተቤ የመምህራን ኮሌጅ አካባቢ በወንጀል መከላከል ስራ ላይ እነደነበር ገለጾ በእለቱ ከቀኑ አራት ሰዓት አካባቢ የአካባቢው ዱርዬዎች ተሰባሰበው ተማሪዎች ዘንድ በመሄድ አትገሉም ወይ እያሉ በማዜም ከተማሪዎች ጋር ተደባልቀው በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ እረብሻ መፈጠሩን በእለቱ መንገድ በድንጋይ በጉማና በጊንዲላ እንጨት እንዲዘጋ ከተደረገ በኂላ አንድ የመከላከያ ፒካፕ ላይ ቢንዚል በማርከፍከፍ ሙሉ በሙሉ እንዲቃጠል መደረጉን በጊዜው ቢንዚኑ ቤንዚል ያለው ጠርሙስ ድንጋይና ገጀራም የያዙ ሰዎች እንደነበሩ ወያኔ ሌባ ፖሊስ ሌባ በማለት የቅንጅትን የጣት ምልክት ሲያሳዩ እንደነበርና የመፈንከትና ሌላ ጉዳት የደረሰባቸው የፖሊስ አባላትን በዝርዝር በመግለጽ ቃሉን አጠናቋል ኪዳኔ አያና የተባለው ፖሊስም ሰኔ 1 እና 2 ቀን 1997 አመተ ምህረት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 አካባቢ ስራ ላይ እንደነበር ገልጾ በእለቱ በርካታ ወጣቶች መንገዶችን ጉማ በማቃጠል በመዝጋት ድንጋይ በፖሊስ ላይ በመወርወር የተለያዩ ብረቶችን ይዘው እንደነበርና የቅንጅትን የጣት ምልክት እያሳዩ ወያኔ ሌባ በማለት ሲያሰሙ እንደነበር መንገዶች እንዳይዘጉ ሲከላከሉ በነበሩ ፖሊሶች ላይም ጉዳት የደረሰባቸው

እንደሉ ኮንስታብል ተዘራ የተባለው ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ጭንቅላቱ ላይ እንደደረሰበት ገልጿል ምስክሮች ከሰጡት ቃል በተጨማሪም ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት የነበረውን የአመጽ ሁኔታ ከፊልሙን በቪድዮ ለመመልከት የቻለ ሲሆን ይዘቱም ከላይ የሰፈረ በመሆኑ የሰፈረ ሲሆን በተለይ በቅንጅት ስለ ድምጽ መሰረቅ ሲቀሰቀስ በነበረው መልኩ በተማሪውም ሲስተገባ እንደነበር ተመልክተናል ከላይ በተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች ማለትም ከግንቦት 7 በኋላ የነበሩት ሁኔታዎች ሲታዩ ምርጫውን ገዢው ፓርቲ አጭበርብሯልና ህዝቡ ይህንን ሁኔታ ለመቀልበስ ዝግጁ ይሁን በማለት በቅንጅት መግለጫዎች በየጋዜጦች ሲወጡ በነበሩ ርእሰ አንቀፆችና ቃለ መጠይቆች ሲቀሰቀስና ሲዛት በነበረው መልኩ ግንቦት 29 ቀን 1997 አመተ ምህረት ጀምሮ እስከ ሰኔ 2 ቀን 1997 አመተ ምህረት በዘለቀው አመጽ በርካታ ወጣቶች በቅንጅት አመራርና በየጋዜጦች ሲስተጋቡ የነበሩትን አቋሞች ማለትም ምርጫው በገዢው ፓርቲ ተጭበርብሯል በመሆኑም ገዢው ፓርቲ ስለጣኑን በሃይል ተነጥቆ ሊወገድ ይገባል በሚል የሃይልና የአመጽ እንቅስቃሴ መደረጉን መገንዘብ ይቻላል በተለይም የአመጹ ሁኔታ ሲታይ በአንድ ቦታ ብቻ ተወስኖ የተገደበ ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች መሆኑና ጥቃት ሲደርስባቸው የነበሩ አካላትም የፖሊስ አባላት የመንግስት ተቋማት ከመንግስት ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ ግለሰቦች ከመሆናቸውም በላይ ይሄንን አመጽና ጥቃት ሲያደርሱ የነበሩ ሰዎችም የቅንጅትን የጣት ምልክት እያሳዩ የተለያዩ ጉዳቶችን ማድረሳቸው ሲታይ ቅንጅቱ ሲያወጣው ከነበሩት መግለጫዎች በየጋዜጣው ሲወጡ የነበሩ መግለጫዎችና ሰኔ 1 ቀን 1997 እና በተከታዩ ቀን በተፈጸመው የአመጽ ተግባር የምክንያትና የውጤት ግንኙነት አላቸው ወይ ብለን ስንመረምር የወንጀል ሕግ ቁጥር 24 ላይ እንደተደነገገው በነገሮች በታወቀ ወይም በተለመደ ሂደት የተከሰተ ድርጊት ውጤቱን ለማስገኘት በቂ ሆኖ ሲገኝ በምክንያትና በውጤት ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻል ሲሆን



Scanned by CamScanner

በእርግጥም ሲሰጡ የነበሩ መግለጫዎች ይዘታቸው በተለይ ከምርጫው ምርጫው ከመደረጉ በርካታ ወራት በፊት ምርጫው ስለሚጭበረበርና መንግስትም ስልጣን ስለማይለቅ መንግስትን በዩክሬንና በጆርጂያ በተደረገው መልኩ ከስልጣን እናስወግዳለን በማለት በተደጋጋሚ ሲዛትና ሲቀሰቀስ እንደነበር እንዲሁም ምርጫው ግንቦት 7 ከተከናወነ በኋላም ድምጽ ተዘርፏል ወያኔ ለአምስት አመታት ሊገዛ ነው እና የመሳሰሉትን ውንጀላዎች በከፍተኛ ሁኔታ በማጠናከር በየጋዜጣውና ከቅንጅት አመራር ሲሰጡ በነበሩ መግለጫዎች መቀጠሉ ከዚህም በተጨማሪ ወጣቶችን በመሰብሰብ ይዘታቸው ህገ ወጥ የሆኑ በራሪ ወረቀቶች በቅንጅት ከፍተኛ አመራር አማካኝነት እንዲባዛና እንዲበተን ከተደረገ በኋላ በተከታዩ ቀን አሁን የተገለጸውን አይነት አመጽ ሲከሰት ቅንጅቱ ሲያደርጋቸው የነበሩ እንቅስሴዎችም ሆኑ በየጋዜጣው ሲሰጡ የነበሩ መግለጫዎችና ሰኔ 1 እና 2 ቀን በነበረው አመጽ ከፍተኛ የሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት መኖሩን ያሳያል በአንድ በኩል በየመግለጫዎቹ ቅንጅት የሚያስተላልፈውን ሰላማዊ የትግል ጥሪ በማለት ሰላማዊ በሚል በማሳደብ ህዝቡ እንዲጠባበቅ በማለት በየመግለጫዎቹ ሲጠቀስ የነበረ ሲሆን በተግባር የታየውና የመግለጫዎቹ ይዘትም ሆነ መግለጫዎችን በማስከተል በከፍተኛ አመራሮች ሲሰጡ የነበሩ ማብራሪያዎች ላይ በግልጽ ለመረዳት የሚቻለው በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የህዝብ ድምጽ ይነጥቃል በሚል በመጨረሻም ነጥቋል በሚል ህዝቡ ይህንን መንግስት በሃይል ወይም በጉልበት እንደ ዩክሬንና ጆርጂያ ከስልጣን ቢያወርደው መብቱ እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲገለጽለት ቆይቷል ዩክሬንና ጆርጂያ የተደረገው ምንም ይሁን ምን የተጠቀሱትን ሃገራት የሚመለከት በመሆኑ የእኛ ትኩረት የሚሆነው በዚህ በተጠቀሰው መልኩ ቅስቀሳ ተደርጐ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለማስወገድ ቢሞከር ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን ይሆናል ይህንን ነጥብ ከሰኔ 1 ቀን በኋላ ይሆናል ከሰኔ 1 ቀን በኋላ እስከ ጥቅምት 22 እና 23 ባሉት ይህንን ነጥብ ከሰኔ 1 ቀን በኋላ ... 

ከቀረቡት መካከል ሰኔ 3 ቀን 1997 አመት ምህረት በኢህአዴግ ቅንጅት እና ህብረት መካከል የተደረሰው ስምምነት ማለትም በምርጫ ታይተዋል የተባሉ ግድፈቶችን ባለው ስርዓት መሰረት ለመፍታት የተደረገ ስምምነት ሲሆን ይህ ስምምነት ኖረም አልኖረም ከምርጫ ጋር የተያያዙ ችግሮችና አለመግባባቶች የተፈጠሩ ከሆነ መፍታት ያለበት ባለው የህግ ማእቀፍ ማለትም በምርጫ ህጉና ተያያዥ በሆኑ ሌሎች ህጎች መሆን እንዳለበት እና ስልጣን ባላቸው አካላት የሚሰጡ ውሣኔዎችን የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መቀበል ግዴታው ሲሆን ማደናቀፍ ደግሞ ወንጀል እንደሆነ ግልጽ ነው ሆኖም ይህ ስምምነት ከተደረሰም በኋላ አሁንም የምርጫ ማጣራቱ ስራ ችግር ውስጥ ነው በማለት በተደጋጋሚ መግለጫዎች መስጠት የተጀመረበት ሁኔታ የሚታይ ሲሆን ሐምሌ 12 እና 20/ 1997 ዓ.ም ባወጧቸው መግለጫዎች የድምጽ ማጣራቱ ችግር ውስጥ ወድቋል ኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ በስመ ማጣራት ሂደት ህዝብን የህዝብን ድምጽ እየነጠቁ እንደሚገኙ እንዲሁም ሌሎች የምርጫ ቦርድን ነፃ መሆንና ተአማኒነት ላይ ህዝቡ ጥርጣሬ የሚፈጥርበት መግለጫዎች በማውጣት በዚህ መልኩ የሚወሰነውን ውጤት እንደማይቀበሉ ምርጫው ገለልተኛ በሆነ ወገን አዘጋጅነት በድጋሚ የማይካሄድ ከሆነ በተከታታይ ለሚወሰዱ እርምጃዎች የኢትዮጵያ ህዝብ በንቃት እንዲጠባበቅ ማሳሰቡን መኢአድ ነሐሴ አራት ቀን 1997 ዓ.ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ የስራ ዘመኑ አንድ አመት የሆነ አዲስ ምርጫ ቦርድ እና ሌሎች ተቋማትን ለማቋቋም እንዲቻል ጊዜያዊ መንግስት መቋቋም አለበት በማለት መወሰኑን ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል የመኢአድ አስቸኳይ ጉባኤ ይህንን ከወሰነ በኋላ ነሐሴ 97 መጨረሻ አካባቢ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ባዘጋጀውና በየወረዳው ማለትም በአዲስ አበባ ከተማ በየወረዳው ከደጋፊዎች ጋር በተደረጉ ውይይቶች ቅንጅት ሲያወጣቸው በነበሩ መግለጫዎች የሚታየውን ማለትም ምርጫውና የድምጽ ቆጠራው መጭበርበሩን ምርጫ ቦርድ እና ገዢው ፓርቲ ልዩነት

የሌላቸው አንድ አካል እንደሆኑና ምርጫ ቦርድም የገገርጡን ፓርቲ አሸናፊነት ለማወጅ እንደተዘጋጀ እንደሚገኝና ሌሎች ውንጀላዎችንም በሰፊው በየመድረኩ በማስተጋባትና ከተሰብሳቢው ሃሳብ እንፈልጋለን በማለትም ከተሰብሳቢው በርካታ ህገ ወጥ ንግግሮችና ቅስቀሳዎች ለማድመጥ ተችሏል ለምሳሌ በአንድ ወረዳ በተደረገ ውይይት ይሄንን መንግስት ለማውረድ ሴቶች መቀነታችሁን ታጠቁ ወንዶች ቀበቷችሁን ጠበቅ አድርጉ እንኳንስ ለነፃነት ሰው በሌላም ይሞታል የኢትዮጵያ ህዝብ እድሉ ዘንድሮ ነው እንዋጋለን ስልጣና ስጡን ስልጣና አንድ ቀን ነው የምትነው ሞተን ትግላችንን እናሳየው ኢህአዴግ አጭበርባሪ ነው ከስልጣኑም መወገድ አለበት ይህንን የተበላሸ ስርዓት ከአናት አውርደን ኢትዮጵያን መመስረት ይኖርብናል የሚሉና የመሳሰሉት ማለትም ህገ መንግስቱ ላይ እንዲሁም ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ማፍረስ አለብን የሚሉ ህገ ወጥ ንግግሮች እና ቅስቀሳዎች ለማድመጥ የተቻለ ሲሆን የዚህ አይነት ህገ ወጥ ንግግሮች እና ቅስቀሳዎች ሲደረጉ መድረኩን በአወያይነት ሲመሩ የነበሩ የቅንጅት አመራር አባ[illegible] [illegible] መሆናቸው በቀረበው የቪዲዮ ማስረጃ ካሴቶችና ከምስክሮች ለማረጋገጥ [illegible] ተችሏል በመድረክ መሪዎችም ቢሆን ሲሰነዘሩ የነበሩ ተመሳሳይ ይዘት [illegible]ላቸው እንደነበሩ ለመመልከት የቻለ ሲሆን በተለይ ተሰብሳቢው ሰኔ 1 በደረ[illegible]ው ሳይደናገጥ እንዲህ መሰብሰቡ መናገሩ ትልቅ ኩራት እንደሆነ፤ ይህ ያ[illegible]መፍራትቸው አንድ እርምጃ ወደ ፊት እንደሆነ ሲገለጽ የነበረ ሲሆን ይህም የሚያሳየው በተሰብሳቢው ሲነገርና ሲባሉ የነበሩ ህገ ወጥ ቅስቀሳዎችን እና የአመጽ ጥሪዎችን በርቱበት የማለት ያህል ነው ተብሉ ሊወሰድ ይችላል፤ በየወረዳዎቹ በተደረጉ ስብሰባዎች ፖርላማ በመግባትና ባለመግባት በሚሉ አማራጮች ላይ ለመወያየት የሚል የሚመስል ቢሆንም በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ገዢው ፓርቲ ምርጫውን አጭበርብሯል ስልጣኑንም በህገ ወጥ መንገድ ለሌላ አምስት አመታት ለማራዘም ወስኗል በመሆኑም ህዝቡ ይህንን ሁኔታ አውቆ ይህንን ስርዓት ለማስወገድ መዘጋጀት አለበት የሚለው ሁኔታ በከፍተኛ ሁኔታ የተቀሰቀሰበት መድረክ ነበር ውይይቱን ያዘጋጁትና መድረኩን ሲመሩ የነበሩት የቅንጅት አመራር አባላት ይህንን መሰል ህገ



Scanned by CamScanner

ወጥ ንግግር እና ቅስቀሳ በተሰብሳቢው መካከል እንዲንሸራሸር በማድረ ያመቻቹ ከመሆኑም በላይ የድርጅቱ መልእክት በማለት ሲነበብ የነበረው ቢሆን ለዚህ አይነት ህገ ወጥ ንግግር የሚጋብዝ ነበር ውይይቱ ሲጠናቀቅ ቅንጅት ወደፊት የሚሰጠውንና የሚያስተላልፈውን ውሳኔ እንዲጠባበቅ ጥ ሲደረግ የነበረ ሲሆን በአጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ በእነዚህ መድረክ ተሰብሳቢው በመንግስት ላይ ያለውን እምነት በከፍተኛ ሁኔታ በመሸርሸ ተሰብሳቢው ከመንግስት ጋር በምንም አይነት ሰላማዊ የሆነ ግንኙነ እንዳይኖረው የተቀሰቀሰበትና ቅንጅት ወደፊት የሚሰጠውን ማንኛው ውሳኔ ንቁ ሆኖ እንዲጠባበቅ ጥሪ ያስተላለፈበት መድረክ ነበር በላእላይ ምክር ቤት የተደረጉ ስብሰባዎች ሲታዩም በአንድ በኩል ከኢህአዴግ ጋ የተጀመረው ድርድር ይቀጥል ፓርላማም መግባት አለብን የሚል ይዘት የነበራቸው አቋሞች ሲሆኑ በመጨረሻ ግን የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ የተላለፈው የተጀመረው ድርድርም መቋረጥ አለበት ፓርላማም አንገባም የሚል ነበር ፓርላማ አለመግባትም ሆነ ድርድር ማቋረጥ በራሱ ወንጀል ባይሆንም ለዚህ በምክንያትነት ከአንዳንድ ላእላይ ምክር ቤት አባላት ሲሰጡ የነበሩትን ማየቱ አላማው ምን እንደነበር የሚያመላክት ነው ስድስተኛው ተከሣሽ ስለሺ ጠና የተባለው ድርድሩ ሊቋረጥ ይገባል በማለት በምክንያትነት ያቀረበው ከኢህአዴግ ጋ ድርድሩ ከቀጠለ ሌላ ማናቸውም እርምጃ ለመውሰድ የሚያስረን ነው በማለት የገለጸ ሲሆን 20ኛ ተከሣሽ አንደለም አራጌ ፓርላማ መግባትና ባለመግባትም የሚለው በተናገረው ፓርላማ ገባን ማለት ሁሉ ነገር ሰላም ሆነ ማለት ነው ምንም አይነት ሌላ ማድረግ አይቻልም ሰላም ሆነ ማለት ኢህአዴግ ኢንተርናሽናል ኮሚኒቴውም ይኸው በሃገሪቱ ሰላም አስፍኚያለሁ ለማለት የሚያስችለው እንደሆነና የውጪ ኮሚኒቲውም ለአምባገነኑ መንግስት ማጉብደዱን ይቀጥላል ፓርላማ ካልተገባ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ስለማይኖር የውጪ ኮሚኒቲውም ሆነ ኢህአዴግ ወደማይፈለገው ድርድር ይመጣል በመሆኑም ፓርላማ መግባት የለብንም

በማለት መናገሩን ተመልክተናል ይህም ማለት የሚፈለገው ነገር ፓርላማ ባለመግባት ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ፓርላማ ባለመግባት ሃገሪቱ ሰላም እንድታጣና ሰላም ከታጣ በኋላ ምናልባትም ሰኔ 1 እና 2 በኋላ እንደሆነው ኢህአዴግ በድጋሚ ወደዚህ ድርድር ይመጣል የሚለው ተፈልጉ ነው ድርድሩ እንዲቋረጥ ሲፈለግም ይሄን ድርድር ማቋረጡ ሌላ እርምጃ ለመውሰድ በራሱ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ነው በሚል ነበር የሆን ሆኖ ከሌሎች አባላት በተለይም ፓርላማ ባለመግባት በሚሉ አባላት ሲነሳ የነበረው ፓርላማ አይገባ ማለት ዝም ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ማለት እንዳልሆነ ይልቁንም ቀጣይ ሰላማዊ ትግሎች እንደሚካሄዱ ሲጠቀስ የነበረ ሲሆን ሲነሱ ከነበሩት አስተያየቶች የሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት አይነት አመጽ ቢደገም አሁንም የኢንተርናሽናል ኮሚኒቲውን ድጋፍ ያስገኝልናልና መፍራት የለብንም በማለት አስተያየት ሲሰጡ ነበር ለምሳሌ 23ኛው ተከሣሽ የኔነህ ሙላት የተባለው ከሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት በፊት ብዙም የኢንተርናሽናል ኮሚኒቲው ድጋፍ እንደልነበራቸው ሆኖም ከዚህ ቀን በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ የኢንተርናሽናል ኮሚኒቲው አስተያየት የተቀየረ ስለሆነ አሁንም ሌላ የሰኔ 1/1997 አመተ ምህረት የተከሰተው አይነት በድጋሚ ቢከሰት ውጤቱ ተመሳሳይ ይሆናል በማለት የጠቀሰ ሲሆን አንዳንድ አባላትን ፓርላማ መግባትና ባለመግባት በሚደረጉ ውይይቶች በግልጽ ሲያንፀባርቁ የነበረው ዋናው ነገር ፓርላማ መግባትና አለመግባት እንዳልሆነ ይልቁንም ትልቁ አጀንዳ ይሄንን መንግስት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከስልጣን ማውረድና አለማውረድ እና ስርዓትን መለወጥ በመሆኑ መስዋእትነት መክፈል ያስፈልጋል በማለት ሲናገሩ እንደነበር ሶስተኛው ተከሣሽ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቱም ድርድሩ መቋረጥ ማለት ትናንትና ሰኔ 1 ድርድሩን ማቋረጥ ማለት ትናንትና ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት ተማሪው የሞተለት እና ዛሬም ተጠባብቆ የሚገኘውን ትልቁን የሰላማዊ ትግል የምንጥልበት አቅጣጫ ነው ማለቱን ሌላ አባልም እንደ ጧፍ እየነደድን እንደ ሻማ እያበራን ህዝቡን ማታገልና መምራት መቻል አለብን በቂ ዝግጅትም አለን ስራ ማቆም አድማ ሰላማዊ ሰልፍ ሌላም ሌላም አለ ድርድሩን አቋሙን ስንጠጣ ይህንን

እናደርጋለን በማለት መናገራቸውን ሌላው አባልም ህዝቡን በስሜት እንዲነዱ አድርገነዋል ኢህአዴግን ጠልቷል ይውደቅ እያለ ነው እኛ ፓርላማ አለመግባትን ስንወስን የህዝቡ ስሜት በስክነና በትክክለኛ አጋጣሚ በላልሆነ ደም ማፍሰስን ያስከትላል ማለቱን ከተደረጉ ውይይቶች ለመመልከት ተችሏል ከዚህ በተጨማሪም ቀርበው ከታዩት የቪዲዮ ካሴቶች አንደኛው ላይ ፓርላማ ልንገባ አይገባም በሚለው አቋም ላይ የአንዳርጋቸው ጽጌ ጽሑፍን ስድስተኛ ተከሣሽ ሙሉነህ ኢዮኤል ጨምቆ ወይንም ሰመራይዝድ አድርጐ ለውይይት እንዲያቀርብ የተነገረው መሆኑንም ለመመልከት የተቻለ ሲሆን የአንዳርጋቸው ጽጌ ጽሑፍ ይዘት ከላይ አስፍረነዋል ጠቅለል ባለ መልኩ ከእነዚህ ውይይቶች ለመረዳት የሚቻለው ላእላይ ምክር ቤት አባላት ፓርላማ ላለመገባት ወይም ድርድር እንዲቋረጥ ሲወስኑ ዝም ብለው እጃቸውን አጣጥፈው ወይም በሚቀጥለው ከአምስት አመት በኋላ የሚደረገውን ምርጫ ለመጠባበቅ ሳይሆን ሰላማዊ በሚሉት ትግል መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ እንደሆነና ሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት የተደረገው የአመጽ እንቅስቃሴም አሁንም እንዲደረግ ግፊት ማድረግ እንዳለባቸው ፓርላማ መግባት ሰላምን የሚያመጣ በአንጻሩ አለመግባት ደግሞ ሰላም እነዳይኖር የሚያደርግና በስልጠን ላይ ያለውን መንግስት ከስልጣኑ ለማስወገድ ለሚደረገው ሰላማዊ ትግል አንድ አካል እንደሆነ በመጥቀስ ውይይት መደረጉን ለመመልከት ተችሏል ላእላይ ምክር ቤቱ ካካሄዳቸው ውይይቶችና መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በተጻፈ ደብዳቤ ፓርላማ ለመግባት የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ሲታዩም አንደኛው ቅድመ ሁኔታ ምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በአዲስ መልክ ይቋቋም የሚለውና የፍርድ ቤት ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን የሚሉት ነጥቦች ሲሆኑ የዚህ አይነት ቅድመ ሁኔታዎችን ማቅረብ ብቻውን ሲታይ ማንም ፖለቲካል ፓርቲ ቢያቀርበው ጥያቄው የአንድን መንግስታዊ ተቋም መቀየር ቢሆንም እንኳን ሊላ ተቀጽላ እስከሌለው ድረስ ወንጀል ነው ሊባል

አይችልም ሆኖም ግን ይህ ቅድመ ሁኔታ መታየት ያለበት በቅንጅት በኩል በተቀመጠው እና ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት ያለው ውጤት ምንድነው የሚለውንና በየወረዳዎቹ ከተደረጉት ስብሰባዎች በላአላይ ምክር ቤት በተደረጉ ስብሰባዎችና በየሚዲያው ሲሰጡ ከነበሩት መግለጫዎች አንጻር መሆን ይኖርበታል ይህም ማለት አንድን ጥያቄ በተለይም ይህንን ፓርላማ ለመግባት ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠበት ሁኔታ ህጋዊ ነው ወይስ ህገ ወጥ ነው የሚለው ሲታይ ጥያቄው በራሱ ህገ ወጥ ነው ለማለት ባይቻልም ያለመግባትን ተከትሎ በቅንጅት ሊወሰዱ የታሰቡት እርምጃዎች ምን እንደሆኑ በማየት አጠቃላይ ሁኔታው መመዘን ይኖርበታል ከላይ እንደታየው ፓርላማ ያለመግባት ማለት ወዴት እንደሚወስድና ምን ማለት እንደሆነ ከላአላይ ምክር ቤት አባላትም ሆነ ከየወረዳዎቹ ሲደረጉ በነበሩ ስብሰባዎችና ጋዜጣዊ መግለጫዎች ይህንን መንግስት በህገ መንግስት ከተደነገገው ውጪ ከስልጣኑ ለማስወገድ ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አንዱ አካል እንደሆነ ከላይ የተመለከትን በመሆኑ ይህንን አድራጎት ህጋዊነት ያሳጣዋል ከዚህ በተጨማሪም ጥቅምት 19 ቀን 1998 አመተ ምህረት ቅንጅቱ ባወጣው መግለጫ እነዚህ መስከረም 30 ያቀረባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች መንግስት እንዲቀበል በመንግስት ላይ ጫና የሚፈጥሩ የተለያዩ እርምጃዎችን በመዘርዘር ጥሪ ያቀረበ ሲሆን ይህ ጥሪን ብቻውን ከሌላ ጋር ሳናነፃጽር ብንመለከተው አንድን መንግስታዊ ተቋም ለምሳሌ ምርጫ ቦርድን ለመቀየር መንግስት ላይ የተለያዩ ጫናዎችን በማሳረፍ መንግስታዊ ስልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል በመሆኑ ሌላ ተቀጽላ ባይኖረውም ድርጊቱ የወንጀል ተግባር ነው የሆነ ሆኖ ይህ ማለትም ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም ለመላው ህዝብ በማለት ከቅንጅት የተላለፈ ጥሪ መታየት ያለበት በቁንጽሉ ለብቻው ሳይሆን ከዚህ ጥሪ በፊትና በኋላ ከሆኑት ተግባሮች ጋር በማዛመድ ነው ከጥሪው በፊት ሲደረጉ የነበሩት ተግባራትን ከላይ የተመለከትን በመሆኑ ከዚህ በኋላ የሆነውን በመቀጠል የማስናር ሲሆን ጥቅምት 19 በኋላ የሆነውን ከማስፈራትን በፊት ግን ከሰኔ 1 ቀን በኋላ እስከ ጥቅምት መጨረሻዎቹ በየጋዜጦቹ ሲዘገቡ የነበሩትንም ተመልክተናል በአጭሩ እንደሚከተለው አስፍረነዋል



Scanned by CamScanner

ከሰኔ 1 ቀን 1997 አመተ ምህረት በኋላ በተለያዩ ጋዜጦች ከወጡ ጽሑፎች ውስጥ የተወሰኑ ጋዜጦች ይዘት እንደሚከተለው ያቀረብናቸው ሲሆን ይኸውም ገገርው ፓርቲ በተዘረፈ ድምጽ ተማምሎ ስልጣን ለመያዝ ከደፈረ ሌባ መንግስት መባሉ እንደማይቀር ቤተመንግስት ለተረኛው እንዲለቅ ማስገደድ እንደሚገባ ተሸንፎ ስልጣን ላይ እቀጥላለሁ ካለ ህዝብ መነሳቱ ሰላም መደፍረሱ አይቀሬ መሆኑን የተቃውሞ ሃይላት ምርጫው ተጭበርብሮ ከቀጠለ የዩክሬንና የጆርጂያ ህዝባዊ ማእበል የሚቀሰቅሱ ስለመሆናቸው የዩክሬንና የጆርጂያ ህዝብ አለም አቀፍ ድጋፍ ያገኘው ሆ ብሎ በመነሳቱ እንደሆነ የክልል ሶስት አራት እና የደቡብ ህዝቦች ክልል ህዝብ ከእንግዲህ በኢህአዴግ ይገዛል ማለት ህዝቡ ባርነት ይፈልጋል ብሎ መሳደብ እንደሆነ የኢህአዴግ ተላላኪ የሆነውን ምርጫ ቦርድንና ዘራፊዎች የተሰባሰቡበት ፍርድ ቤትን ጠራርጎና አጽድቶ ለመንቀሳቀስ የብሄራዊ አንድነት መንግስት አስፈላጊ መሆኑን ገልጽዋል ከዚህ በተጨማሪ በጋዜጦች በተደረገው ቃለ ምልልስ የአዲስ አበባ ነዋሪ ኢትዮጵያ በሙሉ ነፃ መውጣት አለበት ማለቱን ያለመስዋእትነት ነፃነት እንደማይገኝ የሰኔ 1/97 አመተ ምህረት የተፈጸመው እልቂት ዳግም ሊኖር እንደሚችል የዘላለም ስልጣን ላይ እንቀጥላለን ብለው የመጡ ሰዎች ቀውጢ ቀን ሲመጣ ያላቸው መሣሪያ ብቻ ስለሆነ መተኮሳቸው እንደማይቀር በጥይት ሲያስፈራሩ በየጉሬው እየገባ የሚደበቅ ህዝብ አለመኖሩን እውነተኛ ምርጫ በወያኔ እንደማይሰራ በዚህ ሁኔታ ህዝቡ ዘላለም መቀጠል እንደሌለበት ህዝቡ ባለበት የፍትህ ተቋማትን ነፃ ማድረግ እንደለበት ይህ ፍትሐዊ ነገሮች ሲሰሩ ማቆም እንዳለበት አልመረጥኩህም አታስተዳድረኝም ማለት መቻል እንዳለበት ይህንኑ ህዝቡ ማለት መጀመሩን ህዝቡ ያለውን አስከፊ ስርዓት ለውጦ የተሻለ ህይወት ለመገንባት ትግሉን በተቻለ ሁኔታ መቀጠል እንዳለበት የተቀሰቀሰበት እንደተቀሰቀሰበት የሚያስረዱ ጋዜጦች ናቸው ከጋዜጦች ሲዘገብ ከነበረው መረዳት የሚቻለው ቅንጅት በተለያዩ መድረኮች ሲያነሳቸው የነበሩትን



Scanned by CamScanner

ዎች የራስ በማድረግ ሲቀሰቀስ የነበረ መሆኑን ሲሆን ምርጫው መጭበርበሩን
ዎ ቦርድ እና ፍርድ ቤትንም ጠራርጎ ማስወገድ እንደሚገባ የብሔራዊ
ርጫ መንግስት ካልተመሠረተ ህዝቡ የጆርጂያና ዩክሬን እንደተደረገው
ገድንት መንግስትን መገልበጥ አለበት የሚሉትንና በቅንጅት ሲቀሰቀስባቸው የነበሩትን
ጋዜጦች ለመመልከት ይቻላል ከጥቅምት 19 ቀን 1998 አመተ ምህረት በኋላ
ሆነውን ሁኔታ አቃቤ ሕግ ምስክሮች በማቅረብ ያስመሰከረ ሲሆን ምስክሮቹን ቃል
ማየታቸን በፊት ከቀረቡት ሰነዶች አንደኛው ጥቅምት 12 ቀን 1998 አመተ
ህረት በአንደኛ ተከሣሽ ለኦነግ በተጻፈ ደብዳቤ ከጥቅምት 22 ጀምሮ በሚደረገው
ራት አንቀጥቅጥ አመጽ የኦነግ አባላት እንዲሳተፍ ጥሪ ያደረገበት ሰነድ መሆኑን
መመልከት ችለናል በርካታ ምስክሮች ጥቅምት 22 እና 23 አለት በወንጀል
መከላከል ስራ ተሰማርተው እንደነበሩ ገልጸው የመሰከሩ ሲሆን በተጠቀሱ ቀናት
በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ በርካታ ክፍለ ከተማዎች የነበረውን ሁኔታ ያስረዱ
ሲሆን በርካታ ወጣቶችና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በየአካባቢው በመሰባሰብ
ድንጋይ ዱላ ጨቤ ገጀራ መጥረቢያ ፌሮ እና ሌሎች ስለታም የሆኑ መሳሪያዎችን
በመያዝ ወያኔ ሌባ ኢህአዴግ ሌባ ወያኔ ምረጫውን አጭበርብሯል ቅንጅት
አሸንፏል ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ ኢህአዴግ ስልጣኑን ይልቀቅ አትነሣም ወይ
ይሄ ባንዲራ ያንተ አይደለም ወይ የሚሉትንና ሌሎች በርካታ መፈክሮች በማሰማት
እና የቅንጅትን የጣት ምልክት በማሳየት በርካታ ተቋማትንና ንብረቶችን በተለይም
የከተማ አውቶቢሶች በከተማ አውቶቢሶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን እንዲሁም
በተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት ለምሳሌ የቀበሌ ጽ/ቤቶች ት/ቤቶች የቴሌኮሙኒኬሽን
መስሪያ ቤቶች ባንኮች እና በመሳሰሉት ላይም ጉዳት እንደደረሱ በእለቱም መንገዶች
በጉማ በድንጋይ እና በቆሻሻ በመዝጋት ምንም አይነት የትራንስፖርት እንቅስቃሴ
እንዳይኖር ሙከራ ከመደረጉም በላይ በተለያዩ ጠርሙሶች እንዲሁም ብሃይላንድ
ላይ ጋዝ እየተሞላ ሲወረወር እንደነበርና የነዳጅ ጣቢያዎችን ለማውደምም ሙከራ
ሲደረግ እንደነበር መስክረዋል በእለቱ በመከላከል ስራ ላይ በነበሩ በርካታ የሲቪል
አባላትም ከፍተኛ በርካታ የፖሊስ አባላትም ከፍተኛ የሆነና ቀላል የሆነ ጉዳት



Scanned by CamScanner

እንደደረሰም መስክረዋል እነዚህ የመሳሰሉ የአመጽ እንቀስቃሴዎች ሁሉ
ቦታ ሊገለጽባቸው የሚችል ሲሆን ከዚህ በተለየ መልኩም አንዳንድ በታ
ላይ ከአመጸኞች በኩል ጥይት ሲተኮስ እንደነበርም አንዳንድ ምስክሮች የገለጹ
ሲሆን ሸሮ ሜዳ አካባቢ ደግሞ አመጹን ሲከላከሉ በነበሩ የፖሊስ አባላት ላይ
ከአመጸኞች ቦንብ መወርወሩንና በዚህ በተወረወረው ቦንብ ወታደር ፈይሳ
የተባለው ወዲያውኑ ሲሞት ሌሎች ላይ ከባድና ቀላል ጉዳት መድረሱን
ፈረንሳይ ተብሎ በሚጠራ ቦታም በተመሣሣይ መልኩ ከአመጸኞች
በተወረወረ ቦንብ በመከላከል ተግባር ላይ የነበረና አሸናፊ ደሣለኝ በተባለ
አባል ላይ የሞት አደጋ መድረሱን ሌሎች ስድስት የሚሆኑ አባላት ላይ
የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ሌላ ቦንብም ተወርውሮ መፈንዳቱና አንድ
ቦንብ ሳይፈነዳ ቀርቶ መጨረሻ በሰራዊቱ እንዲፈነዳ መደረጉን የተመሰከረ
ሲሆን በአጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ በተጠቀሱት ቀናት ከፍተኛ የሆነ ንብረት
መውደምና በሰው ህይወት ላይ አደጋ የደረሰውን አደጋ ለማስረዳት የተሞከረ
ሲሆን የአመጹን ክፊል ሁኔታም በቀረበው የቪድዮ ማስረጃ ስንመለከት
የነበረው ሁኔታ ዘግናኝና ስፋት ያለው የነበረና አጠቃላይ የከተማውን
አካባቢዎች ያካለለ እንደነበር ለመመልከት ችለናል እንግዲህ ጥቅምት 21 22
23 እና በተከታዮቹ ቀናት ይህንን የሚመስል ገጽታ ባለበት ግዜም ጭምር
ቅንጅት ጥቅምት 22 ቀን ባወጣው መግለጫና የድርጅቱ ማህተም ባለበት
እና የሁለተኛው ተከሣሽ ፊርማ ባለበት በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ
ቦታዎች በመንግስት የተገፋ አመጽ መቀስቀሱን ገልጾ ሕዝቡ አሁንም
የመንግስትን አሸባሪነት አፈናና ህገ ወጥ ተግባር እስካሁን ካደረገው በላቀ
ሁኔታ አጠናክሮ እንዲቀጥል በማለት ጥሪ ማቅረቡንም ከሰነድ ማስረጃው
የተመለከትን ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለው በተጠቀሱት ቀናት በጥቅምት
21 ቀን የተጀመረው የአመጽ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የድርጅቱ
እና በድርጅቱ ዙሪያ የተሰባሰቡ አመራሮች እምነት መሆንን ለማረጋገጥ
ይቻላል በወንጀል ህግ ቁጥር 24 መሰረት በምክንያትና ውጤት መካከል

ግንኙነት አለ የሚለው ከላይ እንደሰፈረው በነገሮች የታወቀ ወይም በተለመደ ሂደት የተከሣሽ ድርጊት ውጤቱን ለማስገኘት ሲችል እንደሆነ ተደንግጓል ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ከምርጫ በፊትም ሆነ በኋላ ድምጽ ይጭበረበራል ተጭበርብሯል አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የህዝብ ይሉኝታ የሌለውና የህዝቡን ስልጣን የነጠቀ ነው በመሆኑም ይህንን መንግስት ከስልጣን ለማስወገድ መብት ነው በማለት ሌሎችንም ከፍተኛ የሆኑና በርካታ ወንጀላዎች በመንግስትና በተቋማቱ ላይ በመሰንዘር ደጋፊዎቹም ሆኑ ሌላ ህብረተሰብ ክፍል በመንግስት ላይ እንዲነሳ በማድረግ ብቻ ሳይወሰን ለተግባራዊነቱም በከፍተኛ ሁኔታ በመንቀሳቀስና ስልቱንም በተለያዩ መግለጫዎች ከተገለጸ በኋላ ጥቅምት 21 እና በተከታዮቹ ቀናት የተደረገውን አይነት የአመጽ እንቅስቃሴ ቢፈጸም በተለይ ጥቅምት 21 እና በተከታዮቹ ቀናት በተፈጸመው የአመጽ እንቅስቃሴም ከጠቀሱት ቀናት በፊት በቅንጅትና በተለያዩ ጋዜጦች ሲስተጋቡ የነበሩት ሁኔታዎች አመጹን በተግባር ሲፈጽሙ በነበሩ ሰዎች ተደግሞ ሲገኝ በየትኛውም መስፈርትና መለኪያ ቢለካ በሁለቱ መካከል ከፍተኛ የሆነ ምክንያትና ውጤት ግንኙነት መኖሩን ለመረዳት ይቻላል በእርግጥ አንዳንዳቹ አንዳንዶቹ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ፓርላማ ያለመግባት ማለት ይኸው እንደሆነም በግልጽ ሲሉት የነበረ ቢሆንም በግልጽ በቅንጅት እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በየጋዜጦቹ ሲስተጋቡ በነበሩ መግለጫዎችና ሰኔ 1 ቀን 1997 እንዲሁም ጥቅምት 21 እና በተከታዮቹ ቀናት በነበሩት የአመጽ እንቅስቅሴዎች ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ያለ ሲሆን ይህ እንቅስቃሴ ወንጀል መሆን አለመሆኑና የትኛውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ እንደጣሰ በመቀጠል እናያለን በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ ዘጠኝ ንዑስ ቁጥር ሶስት መሰረት ከህገ መንግስቱ ከተደነገገው ስርዓት ውጪ በማናቸውም አኳኋን የመንግስት ስልጣን መያዝ ክልክል እንደሆነ የተደነገገ ሲሆን ከፌደራል መንግስቱ ከፍተኛ አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሁሉ አቀፍ ነፃ ቀጥተኛ በሆነና ድምጽ በሚስጢር በሚሰጥበት ስርዓት በየአምስት አመቱ በህዝብ እንደሚመረጡ አስፈጻሚው አካልም እንዴት እንደሚደራጅና እንደሚሰየም በዚሁ



Scanned by CamScanner

ህገ መንግስት ተደንግጓል የፖለቲካ ስልጣን በምርጫ የሚገኝ መሆኑን ይህ ህገ መንግስት የደነገገ ሲሆን ከምርጫ ስርዓት ውጪ የፖለቲካ ስልጣን ለማግኘት መሞከርም ኢ-ህገ መንግስትዊ እንደሆነ ተደንግጓል በዝርዝር ህጉ ማለትም በወንጀል ህግ ቁጥር 238 ህገ መንግስቱን ወይም በህገ መንግስቱ የተቋቋመውን ስርዓት በማናቸውም ህገ ወጥ መንገድ ለመቀየር ለማፍረስ ወይም ለማገድ ወይንም ለመለወጥ መሞከር ወይንም መፈጸም ወንጀል እንደሆነ ተደንግጓል ህገ መንግስቱንም ሆነ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በጆርጂያና በዩክሬን በተደረገው አይነት እንቅስቃሴም ሆነ በሌላ በማናቸውም ከምርጫ ስርዓት ውጪ ለመለወጥ መሞከር ኢ-ህገ መንግስታዊና የወንጀል ተግባር ነው በ1997 አመተ ምህረት ከተደረገው ምርጫ በፊት በ1992 አመተ ምህረት በተደረገው ምርጫ አሸናፊው ፓርቲ በስልጣን ላይ የነበረ መሆኑ የማያጠያይቅና ፍርድ ቤቱ ጁዲሻል ኖቲስ የሚወስድበት ሲሆን በምርጫ 97 ቅስቀሳ ጊዜም ሆነ ከቅስቀሳ በኋላ ይህንን ስርዓት ነበር ዩክሬንና ጆርጂያ በተደረገው መልኩ እናስወግዳለን በመባል ሲዛትና ሲቀሰቀስ የነበረው በተመሳሳይም በ1997 አመተ ምህረት በተደረገው ምርጫም የምርጫው ውጤት ይህንን ለመግለጽ ስልጣን ባለው አካል ማለትም ምርጫ ቦርድ መንግስት ለመመስረት የሚያበቃውን መቀመጫ ያገኘው የፖለቲካ ፓርቲ በይፋ ከተገለጸ በኋላም ቢሆን ይሄንን ከላይ በሰፈረውና በዝርዝር ባስቀመጧቸው ምክንያቶች ውጤቱን እንደማይቀበሉ ገልጸው ዩክሬንና ጆርጂያ እንደተደረገው መንግስት ይወገዳል በማለት ሲዛትና ሲቀሰቀስ ከቆየ በኋላ በተግባር ደግሞ ሰኔ 1 1997 እና ጥቅምት 21/1998 እና በተከታዮቹ ቀናት የተደረጉት አመጾች ሊፈጸሙ ችለዋል በእነዚህ ቀናት ሲደረጉ የነበሩ እንቅስቃሴዎች ቢሆኑ የመንግስት ተቋማትና ከመንግስት ጋር በየትኛው መልኩ ግንኙነት አላቸው ሊባሉ የሚችሉትን ግለሰቦችንም ሳይቀር በማጥቃትና በአጠቃላይ ሃገሪቱ ላይ ቀውስ በማስከተል በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ለማስወገድ ሙከራ መደረጉን የተደረጉት እንቅስቃሴዎች



Scanned by CamScanner

ማግባባ ያስረዳሉ በተለይ በሰነድ ማስረጃዎቹ እንደተገለጸው የደረሰው አደጋ
ህይወትም ሆነ በንብረት ላይ እጅግ ከባድ የነበረ መሆኑ ሲታይ በህዝብ ደህንነትና
ር ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከትል እንደነበር መገንዘብ ይቻላል በአጠቃላይ ሁኔታ
ታይ በቅንጅት ሲደረጉ የነበሩና ከላይ በስፋት የተዘረዘሩ እንቅስቃሴዎችና ሰኔ
/1997 እንዲሁም ከጥቅምት 21 እና በተከታታይ በነበሩ ቀናት በተፈጸመው
አመጽ ተግባር ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ከመኖሩም በላይ
ርጊቱም ቢሆን በወንጀል ህግ ቁጥር 238 1 እና 2 የተጠቀሰውን ህገ መንግስታዊ
ርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ በሃይል ለማስወገድ በህግ መሰረት ስልጣን ላይ
ለውን መንግስት የማስወገድ ሙከራ ወንጀል እንደነበር በቀረቡት ማስረጃዎች
ማረጋገጥ ችለናል በቅንጅት ስም ሲወጡ የነበሩ መግለጫዎችና ውሳኔዎች
አጠቃላይ በቅንጅቱ ሲደረጉ የነበሩ እንቅስቃሴዎች የወንጀል ኃላፊነት
ሚያስከትሉት ማን ላይ ነው የሚለው ሲታይ የተከሣሾችን ተሳትፎ ማየቱ የግድ
ይላል የተከሣሾች ተሳትፎን በዝርዝር ከማየታችን በፊት አድማን ወይም
ንስፓይረሲን በሚመለከት በሃገራችን ህግ እንዴት እንደተሸፈነ እናያለን በአንዳንድ
ገራት በተለይም ከመን-ሎው ስርዓትን በሚከተሉ ሃገራት አንድ ወንጀል
መፈጸም ማደም ማለትም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ግለሰቦች
ትኛውንም አይነት ወንጀል ለመፈጸም ስምምነት ላይ ቢደርሱና በጣም ጥቂት
ባል የሚችል እንቅስቃሴ ቢያከናውኑ ይህንን በማድረጋቸው ብቻ የወንጀል
ርጊት እንደተፈጸመ የሚቆጥሩ ሃገራት አሉ ለምሣሌ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ
ሆኑ ግለሰቦች የስርቆት ወንጀል ለመፈጸም ስምምነት ላይ ቢደርሱ ይህ ስርቆት
መፈጸም ቀርቶ ሞክረውት ባይሆን እንኳን ስምምነት ላይ በመድረሳቸው ብቻ
ራሱን በቻለ እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት ይቆጠራል ማለት ነው በሌሎች
ገራት ደግሞ በተለይ አብዛኛውን የሲቪል ሎው ስርዓትን በሚከተሉ ሃገራት ይህ
አድማ ወንጀል ወይንም ኮንስፓይረሲ በራሱ እንደ ወንጀል ተደርጎ እምብዛም
ሚታወቅ ባይሆንም በጣም ከባድ ወንጀል በሚባሉና እንደ ሃገር ደህንነትና
ሉአላዊነት የህዝብን ኑሮ በከፍተኛ አደጋ በሚጥሉ ወንጀሎች ዘርን ማጥፋትና



Scanned by CamScanner

በመሳሰሉት ወንጀሎች ጉዳዮች ላይ ማደም ወይም ስምምነት ላይ መድረስ እ ራሱን እንደቻለ እንደ አንድ ወንጀል ይቆጠራል ይህም ማለት ሁለት ወይም ከዚህ በላይ የሆኑ ሰዎች የሃገር ደህንነትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም ስምምነት ላይ ቢደርሱ ይህ የተባለው ወንጀል ድርጊት ባይፈጸምም ወይም የሙከራ ደረጃ ባይደርስም ስምምነት ላይ በመድረሱ ብቻ እራሱን እንደቻለ ወንጀል ይቆጠራል ይህ የተባለው ወይም ስምምነት የተደረሰበት ወንጀል ድርጊት ከተሞከረ ወይም ከተፈጸመ ደግሞ አሁንም የተለያዩ ልምዶች ያሉ ሲሆን አንዳንድ ሃገራት በዚህ በተጠቀሰው መልኩ ወንጀል ተፈጽሞ ወይም ተሞክሮ ከተገኘ በሁለት የወንጀል ድርጊት ማለትም በተደራራቢ ክስ ፍጻሜ ላገኘውና ስምምነት ላይ ለተደረሰበት ለየብቻ በሁለት ተደራራቢ ክስ የሚያቀርቡ ሃገራት ያሉ ሲሆን በሌሎች ደግሞ ይህ ስምምነት የተደረሰበት ወንጀል ተሞክሮ ወይም ፍጻሜ ካገኘ ስምምነቱንም አጠቃሉ ስለሚይዝ ምናልባት ለቅጣት ማክበጃነት የሚጠቅም ካልሆነ በቀር ክስ መቅረብ ያለበት በአንድ የወንጀል ድርጊት ብቻ እንደሆነ ይደነግጋሉ በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀጽ 38/1 መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ከተደነገጉ የወንጀል አይነቶች ውጪ ማለትም በአንቀጽ 257 274 300 እና 478 ከተመለከቱት ውጪ ባሉት ሁኔታዎች ወንጀል ለመፈጸም ማደም ወይም ስምምነት ላይ መድረስ በራሱ ወንጀል እንዳልሆነ ሆኖም ግን ወንጀሉ ተፈጽሞ ከሆነ ለቅጣት ማክበጃነት እንደሚያገለግል ተደንግጓል በአንቀጽ 257 መሠረትም በወንጀል ህግ ቁጥር 238 እንደተመለከተው በህገ መንግስትና ስርዓቱ ላይ ወንጀል ለመፈጸም ማደም ወይም ስምምነት ላይ መድረስ ብቻውን እራሱን የቻለ ወንጀል እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም ይህ የወንጀል ድርጊት ተሞክሯል በማለት በአቃቤ ህግ ከቀረበው የወንጀል ህግ ቁጥር 238 በተጨማሪ በተደራቢነት መቅረብ ነበረበት ወይ የሚለው የወንጀል ህግ ቁጥር 60 እና ተከታዮቹን በማየት የሚጠሱን ቢሆንም አሁን በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አቃቤ ህግ አንድ የወንጀል ክስ ብቻ ማለትም

Scanned by CamScanner

የወንጀል ህግ ቁጥር 238 በሙከራ ደረጃ ተጥሷል በሚለው እንጂ ይህንን ወንጀል ለመፈጸም ስምምነት ላይ ደርሰዋል በሚል በተደራቢነት ክስ ያላቀረበ በመሆኑ መተቸት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም እንደ አቃቤ ህግ የክስ አቀራረብ አድማ የሚለው በተደጋጋሚ መጠቀሱ ለቅጣት ማክበጃ ከተጠቀሰው ጋር የሚዛመድ ካልሆነ በቀር ይህንን ወንጀል ድርጊት ማለትም በወንጀል ህግ ቁጥር 238 የተመለከተውና በሙከራ ደረጃ የተፈጸመውን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም በተከሣሾች መካከል ስምምነት ነበር ወይስ የሚለውን ቀጥሎ እናያለን እደግመዋለሁ እንደ አቃቤ ህግ ክስ አቀራረብ አድማ የሚለው በተደጋጋሚ መጠቀሱ ለቅጣት ማክበጃ ከተጠቀሰው ጋር የሚዛመድ በመሆኑ ይሄንን የወንጀል ድርጊት ማለትም በወንጀል ህግ ቁጥር 238 የተመለከተውና በሙከራ ደረጃ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የመፈጸም በተከሣሾች መካከል ስምምነት ነበር ወይ የሚለውን በሙከራ ደረጃ ለመፈጸም በተከሣሾች መካከል ስምምነት ነበር ወይ የሚለውን ቀጥሉ እናያለን አንድ በተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ወይም በተሞከረ የወንጀል ድርጊት በተከሣሾች መካከል ስምምነት አለ ወይም ነበር የሚለው እንዴት ይረጋገጣል ለሚለው በተከሣሾች መካከል ያለ ግንኙነት የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት አይነት እና ባህሪ በወንጀል አፈጻጸሙ ዙሪያ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይ ክስ ከቀረበባቸው ተከሣሾች መካከል አንደኛ ተከሣሽ ኢንጂነር ሃይሉ ሻወል ሁለተኛ ተከሣሽ አባይነህ ብርሃኑ ሶስተኛ ተከሣሽ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም አራተኛ ተከሣሽ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው አምስተኛ በተከሣሽነት ቅደም ተከተል ሳይሆን ሁለተኛ ተከሣሽ አባይነህ ብርሃኑ ሶስተኛ ተከሣሽ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ሃይሉ አርአያ ሙሉነህ ኢዩኤል ብርሃኑ ነጋ በፍቃዱ ደግፌ ጌታቸው መንግስቴ ሃይሉ አርአያ ሙሉነህ ኢዩኤል ብርሃኑ ነጋ በፍቃዱ ደግፌ ጌታቸው መንግስቴ ከማለቱ እና ስለሺ ጠና የተባሉት ቅንጅት በመስከረም ወር ውህደት ፈጽማያለሁ ከማለቱ በፊት የምክር ቤት አባላት የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ በተጨማሪ ቅንጅቱ መስከረም 1998 ዓ.ም ውህደት ከፈጸመ በኋላ አሰፋ ሃብተወልድ አስቻለው ከተማ ብሩክ ከበደ ገብረጻዲቅ ሃይለማርያም ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ መስፍን አማን አንዱአለም አራጌ



Scanned by CamScanner

ታምራት ታረቀኝ ብርቱካን ማይደቅሳ ደበበ እሸቱ ንግስት ገብረህይወት የኒህ ሙላት የተባሉትም የላእላይ ምክር ቤት አባላት እንደሆኑ ከቀረቡት ሰነድ በተጨማሪነት የላእላይ ምክር ቤት አባላት እንደሆኑ ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል ከቀረበው የቅንጅት መተዳደሪያ ደንብ የተለያዩ አንቀጾች መሠረትም የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር እንደሆነና ማንኛውም ከፍተኛ ውሣኔ በዚህ አካል እንደሚሰጥ ተደንግጓል ይህንን ሁኔታ የቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት ሲያደርጋቸው በነበሩና በማስረጃነት ለችሎቱ በቀረቡት የቪድዮ ካሴቶችም ለመመልከት ተችሏል ምርጫው ከመደረጉ በፊትም ሆነ በኋላ በሰነድ ማስረጃነት በቀረቡና የቅንጅት መግለጫዎች በሚል ሲቀርቡ በነበሩ ጽሑፎች የድርጅቱ ውሳኔዎች እና መግለጫዎች እስከሆኑ ድረስ በተለይም እነዚህ መግለጫዎች እና ጽሑፎች ላይ ሲታዩ የነበሩ የጽሑፍ ይዘቶች ክስ የቀረበባቸውንና የላእላይ ምክር ቤት አባላት በሆኑት አጠቃላይ እንደዚህ አይነት መግለጫና ውሳኔ እንዲወጣ ስምምነት ነበር ለማለት ይቻላል በየወረዳዎቹ ሲደረጉ የነበሩት ስብሰባዎችም ቢሆኑ በቅንጅት ማለትም ከውህደቱ በፊት በነበሩት የቅንጅት ምክር ቤት አባላት ውሳኔ መሆኑ ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ይህም በምክር ቤት አባላት መካከል ማለት ከቅንጅት ውህደት በፊት የነበሩ እንቅስቃሴዎች በቀድሞው ምክር ቤት አባላት ከውህደት በኋላ የነበሩ መግለጫዎችና ውሣኔዎች ደግሞ ቀድሞ ከነበሩት የምክር ቤት አባላት በተጨማሪነት በተመረጡ የምክር ቤት አባላት መካከል ስምምነት መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው በቅንጅት ሲደረጉ የነበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች ማለትም መግለጫዎች ቃለ መጠይቆች በየወረዳው የተደረጉ ውይይቶች እንዲሁም በላእላይ ምክር ቤት የተደረጉ ውይይቶችና ሰኔ 1/1997 እንዲሁም ከጥቅምት 21 እና በተከታዩ ቀናት የተደረጉት የአመጽ እንቅስቃሴዎች ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት እንደነበርና ድርጊቱም በወንጀል ህግ ቁጥር 238/1 እና 2 ስር የተሸፈነውን የወንጀል ተግባር በመምከር ደረጃ የተደረገ

Scanned by CamScanner

ወንጀል እንደሆነ ከላይ በሰፊው የተገለጸ በመሆኑ የቅንጅት ላአላይ ምክር ቤት አባላት የሆኑና ክስ የቀረበባቸው ተከሣሾች በጠቅላላ ማለትም አንደኛ ተከሣሽ ኢንጂነር ሃይሉ ሻወል ሁለተኛ ተከሣሽ ኢንጂነር አባይነህ ብርሃኑ ሶስተኛ ተከሣሽ ሽለቃ ጌታቸው መንግስቴ አራተኛ ተከሣሽ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው አምስተኛ ተከሣሽ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ስድስተኛ ተከሣሽ አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል ሰባተኛ ተከሣሽ አቶ ስለሺ ጠና ስምንተኛ ተከሣሽ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዘጠነኛ ተከሣሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ አስራ አንደኛ ተከሣሽ ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማርያም አስራ ሁለተኛ ተከሣሽ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ አስራ ሶስተኛ ተከሣሽ አቶ አስቻለው ከተማ አስራ አራተኛ ተከሣሽ ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ አስራ አምስተኛ ተከሣሽ ገብረጻዲቅ ሃይለማርያም አስራ ስድስተኛ ተከሣሽ አቶ አሰፋ ሃብተወልድ አስራ ሰባተኛ ተከሣሽ አቶ ብሩክ ከበደ አስራ ስምንተኛ ተከሣሽ አቶ መስፍን አማን በሌለበት አስራ ዘጠነኛ ተከሣሽ አቶ ታምራት ታረቀኝ ሃያኛ ተከሣሽ አቶ አንዷለም አራጌ ሃያ አንደኛ ተከሣሽ ወ/ሮ ንግስት ገብረህይወት ሃያ ሁለተኛ ተከሣሽ አቶ ደበበ እሸቱ ሃያ ሶስተኛ ተከሣሽ አቶ የኔነህ ሙላት የተባሉ ተከሣሾች አንደኛ ክስን በሚመለከት በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ለ 3827/1 እና 238/1 እና 2 በመተላለፍ ሊከላከሉ ይገባል ብለናል ክስ የቀረበባቸውና የላእላይ ምክር ቤት አባላት ውጪ የሆኑ ተከሣሾችን በሚመለከት መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ እነዚህ ተከሣሾች በተለየ ሁኔታ ይህንን በአንደኛ ክስ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት በመፈጸም እረገድ ያላቸው ተሳትፎ እንዲሁም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት አባላት ሲተላለፍ በነበሩ መግለጫዎች ውሳኔዎች ቅስቀሳዎችና የመሳሰሉትን የራሱ ውሳኔ በማድረግ ለተግባራዊነቱም ሲንቀሳቀሱ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያስፈልጋል ከዚህ አንጻር የሌሎችን ተከሣሾች ተመልክተናል ሌሎችን ተከሣሾች በሚመለከት

በአዳሪ እናሰማለን፡፡

4324

መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች :- አዲል አህመድ
ልዑል ገብረማርያም
አህመድ አሚንሳኒ

ከሳሽ :- የፌዴራል ዐቃቢ ህግ ሽመልስ ከማል፣ ሚካኤል ተክሉ፣ አብረሃ ተጠምቀ ቀርበናል::

ተከሳሾች :- እነ ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል በተከሰሱበት ሁሉም ቀርበዋል::

- የተከሳሽ ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴ ጠበቃ ኮ/ል መንግስቱ ሃይለማርያም ቀርበዋል የተከሳሽ ካሳሁን ከበደ ጠበቃ አቶ ወንድአወክ አየለ ቀርበዋል መዝገቡ ያደረው የተጀመረውን ብይን ማሰማት ለመቀጠል ነው በእዚህ መሰረት ከአቆምንበት እንቀጥላለን ማለት ነው:: እሺ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ተሳትፎ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን ከላዕላይ ምክር ቤት ውጭ ያሉ ተከሳሾችን በሚመለት መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ የእነዚህ ተከሳሾች በተለየ ሁኔታ እዚህ የተጠቀሰውን ወንጀል ከመፈጸማቸው ረገድ ያላቸው ተሳትፎ እንዲሁም በአንድ ወይም በሌላ ሁኔታ ከቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ሲተላለፍ በነበሩ መግለጫዎች፣ ውሳኔዎች፣ ቅስቀሳዎች እና የመሳሰሉትን የራሱ ውሳኔ በማድረግ እና ለተግባራዊነቱም ሲንቀሳቀስ የነበረ መሆኑን መረጋገጥ ያስፈልጋል ከእዚህ አንፃር የሌሎቹን ተከሳሾች ተሳትፎ ተመልክተናል 10ኛ ተከሳሽ የሆነው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል ባይሆንም ምርጫው ከመደረጉ በፊት የካቲት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ሰሜን ሆቴል ቅንጅት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ስልጣን ባለው መንግስት ከፍተኛ ውንጀላዎችን ከሰነዘረ በኋላ ዩክሬን እና ጆርጂያ የተደረጉት ለእኛም ለወያኔም ምሳሌ ናቸው ማለቱ እንዲሁም ቅንጅትን በመወከል በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል በተደረገው ክርክር በተመሳሳይ ውንጀላዎች ካቀረበ በኋላ ዲሞክራሲ ከማናቸው አይነት አገዛዝ ልዩ ነው መስጉን የሚያደርገው በልምድና በህግ እራሱን እያረመ እና እያሻሻለ የሚያርም እንደሆነ የእዚህ አገዛዝ ግን መሰረቱ ጉልበት እንደሆነ እና ሊሻሻልም የማይችል እንደሆነ መታረምም ባህሪው ስላልሆነ ለእዚህ አይነት አገዛዝ ለውጥ የሚባለው ቀኝ ኋላ ዙር ሲባል ነው በማለት የተናገረው ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ በተከሳሹ እና በቅንጅት መካከል ያለው

ግንኙነት የሚታይ ሲሆን በተከሳሹ ሲነገሩ የነበሩትም ቢሆን በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ወይም ወያኔን ከስልጣን ለማስወገድ ጆርጂያ እና ዩክሬን ምሳሌ ማቅረቡ እንዲሁም በስራ ላይ ያለውን ህገ መንግስትም ሆነ ስርዓቱ የዴሞክራሲያዊ ባህሪ የማይታይባቸው በመሆናቸው ሊሻሻሉ የማይችሉ ስላልሆነ የዚህ ስርዓት አገዛዙ መሰረትም ጉልበት በመሆኑ ይሄንን አገዛዝ ሊታረም እና ሊሻሻል ስለማይችል ቀኝ ኋላ ዙር ሲባል ነው ማለቱ ያለውን ስርዓት እና ህገ መንግስቱን ሙሉ በሙሉ ከማስወገድ ውጭ መሻሻል እና መታረም የማይታሰብ እንደሆነ ሲቀሰቅስ መቆየቱ ሲታይ ከእዚህ ቅስቀሳ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ማለትም ስለ ጆርጂያ እና ዩክሬንም ሆነ ህገ መንግስቱን በሚመለከት በሌሎች ከፍተኛ የቅንጅት አመራሮች ሲሰነዘር የነበሩ እና በቅንጅት ማንፌስቶ እና ቅስቀሳዎችም ተመሳሳይ ይዘት የነበራቸው መሆኑ ሲታይ ተከሳሹ በቅንጅት ዙሪያ በተሰባሰቡ ግለሰቦች ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን እና ህገ መንግስቱን አደጋ ላይ በመጣል በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ለማስወገድ በተደረገው ሙከራ በእንቅስቃሴም ሆነ በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ለሙሉ ተካፋይ መሆኑን ለማረጋገጥ የቻልን በመሆኑ በእዚህ በቀረበው 1ኛ ክስ ከ1 እስከ 23 የተዘረዘሩት ተከሳሾች እንዲከላከሉ በተበየነበት የህግ አንቀጽ መሰረት ሊከላከል ይገባል ብለናል ከ24ኛ ተከሳሽ ጀምሮ ያሉትን በሚመለከት እንደሚከተለው አይተናል 24ኛውን ተከሳሽ ማሙሸት አማረን በሚመለከት ተከሳሹ ኢህአዴግ የፌደራል መንግስትን ለመመስረት የሚያበቃ ድምጽ አላገኘም ይሄንን መቃወም አለብን የሕዝባችንን ድምጽ ማስከበር አለብን ለእዚህም ሲባል ሕዝቦችንን ማደራጀት እና አለምአቀፉ ጫና በኢህአዴግ እንዲደረግ ድርጅታችን በሚሰጠው አመራር ሕዝቡ ለስራ ማቆም አድማ እንዲተባበር ማድረግ ይኖርብናል በማለት ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም በመኢአድ ጽ/ቤት በተደረገው የቅንጅት ደጋፊዎች እና አባላት እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ያካተተ ስብሰባ ላይ ቅስቀሳ ያደርግ እንደነበረ እና በወቅቱ ከ2ኛው ተከሳሽ ጋር ሆኖ ስብሰባውን በመምራት እና በማስተባበር ይሰሩ እንደነበረ እንዲሁም ተከሳሹ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የረሃብ አድማ አድርገው ስለታፈነባቸውና እንግልትም ስለደረሰባቸው ከጐናቸው በመቆም እስከ መጨረሻው በድርጅቱ በኩል እገዛ እንደሚደረግላቸው መናገሩን በእለቱ በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር በተራ ቁጥር 19 የተመለከተው እና ጥሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በሚል እርእስ የተዘጋጀው በራሪ ጽሑፍ መበተኑን ኢህአዴግ በምርጫ ካሸነፈ በቅንጅት አመራሮች ላይ እርምጃ ሊወስድ ስለሚችል ያሀፋ እርምጃ የሚወስድ እንዲሁም ኢህአዴግ በምርጫ ከተሸነፈ ትግራይን ከሌላው ኢትዮጵያ ክፍል በመገንጠል የትግራይን ግዛት



Scanned by CamScanner

ስለማመሰርት ወደ ትግራይ የሚሄዱ እንደ መብራት እና ሌሎች መሰረተ ልማት አውታሮችን ለማቋረጥ የሚችል ጠንካራ ሃይል ማደራጀት አለብን በማለት ሰዎችን ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ ለአመጽ እንዲደራጁ ትኩረት ያላቸውን በምርጫው ውጤት ከተናገረም በኋላ ስለ ተመለመሉ ሰዎች የትጥቅ ይዞታ እና ጥንካሬ ከመልማዮቹ ጋር በአካል እና በስልክ በመገናኘት ክትትል ያደርግ እንደነበረ 107፣ 108፣ 45 እና በ51 ምስክሮች ተነግረዋል፣ 29ኛውን ተከሳሽ በተመለከተ ተከሳሹ ቅንጅትን ወክሉ በ1997 ዓ.ም በአሰላ ከተማ ምርጫን አስመልክቶ ባደረገው ቅስቀሳ የፌደራሉ መንግስታዊ ስልጣን በትግራይ ተወላጆች ብቻ ተጠቅልሎ የተያዘ አስመስሎ በዘር የተያዘውን ስልጣን እናስመልሳለን ብሎ መቀስቀሱን በመስቀል አደባባይ ተገኝቶ ባደረገው ንግግርም በተመሳሳይ ሁኔታ በዘር ስልጣን በቤተሰብ በአምቻ በጋብቻ እየገዛ እያታለለ ያለውን የወያኔ መንግስት በእናንተ ጡንቻ ወደ መጣበት ይመለሳል በማለት በወቅቱ ለተሰብባቢው ሕዝብ በይፋ መቀስቀሱን ከእዚህም ሌላ የቅንጅት የአመጽ ጥሪ ለማሳካት ጥቅምት 22 ቀን እና 23/98 ዓ.ም የተደረገውን ሁከት እና እረብሻ በመምራት እና አይዞአችሁ ድሉ የእኛ ነው ወያኔ ወደ መጣበት ጫካ ይመለሳል በማለት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አካባቢ ተከስቶ በሕዝብና በግል ንብረት እንዲሁም በመንግስት እና በድርጅት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት ያስከተለውን በመምራት አመፀኞችን ሲያበረታታ እንደነበረ በዐቃቢ ህግ የቪዲዬ ካሴቶች ማስረጃ እና እንዲሁም በ97ኛው የዐቃቢ ህግ ምስክር ተረጋግጦበታል፡ 33ኛ ተከሳሽ አንተነህ ሙሉጌታን በሚመለከት ተከሳሽ ነሐሴ 19/1997 ዓ.ም በወረዳ 20 ቀበሌ 42 የመሰብሰቢያ አዳራሽ ቅንጅት በጠራው ስብሰባ ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ስብሰባውን ሲመራ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በወያኔ ኢህአዲግ ተጨፈጨፉ ያላቸውን ሰዎች በማውሳት ስብሰባውን ማካሄዱን በስብሰባው የቅንጅት ተመራጮች ወደ ፓርላማ መግባት የለባቸውም ፓርላማው በደም ተጨማልቋል የሚል ቅስቀሳ ይራመድበት እንደነበረ እና በመጨረሻም ተከሳሹ ሕዝቡ ለቀጣይ የአመጽ ጥሪ እንዲዘጋጅ ቅስቀሳ ማድረጉን እንዲሁም ጥቅምት 20 ቀን 1998 ዓ.ም በቅንጅቱ ጽ/ቤት በተደረገ እና 89 ለሚሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ የቅንጅት ተመራጮች በተገኙበት ስብሰባ በወቅቱ ስብሰባውን ከመሩት የቅንጅቱ አመራሮች ጋር በመሆን በመድረክ መሪነቱ መሳተፉን የስብሰባው አላማም በኢህአዲግ ደጋፊዎች እና አባላት ላይ የማግለል ተግባር እንዲፈጸም፣ ሕዝቡ የስራ ማቆም አድማ እንዲያደርግ የመኪና ጡሩንባ በማሰማት አመጽ እንዲያካሂድ በቅንጅት የቀረበውን የአመጽ

ጥሪ አፈጻጸም ለአባላት ገለጻ ለማድረግ እና ሰነዱን ለማሰራጨት እንደነበረ ሰነዱም በዐቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃ ተራ ቁጥር 29 የተመለከተው እንደሆነ እና ሰነዱም ለሚመለከታቸው አባላት መሰራጨቱንና ስለአፈጻጸሙ ገለጻ መደረጉን በ157 እና 48ኛው የዐቃቤ ህግ ምስክር ተነግሮበታል፡ 34ኛው ተከሳሽ መላኩ ፋንታዬን በተመለከተ ተከሳሹ በወረዳ 3 መሰብሰቢያ አዳራሽ ቅንጅት ጠርቶት በነበረው ስብሰባ ተገኝቶ ስብሰባውን ሲያስተባብር እና በሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በመንግስት ተገደሉ ስላላቸው ህፃናት በሚመለከት የቅስቀሳ ጽሑፍ ሲያነብ እንዲሁም የገጠሩን ሕዝብ የሚወክለው የከተማው ነዋሪ በኢህአዴግ የተቀማውን የገጠሩ ነዋሪ ሕዝብ ድምጽ የማስከበር ሃላፊነት እንዳለበት እና በወያኔ የተጭበረበረውን የምርጫ ውጤት በትግል እናስመልሳለን እያለ ሕዝቡን ለአመጽ ተግባር የሚያነሳሳ እና ንግግር ሲያደርግ እንደነበረ በስብሰባውም እንዋጋለን ሰው እንኳን ለሃገሩ ለሌላ እንኳን ለአጉል ተግባር ይሞታል በማለት የአመጽ ትግል ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን ተሰብሳቢዎች እንዲናገሩ ሲጋብዝ እንደነበረ በዐቃቤ ህግ የቀረበው የቪዲዩ ካሴት ማስረጃ ታይተዋል፡ 36ኛ ተከሳሽ በሚመለከት መቶ አለቃ ግርማ አማረን በሚመለከት ተከሳሹ ነሐሴ 22 ቀን 1997 ዓ.ም ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 42 መሰብሰቢያ አዳራሽ በተጠራው የቅንጅት ስብሰባ ተገኝቶ ቅንጅት ፓርላማ መግባት እንደሌለበት እና ቢገባም እንኳን የኢህአዲግ አሻንጉሊት የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን እንደማይድን መናገሩን ከስብሰባው በኋላም በርካታ ወጣቶችን በማሰባሰብ እንደ ጂዎርጂና እና ዩክሬን ብርቱካናማ አብዮት በእኛም ሀገር የአደይ አበባ ሰላማዊ አብዮት መካሄድ ይገባዋል እያለ ሲቀሰቅስ እንደነበረ እንዲሁም ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም 4ኛ ክፍለ ጦር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ድንጋይ በመወርወር እና የአካባቢውን ፀጥታ በማደፍረስ የአመጽ ተግባር ሲፈጽሙ ከነበሩ ወጣቶች ጋር መታየቱን በ81ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ተረጋግጦበታል፡ 96ኛው ተከሳሽ መስፍን ድቤሳ 97ኛው ተከሳሽ ብርሃኑ አለማየሁ እና 98ኛ ተከሳሽ ውድነህ ደጂ ጥቅምት 23 እና 24 ቀን 1998 ዓ.ም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አካባቢ ከምርጫው ጋር በተያያዘ የተከሰተውን ሁከት በመምራት እና በማስተባበር ወያኔ ይጠፋል አትነሳም ወይ እያሉ በመጮህ እና እስከ 300 የሚገመቱ የሁከት ተሳታፊዎችን በመምራት የኢህአዲግ ደጋፊዎች እና የትግራይ ብሄር ተወላጅዎች ነን ወዳሉት የአካባቢ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤት በማምራት በተለይም በወቅቱ 96ኛው ተከሳሽ ይህ ነው የትግሬ ቤት እያለ በሚሰጠው ጥቆማ እና መመሪያ የትግራይ ብሄር ተወላጆች ከሌሎች ጉረቤቶቻቸው ተለይተው እንዲደበደቡ እንዲፈራርሱ በተለይም አንዱ መኖሪያ ቤት ከእነ ሙሉ ንብረቱ እንዲቃጠል በቤቱ ባለቤት ኮሎኔል አርያ ገብረዮሐንስ ላይ በተወረወረው የጦር መሳሪያ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እንዲደርስ



Scanned by CamScanner

ማድረጋቸውን 97ኛ ተከሳሽ በንብ በመወርወር እንዲሁም 98ኛው ተከሳሽ በመቀጣጠል ላይ በነበረው በእዚሁ ቤት ጣሪያ ላይ በመውጣት ቃጠሎው እንዳይጠፋ ማድረጉን በ68ኛ በ69ኛ እና 75ኛ የዐቃቢ ህግ ምስክሮች ተረጋግጦበታል፡ 112ኛ ተከሳሽ መላኩ ኡንቻ በተመለከተ ጥቅምት 22 እና 23/98 ዓ.ም ሽሮ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተከስቶ በነበረው አመጽ ይኸው ተከሳሽ ከሌሎች የአመጽ ተባባሪዎች ጋር በመሆን ታክሲዎች የተለመደውን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጡ መከልከሉን በእዚህ የአመጽ ተግባር አስተድሞ ትግሬ ኢህአዴግ እያለ ሲዝትበት የነበረውን ኑርሁሴን እድሪስ የተባለውን ግለሰብ ከሌሎች የአድማ ግብረአበሮቹ የቅንጅት ደጋፊዎች ጋር በመሆን በገጀራና በድንጋይ ደብድቦ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረሱን እና የተጐጂውን ሽጉጥ መውሰዱን በወቅቱ የተከሳሹ ግብራበሮች እና የአድማው ተካፋዬች ወያኔ አይገዛንም እያለ ሲጮሁ እንደነበረ እና ድንጋይ በመወርወር በአካባቢው ቤቶች በተለይም በአካባቢ የነበሩ የፖሊስ ተሽከርካሪዎች በመሰባበራቸው እና በሌሎች ግለሰባዊ እና የድርጅቶች ተቋሞች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ማድረጋቸውን በ365 እና 362 ምስክሮች ተነግሯል፡ 113ኛ አብዬት ዋቅጅራ 115ኛ ሙብራቱ ከበደ 117ኛ ዳንኤል በሪሁን እና 118ኛዋ ቅድስት በቀለ የተባሉት ተከሳሾችን በተመለከተ ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ከጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አካባቢ ተከሳሾቹ በተሳተፋበትን አመጽ የቀበሌ 13 እና 15 ጽ/ቤት እና አዳራሽ ላይ በድንጋይ ናዳ በእሳት ቃጠሎ ጉዳት ማድረሳቸውን የአካባቢ መንገዶች እንዲዘጉ በማድረግ የሕዝቡን ሰላማዊ እንቅስቃሴ ማወካቸውን እና አትነሳም ወይ እያሉ ሕዝቡን ወደ አመጽ መገፋፋታቸውን እንዲሁም እቺ ትግሬ ወያኔ በሉአት እያሉ ሲዝቱባት የነበረችውን የአካባቢ ነዋሪ 100ኛ የዐቃቢ ህግ ምስክር ንብረት እንዲወድም ማድረጋቸውን እንዲሁም ህዝብ በሚገለገሉባቸው የከተማ አውቶብሶች ላይና በአካባቢው አገልግሎት ሲሰጥ በነበረ የፖሊስ ተሽከርካሪ ላይ የድንጋይ ናዳ እንዲወረወር በማድረግ መሰባበራቸውን 97ኛ እና በ100ኛ የዐቃቢ ህግ ምስክሮች ተረጋግጠባቸዋል፡ 122ኛ ተስፋዬ ታሪኩ 123ኛ ዋልታ ንጉስ እና 124ኛ ሙሉ ጋሹ የተባሉ ተከሰሾችን በሚመለከት እነዚህ ተከሳሾች በምስራቅ ጐጃም ደጀን ወረዳ ገላገል ቀበሌ ገበሬ ማህበር በተባለ የአካባቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሚያዝያ 16 ቀን 97 ዓ.ም እንዲሁም ነሐሴ 1997 ዓ.ም እና መስከረም 8 ቀን 1998 ዓ.ም የአካባቢውን ሕዝብ በመሰብሰብ ቅንጅት በምርጫው አሸናፊ እንደሚሆን ምርጫው ከመካሄዱ በፊት የተረጋገጠ

አቦ መስሉ በመናገር ማንም ታጣቂም ሆነ ፖሊስ ወደ አካባቢው ቢሄድ በመጥረቢያ ጨዱት እያሉ ሕዝቡን መቀስቀሳቸውን ከምርጫው በኋላም ለኢህአዲግ አትገዙ ያለቀለት መንግስት ነው በውድም በግድም ገገርዎች እኛ ነን በማለት የአመጽ ጥሪ ማድረጋቸውንና ሕዝቡን ህገ ወጥ ለሆነ ተግባር መቀስቀሳቸውን በተለይም 122ኛው ተከሳሽ የአካባቢ ሕዝብ የተነጠቀ ድምጹን ማስከበር አለበት በሚል ሕዝቡ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ የትጥቅ ትግል ማካሄድ እንዳለበት እና ለአፈጻጸሙም ከ5 እስከ 6 ሰዎች እየተደራጁ በማጥቃት እና በመከላከል ተግባር እንዲሰማራ እና ለአየቤቱ እንዳይተኛ ከመቀስቀስም በተጨማሪ መሳሪያ እንደሚሰጥ መናገሩን ለዚህ ትጥቅ ትግል መሳካትም ከደጀን ወረዳ ሰዎች ተመልምለው ጫካ መግባታቸው እና ሌላ ሕዝብ 15፣15 ሰው ሆኖ መደራጀትና እንዲሁም በመከላከል እንዲሰማራ 122ኛ ተከሳሽ ሲቀሰቅስ እንደነበረ 101፣102፣103 እና 104 የዐቃቤ ህግ ምስክሮች መስክሮባቸዋል፡ እነዚህ ተከሳሾች ምርጫ ተጭበርብሯል በሚል ምክንያት ቅንጅት አመራሮች የኢፌዲሪ ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ህጋዊ ልሆነ መንገድ ለማፍረስ አስበው ፈጽመውታል የተባውን የወንጀል ተግባር ሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሃሳባቸው በመስማማት ተከሳሾቹ ንደየ ደረጃቸው በአነሳሽነት በአመራር ሰጭነት በአመጽ ተግባር በአድማ እና ግበረአበርነት በመሳተፍ ሕዝቡ በመንግስት ላይ እንዲያምጽ እና የትጥቅ ትግል ንዲያደርግ ታጣቂዎችን በመመልመል እና በማስመልመል የወንጀል ተግባር መፈጸም የአካባቢውን ፀጥታ እንዲደፈርስ በማድረግ በግለሰቦች የዘር ማንነታቸውን ና የፖለቲካ አቋማቸውን ምክንያት በማድረግ በንበረታቸው በአካላቸው እና ሕሊናቸው ላይ ጉዳይ እንዲደርስባቸው ቅስቀሳ በማድረግ እና ወንጀሉን በቀጥታ መፈጸም በመንግስታዊ እና ሕዝባዊ ተቋማት ላይ አደጋ በመጣል የንብረት ድመት ማድረስ እንዲሁም የሕዝብ እና የግል ተሽከርካሪዎች የተለመደ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጡ በማገድ እና በመሰባበር በማቃጠል ከጥቅም ጭ እንዲሆኑ በማድረጋቸው በዐቃቤ ህግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በመሆኑ ከሳሾቹ በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ለ 38/27/1 እና 238/1/2 ስር እንዲከላከሉ ወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ብይን ሰጥተናል፡፡ 25ኛው ከሳሽ ስለሺ አንዳርጌን በተመለከተ ተከሳሹ የመኢአድ አመራር አካል አባል ቅንጅት አባል መሆኑ በክሱ ከመመልከቱ እና የካቲት 19/97 ዓ.ም ቅንጅት በሰሜን ቴል ባካሄደው ስብሰባ የድርጅቱን መግለጫ ሲያነብ በዐቃቤ ህግ የቪዲዬ ካሴት ማስረጃ ከመታየቱ በቀር 30ኛው ተከሳሽ ኮሎኔል ታምሩ ጉልላት የመኢአድ እና ቅንጅት አባል መሆነ ከክስ ማመልከቻው ከመመልከቱ እና ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በመኖሪያ ቤቱ እና በቢሮው ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወጡ የተባሉትን



Scanned by CamScanner

የተቀረፀ እና የቀረባቸው የተባሉት የቪዲዮ ካሴቶች ተገኙ ከመባሉ በቀር መግለጫዎች እና የቀረፃቸው የተባሉት የቪዲዮ ካሴቶች ተገኙ ከመባሉ በቀር ተከሳሾቹ ህገ መንግስቱን እና በህገ መንግስቱ የተቋቋመውን ስርዓት ለማፍረስ በአድማና በግብረአበርነት የወንጀል ተግባር የፈጸሙ መሆናቸውን በማስረጃ አልተረጋገጠባቸውም የቅንጅቱ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ናቸው ባለመባሉ የውሳኔ ሰጭነት ሚና የነበራቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበባቸውም፡ ስለሆነም መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ቁጥር 141 መሰረት ብይን ሰጥተናል:: 27ኛ ተከሳሽ ሐብታሙ ገብረህይወት 28ኛው ተከሳሽ አስራት ጣሴ 31ኛ ተከሳሽ በቀለ ግርማ 35ኛ ተከሳሽ አብዱት በየነ 37ኛ ተከሳሽ አለማየሁ መሰለ እና 38ኛ ተከሳሽ ሰብለወርቅ ታደሰ የተባሉት ተከሳሾች የቅንጅት አባላት መሆናቸው ቢገለጽም በድርጅቱ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ሆነው ውሳኔ ስለመስጠታቸውም ሆነ በየግላቸው ስለፈጸሙት ወንጀል ወይም በአድማ በግብረአበርነት ከሌሎች ጋር በመሆን በቀረቡባቸው ክሶች መሰረት ወንጀል መፈፀማቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ ስለአልቀረበባቸው መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ብይን ሰጥተናል:: 39ኛ ተከሳሽ እስክንድር ነጋን በሚመለከት በተከሳሽ ላይ የቀረበው ክስ የኢፌዲሪ ህገ መንግስትን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ ይህ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት ስም የአድማ እና የግብርአበርነት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው በጉዳዩ ላይ የቀረበው የዐቃቢ ህግ የሰነድ ማስረጃ በተከሳሹ የተጻፈው ምርጫ 97 መረጃ እና ትንታኔ የሚል ባለ 226 ገጽ መፀሐፍ ሲሆን ከመፀሐፉ ክሱን ለይቶ ሊያስረዳ የሚችል ክፍል ወይም ገጽ ካለመገለጹም በተጨማሪ በተከሳሹ ላይ ማስረጃው እንዲያስረዳ የተፈለገው ጭብጥ ዐቃቢ ህጉ አላስያዘም በመሆኑም የመፀሐፉን ሙሉ ክፍል እና ይዘት የወንጀል ክሱን ለማስረዳት እንደማስረጃነት መጠቀሙ የወንጀሉን አድራጉት ለይቶ ለማመልከት እና ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት ስለማያስችል፤ እንዲሁም መፀሐፉ በጥቅሉ የተከሳሽን የወንጀል ተግባር ያሳያል እንዳይባል መፀሐፉ በተለያያ እርዕሶች ስር ስለተለያዩ ጉዳዮች ሀተታ የቀረበበት በመሆኑ ተከሳሹ ፈጸመ ከተባለው የወንጀል ድርጊት ጋር ተያያዥነት ያለው የትኛው ክፍል እንደሆነ ተለይቶ ባልቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በእዚህ ክስ ተከላከል ለማለት ፍትሃዊ ሆኖ አላገኘውም በመሆኑም ተከሳሹ በእዚህ ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ቁጥር 141 መሰረት ብይን ሰጥተናል:: 125ኛ ተከሳሽ እንተነህ ጌትነት በሌለበት ነው ይሄ ተከሳሽ 126ኛ ተከሳሽ ውድነህ

ተመስገን እና 127ኛ ተከሳሽ ወንድሜነህ ደሳለኝ ዐቃቢ ህግ በ1ኛ፣ በ2ኛ እና በ3ኛ ክሶች ከመሰረታቸው የወንጀል ጉዳዮች ተጠያቂ ናቸው ተብለው እና የወንጀል አድራጐታቸውም በ45ኛ፣ በ101ኛ፣ 102ኛ፣ በ103ኛ እና በ104ኛ፣ 105ኛ እንዲሁም 106ኛ ምስክሮች ይረጋገጣል በማለት ዐቃቢ ህግ ጭብጥ ያስያዘ ቢሆንም ተከሳሾቹ ስለፈጸሙት የወንጀል ተግባር በምስክሮቹ ያልተነገረባቸው ስለሆነ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበቱ ብይን ሰጥተናል:: 107ኛ ተከሳሽ ታዬ ጌታቸው እና 119ኛ ተከሳሽ ተስፋዬ ጋንታን በተመለከተ ተከሳሾቹ በህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በህገወጥ መንገድ ለማፍረስ የሌሎችን ተከሳሾች የወንጀል ድርጊት እና የሚያስከትለውን ወጤት ለመቀበል በሙሉ ሃሳባቸው በመስማማት በአድማ እና በግርአበርነት የወንጀል ተግባር መፈጸማቸውን በዐቃቢ ህግ ክስ የተነገረባቸው ቢሆንም የዐቃቢ ህግ ማስረጃ እነዚህን ተከሳሾች በተመለከተ ያለው ነገር የለም ስለዚህ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ብይን ሰጥተናል:: እዮብ በቀለ፣ መሀመድ ሰማን፣ ካሳ ታደሰ፣ ፍቃዱ አሰፋ የተባሉት 108ኛ፣ 109ኛ፣ 110ኛ እና 111ኛ ተከሳሾች ጥቅምት 22 ቀን እና 23/98 ዓ.ም ሽሮ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተከሰተው ሁከት የአድማው ተሳታፊዎች እንደነበሩ እና ኑርሁሴን እድሪስ በተባለው የትግራይ ብሔር ተወላጅ ላይ ማንነቱን እና የፖለቲካ አመለካከቱን ምክንያት በማድረግ ከ112ኛ ተከሳሽ መላኩ አንቻ ጋር በግብረአበርነት ከፍተኛ የአካል ጉዳት በማድረሳቸው በዚህ ተግባር በፈጸሙት የአድማ እና የግብረአበርነት ወንጀል ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም እንደ ዋና ምስክር ሆነው የቀረበው ተጐጂ በዋና ጥያቄ ተከሳሾቹ 112ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ጉዳት እንዳደረሱበት ቢገልጽም ከተከሳሾቹ በቀረቡለት መስቀለኛ ጥያቄ በወቅቱ በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት የተነሳ ጉዳቱን ያደረሱበት ሰዎች ማንነት እንደማያስታውስ ገልጸ ተከሳሾቹ እናንተ ምንም አላደረጋችሁኝም በማለት በዋናው ጥያቄ ለሰጠው የምስክርነት ቃል የሚቃረን ምላሽ በመስጠቱ ማስረጃውን አጠራጣሪ አድርጐታል ስለሆነም ጥርጣሬ ላይ በወደቀ ማስረጃ ተከሰሾቹ መከላከል ስለማይኖርባቸው መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ 142 ብይን ሰጥተናል:: 114ኛ ተከሳሽ ምናለ ገብሬን እና 116ኛ ተከሳሽ ገዛኸኝ ተስፋዬን በተመለከተ ተከሳሾቹ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም እና በተከታታይ ቀናት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተከስቶ በነበረው አመጽ ተካፋይ እንደነበሩ እና በግለሰቦች ንብረት፣ በመንግስት እና በሕዝብ መገልገያ ተቋማት ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ከ115ኛ፣ 117ኛ እና 118ኛ ተከሳሽ ጋር በግብረአበርነት ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው በቀረበባቸው ክስ በ97ኛ እና 100ኛ የዐቃቢ ህግ ምስክሮች የተነገረ ቢሆንም ምስክሮቹ የተከሳሾቹን ማንነት



Scanned by CamScanner

ለይተው እንዲያሳዩ ተጠይቀው ለፍ/ቤቱ ለይተው ማሳየት ባለመቻላቸው ምስክርነቱ አጠራጣሪ አድርጕታል ስለሆነም በአጠራጣሪ ማስረጃ ተከሳሾችን እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ፍትሐዊ ስለማይሆን በነፃ እንዲሰናበቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሰረት በይነናል።

26ኛ፣ 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ በተከሳሾች ላይ የቀረቡት ምስክሮች ተከሳሾቹ ከግንቦት 97 ምርጫ በፊት እና በኋላ ስለነበራቸው እንቅስቃሴ ሲያስረዱ የግንቦት ምርጫ ከመካሄዱ በፊት ሲቪል ማህበራትን በመወከል ግንቦት 2 እና 3 ቀን 1997 ዓ.ም ለምርጫ ታዛቢዎች ከተዘጋጀው የስልጠና መድረክ በተለይ 94ኛው እና 95ኛ ተከሳሾች አሰልጣኖች ሆነው ሲሰሩ ኢህአዲግ ምርጫውን አጭበርብሮ ለማለፍ ይጥራል ኢህአዲግ ሌባ ነው መብራት ያጠፋል ስለሆነም መብራት ሲጠፋ በስራ ላይ ችግር እንዳይፈጠር በምርጫው ቀን ምሽት የሚያገለግል ባትሪ ይሰጣችኋል ተብሉ በእዚህ መሰረት ግንቦት 6 ቀን 97 ዓ.ም በሲአርዲኤ በተደረገው የምርጫ ገለጻ ወቅት ለየቡድኑ ባትሪ መታደሉን በመግለጽ በየስልጠናው መድረክ ኢህአዲግ ምርጫውን ያጭበረብራል ከመባሉ በቀር ቅንጅት ወይም ሌላ ምርጫውን ሊያጭበረብር ይችላል የሚል ግምት አለመነገሩን እንደመነሻ ሃሳብ በመውሰድ የሲቪል ሶሳይቲው አቋም ወደ አንድ በኩል ያዘነበለ እንደነበረ በተለይም በ92ኛው የዐቃቢ ህግ ምስክር የተነገረ ሲሆን 91ኛዋ ምስክር በበኩልዋ የሲቪል ማህበረሰቡ ሐምሌ 29 ቀን 97 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበርን በመወከል በስብሰባው መገኘትዋን ገልጻ ስብሰባው ሲመሩ እና ሲያስተባብሩ የነበሩት 94ኛው እና 95ኛው ተከሳሾች ምርጫው ተጭበርብሯል ኢህአዲግ አፋኝ ነው በ299 የምርጫ ጣቢያዎች የተገኘው ድምጽ የተጭበረበረ ስለሆነ ምርጫው ይደገም እያሉ ተከሳሾቹ ንግግር ሲያደርጉ መስማትዋን በተለይም 94ኛው ተከሳሽ ጊዚያዊ መንግስት መቋቋም የኖርበታል ምርጫ ቦርድ የአህአዲግ ደጋፊ በመሆኑ መቀየር አለበት ቦርዱ የምርጫ ውጤቱን ለማሳወቅ ብቃት የለውም ሲል መስማትዋን እንዲሁም ተከሳሾቹ በስብሰባው ወቅት ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ የማነሳሳት ስራ ይሰሩ ነበረ በማለት የመሰከረች ሲሆን 89ኛው የዐቃቢ ህግ ምስክር የግንቦት 97 ምርጫ ጋር በተያያዘ ከሶስቱም ተከሳሾች ጋር ስለነበረው ግንኙነት ሲመሰክር ምርጫው ከመካሄዱ በፊት የአካባቢ ሕብረተሰብ ቅንጅትን እንዲመርጥ እንዲቀሰቅስ 95ኛ ተከሳሽ እንደነገረው እና ወጣቱንም ለስራ አጥ ያደረገው የኢህአዴግ መንግስት ለአንድ ብሔር የሚያደላ የጥቂት የትግሬ ብሔር መጠቀሚያ ብቻ በመሆኑ በተለይ ወጣቱ ቅንጅትን



Scanned by CamScanner

እንዲመርጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ስለሚኖርበት ወጣቱን እንዲያስተባብር እንደነገረው እና ከምርጫም በኋላ ኢህአዴግ ምርጫውን አጭበርብሮአል በማለት አመጽ እና ሁከት እንዲነሳሳ የአካባቢውን ወጣቶች እንዲያስተባብር እና መስከረም 22 ቀን 1998 ዓ.ም ቅንጅት እና ሕብረት በጠሩት ሰልፍ ፖሊስን በመጋፈጥ ሕዝቡ ሰልፍ እንዲወጣ ቅስቀሳ እንዲያደርግ ተከሳሹ እንደነገረው ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም ምስክሩ በሚኖርበት አዲስ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ወጣቱ ረብሻ እንዲያነሳ ተከሳሽ በአካል ተገኝቶ እንደነገረው እና በሁኔታውም በአካባቢው ሁከት ተቀስቅሶ በንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን ለእዚህ ተግባሩ ማከናወኛም ክፍያ ይደረግለት እንደነበረ እና ቅንጅት ምርጫውን ቢያሸንፍ ስራ እንደሚሰጠው ቃል እንደተገባለት 26ኛው እና 94ኛ ተከሳሾችን በተመሳሳይ ሁኔታ የአመጽ ቅስቀሳውን እንዲቀጥልበት እና በራሪ ወረቀትም እንዲበትን ሲያበረታቱት እንደነበረ ይበትናቸው የነበሩት ወረቀቶችም በዐቃቢ ህግ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ እንደተመለከተው እና ለይተው ለፍ/ቤቱ እንዳሳየው የካርዳችን ድምጽ ይሰማ ጥሪ ለአዲስ አበባ ወጣቶች የሚሉ እና ባለስልጣኖች በውጭ ባንኮች አስቀመጡት የተባለውን ገንዘብ ልክ እና የባለስልጣኖቹን ስም የያዘ ሰነድ እንደነበረ ገልጸዋል 11ኛው የዐቃቢ ህግ ምስክር በበኩሉ ሰኔ ወር 1997 ዓ.ም ከ94ኛው ተከሳሽ ጋር መገናኘቱን ገልጾ ተከሳሹ ስለ ቀጣዩ የቅንጅት በምርጫ የማሸነፍ ሁኔታ አስመልክቶ ወጣቶችን እና ሌላውን የሕብረተሰብ ክፍል እንዲቀሰቅስ ኢህአዴግ በአፈ ሙዝ በመግዛት ላይ ያለ ፓርቲ በመሆኑ መወገድ አለበት ብሎ እንደነገረው እና ለዚሁም ጉዳይ ወጣቶችን ለአድማ እንዲያነሳሳ እና በራሪ ጽሑፎችን እንዲበትን ተከሳሹ እንደነገረው እና ለስራ ማስኬጃም እንዲሆን ብር ሁለት መቶ እንደሰጠው እንዲሁም መንግስትን ለመጣል ሕዝቡ የተወሰደበትን ድምጽ ለማስመለስ አመጽ ለማድረግ እንዲቀሰቅስ ተከሳሹ እንደነገረው እና ከእዚህም በመነሳት በየአካባቢው የሚገኙትን ወጣቶች እየቀሰቀሰ እንደነበረ ጥቅምት 22 እና 23/98 ዓ.ም ረብሻ ተከስቶ በተለያዩ ንብረቶች ላይ ጉዳት መድረሱን መስክረዋል ከእዚህም በተጨማሪ በተለይ 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች የወከሉአቸውን ማህበራት ከተመሰረቱባቸው አላማዎች እና ተግባራት ውጭ በመንቀሳቀስ በማህበራቱ ስም የወንጀል ሃሳባቸውን እና ተግባራቸውን የሚገልጹ ውሳኔዎች እና መግለጫቸውን አስተላልፈውባቸዋል ያላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ዐቃቢ ህግ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ተመልክቶአቸዋል ሰነዶቹም የሲቪል ማህበረሰብ የግማሽ ቀን ስብሰባ ሪፖርት ነሐሴ 2 ቀን 1997 ዓ.ም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቅም የሃገር ጥቅም ይቅደም የግንቦቱ ምርጫ ሂደት እና ሃገራችን የምትገኝበት አጣብቂኝ በሚሉ ጉዳዬች ተከሳሾቹ በማህበረሰቡ ስም መግለጫ እና ውሳኔ አሳልፈውባቸዋል በሚል እንዲሁም ከኤልያስ ክፍሌ ሰሜን አሜሪካ ለፍሬዘር ነጋሽ እና ለብርሃን ሃይሉ አዲስ

የተጣሩ ደብዳቤዎች ሲሆኑ ተከሳሾቹ በቅንጅት አበባ በሚል በየስማቸው የተፃፉ ደብዳቤዎች ሲሆኑ ተከሳሾቹ በቅንጅት የሚገልጹ መሆናቸውን ችሎቱ አገናኝ መሆኑንነት እንደሚሰሩ የሚገልጹ መሆናቸውን ችሎቱ ተመልክቶአቸዋል እነዚህ ሰነዶች እንደ አካባቢ ማስረጃ ሆነው ሲቆጠሩ ከሚችሉት ለየግለሰቦቹ የተፃፉ ተከሳሾች ቅንጅት ከተሰኘው ድርጅት ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ከሚያመለክቱ የግል ደብዳቤዎች በቀር ሰነዶቹ በጥቅሉ ሲመረመሩ ተከሳሾቹ በምስክሮቹ የተነገረባቸውን የወንጀል ድርጊት መፈጸማቸውን የሚያመለክቱ በመሆናቸው ማስረጃው ተደጋጋፊነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል ከእዚህ ማስረጃ መረዳት የሚቻለው ተከሳሾች በአንደኛው ክስ የተጠቀሰውን የወንጀል አድራጉት ለማሳካት በማሰብ ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት የተሰባሰቡት አመራሮች ምርጫው ተጭበርብሯል የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም ጥምር መንግስት ይቋቋም በማለት ህገ መንግስታዊ ስርዓትን በሀይል ለማፍረስ የአመጽ ተግባር ሲያካሂዱ ተከሳሾቹ ይሄኑን የወንጀል አድራጎት እና የሚያስከትለው ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሃሳባቸው በመስማማት ለአመጽ ተግባር መንቀሳቀሳቸውን፤ ይሄንኑ የወንጀል ተግባር ለማሳካት የወከሉት የሲቪል ማህበረሰባዊ ድርጅት ከመሰረታዊ አላማው ውጭ በሆነ አኳን ፖለቲካዊ ስራ እንዲሰራ በማሰብ ቅድመ ምርጫ ኢህአዴግ በምርጫው ሂደት ያጭበረብራል ከምርጫው በኋላ ደግሞ ምርጫው ተጭበርብሯል በሚለው አቋማቸው በመጽናት መንግስት በምን አይነት ሁኔታ መመስረት እንዳለበት በህግ የተወሰነ መሆኑ እየታወቀ ህግ በማይፈቅደው አሰራር ጥምር መንግስት ይቋቋም የሚለውን ፍላጐታቸውን ከማራመዳቸውም ባሻገር እንደ ማስተባበያነት ያገለግላል ተብሎ በተከሳሾቹ በተጠቀሰው እና በዐቃቢ ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር በቁጥር 62 የተመለከተው ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቅም የሃገር ጥቅም ይቅደም በሚለው መግለጫ ካሰፈሩአቸው ጉዳዩች አንዱ ፓርቲዎች አሸናፊነታቸው የተረጋገጠላቸው ወንበሮችን በመቀበል ወደ ፓርላማ እንዲገቡ የሚል ሃሳብ የተገለጸበት ቢሆንም ሌሎቹ የእዚህ መግለጫ ይዘቶች የሚያመለክቱት በሌሎች ሰነዶቻቸው እንዳሰፈሩት እና በቃልም በየአጋጣሚው መናገራቸውን እንደተመሰከረባቸው የምርጫ ውጤት መጭበርበሩን የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆኑን ጉልተው የታየበት ሆኖ ተገኝቷል ይህ ደግሞ የሲቪል ማህበረሰቡ በመንግስት እና በተቃዋሚ ቡድኖች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር አወንታዊ መግለጫ አስተላልፉል ከሚያሰኝ ይልቅ ለምርጫው ሂደት ከፍተኛ ማጭበርበር አለ የሚለውን የተከሳሾች አቋም የሚያጉላ ነው ከእዚህም ሌላ በተከሳሾች ላይ የቀረቡት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል እርስ በእርስ

የሚቃረን እና ታማኝነት የጐደ ነው በሚል የቀረበው ማስተባበያም ቢሆን በግልጽ እንደሚታየው የዐቃቢ ህግ ምስክሮች ዋናውን ጭብጥ ከማስረዳት አንፃር እርስ በእርሱ የተቃረነበት ሁኔታ የለም የምስክርነት ቃል ከዋናው ጭብጥ ማስረዳት አንፃር የሚመዘን እንጂ ከዋናው ጭብጥ በራቀ መስል ጉዳዬች አኳያ አይደለም በመሆኑም በእዚህ ረገድ በተከሳሾች የቀረበው ማስተባበያ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡ 26ኛው ተከሳሽን በሚመለከት ተከሳሹ በቀረበበት ክስ የተመለከተው የወንጀል አድራጐት ለማሳካት ከ94ኛው ተከሳሽ ጋር በመሆን የአመጽ ቅስቀሳ ሲያራምድ እንደነበረ በ89ኛው የዐቃቢ ህግ ምስክር የተነገረበት ሲሆን ከእዚህም በተጨማሪ በዐቃቢ ህግ የሰነድ ማስረጃ በተራ ቁጥር 20 የተመለከተውንና ነሐሴ 4 ቀን 1997 ዓ.ም የመኢአድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ባደረገው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በአገሪቷ ጠቅላይ ሚኒስቴር የተላለፈውን ህገወጥ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ እገዳ አንቀበልም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫን አስመልክቶ የሰጠው መግለጫን አንቀበልም የሕዝብ ድምጽ ይከበር ነፃ የምርጫ ቦርድና የፍትህ አካላት ይቋቋሙ ጊዜያዊ መንግስት ይመስረት ከእዚህ አንፃር በሚቀረጸው እስትራቴጂና ስልት መሰረት ድርጅቱ የሚሰጠን መመሪያ ተግባራዊ እናደርጋለን የሚሉና ሌሎችም የአመጽ ጥሪዎች በተላለፉበት የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ በስብሰባው ከተገኙ የፕሬዚዲየም አባላት አንዱ ሆኖ መሳተፉን ይኸው ማስረጃ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ተከሳሾቹ የቀረበባቸውን ክስ በዐቃቢ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸው ስለሆነ ተጠቅሶ በቀረበባቸው የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1/ሀ/ለ 38፣ 27 ንዑስ ቁጥር 1 እና 238/1/2 ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 ንዑስ ቁጥር 1 መሰረት ብይን ሰጥተናል ይህ ብይን በአብላጫ ድምጽ ተሰጠ፡፡

ብይኑን እንቀጥላለን 26ኛ፣94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾችን በሚመለከት ስሜ 1ኛ ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኛ የልዩነት ሃሳብ ስላለኝ የልዩነት ሃሳቤን በማስቀደም እጀምራለሁ 94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾች ዳንኤል በቀለ እና ነፃነት ደምሴን በሚመለከት ዐቃቢ ህግ በተለየ ሁኔታ የተከሳሾችን ተሳትፎ ያሳያል በማለት በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ጽሑፎች ያቀረበ ሲሆን የሰው ምስክሮችንም አቅርቦ አስምቷል የምስሮች ቃል በአጭሩ እንደሚከተለው አይቼአቸዋለሁ ወ/ሮ መሰረት የተባሉት ምስክር ተከሳሾቹን በምርጫ 97 ወቅት በታዛቢነት ስልጠና ሲሰጥ እንደሚያውቋቸው በጊዜው ነፃነት እና ዳንኤል መድረኩ ላይ ሲመሩ እንደነበሩ እና ኢህአዲግ ምርጫውን ያጭበረብራል ኢህአዴግ ሌባ ነው መብራት ቢጠፋ ባትሪ እናዘጋጃለን ተጠንቀቁ በማለት ሲናገሩ እንደነበረ የተገለፀ ሲሆን ወ/ሮ ንግስት የተባሉትን በምርጫ 97 በተከሰተው ችግር የሲቪል ሶሳይቲ የምክክር መድረክ ላይ የተነሱ ነገሮችን ለፍ/ቤቱ ለማስረዳት እንደቀረቡ ገልፀው ሐምሌ 29 ቀን በቀይ



Scanned by CamScanner

ስብሰባ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበርን መስቀል በተደረገው የግማሽ ቀን ስብሰባ የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበርን
በመወከል የተሰባሰበ መሆኑን ስብሰባውን የጠራው ሲቪል ሶሳይቲ ኔትወርክ
እንደነበረ ስብሰባውን ሲመሩ የነበሩትም አቶ ፍቅሩ ዘውዱ፣ ዳንኤል እና
ነፃነት እንደነበሩ ወይይቱም ያተኮረው ተቃዋሚዎች ፓርላማ መግባት እና
ካለመግባት ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚል ይዘት የነበረው ሲሆን አቶ
ዳንኤል 299 ምርጫ ተጭበርብሯል መንግስት አፋኝ ነው በማለት መናገሩን
ሁለቱ ተከሳሾች ተቃዋሚዎች አማክረውናል አንድ ነገር ማድረግ አለብን ምን
እናድርግ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም የሚል አይነት ሁለቱም ሲናገሩ
እንደነበረ 5 አባላት የአቋም መግለጫ እንዲያወጡ ይኸውም ለሕብረተሰቡ
እሮሮ ጩኸታችንን እናሰማ በሚል 5 አባላት እንደተጠቆሙ እነሱም አቶ
ፍቅሩ 2ኛ አቶ ነፃነት 3ኛ አቶ ዳንኤል 4ኛ አቶ እሸቱ 5ኛ ወ/ሮ ብዙወርቅ
የተባሉት እንደነበሩ ገልጸው በአጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ እኚህ ምስክር ሁለቱ
ተከሳሾች በየስብሰባዎቹ ሲያራመዱት የነበረው አቋም እራሳቸውን
ከተቃዋሚዎች ያሰለፉ እና ለመንግስት እና ገዢውን ፓርቲ ጥላቻ
ሲያንፀባርቁ ነበረ የሚለው ለመመስከር ሞክረዋል አቶ አዳነ በቀለ የተባለው
ምስክር በሰጠው ቃል አቶ ነፃነት ደምሴ የአንድ ሰፈር ልጆች መሆናቸውን
ከረጅም ጊዜ በፊት እንደሚያውቁቸው ገልጸው ምርጫ 97 አካባቢ ተከሳሹ
ገዢው ፓርቲ የአንድ ብሔር የወገነ እንደሆነ እና የመሳሰሉት በመግለጽ
ሕዝቡ ድምጹን ለቅንጅት መስጠት እንዳለበት ሲነግረኝ ነበረ እኔም በእዚሁ
መሰረት ስቀሰቅስ ነበረ ከምርጫው በኋላ ሕዝቡ ድምጹን ለቅንጅት የሰጠ
ቢሆን ኢህአዲግ ስላጭበረበረ ይሄንን መንግስት በአመጽ ማስወገድ አለበት
በማለት በተደጋጋሚ ሲነጋገሩ እና ሲወያይ እንደነበረ ከእዚህ በተጨማሪ
በሰነድ ማስረጃ ከቀረቡት እና የካርዳችን ድምጽ ይሰማ የሚለውን አንድ ገጽ
ጥሪ ለአዲስ አበባ ወጣቶች የሚል አንድ ገጽ እና ባለስልጣኖች ከውጭ ሃገር
ባንክ ያላቸው ገንዘብ የሚል አንድ ገጽ ሲሆን ከእነዚህ ሰነዶች በስተመጨረሻ
ገጽ ነፃነት ደምሴ በ5 አባዝተህ ለሌሎች ስጥ ብሎኛል የሚል የአዳነ በቀለ
ስም እና የማይነበብ ፊርማ ይታያል አዳነ በቀለ ቀርቦ በሰጠው የምስክርነት
ቃልም እነዚህን ሰነዶች ነፃነት በቀለ ነው የሰጠኝ በማለት ለችሎቱ የገለፀ
ሲሆን የእነዚህ ሰነዶች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሰነዶች ምርጫው
መጭበርበሩን በመግለጽ ያለው አማራጭ ይሄንን መንግስት በሃይል ብቻ
ማስወገድ ብቻ እንደሆነ የሚገልጹ ሰነዶች ናቸው ይኸው ምስክር ተከሳሽ
ነፃነት ከዳንኤል በቀለ ጋር እንዳስተዋወቀው እና ከዳንኤል ጋ ከሶስት ወይም
ከአራት ጊዜ ለማይበልጥ ጊዜ ተገናኝተው እንደነበረ አቶ ዳንኤልም



Scanned by CamScanner

በተመሳሳይ ይሄን ወረቀት እንድበትን ነግረውናል ካለ በኋላ ከተከሳሹ ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ ስስቱንም ጊዜ ከአቶ ዳንኤል ጋር ሲገናኙ ምስክሩ በቻውን እንደነበረ የጊዜአዊ ጥምር መንግስት መቋቋም አለበት ይሄ ካልሆን ለቀጣይ የተለያዩ የምንቃወምበት ስልቶች አሉ እንቅስቃሴው በድፍን አዲስ አበባ እና በብዙ ሃገሪቱ ክፍሎች ስለሆነ በእዚሁ ተነስተን ኢህአዴግን ከስልጣን እናስወግዳለን በማለት ተከሳሹ እንዳወያየው እና በእዚሁም መሰረትም ወጣቶችን እንዳስተባብር ነግሮኛል ያለ ሲሆን በእዚሁ መሰረት በርካታ ወጣቶችን ያስተባበረ መሆኑን ሆኖም ግን ማንንም በስም እንደማያውቅ እዚሁ ሰፈር ከ25 ዓመት በላይ እንደኖረ ማንኛውንም ሲያገኙት የነበረውን ሲቀሰቅሱ እንደነበረ በመመስከር ቃላቸውን ሰጥተዋል፡ አቶ ወንድወሰን የተባሉ የዐቃቢ ህግ ምስክር በሰጡት ቃል ከአቶ ዳንኤል ጋር ከምርጫ 97 በኋላ እንደተዋወቀ ሊተዋወቁ የቻሉትም በአጋጣሚ ሻይ ቤት ውስጥ እንደሆነ እና እኔ እና አንድ ግለሰብ አንድ ሻይ ቤት እያወራን ንግግራችንን እየሰሙ ነበረ መሰለኝ ከእዛም ተዋወቅን በርታ አለኝ እና ስልኩን ሰጠኝ በዚህ መሰረትም አንድ ሁለት ጊዜ ነው ያገኘሁት ከእዛ በኋላ አላገኘሁትም በዚህ ሁለት ጊዜም ወጣቶች እንዴት መደራጀት እንዳለባቸው ኢህአዲግን እንዴት ማስወገድ እንደምንችል ተነጋግረን በወቅቱ ሁለት መቶ ብር ሰጥተውኝ በእዚሁ መሰረት ስቀሰቅስ ነበረ ካለ በኋላ ለቀረበላቸው በርካታ መስቀለኛ ጥያቄዎች ምላሻቸውን የሰጡ ሲሆን ከረብሻው በኋላ ለሁለት ወር አካባቢ ከሰው ቤት እንደተደበቁ ሆኖም የባለቤቶቹን ስም እንደማያውቋቸው የገለጹበት ይገኛል በተከሳሽ ላይ ዐቃቢ ህግ የተለያዩ ይዘት ያላቸው የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን የተወሰኑ ተከሳሾች ዳንኤል በቀለ ቢሮ ተገኝተዋል የተባሉ ናቸው ሌሎች ደግሞ ሲቪል ማህበረሰቡ ሲያደርጋቸው የነበሩ የተለያዩ ስብሰባዎች እና ተከሳሾች ከቅንጅት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያመለክታል በማለት የቀረቡ ሰነዶች ናቸው የሲቪል ማህበረሰቡ እንቅስቃሴን የሚያሳይ እና ከቅንጅት ጋር ያላቸው ግንኙነት ያመላክታል በተባሉ ሰነዶች ላይ ትኩረት አደርጋለሁ ተከሳሾች ከቅንጅት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያመላክታል በማለት የቀረበው ሰነድ ኤልያስ ክፍሌ የተባለው 51ኛ ተከሳሽ ፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃኔ ሃይሌ ለተባሉት በፃፈው ደብዳቤ ነፃነት እና ዳንኤል የቅንጅት ኮንታክት ፐርሰን እንደሆኑ በአቶ ሃይሉ ሻውል ተገልጾልናል የሚለው ነው ተከሳሾች ይሄንን ሰነድ የተገኘበትን ሁኔታ በመዘርዘር ህጋዊ ስላልሆነ በማስረጃነት ሊያያዝ አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በማስረጃነት ቢያያዝ ስለ እኛ ያወራውን በሚመለከትም እኛ ፀሐፊውንም ሆነ የተፃፈላቸውን ሰዎች አናውቃቸውም የሚሉ እና የመሳሰሉት ትችት ሰነዱ በፍ/ቤት ይገኙበታል ከላይ 51ኛው ተከሳሽን በሚመለከት በተሰጠው ትችት ሰነዱ በፍ/ቤት ብርበራ የተገኘ ሲሆን ሰነዱ ሲገኝም ታዛቢዎች እንደነበሩ ከታዛቢዎች አንደኛው



Scanned by CamScanner

የብርበራ ትዕዛዝ ይኑር አይኑረው አላውቀም በላለ ብቻ ሰነዱ ህገ ወጥ ሊባል እንደማይችል እንዲሁም በአንዱ ሰነድ ላይ ፍሬዘር የተባለችው አልፈርምም በማለትዋ ብቻ ሰነዱ ህገ ወጥ ነው ሊባል አይችልም ይሄም በመሆኑ የ51ኛ ተከሳሽ ተሳትፎውን ስናይ ሰነዱ ከተጠቀሰው አንፃር የምንመለከተው ሲሆን ይህ ሰነድ ሰነዱን ከፃፈው ውጭ በሰነዱ ላይ ስማቸው በሚታዩ ሰዎች ሁሉ በማስረጃነት ሊቆጠርባቸው ይችላል ወይ የሚለው ጥያቄ ሲታይ ተከሳሾች ሰነዱን በሚመለት ማስተባበያቸው ላይ የጠቀሱትን ግንዛቤ ውስጥ መውሰድ የግድ ይላል ፀሐፊውንም ሆነ የተፃፈላቸው ሰዎች በማያውቁበት ሁኔታ ይሄም ስለመሆኑ ማረጋገጫ ባልቀረበበት ሁኔታ እንዲሁም በሰነዱ ላይ ሃይሉ ሻውል ዳንኤል እና ነፃነት ኮንታክት ፐርሰን ናቸው ብሎኛል የተባለው ትክክል ይሁን አይሁን ባልታወቀበት ሁኔታ ይህ የተጠቀሰው ማስረጃ በተከሳሾች ላይ ማለትም በተከሳሾች እና ቅንጅት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማስረዳት ብቃት ያለው ሆኖ አላገኘሁትም፡ የሲቪል ማህበረሰቡ ሲያደርጋቸው የነበረው እንቅስቃሴዎችን የሚያሳዩ ናቸው የተባሉትን እንደሚከተለው አይቼአቸዋለሁ ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች አንደኛው ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም ሲቪል ማህበረሰቡ ያደረገው የግማሽ ቀን ስብሰባ ሪፖርት የሚለው ሲሆን በዚህ ስብሰባ ግንቦት 7 ቀን በኋላ በሃገሪቱ የተከሰተውን ችግር በሰፊው መወያየታቸውን የሲቪል ማህበረሰቡ የተፈጠረውን ችግር ለማርገብ ምክር መስጠት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በውይይቱ የተንፀባረቁት የተለያዩ አመለካከቶችም ከሰነዱ ሰፍሯል በተነሱት ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች የሚከተለው ሁለት ነጥብ ብቻ በማየት መገንዘብ ይቻላል አንደኛው ሃሳብ ሰላምን ለማስፈን የተጀመረው የዲሞክራሲ ተስፋ እንዳይመክን በደል ቢኖርም ተቃዋሚዎች ፓርላማ ይግቡ ሲሆን ሌላኛው የእዚህ በቃራኒ ሃሳብ ደግሞ ተቃዋሚዎች ውጤቱን ተቀብላችሁ ፓርላማ ግቡ ማለት የሕዝቡን ድምጽ ከንቱ ማስቀረት ነው በሚል ይዘት ያለው ነው ከእዚህ ውጭ ጥምር መንግስት ማቋቋም የሚል ሃሳብ የተንፀባረቀ መሆኑን ከሰነዱ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በእለቱ ይሄንን ሃሳብ ልዩነት ማስወገድ ባለመቻሉ 5 አባላት ያሉት የስራ ብድን ወይም ወርኪንግ ግሩፕ መቋቋሙ እና ከተከሳሾች መካከልም ዳንኤል በቀለ የተመረጠ መሆኑን ከሰነዱ ለማየት ችለናል ሌላው የቀረበው ሰነድ ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች ባወጡት መግለጫ የሐምሌ 29 እና ነሐሴ 3 ላይ የተካሄዱ ስብሰባዎች በመጥቀስ መግለጫ ማውጣታቸውን ለማየት የሚቻል ሲሆን በእዚሁ ሰነድ ሐምሌ 29 የተጠቀሰ በመሆኑ ይህ ሰነድ የተዘጋጀው

ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም በተቋቋመው የስራ ቡድን ወይም ወርኪንግ ግሩፕ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት መያዝ ይቻላል በእዚህ ሰነድ ርዕስ ከፖለቲካ ፖርቲዎች ጥቅም የሃገር ጥቅም ይቅደም የሚል ሲሆን ይዘቱም ተቃዋሚዎች ፖርላማ እንዲገቡ በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ መሰረት ስልጣን የሚረከበው መንግስት እንዲመሰረት ቅሬታ ያለው ወደ ፍ/ቤት እንዲሄድ የመገናኛ ብዙሃን አሁን በስራ ላይ ባለው ኢዲቶሪያል ፖሊሲ መሰረት በአግባቡ መስራት ለተቃዋሚ ቢድኖች የአየር ጊዜ እንዲመደብ ምርጫ ቦርድ ብቃቱ በተሻሻለ መልኩ እንዲደራጅ ዳኞች ነፃ የዳኝነት ስራ ምግባር መርህን መሰረት በማድረግ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ከግንቦት 7 በኋላ የተነሳውን ሁከት ማጣራት እርምጃ እንዲወሰድ ከምርጫ በኋላ በወጡ ህጐች ላይ ፖርቲዎች የጋራ መድረክ በማዋቀር እንዲወያዩ የሚል ይዘት ያለው ነው ከሲቪል ሶሳይቲ ወጥተዋል የተባሉት ሰነዶች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ ፍ/ቤቱ የምስክሮችን ቃል እና ሰነዱን በማጣመር እንደሚከተለው ማለት ሃሳቤን በልዩነት የሰጠሁት ዳኛ እነዚህ በማጣመር እንደሚከተለው መርምሬአቸዋለሁ ሐምሌ 29 ሲቪል ሶሳይቲው ባካሄደው ውይይት ሁለት ወይም ሶስት የተለያዩ ሃሳቦች የተንፀባረቁ መሆኑን ከሰነዱ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ይሄንን ውይይት ተከታትላ የነበረችው አንድ የዐቃቢ ህግ ምስክር በተከሳሾች ሲራመድ የነበረው አቋም የትኛው እንደሆነ ለማስረዳት ሞክራለች ይኸውም የጥምር መንግስት መቋቋም አለበት የሚለው እና 299 ድምጽ መጭበርበሩን ሲገልጹ እንደነበረ የገለፀች ሲሆን አንዷ ምስክርም ከምርጫው በፊት ሁለቱ ተከሳሾች ኢህአዲግ ምርጫውን ያጭበረብራል ሌባ ነው ተጠንቀቁ ሲሉ ነበረ በማለት ገልጻለች ተከሳሾች ባቀረቡት መስቀለኛ ጥያቄ እነዚህን ምስክሮች በሚመለከት ያስተባበሉት ነገርም የለም ይህ ሁኔታ የሚያሳየን ተከሳሾች በስልጣን ላይ ባለው ፖርቲ ወይንም መንግስት ከፍተኛ የሆነ ጥላቻ እንዲሁም ለተቃዋሚዎች በተለየ ሁኔታ ወገንተኝነታቸውን ማሳየታቸውን የሚያሳዩ ናቸው ሆኖም ግን ክሱ ከእዚህ በላይ ነው ክሱ ህገመንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማፍረስ ነው ሙከራ ማድረግ ነው ይሄንን የሚያሳያይ ነገር አለ ወይ ብለን ስንጠይቅ ሌሎች ሁለት ምስክሮች እና ሰነዶችን በድጋሚ ማየት ያስፈልጋል አዳነ በቀለ የተባለው ከነፃነት ደምሴ ጋር አብሮ አደግ እንደሆነ እና 25 ዓመት አብሮ በአንድ ሰፈር የኖሩ ቢሆንም ከላይ የሰፈረውን የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ በሰጠው ቃል የምስክርነት ቃሉ በሁለቱ ሰዎች ብቻ ታጥሮ እንዲቀር ነው ያደረገው ይኸውም ከነፃነት ጋር ስላለው ግንኙነት እና ከዳንኤል ጋር ስላለው ግንኙነት እንጂ ሲያደርገው የነበረው እንቅስቃሴ ሁሉ በስም ከማያውቃቸው ጋር እንደነበረ ገልጾአል የአንድ ምስክር ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ሲገባ በምስክሩ የሚነገረው ነገር በተለምዶ በተራ ሁኔታ እንዴት ነው የሚታዩት

የሚለውን ማወቅ ወሳኝ ነው አንድ ሰው 25 ዓመት ከኖረበት ሰፈር ውስጥ በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ወይም ከዚህ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ቅስቀሳ ሲያደርግ ወይም ስላለው ችግር ሲወያይና ሲቀሰቅስ በተለምዶ የሚጀምርው በአቅርባቢያው ካሉ ሰዎች እና በቅርበት የሚያውቃቸው እንደሆነ ግልጽ ነው ነገር ግን ይህ ምስክር ማንንም በስም አሳውቅም ማለቱ ሲታይ በተለይ ደግሞ ከዳንኤል በቀለ ጋር ትውውቁ ለሶስት ወይም ለአራት ቀን ብቻ ሆኖ ሳለ መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ የመሰለውን ውይይት ያደርጋል የሚለው ከነገሮች በተለምዶ ሁኔታ ይሆናል ለማለት አስቸጋሪ ያደርገዋል በተመሳሳይ ሁኔታ ሁለተኛው ምስክርም ቢሆን ከዳንኤል ጋር የነበረው ትውውቅ ከሁለት እና ከሶስት ቀን ያልበለጠ ሆኖ ሳለ ተመሳሳይ አጀንዳ በመያዝ ውይይት ማድረግ የምስክሩን አባባል ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል በተለይ ይህ ምስክር ለሁለት ወር አካባቢ ተደብቆበት የነበረውን ቤት የባለቤቶቹን ስም እንደማያውቅ መግለጹ ምስክሩ የሰጠውን ቃል ታማኝነት የሚያሳጣው ነው የእነዚህ ምስክሮች ቃል ከሰነድ ማስረጃው ጋር ተገናዝቦ ማየት ሚያስፈልግ ሲሆን በእርግጥ ሐምሌ 29 ቀን በተደረገው የሲቪል ሶሳይቲ ግማሽ ቀን ስብሰባ የተከሳሾች አቋም ምን እንደነበረ ለመረዳት የሚቻል ቢሆንም ማለት ከላይ እንደሰፈው በመንግስት ላይ ያላቸውን አመለካከት ያንፀባረቁበት ቢሆንም ይህ ሁኔታ በውይይት ጊዜ የተነሳ ከመሆኑም በላይ በመጨረሻ ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም በሲቪል ሶሳይቲ የወጣው መግለጫ ሲታይ ሐምሌ 29 የተደረው ውይይት ሃሳብን በነፃ ከመግለጽ ባሻገር በዚህ ጊዜ በተከሳሾች ሲንፀባረቅ የነበረው የጥምር መንግስትም ሆነ ሌላ በሃይል ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል በሚል የተንቀሳቀሱ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም ይህም ማለት ማንም ሰው የመሰለውን ሃሳብ ቢያራምድ የሽግግር መንግስት ይመስረት የሚለውንም ቢሆን ሌላ የዛቻ የሃይል የአድማ ወይም የአመጽ ተግባር ጋር ካላቆራኘው እና ካላያያዘው ስለተወያየ ብቻ ወንጀል ፈጽሟል ለማለት ከሆነ አይቻልም ወንጀል የሚሆነው ይሄንን ሲያራምድ የቆየውን ሃሳብ ከሀገ መንግስት ውጭ በሃይል ሊያሳካው ሲሞክር ነው በመሆኑም ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ስብሰባ ላይ በተከሳሾች የተንፀባረቀው ምን እንደሆነ በምስክር የተረጋገጠ ቢሆንም 1ኛን ክስ ለማስረዳት ብቃት የለውም በተለይ ነሐሴ 3 ቀን 1997 ዓ.ም በሲቪል ሶሳይቲው ያወጣው መግለጫ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ተከሳሾችም ሆነ ሌሎች በራሳቸው ግምት እና እምነት አማራጭ ብለው ያቀረቡት እንጂ የወንጀል ይዘት ያለው አይደለም አዳነ በቀለ እና ሌላ አንደኛው ምስክር የሰጡት ቃልም ቢሆን ከላይ ለማስረዳት እንደተሞከረው

የሰውት ቃል እምነት የሚጣልበት ሆኖ ስላላገኘሁት ሁለቱ ተከሳሾች በቀረበባቸው ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ ሊሰናበቱ ይገባ ነበረ በማለት ከአብላጫው ድምጽ ተለይቻለሁ፡ በተመሳሳይ ሁኔታ 1ኛው ከእነዚህ ከቀረቡት ከምስክሮች 1ኛው ስለ 26ኛው ተከሳሽ የሰጠው የምስክርነት ቃል እጅግ ጠቅለል ያለ ከመሆኑም በላይ ከላይ የ94ኛ እና 95ኛ ተከሳሾችን በሚመለከት በተሰጠው ምክንያት ምስክሩ የሰጠው ቃል እምነት የሚጣልበት አይደለም ተከሳሹን በሚመለከት ከቀረቡት ሰነዶች አንደኛው ማለትም መኢአድ ነሐሴ ወር ላይ ባደረገው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በፕሬዝደም አባልነት ስሙ የሚታይ ቢሆንም ከላይ በመነሻው ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ሁኔታ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ እንደተገለፀው ህገመንስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማፍረስ በተደረገው ሙከራ ተሳትፎውን የሚያሳይ ባለመሆኑ ተከሳሹ ማለትም 26ኛ ተከሳሽም መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ሊሰናበት ይገባል በማለት ከአብላጫው ድምጽ ተለይቻለሁ::

በክስ ማመልከቻው በተራ ቁጥር 40 እስከ 69 ያሉ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ ጉዳያቸው በሌሉበት እየታየ ያለ ሲሆን በተከሳሾች ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች እንደሚከተለው መርምረናል 40ኛ ተከሳሽ አንዳርጋቸው ጽጌ በእንግሊዝ ሃገር የቅንጅት ተወካይ እንደሆነ የሚገልጽ ከ1ኛ ተከሳሽ በተፈረመ እና የድርጅቱን ማህተም በያዘ ደብዳቤ የተገለጸበት በሰነድ ማስረጃነት ቀርቦ የተያያዘ ሲሆን ይኸው በ40ኛው ተከሳሽ የተፃፈው እና ነፃነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ የሚለውን መፀሐፍ በተመለከተ በቀስተ ደመና ለዲሞክራሲ እና ለፍትህ ንቅናቄ ውክል የተሰጠ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃም ቀርቧል ከዚህ በተጨማሪ ይኸው ተከሳሽ መስከረም 19/98 ዓ.ም የግንቦት 7ቱን ምርጫ መጭበርበር ያስነሳቸው ጥያቄዎች በሚል የተፃፈው 19 ገጽ ሰነድ ቅንጅቱ ሲያደርጋቸው በነበሩት የላዕላይ ምክር ቤት ወይይቶች ተነስቶ እንደነበረ ከቀረበው ቪዲዮ ለመመልከት ተችሏል ይኸውም አንዳንድ የውይይቱ ተሳታፊ የነበሩ አንዳርጋቸው ጽጌ በፃፈው ጽሑፍ በሚል ተከሳሹን ሲጠቅሱ የነበረ ሲሆን አንድ ተሳታፊ ደግሞ ይህ ጽሑፍ በተለይ ፖርላማ አንገባም በሚለው ሃሳብ ላይ የሚያተኩረው ተጨምቆ ወይም ሰመራይዝ ተደርጐ ማለትም በአቶ ሙሉነህ ሰመራይዝ ተደርጐ ለውይይት እንዲቀርብ በተባለው መሰረት ለምን እንዳልቀረበ ጥያቄ ቀርቦ እንደነበረ ለመመልከት የተቻለ ሲሆን እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩት ተከሳሹ ከቅንጅት ጋር የነበረው ግንኙነት ሲሆን ተከሳሹ በእዚህ ማለት የግንቦት 7ቱ ምርጫ መጭበርበር በሚለው ጽሑፍም ምርጫው ከኢህአዴግ መጭበርበሩን ከገለፀ በኋላ የሕዝቡን ድምጽ ከኢህአዴግ ዘረፋ መከላከል የሚቻለው ወያኔን በሰላማዊ ሕዝባዊ እንቢተኝነት ማንበርከር ሲቻል ብቻ እንደሆነ እና ፖርላማ ያለመግባት የእዚህ ትግል . ጎድ አካል እንደሆነ እንደ ወያኔ ካለ አንባ ገነን ሃይል ጋር



Scanned by CamScanner

በሚደረገው ትግል በዋነኛነት ሕዝባዊ እንቢተኝነት እና አልገዛም ባይነት ትግል በማቀጣጠል መሆን እንዳለበት ወያኔ አንባገነን ስለሆነ በእሱ ፍ/ቤት እና የምርጫ አስፈፃሚ አባላት በኩል ተሄዶ የተጭበረበረን ድምጽ ማስመለስ እንደማይቻል ወያኔን ቢቻል የሕዝቡን ፍላጐት እንዲያከብር ማድረግ ይሄንን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ የሐገሪቱ እና በሌሎች ሐገሮች ሕዝቦች ታሪክ እንደታዩት አንባገነኖች በሙሉ ከምድራችን ላይ ጠራርጐ ማስወገድ እንደሚገባ ለእዚህም አብዛኛዎቹ ቁልፍ ሁኔታዎች ተሟልተዋል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን በዚህ ጽሑፍ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ምርጫውን ስላጭበረበረ በሕዝባዊ አመጽ ሊወገድ ይገባል የሚለውን አንፀባርቋል ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ ተከሳሽ በአንድ የውጭ ሃገር የቅንጅት ተወካይ መሆኑ እና ጽሑፉም ቢሆን በላዕላይ ምክር ቤት ደረጃ መነሳቱን ግንኙነቱን የሚያሳይ ሲሆን በቅንጅት በኩል ሲደረጉ በነበሩ ህገመንግስታዊውን ስርዓት ኢ-ህገመንግስታዊ በሆነ ሁኔታ በመሻር እና በማፍረስ ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ለማስወገድ በተደረገው እንቅስቃሴ እና በሚሰጠው ውጤት በሙሉ ተካፋይ እንደነበረ ለመረዳት ይቻላል በመሆኑም ተከሳሹ በዚህ በቀረበው በ1ኛ ክስ በማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑ ሊከላከል ይገባው የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ በሌለበት እየታየ ስለሆነ ተከሳሹ የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ/ለ 38/27/1 238/1/2 ላይ በተመለከተው ጥፋተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡ በተመሳሳይ በትላንትናው እለት በተነበበው መስፍን አማንን በሚመለከት በሌለበት ጉዳዩ እየታየ የነበረ ስለሆነ ይከላከል ተብሎ የተነበበው በሌለበት እየታየ ስለሆነ ጥፋተኛ ነው ተብሎ በመስፍን አማንም ላይ ብይን ሰጥተናል፡፡ 41ኛ ተከሳሽ ዶክተር ነገደ ጐበዜን በሚመለከት ይህ ተከሳሽ በፃፈው መፅሐፍ በወያኔ መንግስት የሚደረገው ምርጫ ለይስሙላ መሆኑን በመጥቀስ ሕዝቡ ወይም ተቃዋሚው ግን ይሄንን ምርጫ በስልጣን ላይ ያለውን አንባገነናዊ የወያኔ መንግስት ለመጣል እንደ አንድ መሳሪያ መጠቀም እንዳለበት በወያኔ ምርጫ መሳተፍ በፍጹም አብላጫ ወንበር ለማግኘት ወያኔ ባዘጋጀው ህገመንግስት መሰረት ለመንቀሳቀስ መሆን እንደሌለበት ይልቁንም የወያኔ ህገመንስታዊ ስርዓት እና ህገመንግስቱን የተለያዩ እስትራቴጂዎችን በመጠቀም ማስወገድ ቀዳሚ ተግባር መሆኑን ይኸውም ሊደረግ የሚችለው በምርጫ ማግስት ተከታታይ እና የማያቋርጥ ሕዝባዊ አመጽ በመቀስቀስ እንደሆነ በመጸሐፉ የተጠቀሰ ሲሆን ይኸው ተከሳሽ በአንድ የግል ጋዜጣም በሰጠው ቃለ መጠይቅ ተመሳሳይ የሆነው መልዕክቱን አስተላልፍዋል ተከሳሽ ህገመንስቱን እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ በሕዝባዊ አመጽ ሊወገድ ይገባል በሚል



Scanned by CamScanner

በመፀሐፉ እና በጋዜጣ የተጠቀሰ ቢሆንም ከቅንጅት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት የቀረበው ማስረጃ ፎቶግራፍም ይሄንን ሁኔታ ለማሳየት ብቃት የለውም ከዚህም በተጨማሪ ከላይ እንደተመለከተ በቅንጅት ሲሰጡ በነበሩ እና መግለጫዎች መሰረት ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ሆነ ጥቅምት 21 እና ተከታዩቹ ቀናት በተደረጉ የአመጽ እንቅስቃሴዎች ስለመሳተፉ ማለትም የአመጹን እንቅስቃሴ የራሱ በማድረግ የሚሰጠውንም ውጤቱን በመቀበል ከ1 እስከ 23 በተጠቀሱት ተከሳሾች ጋር በመሆን ስለመንቀሳቀሱ የቀረበ ማስረጃ የለም ሆኖም ግን የመፀሐፉ ይዘት እንዲሁም በጋዜጣ የሰጠው መግለጫ በወንጀል ህግ ቁጥር 257/ሀ ላይ የተመለከተው የሚተላለፍ የወንጀል ተግባር ነው ይህ የወንጀል ድርጊት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 161 መሰረት ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ ሊታይ የሚችል ባለመሆኑ ተከሳሹ ባለበት ዐቃቢ ህግ የመክሰስ መብቱ ተጠብቆ ክሱ ሊቋረጥ ይገባል ብለናል : 42ኛ ተከሳሽ ሰለሞን በቀለን በሚመለከት የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተከሳሹ ከቅንጅት ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክት ቢሆንም በኦዲዩ ካሴት የቀረበው ማስረጃ ከ1ኛ ክስ አንፃር ተሳትፎውን ሁኔታ የሚያሳይ ባለመሆኑ ተከሳሹ ሊከላከል አይገባም ብለናል : 43ኛ ክፍሌ ታደሰ 1ኛ ክስን በሚመለከት ያቀረበው ማስረጃ በተከሳሹ ላይ ክሱን የሚያስረዳ ሆኖ ስላላገኘው ሊከላከል አይገባም በማለት ብይን ሰጥተናል : 44ኛ ተከሳሽ ብርሃነ መዋን በሚመለከት ተከሳሹ በሰሜን አሜሪካ የቅንጀት የገንዘብ አሰባሰብ እና የፖለቲካ ስራ አስተባባሪ በመሆን የተመደበ መሆኑን ከድርጅቱ የተገለፀበት ደብዳቤ እና በማስረጃነት ከቀረበው ሰነድ ለመረዳት ቢቻልም ከ1ኛ ክስ አንፃር የተከሳሹን ተሳትፎ የቀረቡት ማስረጃዎች ስለማያሳዩ ተከሳሹ በዚህ 1ኛ ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት ይገባል ብለናል : 48ኛ ተከሳሽ ያሬድ ጥበቡ በአንድ የሬዲዩ ፕሮግራም ባደረገው ገለጻ ወያኔ አገዛዝን ለማስወገድ የአመጽ ሃይል ማዳበር እንደሚቻል በሰላማዊ ትግል መለወጥ ያልተቻለውን ዘረኛ መንግስት እንዴት አድርገን ነው የምንለውጠው የሚል ነገር ላይ ቆጭ ብለው መወያየት እና አማራጭ እስትራቴጂዎች መንደፍ እንደሚያስፈልግ እና በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የመጣበትን መንገድ ተጠቅሞ ማውረድ እንደሚቻልም እንዲያውቁት መደረግ አለበት በማለት መግለጫ መስጠቱ የሰማን ሲሆን ከላይ በ41ኛ ተከሳሽ ከተሰጠው ላይ እንደተገለፀው ይህ ተከሳሽ ከቅንጅት ጋር ያለው ግንኙነት በማስረጃ ያልተደገፈ ሲሆን የተከሳሹ ቅስቀሳ በወንጀል ህግ ቁጥር 257/ሀ የተደነገገውን የሚጥስ ነው ሆኖም የዚህ አይነት ወንጀል ድርጊት ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ባለመሆኑ ዐቃቢ ህግ የመክሰስ መብቱ ተጠብቆ ክሱ ሊቋረጥ ይገባል ብለናል። 47ኛ ተከሳሽ ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌን በሚመለከት የተከሳሹን የተለያየ ተሳትፎ ለማሳየት የቀረበው የሰነድ ማስረጃ የቤተዘመዱ ይታያል ጉዱ በሚል ጥቅምት

19/98 ዓ.ም ይድረስ ለውድ ወገኖቼ የኢትዮጲያ ልጆች በሚል ከተፃፈ 1 ገጽ ሌላ የግንቦት 7 ቀን ምርጫ በሚል የተፃፈ 6 ገጽ ያለው ሰነድ ነው እነዚህ ሰነዶች ላይ የሰፈረው ጸሑፍ ምንም ይሁን ምን እነዚህ ሰነዶች በተከሳሹ ነው የተፃፉት ለሚለው ወይም የእሱ ናቸው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም በጽሑፉ ላይ የተከሳሽ ስም ከሚታይ በስቀር ምንአልባት እንኳን ከተከሳሹ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚባሉት ሰዎች ዘንድ እንኳን ስለመገኘቱ እና ፍ/ቤቱ ጽሑፉ የተከሳሹ ናቸው ለማለት የሚገምትባቸው ሁኔታዎችም ባለመኖሩ የጽሑፉ ይዘት ምንም ይሁን ምን መመርመር ሳያስፈልገን ተከሳሹ በቀረበበት በዚህ 1ኛ ክስ መከላከል አያስፈልገውም ብለናል 50ኛ ተከሳሽ ታማኝ በየነ የተለየ ተሳትፎን ለማሳየት የቀረበው ተከሳሹ በአንድ ወቅት ከነፃነት ለኢትዮጲያ ሬዲዮ ድምጽ የተወሰደ ነው በማለት ያቀረበው ሲሆን ይህም ሆነ ሌላ ማስረጃ ተከሳሹ 1ኛ ክስን ለማስረዳት ብቃት ያለው እና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም ይኸው ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ሊሰናበት ይገባል ብለናል፡፡ 51ኛ ተከሳሽ ኤልያስ ክፍሌን በሚመለከት የቀረበው ማስረጃ በኦዲዮ ማስረጃ ከዳዊት ከበደ ጋር በመሆን ጥያቄ ያቀረበበት የነበረ ሲሆን ይህ ኦዲዮ አግባብነቱ ሆነም ክብደቱ ክሱን ለማስረዳት በራሱ በቂ አይደለም በተከሳሹ እንደተፃፈ በተገለፀው እና በሰነድ ማስረጃነት የቀረበው ሲታይ ማለትም ለፍሬዘር ነጋሽ እና ለብርሃኔ ሃይሉ በማለት የፃፈው ደብዳቤ ዐቃቢ ህግ በማስረጃነት ያቀረበ ሲሆን ይሄንን ማስረጃ እንደሚከተለው አይተነዋል ይሄ የተጠቀሰው ማስረጃ የተገኘው በፖሊስ በተደረገ ብርበራ ማለትም የፍሬዘር ነጋሽ እና ብርሃኔ ሃይሌ የተባሉት ግለሰቦች ሲኖሩበት በነበረ መኖሪያ ቤት ፖሊስ ባደረገው ብርበራ ሲሆን በእነዚህ ቤቶች ብርበራው ሲደረግ ከፖሊስ በተጨማሪ ታዛቢዎችም እንደነበሩ የዐቃቢ ህግ ምስክር በማስቀረብ አስረድቷል የቀረቡት ታዛቢዎችም ብርበራው ሲከናወን በተጠቀሱት ቤቶች በተገኙ ዶክመንቶች ሲፈርሙ እንደነበረ የመሰከሩ ሲሆን አንዱ ሰነድ ላይ ግን ፍሬዘር ነጋሽ የተባለችው የእኔ አይደለም በማለት አልፈርምም እንዳለች በአንድ ምስክር ተገልጾአል በፊት የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት ቃል ቤቱ ውስጥ ለብርበራ ከመግባታቸው በፊት ቤቱ ዝግ ሆኖ እንደነበረ እና እንዲከፈት ከተደረገ በኋላ ታዛቢዎች በመቅደም ፖሊሶች እና በቁጥጥር ስር የነበሩ በመከተል በመግባት ብርበራው የተከናወነ መሆኑ እና በተለያዩ ቦታዎች ዶክመንቶች መገኘታቸው ተመስክሯል በእዚህ መልኩ የተገኘው ሰነድ እና በማስረጃነት የቀረበው ከኤልያስ ክፍሉ ለብርሃኔ ባለበት እና ለፍሬዘር የሚለው ሁለት የተለያዩ ሰነዶች ከብርበራው ታዛቢ

በድንገት መደረት እና እነዚህ ሰነዶች ከበርካታ ዶክመንቶች መካከል መገኘታቸው በ51ኛ ተከሳሽ በአልያስ ክፍሌ አማካኝነት የተፃፈ መሆናቸው የሚያመለክት በመሆናቸው 51ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ በማስረጃነት ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው ይዘታቸውንም መርምረናል በእዚህ በተገለጸው ሰነድ ይህ 51ኛ ተከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን በሚገልጽ መልኩ የተፃፈ ሲሆን እራሱንም ከተቃዋሚዎች ሃይል ጎራ በማሰለፍ ምርጫው በገገርው ፓርቲ እና በምርጫ ቦርድ በመጭበርበር መስረቁን በመግለጽ ወያኔ በሰላማዊ መንገድ ስልጣኑን ለአሸናፊው ፓርቲ እንደማያስረክብ የሚታወቅ መሆኑን ገልጾ ይሄንን የሕዝብ ድምጽ ማስከር የሚቻለው የተነሳው የሕዝብ ስሜት ሳይበርድ በሃገር ውስጥ እና በውጭ የምንገኝ ተቃዋሚ ሃይሎች መስዋትነትን የሚጠይቅ መሪር ትግል ብቻ እንደሆነ ገልጾ በውጭ ያለን ተቃዋሚዎች የወያኔ ኢህአዲግን ስርዓት ለመጣል ከማንኛውም ጊዜ በላይ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ የሞራል ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ በውስጡ ያሉ ሃይል ደግሞ ይሄንን የወያኔ ስርዓት ለአንዴ እና ለሁሌም በማያዳግም መልኩ ለማፍረስ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ማጥበብ እንደሚገባቸው የጠቆሙበት ሰነድ ነው በቀረበው ሰነድ ተከሳሹ ምርጫው መጭበርበሩን በመጥቀስ ለዚህ መፍትሔ ብሎ ያስቀመጠው ደግሞ የወያኔ ኢህአዲግን መንግስት ማስወገድ መሆኑን በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን በጽሑፉ መንፈስም እራሱን ከቅንጅት ጋር ያቆራኘ መሆኑ መረዳት የሚቻል ሲሆን ይሄም በ1ኛ ክስ በተመለከተው አኳሁን ህገመንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ በመጣል በስልጣን ላይ ያለውን ለማስወገድ በተደረገው ሙከራ ተካፋይ መሆኑን እና የሚሰጠውን ውጤት መቀበሉን የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም በ1ኛ ክስ መሰረት መከራከር በተገባው ነበረ ሆኖም ጉዳዩ በሌለበት የታየ ስለሆነ በዚሁ 1ኛ ክስ ከ1 እስከ 23 ተከሳሽ ሊከላከሉ ይገባል በተባለው የህግ አንቀጽ ስለሆነ በዚሁ 1ኛ ክስ ከ1 እስከ 23 ተከሳሽ ሊከላከሉ ይገባል በተባለው የህግ አንቀጽ መሰረት ጥፋተኛ ብለነዋል። 69ኛ ተከሳሽ ጌታቸው ጋረደውን በሚመለከት በተለይ የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹ ቅንጅት በምርጫ በአሸናፊነት ለመወጣት ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ብር አስር ሺህ የላከውን በሚመለከት በ1ኛ ተከሳሽ የምስጋና ደብዳቤ የተላከ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ሲሆን ይህ ሰነድ ምንአልባት በተከሳሹ እና በቅንጅት መካከል ያለውን ግንኙነት ሊያሳይ ከሚችል በቀር ሌላ የተለየ መልዕክት የለውም ሌላው ከተከሳሹ ላይ የቀረበው ሰነድ የ47ኛ ተከሳሽ ፕሮፌሰር ጌታቸው ላይ የተሰጠው ትችት ለእዚህም አግባብነት ያለው በመሆኑ ይህ ተከሳሽ በዐቃቤ ህግ የክስ ማመልከቻ ላይ የተመለከተው 1ኛ ክስ ስለመፈጸሙ በበቂ ሁኔታ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑ ተከሳሹ ሊከላከል አይገባም ብለናል። 92ኛ ተከሳሽ ካሳሁን ከበደን የነበረ አባል አካል አመራር መምህራን የኢትዮጵያ የቀድሞ ተከሳሹ በሚመለከት



Scanned by CamScanner

እንደሆነ በክስ ማመልከቻ የተጠቀሰ ሲሆን በክስ ማመልከቻው እንደተጠቀሰው በሚወክሉትን ማህበር ስም ውሳኔ በማሳለፍ እና መግለጫ በማውጣት በ1ኛ ክስ በተመለከተው አኳሃን ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን ዐቃቢ ህግ ይሄንን በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የተለያየ ይዘት ያላቸው የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል በሰነድ ማስረጃነት በቀረበው ማለትም የኢትዮጲያን መምህራን ማህበር ቃለ ጉባኤዎች ናቸው የተባሉትም ሆነ መግለጫዎች የተባሉት ሁሉም ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ ካሳሁን ከበደ ቢሮ ውስጥ የተገኘ የሚል ስም እና ፊርማ የሚታይ ሲሆን ይህ ጽሑፍ ማለትም ካሳሁን ከበደ ቢሮ ውስጥ የተገኘ የሚለው በካሰሁን ከበደ የተፃፈ ስለመሆናቸው በፎረንሲክ የተረጋገጠበት ማስረጃም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል በ04/10/97 ዓ.ም በኢትዮጲያ መምህራን ማህበር የአዲስ አበባ መምህራን አባላት ስብሳቢ እና አወያይ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት የሚል ሲሆን ይህ ሰነድ ማህተምም ሆነ ፊርማ የሌለው ከመሆኑም በላይ የተሰብሳቢዎችን ስም እንኳን የሚታይበት አይደለም የ6/9/97 እና የ20/9/97 ዓ.ም በተመሳሳይ የእጅ ጽሑፍ እንጂ ተወያይዎችንም ሆነ የትኛውንም ድርጅት ማህተም አልያዘም ከእዚህ በተለየ መልኩ የኢትዮጲያን መምህራን ማህበር 16ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚለው ሰነድ የኢትዮጲያን መምህራን ማህበር አርማ የያዘ ክብ ማህተም ያለው ሲሆን በእዚህ ያቋም መግለጫ በርካታ ህገወጥ ይዘት ያላቸው የሚታዩበት በመሆኑ ይህ ተከሳሽ እርግጥ የኢትዮጲያን መምህራን ማህበር አመራር አካል አባል መሆን አለመሆኑን ማጣራት በማስፈለጉ ይህንን ሁኔታ ለማጣራት ፍ/ቤቱ ዐቃቢ ህግ እና ተከሳሹ ከጠበቃው ጋር በመሆን ቀጠሮውን በመስበር መጋቢት 11 እና 12 ችሎት በመሰየም ዐቃቢ ህግ ይሄንን ሁኔታ ሊያረጋግጥ የሚችልበት ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ በመታዘዙ መጋቢት 12 ቀን 4 ሰነዶች ማለትም ከእዚህ ቀደም ለችሎቱ ያቀረብናቸው 4 ሰነዶች ብቻ ሌላ ማቅረብ ሳያስፈልገን ይሄንን የተከሳሹ ሃላፊነት ያስረዱልኛ በማለት ለችሎቱ አመልክቷል በዐቃቢ ህጉ የቀረበው 4 ሰነድ በፍ/ቤቱ መዝገብ ያልተያያዘ ለተከሳሹም ያልደረሰ የነበረ በመሆኑ ችሎቱ እነዚህን 4 ሰነዶች በመያዝ በእርግጥ ቀደም ሲል ለፍ/ቤት ከቀረቡት ሰነዶች አሉ ወይስ የሉም የሚለውን እንደሚያጣራ በችሎት በገለፀው መሰረት ሰነዶቹን ለማየት ሞክሯል በ12/7/99 ዓ.ም በችሎት የቀረበው 4ቱ ሰነዶች ሲታዩ ደግሞ ከእነዚህ ሰነዶች 3ቱ ከኢትዮጲየን መምህራን ማህበር ሲወጡ የነበሩ መግለጫዎች መሆናቸውን አይተናል ይህ ችሎት በ11/7/99 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ማለትም ተከሳሹ የኢትዮጵያን መምህራን ማህበር



Scanned by CamScanner

አመራር አካል አባል መሆኑን የሚያሳይ አይደለም ሌላኛው አንድ ሰነድም የአዲስ አበባ መምህራን አጠቃላይ ስብሰባ የሚል እና ሰብሳቢ ካሳሁን ከበደ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ተከሳሹ የኢትዮጵያን መምህራን አመራር አካል አባል መሆኑን የሚያሳዩ አይደሉም በመሆኑም እነዚህ 4ቱ ሰነዶች ቀደም ሲል ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር ቢያያዙም ባይያያዙም ተከሳሹ የጠቀሰው ማህበር አመራር አካል አባል መሆኑን የሚያሳዩ አይደሉም በመሆኑም ተከሳሹ ላይ የቀረበው ክስ በማስረጃ ስላልተደገፈ መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ሊሰናበት ይገባል ብለናል። በመቀጠል በእዚሁ 40 እስከ 69 ያሉ ተከሳሾች እና በእኔ ያልተነሱ ተከሳሾችን በሚመለከት አቶ መሀመድ ያነባቸዋል

የሚከተሉትን ተከሳሾች በተመለከተ ማስከተልም የሚከተሉትን ተከሳሾችን በተመለከተ ዐቃቤ ህግ የመሰረተውን ክስ በማስረጃ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረነዋል ከእዚህ አንፃር በ45ኛ ተከሳሽ ዶክተር ማሞ ሙጨ 46ኛ ተከሳሽ አብረሃ በላይ 49ኛ ተከሳሽ ምርጫው እንሻው በ60ኛ ተከሳሽ ዶክተር ሞገስ ወልደማርያም 52ኛ ተከሳሽ ዳዊት ከበደ 53 ተከሳሽ ሊሻን ግዛው 61ኛ ተከሳሽ ፋሲል በለጠ በ63ኛ ተከሳሽ ሰለሞን ተካልኝ በ66ኛ ተከሳሽ ከፈለኝ ማሞ እና 68ኛ ተከሳሽ ዶክተር አሰፋ ነጋሽ ላይ ዐቃቤ ህግ የመሰረተው ክስ ተከሳሾቹ በ1ኛ ክስ በ1ኛ እስከ 39 የተጠቀሱት ተከሳሾች የወንጀል አድራጐት እና ሃሳብ የራሳቸው በማድረግ ህገወጥ እንቅስቃሴአቸውን ለማካሄድ የሚረዱ ጽሑፎችን በማዘጋጀት እና በማሰራጨት የገንዘብ እና ማቴሪያላዊ ድጋፍ በማሰባሰብ እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ እንዲፈርስ አለምአቀፍ ተጽህኖ በመንግስት ላይ እንዲያርፍ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ በመቆየታቸው ምክንያት መከሰሳቸውን የሚገልጽ ነው ሆኖም ግን የሚከተሉትን ተከሳሾች በተመለከተ ዐቃቤ ህግ ክሱን ለማስረዳት ማስረጃ አላቀረበም ይኸውም 46ኛ ተከሳሽ አበረሃ በላይ 49ኛ ተከሳሽ ምርጭው ስንሻው 60ኛ ተከሳሽ ዶክተር ሞገስ ወልደማርያም 61ኛ ተከሳሽ ፋሲል በለጠ 63ኛ ተከሳሽ ሰለሞን ተካልኝ 66ኛ ተከሳሽ ከፈለኝ ማሞ እና 68ኛ ተከሳሽ ዶክተር አሰፋ ነጋሽ ይመለከታል በመሆኑም ተከሳሾቹ ክሳቸው በሌሉበት እየታየ የነበረ ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 149/2 መሰረት በውሳኔ በነፃ እንዲሰናበቱ ወስነናል፡ 53ኛ ተከሳሽ ሊሻን ግዛው በተመለከተ የቀረበው መረጃ ተከሳሹ በጀርመን የቀስተደመና ኢትዮጲያ የዲሞክራሲ እና የማህበራዊ ፍትህ ንቅናቄ ተወካይ መሆኑን ብቻ የሚያስረዳ መረጃ በመሆኑ ተከሳሹ በተመሳሳይ መልኩ በነፃ እንዲሰናበት



Scanned by CamScanner

ወስነናል፡ በ45ኛ ተከሳሽ ዶክተር [illegible] [illegible] ላይ ዐቃቤ ህግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ ነሐሴ 8 ቀን 1997 ዓ.ም በወጣው የሳተናው ጋዜጣ የኢትዮጲያ ምሁራን ኔትወርክ አባላት ወቅታዊ የኢትዮጲያን ሁኔታ በተመለከተ የሰጡት አስተያየት ሲሆን የተከሳሹም የኢትዮጲያ ምሁራን ኔትወርክ /እስካዲቪያ/ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር መሆኑ ጋዜጣው ላይ ተመልክቷል ወደ ጋዜጣው ዝርዝር ሂደት ስንገባ አባላቱ በኢትዮጲያ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የተካሄደው ሃገር አቀፍ ምርጫ ምርጫን ተከትለው የተፈጠሩትን ችግሮች አንዳንድ የፖለቲካ ፖርቲዎች እምነት ምን እንደሆነ እና ከምርጫው በኋላ የነበሩትን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ ለሃገሪቷ ሰላም እና እድገት ይበጃል በማለት በሁሉም የፖለቲካ ፖርቲዎች ዘንድ የብሄራዊ እርቅ መካሄድ ያለበት መሆኑን የገለጹበት ማስረጃ ነው ይሄ የቀረበው ማስረጃ አግባብነት ካለው ህግ ጋር አገናዝበን መርምረነዋል ከእዚህ አንፃር በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 42 መሰረት በጋዜጣ አማካኝነት የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሊፈጸሙ የሚችሉት ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት ገደብ በማለፍ የግል ወይም የጋራ ደህንነትን በማደፍረስ እና በወንጀል ህግ ተከብሮ የሚኖረውን ማንኛውም ህጋዊ መብት ሲነካ መሆኑን መረዳት ይቻላል ሆኖም ይህ ተከሳሽ ከኔትወርክ አባላት ጋር በመሆን በኢትዮጲያ ውስጥ ምርጫውን ተከትሎ ለተፈጠረው ውዝግብ መፍትሔ ይሆናል ብሎ ያመነበትን የብሄራዊ እርቅ መመስረት እንደአማራጭ ከማቅረብ ባለፈ መልኩ ይሄንን አማራጭ ተፈጻሚ ለማድረግ የፈጸመው ህገወጥ እንቅስቃሴ ለመኖሩ ዐቃቢ ህግ ያቀረበው መረጃ የለም በመሆኑም የተከሳሹ ድርጊት ሃሳብን በነፃ የመግለጽ ነፃነት አለፎአል ለማለት የሚያስችል ሆኖ ያላገኘነው ስለሆነ ተከሳሹ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 149/2 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ወስነናል፡ ሌላው 52ኛ ተከሳሽ ዳዊት ከበደን በተመለከተ ዐቃቢ ህግ ያቀረበባቸው ማስረጃዎች ስንመረምራቸው 1ኛ ተከሳሹ በሬዲዮ ቃለ መጠይቅ በመጠየቅ ይሳተፍ እንደነበረ የሚገለጽ ሲሆን 2ኛ ደግሞ ሐምሌ 24 ቀን 1997 ዓ.ም ታትሞ በወጣው አንድነት ጋዜጣ ውስጥ ተከሳሹ ለኢትዮጲያ ሕዝብ እንዲደርስ በማለት የጻፈጡ ጽሑፍ ነው የተፃፈው ጽሑፍም ኢህአዲግ ደብተር እና እርሳስ ይዞን የወጣን ተማሪ በጥይት አረር እየቆላ



Scanned by CamScanner

የነገውን ትሰፋውን እንዳጨለመው፤ አንድ ቀን ልጄ ይጠረኛል እያለች በተስፋ የነበረች እናት ማቅ ማስለበሱን እንዲሁም ደም እንባ እንዳላቀሰ ኢህአዴግ በምርጫ ካርድ ሲሸነፍ ብበሸቀቱ ሰው ሊገል መነሳቱን ወንዶችን እና ሴቶችን መደብደቡን ማሰሩን እና መግደሉን በመግለጽ ከዚህ በላይ ጨኳኝነት የለም እንግዲህ ምንድነው የምንጠብቀው በማለት በኢትዮጲያ ውስጥ የለውጥ ማዕከል ዳግም ወደ ኋላ የማይመለስ ደረጃ ደርሶአል ካለ በኋላ ከእንግዲህ ወያኔ በኢትዮጲያ ያመሸ እንደሆነ እንጂ አያድርም በማለት ጽፎአል ተከሳሹ በአንድነት ጋዜጣ ለኢትዮጲያ ሕዝብ ያስተላለፈው መልዕክት ተከሳሹን የጽሑፉ አመንጭ ያደርገዋል በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 44 መሰረት አመንጭው ጭምር ተጠያቂ ሊሆንባቸው የሚችሉ የህግ አንቀጾች በዝርዝር የሰፈሩ ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 238 ግን በዝርዝሩ ውስጥ አልተሸፈነም ከእዚህ መረዳት የሚቻለው የአመንጭ ጽሑፍ ይዘት የአዋጁ አንቀጽ 238 የሚያሟላ ቢሆን እንኳ አመንጭው በአንቀጽ 238 ተከሶ ሊቀጣ የማይችል መሆኑን መረዳት ይቻላል ተከሳሹ በጽሑፉ ካስተላለፈው መልዕክት መረዳት የሚቻለው ጽሑፉ የሕዝብ ስሜትን በከፍተኛ ሁኔታ በማሳዘን እና እንዲሁም በገገርው ፖርቲ ላይ ሕዝቡ እንዲነሳ በመገፋፋት መቀስቀሱን ያስረዳል ይህም በአዲሱ የወንጀል አንቀጽ 257/ሀ ስር የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል ሆኖም የእዚህ አንቀጽ ቅጣቱ ጣሪያ ከ10 ዓመት ጽኑ እስራት የማይበልጥ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ቁጥር 161/2/ሀ መሰረት ተከሳሹ በሌለበት ፍርድ መስጠት አይቻልም ምክንያቱም ተከሳሹ የፈጸመው ወንጀል ከ12 ዓመት ጽኑ እስራ በታች ሊያሳስር የሚችል ወንጀል በመሆኑ ነው በመሆኑም ተከሳሹ ላይ የቀረበው ክስ ለጊዜው አቋርጠነዋል፡ 62ኛ ተከሳሽ አረጋዊ በርሄን በተመለከተ ዐቃቢ ህግ ያቀረበው ማስረጃ የካቲት 26 ቀን 1997 ዓ.ም ታትሞ በወጣው አባይ ጋዜጣ ተከሳሹ ድርጅቱን በመወከል የሰጠው መግለጫ ሲሆን ይኸውም ሕዝቡ ኢህአዴግን መልሶ ወደ ስልጣን የሚያወጣ የምርጫ ሂደት መሳተፉን አቁሞ ይህ አፋኝ አገዛዝ የሚወገድበትን ሰላማዊ ሕዝባዊ አመጽ እንዲነሳ መቀሰቀስ ማደራጀት እና መምራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጾአል የጽሑፉ ሂደት ሲታይ ሕዝቡ በመንግስት ላይ እንድያምጽ የሚያነሳሳ ሲሆን ይሄም ማነሳሳት የተፈጸመው አዲሱ የወንጀል ህግ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ስለሆነ ተፈፃሚነት የሚኖረው በ1949 ዓ.ም የወጣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 269/ሀ ነው ይህም ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል



Scanned by CamScanner

ወንጀል ስላልሆነ ተከሳሹ [illegible] [illegible] [illegible] አይቻልም በመሆኑም በተከሳሹ ላይ የቀረበው ክስ ለጊዜው አቋርጠነዋል። ከእዚህ በመቀጠል በ91ኛ ተከሳሽ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት እና በ93ኛ ተከሳሽ ክፍሌ ሙላት ላይ ዐቃቢ ህግ ያቀረበው ክስ እና ማስረጃ ከህጉ አኳያ መርምረነዋል በመጀመሪያ በተከሳሾቹ ላይ የቀረበው ክስ ተከሳሾቹ በ1ኛ ክስ ከ1ኛ እስከ 39ኛ የተጠቀሱት ተከሶሾች የወንጀል አድራጉት እና ሃሳብ የራሳቸው በማድረግ የሚወክሉትን ማህበር ከተመሰረተ አላማ እና ተግባር ወጭ በመቀስቀስ ለእዚህ ወንጀል ማስፈጸሚያ እና መጠቀሚያ በማድረግ በማህበራቱ ስም ውሳኔ በማሳለፍ መግለጫ በማውጣት በመቀስቀስ የማህበሩ አባላቶች የአመጽ ተግባሩን እንዲገፉ በማነሳሳታቸው እና አመራር መስጠታቸው ወጣቶች የአመጽ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በመደገፋቸው እና በመገፋፋታቸው ተከሰዋል የሚል ነው 91ኛ ተከሳሽ በተመለከተ የቀረበው ማስረጃ ስንመረምረው የኢትዮጲያ መምህራን ማህበር 16ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከሐምሌ 25 እስከ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ተካሂዶ ጉባኤው ውሳኔ እና የአቋም መግለጫ ያወጣ ሲሆን በመግለጫውም በቅድመ ምርጫ በምርጫው እና በድህረ ምርጫው መላው የኢትዮጲያ ሕዝብ ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት የከፈለው መስዋትነት ከንቱ የሚያደርግ በምርጫው ማግስት በገዢው ፖርቲ እና እራሱ ለእራሱ ሲል ባዋቀረው ምርጫ ቦርድ አማካይነት የመራጩን ሕዝብ ድምጽ መሰረቁ አግባብ አለመሆኑን የገለጸ ሲሆን በሌላ በኩል ተከሳሹ በጋዜጦቹ ላይ በሰጠው ቃለ ምልልስ መረዳት የሚቻለው ተከሳሹ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዝዳንት መሆኑን ምርጫው ወያኔ ለእራሱ ብሎ የፈጠረው አጀንዳ እንጂ እውነተኛ ምርጫ በወያኔ እንደማይሰራ ሕዝቡ በዚህ ሁኔታ ለዘለአለም መቀጠል እንደሌለበት እና ተስፋ ሳይቆርጥ ትግሉን መቀጠል እንዳለበት ሕዝቡ ባለበት የፍትህ ተቋማት ነፃ ማድረግ እንዳለበት ኢፍትሐዊ ነገሮች ሲሰሩ ማቆም እንዳለበት ሕዝቡ አልመረጥኩም አታስተዳድረኝም ብሎ ማለት መቻል እንዳለበት ማለትም መጀመሩን ሕዝቡ ያለውን አስከፊ ስርዓት ለውጦ የተሻለ ሕይወት ለመገንባት ትግሉ በተቻለ ሁኔታ መቀጠል እንዳለበት ምርጫ ቦርድ የተበላሸ መሆኑን ሕዝቡ የመረጣቸው ፖርላማ እንዲገቡ እንጂ ገዢው ፖርቲ የመረጣቸው ፖርላማ በማስገባት አስመሳይ ግለሰቦች 5 ዓመት

እንዲቀመጡ አለመሆኑን ገልጾአል ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው ተከሳሹ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ገዢው ፓርቲ የሕዝቡ ድምጽ ሰርቀዋል ስርዓቱም አስከፊ ነው በማለት እና ስርዓቱ የሚለወጥበት ዘዴ ለሕዝብ በግልጽ ሕዝቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳ ቀስቅሰዋል ተከሳሹ ይህንን ቅስቀሳ ያካሄደው በጋዜጣ ውስጥ በአመንጭነት ስለሆነ በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 44 መሰረት አመንጭው በአዋጁ አንቀጽ 238 መሰረት በወንጀል ሊጠየቅ አይችልም በመሆኑንም ዐቃቢ ህግ በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ማስረጃ ከህጉ አንፃር ተገናዝቦ ሲመዘን የተከሳሹ የወንጀል ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 257/ሀ ስር የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል ሆኖም የእዚህ አንቀጽ የቅጣት ጣሪያ ከ10 ዓመት ጽኑ እስራት በላይ ሊያስቀጣ የማይችል ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ቁጥር 161/2/ሀ ስር ተከሳሹ በሌለበት ፍርድ መስጠት ስለማይቻል በተከሳሹ ላይ የቀረበውን ክስ ለጊዜው አቋርጠነዋል፡፡ 93ኛን ተከሳሽ ክፍሌ ሙላቱን በተመለከተ ዐቃቢ ህግ ክሱን ለማስረዳት ግንቦት 29 እና 26 ቀን 1997 ዓ.ም የወጡ ሁለት የልሳነ ሕዝብ ጋዜጦች እና ሚያዝያ 27 ቀን 1997 በወጣው የኢትዮጵ ጋዜጣ ተከሳሹ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ለኢትዮጲያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች እና ለቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ያስተላለፋትን ጥሪ በማስረጃነት አቅርቧል የቀረበው ማስረጃ ዐቃቢ ህግ ከመሰረተው ክስ አንፃር ሰታይ ተከሳሹ በኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር ሊቀመንበርነቱ ጥሪ ያቀረበው ሚያዝያ 7/97 በወጣው የኢትኦጵ ጋዜጣ ሲሆን በዚህም ጥሪው ተከሳሹ የቅንጅትን አንድነት እና ዲሞክራሲ እንዲሁም የኢትዮጲያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረት ደጋፊ መሆኑን መግለጹን ከማሳየት ውጭ ተከሳሹ ወንጀል ስለመፈጸሙ የሚያስረዳ አይደለም በሌላ በኩል ዐቃቢ ክሱን ለማስረዳት በተከሳሹ ዋና አዘጋጅነት የወጡትን ጋዜጦች በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም ዐቃቢ ህግ ተከሳሹን የከሰሰው በጋዜጣ ዋና አዘጋጅነት ሳይሆን ተከሳሹ የሚመራው ማህበር ወንጀል ለመፈጸም መጠቀሚያ አድርጎታል የሚል ሲሆን ይህንን ደግሞ በዐቃቢ ህግ ክስ አመሰራረት መረዳት ይቻላል ከእዚህ በተጨማሪ በጋዜጦቹ ላይ በወጡ ጽሑፎች ተከሳሹ የኢትዮጲያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር በመወከል የሰጠው መግለጫ የለም ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የጋዜጦቹ ይዘት ይመርመር ቢባል እንኳን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 161/2/ሀ መሰረት ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ የሚያስችል ማስረጃ አይደለም በመሆኑም ዐቃቢ ህግ ከመሰረተው ክስ



Scanned by CamScanner

እንዛር ክሱን የሚያስረዳለት ማስረጃ ያላቀረበ ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት 163 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 149 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ተከሳሹ በሌለበት በነፃ እንዲሰናበት ፍ/ቤቱ ወስኖአል::

- የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል

## ት ዕ ዛ ዝ

- 1ኛ ክስ ላይ ብቻ ተከሳሽ ሆኖ የቀረበው ካሳሁን ከበደ ከክሱ በነፃ የተሰናበቱ ስለሆነ ሌላ በሌሎች ክሶች ደግሞ በተከሳሽነት ያለቀረበ ስለሆነ በዛሬው እለት ከማረሚያ ቤት እንዲወጣ የመፍቻ አራንት ይፃፍ ብለን አዘናል:: ሌሎች ተከሳሾችን በሚመለከት በበርካታ ክሶች የተከሰሱ በመሆኑ ሌሎችን ካየን በኋላ የምንሰጠው ትዕዛዝ ይሆናል ማለት ነው ስለዚህ እንደ ከእዚህ ቀደሙ ከሰዓት አንሰየምም ሰኞ ነው የምንሰየመው ሰኞ ከጠዋቱ 4:00 ላይ:: ንግስት ምንድነው?

- ክቡር ፍ/ቤቱ እንደሚያስታውሰው ቀደም ሲል በልጆቼ ላይ በደረሰው ችግር ምክንያት ፈቃድ ጠይቄ ለማረሚያ ቤቱ በተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት እየሄድኩ ስጠይቅ እና ሳሳክም ቆይቻለሁ በመጨረሻ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ግን ግልባጩ ለእኔ ያልደረሰ በመሆኑ እና በማረሚያ ቤት ጽ/ቤት በኩል የሄደ በመሆኑ መቼ እንደሚያበቃ ባለማወቄ ምክንያት በየካቲት 12 ቀጠሮ ላይ ሳልጠይቅ አልፎኛል አሁን ደግሞ በትላንትናው ብይን ምንም ማስረጃ በእዚህ ችሎት ላይ ባልቀረበብኝ ሁኔታ ይሄ በዚህ እንዳለ አሁን ክቡር ፍ/ቤቱን ልጠይቅ የፈለኩት በተለይ የ1ኛ ልጄ የጤንነት ሁኔታ ወደ ኋላ እየተመለሰ ስለሆነ ቀጣይ ትዕዛዝ እንዲሰጥልኝ እጠይቃለሁ::



Scanned by CamScanner

የመዝገብ ቁጥር 43246

ሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም

2ኛ ወ/ችሎት

ዳኞች:- አዲል አህመድ

ልኡል ገ/ማርያም

መሃመድ አሚን ሳኒ

ከሳሽ............ ፌዴራል ዐ/ሕግ ሽመልስ ከማል ሚካኤል ተክሉ አብርሃም

ተጠምቀ ቀርበናል

ተከሳሾች............እነ ኢ/ር ሐይሉ ሻወል በተከሰሱበት መዝገብ ሁሉም ተከሳሾች ቀርበዋል የነፃነት እና ዳንኤል ጠበቃ ክ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም

- እርሶ ማንን ወክለው ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ወክዬ ነው የቀረብኩት ክቡር ፍ/ቤቱ ደንበኛዬ እንዲፈታ ያዘዘበትን ደብባቤ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ለዘጠኝ አምስት ጉዳይ ሐሙስ ለዕት ያዘዘበትን ደብባቤ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ለዘጠኝ አምስት ጉዳይ ሐሙስ ለዕት አድርሻለሁ መዝገቡ ጋር ተያይዟል ከዛ ውጪ ጠብቁ ተባልኩኝ መኪና ሰርቪስ ለመስጠት አቅጀ ስለነበረ ከባለቤትዬዋ ጋር ደጃፍ ላይ 12 ሰዓት ከርቡ ድረስ ቆይቼያለሁ መጨረሻ ላይ አንድ ፖሊስ መተው በሌላ መዝገብ ስላለባቸው ያንን ክሊር ሳናደርግ ልንፈታ አንችልም አራንት የተቆረጠባቸው በሌላ መዝገብ ነው አሉን ያንንም መዝገብ አሳዩን በዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ሦስት በደል ፈፅሞብኛል የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት መጀመሪያ ይሄ ተግባር በጊዜ ቀጠሮ የተከፈተው መዝገብ ተዘግቶ ይሄ መዝገብ መከፈቱን ያውቃል ይሄንን እንደ ማረሚያቤትነቱ ዱዲሻል ዱቲስ መውሰድ ነበረበት ይሄንንም እንኳን ማረግ ባይችል ደንበኛዬ ሁለት መዝገብ እንዳለበት ካወቁ ከመጀመሪያውኑ ያ የመጀመሪያው መዝገብ ምን ላይ ደረሰ ብሎ ከፍ/ቤቱ ጋር ተነጋግሮ አንድ እልባት መስጠት የነበረበት ነገር ነው ሦስተኛው እኔ እራሴ ጊዜ ነበረኝ ተመልሼ ፍ/ቤት ይሄን ነገር ክሊር አርጌ ለማውጣት በጣም ብዙ ጊዜ ነበረኝ ምክንያቱም እስከ 11 ሰዓት 30 እኔ ለዘጠኝ ሰዓት አምስት ጉዳይ ነው እዛ የደረስኩት ተመልሼ ኢሸን ያንን ትዕዛዝ ክሊር አርጌ ማውጣት እችል ነበር በዛን ምክንያት ነፃ የወጣ ሰው የተከበረው ፍ/ቤት አይደለም አራት ቀን አራት ደቂቃ መታሰር ለሂሊና የሚከብድ ሰው አራት ቀን ሙሉ ያለ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እና እውቅና ታስሮብኛል ይሄን ለማመልከት ነው የመጣሁት፣ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት::



Scanned by CamScanner

- የካሣሁን ክበደ ጠበቃ ናቸው ስሞትን አላስመዘገቡንም ስለዚህ የካሣሁን ጠበቃ ከዚህ በላይ ያለውን አመልክተዋል ለማንኛውም ወደ መጨረሻ እምነለው አለን፣ መዝገቡ ያደረው የተጀመረውን ብይን ማሰማት ለመቀጠል ነው በዚሁ መሠረት ካቆምንበት ማለትም ከ70 እስከ 90ኛ ያሉትን ተከሣሾች የሚመለከት ማሰማቱን እንቀጥላለን
- ዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ መሠረት 70ኛ እስከ 90ኛ ድረስ የተጠቀሱት ተከሣሾች የተለያዩ ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅቶች፤ የጋዜጣው ዋና አዘጋጆች፤ ምክትል ዋና አዘጋጆች፤ የጋዜጣ ባለቤቶች እና ስራአስኪያጅ መሆናቸውን ከክሱ መረዳት ይቻላል:: በነዚህ ተከሣሾች ላይ ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ክሱን አስረድተዋል ወይስ አላስረዱም? የሚለውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ህጉ ምን ይላል የሚለውን ጠቅለል ባለ መልኩ መጀመሪያ መመልከቱ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን:: በዚህም መሠረት በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 42 እስከ 47 ድረስ ያሉት አንቀጾች በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የሚደረጉ ወንጀሎች ተካፋይ መሆንን የሚመለከቱ ናቸው:: የነዚህ የወንጀል ህግ አንቀጾች አስፈላጊነትም በአንድ በኩል የሐሣብ መግለፅ ነፃነት ለመጠበቅ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሐሣብን የመግለፅ ነፃነት ከመጠን እንዳያልፍ ለማገድ ነው:: በኤፌዲሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 29 መሠረትም የአመለካከት እና ሐሣብን በነፃ የመያዝ እና የመግለፅ መብት ተረጋግጧል:: በዚህ ውስጥ የፕሬስ እና የሌሎች የመገናኛ ብዙኃን ነፃነትም ተካቷል የዲሞክራሲ ስረዓት በሚከተሉ ሐገሮች ነፃው ፕሬስ በተለይ ገገርው ፖርቲ በህዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት በሚወጣበት ጊዜ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች ለይተው ስህተቶቹ እንዲስተካከሉ ገንቢ የሆኑትን ትችቶችን በመስጠት የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታው እንዲጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: በመሆኑም በአንድ ሐገር ነፃ ፕሬስ ከሌለ በዛች አገር ዲሞክራሲ የለም እስከማለትም ተደርሷል:: ነፃው ፕሬስ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ነፃ እና ገለልተኛ መሆን መቻል አለበት:: ነፃ ፕሬስ ነፃ መሆኑ ቀርቶ ወገንተኛ ከሆነ ከአገር ጥቅም ይልቅ ለአንድ የፖለቲካ ፖርቲ የወገነ ከሆነ በአንድ አገር የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አወንታዊ ሚና ከመጫወት ይልቅ አሉታዊ ሚና ይጫወታል ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የሚያስከትለው ውጤት የሚታወቅ ስለሆነ መዘርዘር አያስፈልግም:: በመሆኑም ነፃው ፕሬስ ሲያሻው ነፃ የሚሆን ሲያሻው ደግሞ ነፃ የማይሆን ሳይሆን በምንም መልኩ ነፃ የመሆን ግዴታ አለበት:: ከዚህም

ጋር በተያያዘ መልኩ ነፃ እና ገለልተኛ ተብለው የተቋቋሙ አካላት ወይም ተቋማት በሙሉ ነፃ የመሆን መብት ሳይሆን ነፃ የመሆን ግዴታ ያለባቸው መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም:: ምክንያቱም ነፃ የመሆን መብት የተሰጣቸው ከሆነ በዚህ መብታቸው ሲፈልጉ ይጠቀሙበታል ካልፈለጉ ደግሞ መብታቸው ነውና አይጠቀሙበትም ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ነፃ እና ገለልተኝነታቸውን ያሳጣዋል ሐሣብን የመግለፅ ነፃነት በኤፌዲሪ ህገ መንግሥት ሆነ በወንጀል ህግ ውስጥ እንደተመለከተው የተወሰኑ ገደቦች ያሉበት መሆኑን ይገልፃል:: ይህ ገደብ በኢትዮጵያ ህጎች ብቻ ያለ ሳይሆን በዲሞክራሲ ስረዓት ግንባታ ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል በተባሉ ሐገሮችም ጭምር ያለ ጉዳይ ነው:: ሆኖም ሐሳብን የመግለፅ ነፃነት ገደብ ከሐገር ሐገር ሊለያይ ይችላል:: በአንድ አገር ህግ አላስፈላጊ የሆነ ሐሣብን የመግለፅ ነፃነት ገደብ አለ ከተባለም በዚሁ ጉዳይ የህግ ጥናት እና ምርምር በማድረግ ተገቢ ማስተካከያ ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው:: ይህንንም ከግብ ለማድረስ የህዝብ እና የባለድርሻዎች ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ነው በመገናኛ ብዙሐን አማካኝነት የሚደረጉ ወንጀሎች በጋዜጦች፣ በመፅሐፍት፣ በበራሪ ፅሑፎች፣ በመፅሔቶች፣ በሚለጠፍ፣ ወረቀቶች፣ በስዕሎች፣ ወይንም በሲኒማ፣ በሬዲዮ፣ ወይንም በቴሌቪዥን ስርጭት ወይንም በማናቸውም ሌላ የህዝብ መገናኛ በመሆን ዜዴ የሚደረጉ ናቸው:: ወንጀሉ የተደረገው በነዚህ አማካኝነት በወሆነ ጊዜ የሰውን ክብር በመንካት ብቻ ሳይሆን የግልን ወይም የጋራ ደህንነት በማደፍረስ እና በወንጀል ህግ ተከብሮ የሚኖረውን ማናቸውንም ህጋዊ መብት መንካት እንደሚጨምር በወንጀል ህግ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 3 በግልፅ ተመልክቷል ሆኖም አንዳንድ የህግ ባለሞያዎች በመገናኛ ብዙሐን አማካኝነት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ደንበኞቻቸው በመወከል በሚያቀርቡት ክርክር የወንጀል ህግ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 3 በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ወደ ጎን በመተው በደንበኞቻቸው ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 34/85 ላይ የተደነገጉት አንቀጾች ብቻ መሆን ይገባቻዋል በማለት ይከራከራሉ:: ይህ ክርክር ከወንጀል ህግ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 3 አንፃር ሲታይ ተገቢነት ያለው ክርክር አይደለም ምክንያቱም በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የሚደረጉ ወንጀሎች በወንጀል ህግ ተከብሮ የሚኖረውን ማናቸውንም ህጋዊ መብት መንካት እንደሚጨምር ንዑሳን ተገልጿል:: በማስከተልም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 43 ስር በተደነገጉት አንቀጾች ወስጥ በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት በሚፈፀም ወንጀሎች ያለው ኃላፊነት በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1 ስር በየጊዜው የሚወጣ የህትመት አማካኝነት የሚፈፀም ወንጀል የሚያስከትለው ኃላፊነት በቅደም ተከተል ተገልጿል:: በዚህም መሠረት በቀዳሚነት ኃላፊነት ያለበት የፕሬሱ ውጤት ሲታተም በዋና አዘጋጅነት የተመዘገበ ሰው ነው:: ከዚህ መረዳት



አዘጋጅነት ወይንም በምክትል ዋና አዘጋጅነት

የሚቻለው ለምሣሌ በየጊዜው የሚወጣ ጋዜጣ የህትመት ውጤት ሲታተም በዋና አዘጋጅነት ሲሰራ የነበረ ሰው ተጠያቂ ከሆነ ምክትል ዋና አዘጋጁ እና ሌሎቹ ተጠያቂ ከመሆን ይድናሉ ማለት ነው። በንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገው ደግሞ የፕሬስ ውጤት በየጊዜው ከሚወጣ ህትመት ውጪ የሆነ ሌላ የህትመት ስራ ሲሆን የደራሲው ስም በህትመቱ ላይ የተገለፀ ከሆነ ደራሲ በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህም ማለት ደራሲው በኃላፊነት ከተጠየቀ ሌሎቹ በኃላፊነት ተጠያቂ አይሆኑም ማለት ነው። በሌላ በኩል የዚሁ ህግ አንቀጽ 46 እንደሚከተለው ይነበባል በህግ ላይ በተደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት ከኃላፊዎቹ አንዱ ከተቀጣ በዚሁ ድርጊት ምክንያት ሌሎቹ ከኃላፊነት ውጪ ሆነው ከቅጣት ይድናሉ ካለ በኃላ ቢሆንም ማናቸውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት በየትኛውም ቅደም ተከተል ከተመለከተው ወንጀል አድራጊ ጋር በተደራቢነት ወይንም በተናጠል በወንጀል ተጠያቂ ከመሆን አይድንም ይላል። ለምሣሌ በአንድ ጋዜ ላይ የወጣው የህትመት ውጤት ህገወጥ ይዘት ያለው ከሆነ በህግ ላይ በተደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት ከኃላፊዎቹ አንዱ ከተቀጣ ከዚሁ ጋር በተጨማሪነት ሊቀጣ የሚችለው የጋዜጣው አሳታሚ ድርጅት መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሆኖም በአንድ የጋዜጣዊ ህትመት ውጤት ይዘቱ ህገወጥነት ያለ በመሆኑ በወቅቱ በዋና አዘጋጅነት የነበረ ሰው ከተቀጣ በዚህ ወንጀል ምክትል ዋና አዘጋጁ ሊቀጣ እንደማይችል ከህጉ መረዳት ይቻላል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ ዐ/ሕግ የመሰረተውን ክስ እና ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸውን መረጃዎችን አግባብነት ካለው ህግ ጋራ አገናዝቦ ከመረመረ በኃላ 70ኛ እስከ 90ኛ ድረስ የተከሰሱት ተከሣሾች በተመለከተ ለብይን አሰጣጥ ያመች ዘንድ በስድስት ምድብ ከፍሎ ክስ እና ማስረጃውን መርምሯዋል። የመጀመሪያው ምድብ 73ኛ ተከሣሽ ሲሳይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት፤ 75ኛ ተከሣሽ አንዱአለም አየለ፤ 87ኛ ተከሣሽ መስፍን ተስፋዬ፤ 83ኛ ተከሣሽ ዘካሪያስ አሳታሚ፤ 85ኛ ተከሣሽ አብይ ግዛው፤ 79ኛ ተከሣሽ ዘላለም ገብሬ እና 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት የሚያካትት ነው። በነዚህ ተከሣሾች ላይ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ማስረጃ እንደሚከተለው መርምረነዋል ይሄውም 73ኛ ተከሣሽ ሲሳይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ማለትም የኢ.ዮጵ ጋዜጣ አሳታሚ እና 75ኛ ተከሣሽ አንዱአለም አየለ፤ የኢ.ትዮጵ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ስንመረምራቸው ዐ/ሕግ ያቀረባቸው የኢ.ትዮጵ ጋዜጣ ህትመት ውጤቶች

በሙሉ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ አዱአለም አየለ፣ የጋዜጣው አሳታሚ ደግሞ ሲሳይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት መሆናቸውን በግልፅ ያስረዳል:: ከጋዜጠኛ ጊደት የተገኘውን ማስረጃ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሳይፈርስ ነፃ ምርጫ ያለመኖሩን በምርጫው ኢህአዴግ ሌብነት መፈፀሙን ቅንጅት እና ህብረት ግን በምርጫው ማሸነፋቸውን:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ዘራፊዎች በተሰበሰቡበት ፍ/ቤት ፍትህ እንደማይኖር:: ድምፅ የተቀማው ህዝብ ኢህአዴግን በቸልታ የማይመለከተው መሆኑን ምርጫው ተጭበርብሮ ከቀጠለ የተቃውሞ ኃይላት የዩክሬንና እና የጆርጂያ ህዝባዊ ማዕበል እንደሚቀሰቅሱ መናገራቸውን:: ኢህአዴግ ቤተመንግሥቱን ለተረኛው እንዲለቅ ማስገደድ እንደሚገባ ቤተመንግሥቱን አለቅም ካለ ሰላም መታወክ እንደማይቀር:: የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አስጨንቆ ለመጣለ ፍቱሁን መንገድ፣ የስራ ማቆም አድማ፣ ሰልፍ፣ እንቢ አልገዛም፣ የርሐብ አድማ፣ አድማ፣ አድማ፣ በአገዛዙ የንግድ ተቋማት ላይ ማእቀብ ማድረግን እንደተግል ስልት ማቅረቡን ከዚህ በተጨማሪ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ፍ/ቤትን ጠራርጐ ማስወገድን የሚቻለው በብሔራዊ አንድነት መንግሥት መሆኑን ጭምር ገልፀዋል:: በሌላ በኩል 87ኛ ተከሣሽ መስፍን ተስፋዬ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች መርምረን መርምረናቸዋል:: ከዚህ አንፃር ይህ ተከሣሽ የአባይ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ መሆኑን ከቀረቡት ማስረጃዎች መረዳት ችለናል ይህ ተከሣሽ በዋና አዘጋጅነት በሚመራው ጋዜጣ ላይ የወጡት ፅሑፎቹን ይዘት ስንመረምር ዘንድሮ ወደ ምርጫ ሲገባ ኢህአዴግ ምርጫውን አያጭበረብርም በሚል በሙሉ እምነት ሳይሆን በተጭበረበረ ምርጫ አሸነፍን በሚሉ ሰዎች ላለመገዛት እና ወደ ህዝባዊ አመፅ ለመሸጋገር የህዝቡ መነሳሳት ትልቅ ትርጉም ስለሚኖረው መሆኑን ምርጫው ከተካሄደ በኃላ ምርጫው ተጭበረበረ ማለቱን ድምፅ ተቆጥሮ ባላለቀበት አካባቢ ተቃዋሚዎች ማሸነፋቸውን እና ኢህአዴግ ኮሮጆ እየሰረቀ እና እየገለበጠ አሸናፊነቱን ማወጅ እንደማይችል መግለፁን ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆኑ እና ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ መቀበል ጨርሶ የሚታሰብ አለመሆኑ ማስረዳቱን በቦርዱ ውሳኔ ባለመስማማት ወደ ፍ/ቤት መሄድ ችግር መፍታት ሳይሆን ችግርን የሚያወሳስብ መሆኑን ኢህአዴግ ሰላማዊ እና ህጋዊ የስልጣን ሽግግር መንገድ መዘጋቱን እና ሐገሪቱን ወደ ሌላ ዙር ትርምስ ምስቅልቅል ሁኔታ እየገፋት ያለ መሆኑን ብጥብጥ እና ትርምስ እንዳይነሳ ከፈለገ ኢህአዴግ ለሕዝብ ፍላጐት ተገዢ መሆን እንዳለበት በህዝብ ድምፅ አደጋ ላይ የወደቀውን ወንበር በጉልበት እና በመሣሪያ ጋጋታ ጠግኖ ለማቆየት የሚደረግ ሙከራ ከንቱ መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ ኢህአዴግ ቡድን በተለይ አቶ መለስ እና በረከት ሁሉም እንደ ክ/ል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም እንደማይቀናው አምነው አሸናፊ



Scanned by CamScanner

ቡድን ለተሸነፈው ቡድን ያቀረበለትን የብሔራዊ አንድነት መንግሥት መቀበል እንዳለበት እና ከቃሊቲ ኑሮ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት የሚሻል መሆኑን ገልፀዋል:: በማስከተልም ድምፅ የተነጠቀው ህዝብ በብረት የማይቆም እንደሆነ በብረት መመካት ብረቱ በወሳኝ ሰዓት ወደአነጣጣሪ እንደሚዞር አላማስተዋል እንደሆነ በነፃ ምርጫ ያልተገኘ ስልጣን በህዝባዊ አመፅ እንደሚረጋገጥ በዚህ ጊዜ ህዝባዊ ስልጣን የሚመነጨው በህዝብ አመፅ ብቻ እንደሆነ እና በተጭበረበረ ምርጫ ኢህአዴግ አሸናፊነቱን የሚያውጅ ከሆነ በዩክሬን እና በጆርጂያ የታየው ህዝባዊ መአበል በኢትዮጵያ ሊደገም እንደሚችል ከምርጫው ቅስቀሳ ጐን ለጐን ህዝቡ በዚህ አረገድም መዘጋጀት እንደሚጠበቅበት እና የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን በምርጫው ካልተቀናጀ ህዝቡ ባለሐገርነቱን በህዝባዊ አመፅ እንደሚያውጅ በህዝባዊ አመፅ የኢህአዴግ አገዛዝ እንዲወገድ ለማድረግ ህዝቡን መቀስቀስ ማደራጀት እና መምራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል በማስከተልም ዐ/ሕግ 83ኛ ተከሣሽ ዘካሪያስ አሳታሚ እና 85ኛ ተከሣሽ አብይ ግዛው ላይ ማስረጃ አቅርቧል ከማስረጃው መረዳት የሚቻለው የነፃነት ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አብይ ግዛው፣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ደረጀ ኃብተ ወልድ፣ የጋዜጣው አሳታሚ ደግሞ ዘካሪያስ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ነው:: የጋዜጣው ይዘትም የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች ወገኝነታቸው አጉልቶ የሚያሳይ መልኩ መራመዳቸውን ምርጫውን እንዲያስተባብሩ እድል የተሰጣቸው የቦርዱ ሰብሳቢ እና ኃላፊዎች ምርጫውን የተበላ እቁብ ማድረጋቸውን ኢህአዴግ በጠመንጃ ቢመካ ተቃዋሚዎች ደግሞ በህዝባቸው ሊመኩ እንደሚገባ ህገመንግሥቱ ይበጀናል ብለው ሊያስከብሩት ቆርጠው እስካልተነሱ ድረስ ህገመንግሥቱ መታፈር እና መከበር ቀርቶ የመመሪያ ደብተር ላይ የተፃፈ የህግ ትምህርት ማስታወሻ ሆኖ እንደሚቀር ቅንጅቱ ለምርጫ ቦርድ ያቀረበው ጥያቄ ቦርዱ መልስ ካልሰጠበት ቅንጅቱ ይህንኑ ለማስፈፀም የሕዝ ማቆም አድማ ወዘተ ሰይሚ? ፕሪ እንደሚያቀርብ ህዝቡ ያለገደብ ለፓርቲ ፓርቲ ጥያቄ እንደማያቀርብ እና ገዢው ፓርቲ መልስ ባለመስጠቱ [illegible] መብቱን ለማስከበር እንደሚነሳ ህዝቡም መብቱን ለማስከበር ሲነሳም ቀላል የማይባሉት ችግሮች ሁከት እና ብጥብጦች እንደሚነሱ በዚህ [illegible] ተጠያቂው መንግሥት እንጂ መብቱ ለማስከበር የተነሳው ህዝብ [illegible] አለመሆኑን በአዲስ ዓመት ህዝቡ በተሰናባቹ ዓመት የተረሸነውን [illegible] ጋር የመሩለም ትግል የሚገፋበት በተጭበረበረ ክንድ አብሮነታችን [illegible] እንዳይኖሩ የማያደርግበት እና መብ የሚፈልግበት እንጂ [illegible]

ራ የሚያጣጥምበት ጊዜ አለመሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአፉ መለስ እና ንተፍናፊቻቸው አምስት ዓመት ቀርቶ አምስት ወራት ለመኖር ትግስት እና ፍላጎት ኔለው መሆኑን የህዝብን ድምፅ ለማስከበር በቁርጠኝነት መነሳት ለነገ የሚባል ራጣኝ እርምጃ ከሁሉም የፓርቲ አመራሮች እንደሚጠበቅ ህዝቡ በተጠናከረ ትግል ዘውን ፓርቲ ከወንበሩ ለማንሳት እስካሁን ከከፈለው የባሰ መስዋእትነት መክፈል ንደሚጠበቅበት እና ሐገርን ከውድቀት ለመታደግ መንገዱ አልጋ በአልጋ ሳይሆን ዙ መስዋእትነት የሚጠይቅ በመሆኑ ህዝቡ ለዚሁ መስዋትነት እራሱን ማዘጋጀት ንደሚጠበቅበት የሰጠው ማሳሰቢያ በመረጃነት ቀርቧል በተመሳሳይ መልኩ ዐ/ሕግ ኛ ተከሣሽ ዘላለም ገብሬ እና 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ላይ ቀረበው መረጃ ይዘት ስንመረምረው የሚኒሊክ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ዘላለም ገብሬ ጋዜጣው አሳታሚ ደግሞ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት መሆኑን ተረድተናል ጋዜጣው ይዘትም ምርጫ ቦርድ የገዢው ፓርቲው ወገን መሆኑን ተቃዋሚዎች ምርጫ ቦርድ ውጤትን ባለመቀበል ወደ ቀጣዩ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ትግል ሄዱ እንደሚችሉ እና ይህም መብታቸው መሆኑን የምርጫ ቦርድ ውጤት ሚያመጣው መሠረታዊ ለውጥ አለመኖሩን የህዝብ ድምፅ ካልተቀማ በስተቀር ዢው ፓርቲ አሸንፏል የሚባል ውጤት ሊኖር እንደማይችል ቅንጅቱ አሸነፍኩ ል እንደሚያምርበት ኢህአዴግ ግን ዘረፋ ማካሄዱን ህዝቡ ገዢው ፓርቲ ልችቶኛል ማለቱ ተዘግቧል ከዚህ በተጨማሪ ምርጫ ቦርድ በእውነተኛ ማስረጃ ወሰነ ሰላማዊ ስልጣን ሽግግር እንደሚደረግ የማይወሰን ከሆነ ግን የህዝብን ተቃውሞ የሚያስነሳ እና የግድ በሰላማዊ ትግል እና ግፊት ይህ ስልጣን መደምደሙ እንደማየቀር፡፡ ገዢው ፓርቲ ወይ በሰላም ወይንም በህዝብ ግፊት ስልጣኑን እንደሚለቅ በሌላ በኩል የተለያየ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚወክሉት ከአንድ ንመት ለማይበልጥ ግዜ የሚሰራ ጊዜያዊ መንግሥት ለመመስረት አማራጭ መቅረብ እንዳለበት የህዝብ ድምፅ ተቀምቶ ምርጫ ቦርድም ተስማምቶ ውጤቱን የሚገልፅ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፁን የሚያስከብርበት የተለያዩ ህጋዊ እርምጃዎች ማለትም ሰላማዊ ሰልፍ፣ ስራ ማቆም፣ ቤት መዋል፣ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ገዢው ፓርቲ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ፍቃድ የማይሰጥ በመሆኑ ሰልፍ ማድረግ ሲያስፈልግ ሰልፍ እንደሚደረግ ከማሳወቅ በስተቀር ፍቃድ መጠየቅ እንደማያስፈልግ በዚህ አረገድ ቅንጅቱን አመራር እንደሚሰጥ በተጨማሪም ህዝባዊ ትግሉ መካሄድ ያለበት ለአዲስ አበባ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆኖ ኢትዮጵያ በሙሉ ነፃ መውጣት እንዳለባት ገዢው ፓርቲ ደግሞ በመሣሪያ ቢያስፈራራ በየጉሬው እየገባ የሚደበቅ ህዝብ አለመኖሩን ያለመስዋትነት ነፃነት ስለማይገኝ የሰኔ 1 እልቂት ሊደገም እንደሚችል ህዝቡ በሰላማዊ እና ህጋዊ መንገድ



Scanned by CamScanner

የሚል እንዳልሆነ እና ምርጫ ቦርዱም ይሄንኑ መብቱን ለማስከበር ወደኋላ የሚል እንዳልሆነ እና ምርጫ ቦርዱም ይሄንኑ ሁኔታ መለወጥ እንደማይችል የተረጋገጠ ቢሆንም ለጊዜው ለኢህአዲግ አጉል ተስፋ ማስጨበጥ ነው እና ኢህአዲግም የትም እንደማይደርስ መግለፁን ማስረጃው ያስረዳል፡፡ በምድብ አንድ የመደብናቸው ተከሣሾችን በተመለከተ ዐ/ሕግ ያቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረነዋል ከዚህ አንፃር ከዐ/ሕግ ክስ መረዳት የሚቻለው ተከሣሾቹ በዚህ ክስ 1ኛ እስከ 39ኛ የተጠቀሱት ተከሣሾች የወንጀል አድራጐት እና ሐሣብ የራሳቸው በማድረግ ሦስተኛው ዙር ምርጫ ተጭበርብሯል ህዝቡ በአመፅ ድምፁን ማስከበር አለበት በማለት በመንግሥት ላይ ህዝቡ ጥርጣሬ እንዲያድርበት የሐሰት ወሬዎችን በመንዛት ህዝቡን ለአመፅ ቀስቅሷል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ እነዚህ ተከሣሾች በተለይ ከተከሰሱት የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት ጋር ያላቸውን ቁርኝት መረዳት የሚቻለው በላዕላይ ምክር ቤት ተከሣሾች ላይ የቀረቡ ማስረጃ ይዘት እና በምድብ አንድ ስር በተመደቡት ተከሣሾች ላይ ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ይዘት ተገናዝቦ ሲመረመር ተመሳሳይ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ማስረጃውን ስንመረምረው በምድብ አንድ ስር የተመደቡት ተከሣሾች እና እንዲከላከሉ የተባሉት የላዕላይ የምክር ቤት አባላት በሚከተሉት ጉዳዬች ላይ ለህዝቡ የሚገለፁት ሐሣብ አንድ እና ተመሳሳይ ነበር፡፡ ይኸውም ምርጫው መጭበርበሩን፣ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆኑን፣ ምርጫ ቦርድ ለኢህአዲግ ወገን የወገነ መሆኑን፣ ቅንጅት በምርጫው ማሸነፉን፣ ኢህአዲግ የህዝብ ድምፅን መስረቁን፣ የምርጫ ቦርድ ውጤት ተቀባይነት የሌለ መሆኑን፣ የምርጫ ውጤት ቅሬታ ወደ ፍ/ቤት ይዞ መሄድ መፍትሔ እንደማያመጣ፣ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት መመስረት አስፈላጊ መሆኑን፣ የተቀማው የህዝብ ድምፅ ሊከበር የሚችለው በህዝብ ብቻ መሆኑን፣ የተቀማው የህዝብ ድምፅ ለማስከበር የስራ ማቆም አድማ ቤት መቀመጥ፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ አድማ፣ እንዲሁም በጆርጂያ እና በዩክሬን አገሮች የተካሄደው ህዝባዊ ማዕበል በኢትዮጵያ ሊደገም እንደሚችል በመግለፅ እና ገዢው ፓርቲ ከስልጣኑ የሚወገድበትን አቅጣጫዎች በሙሉ የሚያመላክቱ ፅሑፉች እንደነበሩ ከማስረጃዎቹ በግልፅ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት ያለ መሆኑን በብይኑ መግቢያ አካባቢ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ ከዚህ አንፃር በምድም አንድ የተመደቡት ተከሣሾች ማለትም 73ኛ ተከሣሽ ሲሳይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት 75ኛ ተከሣሽ አንዱአለም አየለ፣ 87ኛ ተከሣሽ መስፍን ተስፋዬ፣ 83ኛ ተከሣሽ ዘካሪያስ አሳታሚ፣ 85ኛ ተከሣሽ አባይ ግዛው፣ 79ኛ ተከሣሽ ዘላለም ገብሬ

እና 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ብይን ከተበየነባቸው የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ሐሣብ አድራጎት በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱ የራሳቸው ማድረጋቸው ማስረጃዎቹ ያስረዳሉ:: ማስረጃዎቹም ተከሣሾቹ አዲስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 1 ሀ ለ 38 34 46 27/1 238 1፣2 መተላለፋቸውን የሚያስረዱ ስለሆነ ተከሣሾቹ ይሄንኑ እንዲከላከሉ በማለት በይነናል:: በሌላ በኩል 79ኛ ተከሣሽ ዘላለም ገብሬ እና 85ኛ ተከሣሽ አብይ ግዛውን በተመለከተ በሌሉበት ክሳቸው እየታየ የነበረ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ ቁጥር 163 3 እና 149 3 መሠረት ጥፋተኞች ናቸው በማለት ውሳኔ ወስነናል:: በማስከተልም በሁለተኛ ምድብ የመደብናቸው 70ኛ ተከሣሽ ፋሲል የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት 72ኛ ተከሣሽ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን፣ 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት 78ኛ ተከሣሽ ወናክሰገድ ዘለቀ እና 89ኛ ተከሣሽ ዳዊት ከበደ ሲሆኑ እነዚህን ተከሣሾች በተመለከተ ዐ/ሕግ ያቀረበባቸው ማስረጃዎች እንደሚከተለው መዝግበነዋል:: ይሄውም 72ኛ ተከሣሽ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን እና 70ኛ ተከሣሽ ፋሲል የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ላይ ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ስንመረምረው የአዲስ ዜና ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን፣ የጋዜጣው አሳታሚ ደግሞ ፋሲል የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ነው:: በተከሣሹ ዋና አዘጋጅነት ታትሞ እንዲወጡ የተደረጉ ጋዜጦች ይዘትም የኢትዮጵያ ህዝብ በግልፅ ድምፁን መዘረፉን፣ የምርጫ ቦርድም የዘረፋው ተባባሪ እና አቀነባባሪ በመሆኑ የህዝብ ተቀባይነት ሊያጣ እንደሚገባ የምርጫ ማጣሪያ ሂደት አደጋ ላይ መውደቁን ፓርቲዎች የመረጣቸውን የህዝብ ድምፅ አሰርቀው ወደ ፓርላማ ቢገቡ የህዝብ አሜኔታ ሙሉ በሙሉ እንደሚያጡ እና ኢህአዲግ መቀለጃ ከመሆን እንደማያልፉ አንዳንድ የሚዲያ ሰዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ አባላት ምርጫው መጭበርበሩ እና ኢህአዲግ ድምፅ ሰርቆ መንግሥት ለመመስረት መዘጋጀቱን እና ምንአልባትም ተቃዋሚዎች ምርጫውን ማሸነፋቸውን እንደሚያውቁ ይሄንን እያወቁ ኢህአዲግን ከመተቸት ተቃዋሚዎችን መተቸት እና ጫና አሳድረው የመንግሥት አጃቢ ሆነው ፓርላማ እንዲገቡ ሲወተውቱ ህገወጥ መንግሥት መደገፊ እራሱ ህገወጥ መሆኑን መርሳታቸውን ገና ለገና ሐገር ልትበታተን ነው ደም ሊፈስ ነው በሚሉ ምክንያቶች መንግሥት ከህዝብ በላይ አድርጎ የሚመለከት ስረዓት እንዲፈጠር መተባበር ማንም መንግሥት ከእንግዲህ እንደፈለገ እየተነሳ በምርጫ ስራ በምርጫ ስም እያጭበረበረ በዲሞክራሲ ስም አባገነን ሆኖ እንዲቀጥል መንገድ የሚከፍት መሆኑን ገገርው ፓርቲ አሁን ባለበት የተዘረፈ ምርጫ ተማመኖ ስልጣን ለመያዝ ከደፈረ ሌባ መንግሥት መባሉ እንደማይቀር ገልጿል:: በሌላ በኩል 78ኛ ተከሣሽ ወናክሰገድ



Scanned by CamScanner

ዘለቀ 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅትን በተመለከተ የቀረቡት መረጃዎች ሲመረመሩ የአስኳል ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ሰርካለም ድርጅት ሲሆን የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ማነው የሚለውን ጥያቄ ስንመረምር በዐ/ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ሁለት ዓይነት ነው:: አንደኛው ከማስታወቂያ ሚ/ር የተፃፈ ሲሆን ይህም የሚለው የአስኳል ጋዜጣ ዋና መዘጋጅ ደረጀ በጋሻው መሆኑን ይገልፃል:: ሁለተኛ ማስረጃ ደግሞ በመረጃነት በቀረበበት ጋዜጦች ላይ በጋዜጣው ዋና አዘጋጅነት ስሙ የተመዘገበው የወናክሰገድ ዘለቀ ስም ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ዐ/ሕግ ለችሎት የሰጠው ምላሽ በችሎቱ የሰጠው ምላሽ ከማስታወቂያ ሚ/ር የተፃፈው ደብዳቤ አላማ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ማን እንደሆነ ለመለየት ሳይሆን የጋዜጣው ባለቤት እና ስራ አስኪያጅን ለመለየት የተደረገው ማጣራት የተከሰተ ስህተት እንደሆነ በመግለፅ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ማን እንደሆነ የሚታወቀው በጋዜጣው ላይ በዋና አዘጋጅነት ስሙ የተመዘገበ ሰው ስላለ ይሄንኑ መረጃ በመመልከት መለየት ይቻላል ብሏል:: ተከሣሹም በችሎት ዐ/ሕግ የሚያቀርበውን ክርክር እየሰማ ምንም መልስ ለችሎቱ አልሰጠም ፍ/ቤቱ ይሄንኑ ጉዳይ ሲመረምረው ዐ/ሕግ በማስረጃነት ያቀረባቸው ሁለት የአስኳል ጋዜጦች ላይ ስሙ በዋና አዘጋጅ ላይ የተመዘገበው የወናክሰገድ ዘለቀ ስም በመሆኑ እና የወንጀል ይዘት አላቸው የተባሉትም እነዚሁ ጋዜጦች በመሆናቸው በጋዜጦቹ ላይ በዋና አዘጋጅ ላይ የተመዘገበው ሰው እንደ ዋና አዘጋጅ መቁጠሩ ተገቢነት አለው ብለን እናምናለን:: የጋዜጦቹም ይዘት ስንመረምር ይህዝብ ድምፅ ይከበር የሚሉት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ህዝቡም ጭምር መሆኑ ከዚህ በፊት በፓርላማ የነበራቹሁ መቀመጫ ብዛት አስር ብቻ ነበር አሁን ግን ሁለት መቶ መቀመጫ ያገኛችሁ ስለሆነ ይሄንን እያጣጣማቹሁ አምስት ዓመት ጠብቁ የሚለው ምክር ፌሬሳ ከመሆኑም ህዝብ እና መሣሪያ የሚፋጠጥበት ጊዜ መቅረቡን ገልጾ የህዝብ ድምፅ ለማስከበር አሁኑኑ ጥርስ ነክሶ መታገል አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል:: 89ኛ ተከሣሽ ላይ ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ስንመረምር ተከሣሽ ዳዊት ከበደ የኃዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሲሆን ምክትል ዋና አዘጋጅ ደሞ ፊለቀ ጥበቡ ነው አሳታሚው ደግሞ አረጋዊ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት መሆኑን መረዳት ችለናል:: የጋዜጣው ይዘትም ይህዝቡ ዲሞክራሳዊ መብት መረገጡን:: ምርጫ ቢካሄድም ውጤቱ መጭበርበሩን ህዝቡም በየእለቱ መንግሥት ፍርፋሪ የሚጥልላቸው ሚዲያዎች አማካኝነት ከብሩ የሚያዋርድ መብቱን የሚጋፋ ዘለፋዎች እየወረዱበት

አንዳለ ኢህአዲግ አንድ በፈጣሪ ሁለት በህዝብ ጡንቻ ይመለሳል መባሉን፡፡ ኢህአዲግ በስልጣን ለመቆየት ተስፋ የሌለው እና ይህም በፍፁም የማይታሰብ እንደሆነ ህዝቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንደመረጠ ስለሚያውቅ ያለ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሳትፉ ኢህአዲግ ብቻውን የሚመሰርተው መንግሥት ህዝቡ በፍፁም እንደማይቀበለው በመግለፅ ህዝቡ አንድ ጊዜ ቆርጦ መጓዝ ከጀመረ ወደኋላ ሊመለስ እንደማይችል የተገለፀበት ይገኝበታል፡፡ በምድብ ሁለት የተጠቀሱት ተከሣሾች በጋዜጦቻቸው የህትመት ውጤቱን አትመው ለህዝብ ከማሰራጨታቸው በፊት የህትመቱ ውጤት የወንጀል ህግን የማይተላለፍ ይዘት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህንን ኃላፊነታቸውን ቸል በማለት ህገወጥ ይዘት ያለው የህትመት ውጤት ለህዝብ የገለፁ ከሆነ ከተጠያቂነት አያመልጡም፡፡ ከዚህ አንፃር ተከሣሾቹ በጋዜጦቻቸው ምርጫው ተጭበርብሯል፣ ህዝቡ እና መሣሪያ የሚፋጠጥበት ጊዜ ተቃርቧል፣ የህዝብ ድምፅ ለማስከበር ህዝቡ መነሣት አለበት፣ ህዝቡ ቆርጦ አንዴ ከተነሳ ወደኋላ አይመለስም ወዘተ በማለት ህዝቡ በገዢው ፓርቲ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥርጣሬ እንዲያድርበት እና የምርጫ መጭበርበር ጉዳይን በተመለከተ ህጋዊን ስርዓት ተከትሎ ከመሄድ ይልቅ የተነጠቀውን ድምፅ ህዝቡ እራሱ ማስከበር አለበት ማለት ህዝቡን በከፍተኛ ሁኔታ መቀስቀሳቸውን ማስረጃዎቹ ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም ዐ/ሕግ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተከሣሾቹ 1ኛ እስከ 39ኛ የተጠቀሱት ተከሣሾቹ የወንጀል አድራጊት እና ሐሣብ እራሳቸው በማድረግ በወንጀሉ ድርጊት እና የሚሰጠው ውጤት ተካፋይ ስለመሆናቸው የሚያስረዳ አይደለም፡፡ በመሆኑም ዐ/ሕግ በተከሣሾቹ ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥ/ሥ ቁጥር 113 2 መሠረት በማሻሻል በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 1 ሀ ለ 34 46 እና 257 ሀ ላይ የተመለከተውን መተላለፋቸውን የተረጋገጠ ስለሆነ ይሄንኑ እንዲከላከሉ በይነናል፡፡ በምድብ ሦስት የተመደቡት ደግሞ 81ኛ ተከሣሽ ናርዶስ መአዛ፣ 82ኛ ተከሣሽ ዳዊት ፋሲል እና 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ሲሆኑ ዐ/ሕግ በነዚህ ተከሣሾች ላይ ያቀረበውን ማስረጃ ስንመረምረው በማስረጃነት ከቀረቡት ሁለት ጋዜጦች ውስጥ ነሐሴ 8/97 በወጣው ጋዜጣ የሳተናው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ደረጃ በጋሻው፣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ዳዊት ፋሲል መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን ሐምሌ 10/97 በወጣው ጋዜጣ ደግሞ ዋና አዘጋጁ ታምራት ሰርቤሳ፣ ምክትል ዋና መዘጋጁ ደግሞ ዳዊት ፋሲል መሆኑ ከጋዜጦቹ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ከማስታወቂያ ሚ/ር በቀረበው ማስረጃ ደግሞ የሳተናው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ናርዶስ ማአዛ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሆኖም ዐ/ሕግ በማስረጃነት ባቀረባቸው ጋዜጦች ላይ የተከሣሽ ናርዶስ መአዛ ስም በዋና አዘጋጅነት

ሲለተመዘገበበት ሁኔታ ተከሣሽ የ[illegible]
ሲያሟሟል ተከሣሽ ዋርዳስ መሰየ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ ቁጥር 141 መሠረት በይነናል:: ዐ/ሕግ በሚያሳዩት ባቀረባቸው ጋዜጦች ላይ ስማቸው በዋና አዘጋጅነት የተመዘገቡ ለሥራ ዐ/ሕግ ክስ ያልመሰረተባቸው ስለሆነ ኃላፊነቱ በቀጥታ የሚመለከተው ምክትል ዋና መዘጋጁን ይሆናል:: በዐ/ሕግ ማስረጃነት በቀረቡ የሳተናው ጋዜጣ ጋዜጦች ውስጥ በምክትል ዋና መዘጋጅነት የተመዘገበው የዳዊት ፋሲል ስም ሲሆን ዳዊት ፋሲልም በዐ/ሕግ ክስ ላይ 82ኛ ከሣሽ ሆኖ ተመዝግቧል:: ይህም ማለት የጋዜጣው ይዘት ህገወጥ ከሆነ 82ኛ ተከሣሽ ኃላፊነት አለበት ማለት ነው:: ወደጋዜጦቹ ይዘት ስንገባ ነሐሴ 8 ቀን 1997 ዓ.ም በሳተናው ጋዜጣው የህትመት ውጤት 45ኛው ተከሣሽ ላይ ጭምር በማስረጃነት የቀረበ ስለነበር ይዘቱን ስንመረምረው ህገወጥነት የለውም ብለን ያገኘነው ስለሆነ በነዚህም ተከሣሾች ላይ ማስረጃው የሚያስረዳው ጭብጥ አይኖርም በማለት አልፈነዋል:: ሐምሌ 10 ቀን 1997 ዓ/ም የወጣው የሳተናው ጋዜጣ ይዘት ደግሞ ህዝቡ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድ ከዳር እስከዳር አምርሮ በመነሳት በቅርቡ በተካሄደው ምርጫ ድምፁን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በመስጠት አገዛዙን ሽንፈት ማከናነቡን ኢህአዲግም በተለመደው ማጭበርበር አሸንፌያለው ማለቱን ገልጾ ሁሉም የተቀዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች እና የጦር ኃይል የፖሊስ ሰራዊት እንዲሁም የፀጥታ ሰራተኞች ከህዝቡ ጎን እንዲቆሙ የተሰጠው ማሳሰቢያ ይገኝበታል:: የፌዴራል ምርጫ ቦርድ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ሲመረምረው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤትን በተመለከተ ይፋዊ መግለጫ ሳይሰጥ በጋዜጣ [illegible] ገዢው ፓርቲ ሽንፈት ተከናንቧል በማለት በሌላ በኩል ሕዝቡ የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ለማስወገድ ከዳር እስከ ዳር አምርሮ በመነሳት በምርጫ ድምፁን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰቷል በማለት የሐሰት ወሬ ለህዝቡ ማሰራጨቱን ማስረጃ ያስረዳል:: በመሆኑም 82ኛ ተከሣሽ ዳዊት ፋሲል እና [illegible] ተቃዋሚ ድርጅት በህትመት ውጤታቸው የሐሰት [illegible] የተረጋገጠባቸው ስለሆነ ዐ/ሕግ በተከሣሾቹ ላይ [illegible] በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥ/ሥ/ቁጥር 113 2 በማሻሻል [illegible] የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 1 ሀ ለ 34 46 እና 4 86 ሀ ስር [illegible] የተመደቡ ተከሣሾች ደግሞ 80ኛ [illegible] ተከሣሽ ፈለቀ ጥበቡ ናቸው:: ተከሣሽ [illegible] ዐ/ሕግ ካቀረበው ማስረጃ አንፃር ስንመረምረው



Scanned by CamScanner

ይህ ተከሣሽ የነፃነት ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ሲሆን የዚሁ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆነው አብይ ግዛው የተከሰሰ ስለሆነ ምክትል አዘጋጅ የሆነው ደረጀ ኃ/ወልድ በተደራቢነት በወንጀል ህግ ሊጠየቅ አይችልም:: በተመሳሳይ መልኩ የሐዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆነው ዳዊት ከበደ በጋዜጣው ዋና አዘጋጅ የተከሰሰ ስለሆነ የጋዜጣው ምክትል ዋና አዘጋጅ የሆነው ፈለቀ ጥበቡ በተደራቢነት ተጠያቂ የሚያደርገው የህግ አንቀፅ የለም:: በመሆኑም 80ኛ ተከሣሽ ደረጀ ኃ/ወልድ እና ዘጠናኛ ተከሣሽ ፈለቀ ጥበቡ በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 43 1 መሠረት ተጠያቂ ሲሆኑ የማይችሉ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ ፍ/ቤቱ በይኗል:: በምድብ አምስት የመደብናቸው 88ኛ ተከሣሽ አረጋዊ የህትመት እና ማስታወቂያ 86ኛ ተከሣሽ አባይ አሳታሚ ናቸው:: እነዚህ የህግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች በወንጀል ሲከሰሱ የድርጅቶቹ ተወካዬች በችሎት ሂደት ተካፋይ ያልነበሩ ስለሆነ ዐ/ሕግ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አስተያየቱን እንዲሰጥ ታዟል:: በምድብ ስድስት የመደብናቸው የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ባለቤቶች እና ስራአስኪያጆች ናቸው:: በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 46 መሠረት የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት በየትኛውም ቅደም ተከተል ከተመለከተው የወንጀል አድራጊ ጋር በተደራቢነት ወይንም በተናጥል በወንጀል ተጠያቂ ከመሆን የማያመልጥ መሆኑን ይገልፃል ሆኖም የጋዜጣው አሳታሚ ድርጅት በወንጀል ሲከሰስ የድርጅቱ ባለቤት እና ስራአስኪያጅ በተደራቢነት በወንጀል ሊጠየቅ የሚችል መሆኑን የሚገልፅ የወንጀል ህግ የለም:: በመሆኑም የአዲስ ዜና ጋዜጣ ባለቤት እና ስራአስኪያጅ የሆነው 71ኛ ተከሣሽ ፋሲል የኔአለም የኢትኦጵ ጋዜጣ ባለቤት እና ስራአስኪያጅ የሆነው 74ኛ ተከሣሽ ሲሳይ አጌና የአስኳል የሚኒሊክ እና የሳተናው ጋዜጦች የሆነው 74ኛ ተከሣሽ ሲሳይ አጌና የአስኳል የሚኒሊክ እና የሳተናው ጋዜጦች ባለቤት እና ስራአስኪያጅ የሆነችው 77ኛ ተከሣሽ ሰርካለም ፋሲል እና የነፃነት ጋዜጣ ባለቤት እና ስራአስኪያጅ የሆነው 84ኛ ተከሣሽ ዘካርያስ ተስፋዬ በወንጀለኛ

መቅጫ ህግ ሥ/ሥ ቁጥር 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ በይነናል::

በመቀጠል አንደኛ ክስ ላይ በተከሣሽነት የቀረቡት የአራቱ ድርጅቶች ማለትም ከ128ኛ እስከ 131ኛ በተከሣሽነት የቀረቡት በህግ ሰውነት የተሰጣቸው አራት የፖለቲካ ድርጅቶች ማለትም መኢአድ፣ ኢዴአፓ መድህን፣ ኢዲሊ እና ቀስተ ደመና፣ ኢትዮጵያዊ ዲሞክራሲ እና ማህበራዊ ፍታዊ ንቅናቄ የተባሉት ሲሆኖ የተጠቀሱትን ድርጅቶች የወንጀል ተካፋይነት ለማየት የወንጀል ህግ ቁጥር 34 መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል:: በወንጀል ህግ ቁጥር 34 1 መሠረት የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በህግ ላይ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በወንጀል አድራጊነት በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ሊቀጣ እንደሚችል ተደንግጓል:: በዚህ አንቀጽ ለመረዳት የሚቻለው በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የሚከሰስበት እና

የሚቀጣበት ሁኔታ ገዘነ በተለየ ሁኔታ በግልፅ ካልተመለከተ በቀር በነዚህ ድርጅቶች ክስ ሊቀርብ እንደማይችል ነው፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ህግ ቁጥር 243 ላይ እንደተመለከተው በህገወጥ መንገድ ከአገር መውጣት ወደ አገር መግባት ወይም በአገሪቱ ውስጥ መኖር በሚለው ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልፅ እንደተደነገገው በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን የወንጀል ድርጊቶች የህግ ሰውነት የሰጠው ድርጅት ፈፅሞ እንደሆነ በሚል በግልፅ ያመላክታል፡፡ በሌሎች ተመሣሣይ አንቀጾችም የዚህ ዓይነት ድንጋጌ በግልፅ ሰፍሮ ይታያል የወንጀል ህግ ቁጥር አንቀጽ 238 እና በነዚህ ተከሣሾች ላይ የተቀረበው የህግ አንቀጽ በሚታይበት ጊዜ የዚህ ዓይነት ድንጋጌ የለውም በመሆኑም ይህ አንቀፅ ተጥሷል በሚል በህግ ሰውነት በተሰጣቸው ድርጅቶች ክስ ሊቀርብ አይገባም፡፡ በመሆኑም የጠቀሱት ድርጅቶች ይሄንን ክስ በሚመለከት እሚከላከሉት ነገር የለም ብለናል፡፡ በመቀጠል የምናየው ከ2ኛ እስከ 7ኛ ያሉትን ክሶች ነው ስለዚህ እነዚህን ክሶች ከአስር ደቂቃ በኃላ እናያቸዋለን፡፡

- ዐ/ሕግ በሁለተኛ ክስ ባቀረበው የወንጀል ክስ ተከሣሽ የሆኑት ከ1 እስከ 39ኛ እንዲሁም 6ኛ እስከ 131ኛ የሆኑት ሲሆኑ ተላልፎታል በማለት የቀረበባቸው የወንጀል ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 239 ሲሆን በዝርዝሩም የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በነፃነት ውሳኔ እንዳይሰጥ ለማደናቀፍ ሞክረዋል ኢኮኖሚም እንዲናጋ አድርገዋል የሚል ነው፡፡ ከላይ አንደኛን ክስን ስንመለከት በዐ/ሕግ በኩል ከቀረቡት ማስረጃዎች በቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት በተደረጉ ስብሰባዎች እና ከቅንጅቱ ሲወጡ በነበሩ መግለጫዎች የምርጫ ቦርድ በህዝቡ ዘንድ ያለውን ታማኝነት እንዲያጣ ከፍተኛ የሆነውን ውንጀላዎች እና ስም ማጥፋቶች ሲፈፀሙ የቆዩ እንደነበር እና ምርጫ ቦርድ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎችም ቢሆኑ ነፃ ሆኖ ለመስጠት እንዳያስችለው ዛቻዎች ለምሳሌ ምርጫ ቦርድ ይሄንን ካላደረገ ህዝቡ በራሱ ይሄንን ያደርጋል እርምጃ ይወስዳል የሚሉትን እና የመሳሰሉትን ዛቻዎች ሲፈፀሙ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የዚህ ዓይነት ስም ማጥፋቶች እና ዛቻዎች ደግሞ በወንጀል ህግ ቁጥር 239 ስር የተደነገገውን የህገመንግሥታዊ ሥልጣንን ተግባራዊነትን ማስናከል ማለትም ምርጫ ቦርድ በህግ የተሰጠውን ስልጣን በአግባቡ እንዳይወጣ በዛቻ እና በመሳሰሉት ሙከራ መደረጉን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ በወንጀል ህገ ቁጥር 30 መሠረት በወንጀል ሙከራ ሂደት ውስጥ የሚደረግ ድርጊትን ድርጊቱ እራሱን የቻለ ሌላ ወንጀል የሚያቋቁም ሆኖ ሲገኝ ለዚሁ የተወሰነውን ቅጣት በአድራጊው ላይ ተፈፃሚ ይሆንበታል በሚል ተደንግጓል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ተከሣሾች በተለይ በቅንጅት ሊዕላይ ምክር ቤት አባላት

ሲደረጉ የነበሩ ውይይቶች እና መግለጫዎች ምርጫ ቦርድ ስራውን በአግባቡ እንዳይወጣ ሙከራ መደረጉን የሚያሳዩ ሲሆን ይህም እራሱን በቻለ ወንጀል ድርጊት እንደሚያስቀጣ በወንጀል ህግ ቁጥር 30 ተጠቅሷል:: በሌላ በኩል ግን በዚህ የወንጀል ድርጊት ክስ ከቀረበባቸው ተከሣሾች መካከል ከ96 እስከ 131 የተጠቀሱት ሲታይ በተለይ ከ96 እስከ 127 ያሉት ተከሣሾች እና በአንደኛ ክስ ይከላከሉ የተባሉት ተከሣሾች ተሣትፎአቸው ሲታይ ከላይ በአንደኛ ክስ እንደተገለፀው ህገመንግሥታዊ ስረዓቱን በኃይል ለማፍረስ በተደረገው ሙከራ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማሩ ከመሆናቸው ውጪ በዚህ በሁለተኛ ክስ የቀረበውን የወንጀል ድርጊት ስለመፈፀማቸው የቀረበ ማስረጃ የለም:: ከ128 እስከ 131ኛ ተከሣሾችን በሚመለከትም ከላይ በአንደኛ ክስ የተጠቀሰው ምክንያት ለዚህም አግባብነት ያለው ስለሆነ በዚሁ ታልፋል በመሆኑም ከ96 እስከ 127 ያሉት ተከሣሾች በዚህ ክስ መከላከል አያስፈልጋቸውም ብለናል:: ከ1 እስከ 39 ያሉት ተከሣሾችን በሚመለከት በአንደኛ ክስ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጣቸው ተከሣሾች እና የቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ሊዕላይ ምክር ቤት አባላት የሆኑ ብቻ ማለትም 1ኛ ኢ/ር ሐይሉ ሻወል፣ 2ኛ አቶ አባይነህ ብርኃኑ፣ 3ኛ ሻአለቃ ጌታቸው መንግስቴ፣ 4ኛ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው፣ 5ኛ ዶ/ር ሐይሉ አርአያ፣ 6ኛ ሙሉነህ እዮኤል፣ 7ኛ ስለሺ ጠና፣ 8ኛ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ 9ኛ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ፣ 10ኛ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም፣ 11ኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደክሳ፣ 12ኛ አስቻለው ከተማ፣ 13ኛ ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ፣ 14ኛ ገብረፃዲቅ ኃ/ማርያም፣ 15ኛ አሰፋ አብተወልድ፣ 16ኛ ብሩክ ከበደ፣ 17ኛ መስፍን አማን፣ በሌለበት ስለሆነ ዐ/ሕግ በኩል በሁለተኛ ክስ በቀረበው 32 1ሀ ለ 38 27 239 የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ተብሏል:: 18ኛ ታምራት ታረቀኝ፣ 19ኛ አዱአለም አራጌ፣ 20ኛ ወ/ሮ ንግሥት ገ/ህይወት፣ 21ኛ ደበበ እሸቱ፣ 22ኛ የኔነህ ሙላት የተባሉት ተከሣሾች በዐ/ሕግ በኩል በሁለተኛ ክስ የቀረበውን ክስ በመተላለፍ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአግባቡ እና በነፃነት ውሳኔ እንዳይሰጥ ለማደናቀፍ መሞከራቸው ባቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን ይህም የወንጀል ህግ ቁጥር 32 1 ሀ ለ 38 እና 27 239 መተላለፋቸውን ስለሚያስረዳ በዚሁ መሠረት ሊከላከሉ ይገባል ብለናል:: ዐ/ሕግ በ3ኛ ክስ ባቀረበው የወንጀል ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 240 ንዑስ ቁጥር 2 የጠቀሰ ሲሆን በዝርዝሩ በዚህ የወንጀል ድርጊት ክስ የቀረበባቸው ተከሣሾች ከ1 እስከ 39 እንዲሁም ከ96 እስከ 131 በህገመንግሥቱ በተቋቋመው አካላት ላይ የትጥቅ አመፅ እንዲነሳ በአዲስ አበባ እና በአንዳንድ የክልል አካባቢዎች ህዝብ የጦር መሣሪያ ይዞ የትጥቅ አመፅን እንዲያነሳ በማደረጀት እና በመምራት የወንጀል ተግባር እንዲፈፀም አድርገዋል የሚል ነው:: ከላይ አንደኛውን ክስ ለማስረዳት ከቀረቡት ማስረጃዎች



Scanned by CamScanner

በምስራቅ ጐጃም እና በሰሜን ሸዋ ያሉት በ39ኛ የተጠቀሰው ሰነድ ሲታይ በምስራቅ ጐጃም እና በሰሜን ሸዋ ያሉት በ39ኛ የተጠቀሰው ሰነድ ሲታይ

በ39ኛ የተጠቀሰው ሰነድ ሲታይ በምስራቅ ጐጃም እና በሰሜን ሸዋ ያሉት ታጣቂ ቡድኖቻችን በ24ኛ ተከሣሽ ማሙሸት አማረ እና በ3ኛ ተከሣሽ ጌታቸው (እንዲመራ) መገለፁን በሌላ በኩልም በዚህ በተጠቀሰው አካባቢ የቀረቡ ምስክሮች ይሄው 24ኛ ተከሣሽ መንግሥትን በኃይል ለመጣል የታጠቁ ኃይሎችን ሲያደራጅ እንደነበር ተመስክሯል:: ይህ ሁኔታ በከተማ አካባቢ ሲሰራ እንደነበረ የቀረበ ማስረጃ የለም በመሆኑም በተጠቀሱት አካባቢዎች ሲደረጉ የነበሩትን እንቅስቃሴዎች በህገመንግሥት በተቋቋሙ አካላት ወይም በለስልጣኖች ላይ የትጥቅ አመፅ እንዲነሳ ሸፍቶችን ሲያደራጁ እንደነበር ነው:: ይህም ከላይ በሁለተኛ ክስ እንደተገለፀው በወንጀል ህግ ቁጥር 30 መሠረት ለብቻው መታየት ያለበት ነው:: ሆኖም ግን ይህንን የማደረጃቱ ማለትም ሸፍታ የማደራጀቱ ስራ በላዕላይ ምክር ቤትም ሆነ ቅንጅቱ ሲያወጣችው በነበሩ መግለጫዎች የሚታዩ አይደሉም በሌላ በኩል ግን በምስክሮች እና አንድ በቀረበ ሰነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚቻለው ይሄንን ማለትም ይሄንን ማደራጀት ማለትም የአመፅ እንቅስቃሴ እንዲነሳ ሸፍቶችን ሲያደራጁ የነበሩ እና በዚህ የወንጀል ተግባር ተሳትፎአቸው በማስረጃ የሚታየው ተከሣሾች 1ኛ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል፣ 2ኛ አባይነህ ብርሃኑ፣ 3ኛ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ፣ 4ኛ ማሙሸት አማረ፣ እና 5ኛ ተስፋዬ ታሪኩ የተባሉት ተከሣሾች እንደሆኑ በቀረበው ሰነድ ማስረጃ እና ምስክሮች ተረጋግጧል:: ይህ ድርጊት በወንጀል ህግ ቁጥር 240 1 ሀ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል መፈፀሙን ያሳያል በመሆኑም እነዚህ ተከሣሾች በህገመንግሥት በተቋቋመ አካላት ላይ የትጥቅ አመፅ እንዲነሳ ሸፍቶችን ሲያደራጁ እንደነበር በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በዚሁ አንቀጽ 32 1 ሀ ለ 38 240 1 ሀ መሠረት ሊከላከሉ ይገባል ብለናል::

በአምስተኛ የቀረበው ክስ ዐ/ሕግ አምስተኛውን የወንጀል ክስ የመሰረተው ከ1ኛ እስከ 39ኛ ከ70ኛ እስከ 90ኛ እና ከ128ኛ እስከ 131ኛ ድረስ በጠቀሱት ተከሣሹ ላይ ነው:: ከነዚህ ውስጥ ከ128ኛ እስከ 131ኛ ድረስ የተጠቀሱት ተከሣሾች የህግ ሰውነት የተሰጣቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ስለሆኑ በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 1 መሠረት በህግ ላይ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ ብቻ ነው ሊቀጡ የሚችሉት:: በመሆኑም ዐ/ሕግ በነዚህ ተከሣሾች ላይ የመሠረተው የወንጀል ህግ አንቀጽ 247 ሀ ሐ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊከሰሱ የሚችሉበት የወንጀል ህግ አንቀጽ ስላልሆነ ተከሣሾቹ ላይ የቀረበባቸው ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ ብለናል:: ዐ/ሕግ በተከሣሾች ላይ የመሠረተው አምስተኛው ክስ ወንጀሉ



Scanned by CamScanner

የሚለው እና የወንጀሉ ዝርዝር ተገናዝቦ ሲመረመር ወንጀሉ በሚለው ስር የአገር መከላከያ ኃይልን የመጉዳት ወንጀል መፈፀም የሚል ቢሆንም የወንጀሉ ዝርዝር በሚለው ውስጥ መጨረሻ ላይ ደግሞ የሐገር መከላከያ ኃይልን የመጉዳት ወንጀል ሙከራ የሚል ነው:: ከዚህ መረዳት የሚቻለው ወንጀሉ በአንድ በኩል ፍፃሚ እንዳገኘ ተደርጐ የቀረበ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ፍፃሚ እንዳላገኘ ወንጀል ተደርጐ ቀርቧል:: ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ከሁለቱ አማራጮች መውሰድ ያለበት ተከሣሾን ይበልጥ የማይጐዳውን አማራጭ በመሆኑ በዚህ ክስ በተከሣሾች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው በወንጀሉ ዝርዝር ላይ የተገለፀው ማለትም የሐገር መከላከያ ኃይልን የመጉዳት ወንጀል ሙከራ የሚለው መሆን እንዳለበት ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል:: ዐ/ሕግ ከ1ኛ እስከ 39 በተጠቀሱት ተከሣሾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ዝርዝር ተከሣሾቹ ቅንጅት በተሰኘ ድርጅት ስር ተሰባስበው እና ድርጅቱን ለህገወጥ አላማቸው መጠቀሚያ በማድረግ ከጥቅምት 29 ቀን 1997 እስከ ህዳር 5/93 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ የመከላከያ ሰራዊት ተሽከርካሪ በማቃጠል በተለይ በአገሪቱ ውስጥ የውጪ ሐገር መንግሥት ጦርነት በሚያስጋበት ጊዜ ወታደሩ የጦር አገልግሎቱን ከመፈፀም እንቢተኛ እንዲሆን ወታደራዊ አመፅ እንዲያነሳ እና እንዲፈታ በግልፅ በማነሳሳት እና በማደፋፈር በአድማ በቀጥታ እና በእጅ አዙር ባፈፀሙት የሐገር መከላከያ ኃይልን ለመጉዳት ወንጀል ሙከራ ተከሷል የሚል ነው:: ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት ካቀረባቸው መረጃዎች መረዳት የሚቻለው በአዲስ አበባ ከተማ ሰኔ 1/97 ዓ/ም እና በተከታዩቹ ቀናት በተፈጠረው የአመፅ እንቅስቃሴ የመከላከያ ሰራዊት መኪና ጭምር የተቃጠለ ሲሆን አመፁም ሊቀሰቀስ የቻለው ቅንጅቱ ከምርጫ በፊት እና ከምርጫ በኃላ ከሰኔ 1/97 በአካሄዳቸው ውይይቶች በሰጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ቅስቀሳዎች ወዘተ መነሻ መሆኑን ከቀረቡቱ መረጃ መረዳት ችለናል:: ይህ የመከላከያ ሰራዊት መኪና የተቃጠለው ቅንጅቱ መስከረም 14/98 ዓ/ም ውህደት ከመፈፀሙ በፊት በመሆኑ በአመፁ እና አመፁ ባስከተለው ውጤት ኃላፊ የሚሆኑት ከቅንጅቱ ውህደት በፊት ቅንጅቱን በበላይነት ሲመሩት የነበሩት የቅንጅቱ ለዕላይ ምክር ቤት አባላት ናቸው:: የአባላቱ ብዛትም 16 ሲሆን ከ16 ውስጥ በዚህ ክስ በተከሣሽነት የቀረቡት 10 ሲሆኑ እነሱም 1ኛ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል፣ 2ኛ አባይነት ብርሃኑ፣ 3ኛ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ፣ 4ኛ ግዛቸው ሽፈራው፣ 5ኛ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ፣ 6ኛ ሙሉነህ እዮኤል፣ 7ኛ ስለሺ ጠና፣ 8ኛ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ 9ኛ ዶ/ር ያቆብ ኃ/ማርያም፣ 10ኛ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ ናቸው በመሆኑም እነዚህ 10 ተከሣሾች ላይ ዐ/ሕግ የመሠረተውን ክስ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ ስለሆነ እንዲከላከሉ በይናል:: በሌላ በኩል 10ኛ፣ 12ኛ፣ 13ኛ፣ 14ኛ፣ 15ኛ፣ 16ኛ፣ 17ኛ፣ 18ኛ፣ 19ኛ 20ኛ፣ 21ኛ፣ 22ኛ፣ 23ኛ፣ 24ኛ፣ 25ኛ፣ 26ኛ፣ 27ኛ፣ 28ኛ፣



Scanned by CamScanner

29ኛ 30ኛ፣ 31ኛ፣ 33ኛ፣ 34ኛ፣ 35ኛ፣ 36ኛ፣ 37ኛ፣ 38ኛ፣ እና፣ 39ኛ ተከሣሾችን በተመለከተ ዐ/ሕግ እንደክሱ ሊያስረዳ ያልቻለ ስለሆነ በዚህ ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ በይነናል፡፡

- በሌላ በኩል በዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ ከተራ ቁጥር 70 እስከ 90 ድረስ የተከሰሱት ተከሣሾች በመከላኪያ ሠራዊቱ ላይ የሐሰት ወሬ በማውራት የመከላኪያ ሰራዊቱ እንዲከፋፈል እና በመንግሥት ላይ እንቢተኛ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ሲቀሰቅሱ እና ሲያነሳሱ በመቆየታቸው በአድማ በቀጥታ በእጅ አዙር በተፈፀሙት የአገር መከላኪያ ኃይልን የመጉዳት ሙከራ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ዐ/ሕግ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች ከህጉ ጋር አገናዝበን ስንመረምር ከቀረበው ክስ አንፃር አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች በአባይ ጋዜጦች ታትመው የወጡት ፅሑፎች ሲሆኑ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ መስፍን ተስፋዬ ሲሆን፣ የጋዜጣው አሳታሚ ደግሞ አባይ አሳታሚ ነው፡፡

ከአባይ ጋዜጦች ውስጥ በተለይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነሐሴ 21/97፣ ጳጉሜ 5/97፣ ጥር 28/97 እና ሚያዝያ 8/97 ታትመው የወጡትን የሚመለከት ነው፡፡ ይዞታቸውም "ሠራዊቱ በዓላማ ከኢህአዴግ ይልቅ ለተቃዋሚዎች ይቀርባል" በሚል ርዕስ ስር ምርጫው ከተጭበረበረ እና ሕዝባዊ አመጽም ከተሰናከለ ያቆጠቆጡት የትጥቅ ትግሎች ተፋፍመው የሚቀጥሉ በመሆናቸው ሰራዊቱ ተረጋግቶ ኑሮውን መምራት እንደሚሳነውና በመጨረሻም ሽንፈት ይከተልና በ1983 የታየው መበተን የሚከተል መሆኑን፣ በማስከተልም የኢትዮጵያ ሠራዊት ነፃ ምርጫ ተካሂዶ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን ካልተቀዳጀ በሕዝባዊ አመፅ ባለሀገርነቱን እንደሚያወጅ፣ አህአዴግ አመነም አላመነም ቤተመንግስት ያሉትን ጨምሮ የአብዛኛው ሠራዊት ልብ ጭምር እንደሸፈተና ሠራዊቱ ሕገመንግስቱን ለማስከበር ባይችል እንኳን ሕገመንግስቱ፣ እንዲጠበቅ የሕዝብ ድምፅ እንዲከበር በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ በሚጠይቁ ዜጎች ላይ ብረቱን ባለማንሳት የሕግ የበላይነት አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅበት የተገለፀው በማስረጃነት ቀርቧል፡፡

ከነዚህ ማስረጃዎች አንፃር የመከላከያ ሠራዊት አባላት ሕገመንግስታዊ ግዴታቸውን እንዳይወጡ ከፍተኛ ቅስቀሳ የተደረገ መሆኑን የሚያስረዳ ስለሆነ ዐ/ሕግ የመሠረተውን ክስ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 113/2/ መሠረት በማሻሻል 87ኛ ተከሣሽ በአዲስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 257/ሀ/ መሠረት እንዲከላከል ተበይኗል፡፡ በሌላ በኩል 86ኛ እና 88ኛ ተከሣሾች አባይ አሳታሚንና አረጋዊ ሐትመትና

የሲታወቂያ በተመለከተ የድርጅቱ ተወካይ በክርክሩ [illegible]
ታዩ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ታዟል።

ከቀሪ ተከሣሾች ውስጥ 71ኛ፣ 74ኛ፣ 77ኛ እና 84ኛ [illegible]
ለሁለትነትና ስራ አስኪያጅነታቸው ምክንያት በወንጀል የተከሰሱ [illegible]
3ኛ፣ 75ኛ፣ 76ኛ፣ 78ኛ፣ 80ኛ፣ 81ኛ፣ 82ኛ፣ 83ኛ፣ 89ኛ እና 90ኛ [illegible]
ተመለከተ ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት በቂ ማስረጃ ያላቀረበ [illegible]
ሙሉ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ/ 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ በይኗል።

79ኛ እና 85 ተከሣሾች በሌሉበት ክሳቸው [illegible]
ወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/ 163/3/ እና 149 መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ ተወስኗል።

በ6ኛ ቁጥር በቀረበው የወንጀል ክስ ከ1ኛ-39ኛ እንዲሁም ከ128ኛ - 131ኛ ባሉ
ተከሣሾች ላይ የተጠቀሰባቸው የወ/ሕግ ቁ 32/1/ሀ/ለ 38፣ 248/ለ፣ 258 ላይ
የተደነገገውን በመተላለፍ ከፍ ያለ ከደት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ሲሆን [illegible]
ተከሣሾች ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት የሚያደርገው የኤርትራ መንግሥት እና በኤርትራ
መንግሥት የሚደገፈው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ለማድረግ [illegible]
የኢትዮጵያ ጠላቶች ድርጊት በመደገፍ ከፍ ያለ ከደት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው
ይህንን ድርጊት ለማስረዳት ከቀረቡት ማስረጃዎች 1ኛው ሰነድ የኢትዮጵያ [illegible]
ግንባር ለቅንጅት የፃፈው ደብዳቤ ሲሆን ይዘቱም ግንባሩ ከቅንጅቱ ጋር [illegible]
የገለፀበት ሲሆን በዚህ ደብዳቤ 1ኛው ተከሣሽ ለግንባሩ የምስጋና ደብዳቤ [illegible]
መፈረሙን ከሰነዱ ተመልክተናል ይህ ፊርማ የተከሣሽ ኢ/ሣይሉ ሻውል መሆኑን
ከፎረንሲክ በቀረበው ማስረጃም ተረጋግጧል።

ሌላው የሰነድ ማስረጃም አጀንዳ በሚል ከኤርትራ መንግሥት ጋር [illegible]
ግንኙነት ማድረግ የሚል ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ዐ/ሕግ ምስክሮችን [illegible]
አሰምቷል። የምስክሮች ቃል በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል።

ካሣሁን በላይ የተባለው ምስክር በሰጠው ቃል የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች
ግንባር ታጋይ እንደነበር ገልፆ በዚህ ግንባር እና በቅንጅት መካከል ያለውን [illegible]
ግንኙነት ለማስረዳት እንዳቀረበ ይህ ግንባር በኢትዮጵያ ያለውን ሥርዓት [illegible]
ለማስወገድ በትጥቅ የሚታገል ድርጅት እንደሆነና ሙሉ ድጋፍም ከኤርትራ መንግሥት
እንደሚደረግለት አስረድቷል በ1997 ዓ.ም ቅንጅት ራሱን በሚደያ [illegible]
ከጀመረበት ግዜ ጀምሮ ይህንን ድርጅት እንደራሳችን አድርገን እንድንቀጥረው [illegible]
ድርጅት ሲተላለፍ የነበሩ መግለጫዎችንም በተለያየ ሚዲያዎች [illegible]
በአለቆቻችን ሲነገረን ነበር የቅንጅት ከፍተኛ አመራሮችም ከግንባሩ [illegible]
ጋር እንደተወያዩም በአለቆቻችን ሲነገረን ነበር በማለት ቃሉን ሰጥቷል።

ተስፋዬ አማረ የተባለው ምስክርም የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አባል እንደነበረና በተለያዩ ጊዜያት ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር በተለያዩ ግንባሮች መዋጋቱን የገለፀ ሲሆን ስለ ድርጅቱ አመሠራረትም ሆነ ድርጅቱ ከቅንጅት ጋር አለ ስለሚለው ግንኙነት ከላይ 1ኛው ምስክር ከሰጠው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በተወሰነ መልኩ በተጨማሪነት የሰጠው የግንባሩ ከፍተኛ አመራር አገር ውስጥ ገብቶ ከቅንጅት አመራሮች ጋር ግንኙነት አድርገናል በማለት የተነገራቸው መሆኑን በመመስከር ቃሉን አጠናቋል።

መሀመድ ሐሰን የተባለውም ከሞላ ጎደል ከላይ ካተሰጡት የምስክሮች ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቃሉን የሰጠ ሲሆን ሁለቱ ምስክሮች ከሰጡት በተጨማሪ 1998 ዓ.ም ታህሣሥ ወር መጨረሻ አካባቢ ብርሃነ መዋ እና አንዳርጋቸው ፅጌ ግንባር ድረስ በመምጣት ያበረታቷቸው መሆኑን በመመስከር ቃሉን ሰጥቷል።

ኢብራሂም ከድር እና ወርቁ ገነት የተባሉት ምስክሮች ተስፋዬ አማረ የተባለው ምስክር ከሰጠው ቃል ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ በመሆኑ ማስፈሩ አላስፈለገም።

አለቱ ብርሃኑ የተባለው በሰጠው ቃል የቅንጅት አመራሮች በማለት ብርሃነ መዋ እና አንዳርጋቸው ፅጌ ታህሣሥ ወር ላይ ኤርትራ ግዛት ውስጥ ግንባር ድረስ በመምጣት እንዳነጋገሯቸው መሀመድ ሀሰን የተባለው ምስክር ከሰጠው ምስክርነት ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የመሰከረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ ኢትዮጵያ ውስጥ በመግባት የተለያዩ ኦፕሬሽኖችን እንዲፈፅም የተነገረው መሆኑንም በመግለፅ መስክሯል የምስክሮች ቃል ከላይ የመሰለውን ሲሆን ማስረጃዎችን ከክሱ ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

በክስ ማመልከቻው የተጠቀሰው የወ/ሕግ/ቁ 248/ለ ይዘት ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከሚያደርግ ሃይል ጋር ወይም ለዚህ ሃይል ጥቅም ከሚሠራ ሰው ወይም ድርጅት ጋር በመተባበር ወይም ሚስጢራዊ ግንኙነት በማድረግ ይኸው ኃይል እንዲመቸውና እንዲቀናው መርዳት ከፍ ያለ ክደት እንደሆነ ተደንግጓል።

በክስ ማመልከቻው ደግሞ ቅንጅት ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከሚያደርገው የኤርትራ መንግስት እና በኤርትራ መንግሥት የሚደገፈው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር እንዲቀናው ለማድረግ አስበውና የእነዚህ የኢትዮጵያ ጠላቶች ድርጊት በመደገፍ ከፍ ያለ ክደት ፈፅመዋል የሚል ነው።

በወ/ሕግ/ቁ 248/ለን ለማስረዳት በዐ/ሕግ መረጋገጥ ያለባቸው ጉዳዮች 1ኛ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት የሚያደርግ ሃይል መኖሩን /2/ ተከሣሾች ከዚህ ሃይል

ጋር ሚስጢራዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን እና 3. ይህ ሃይል እንዲቀናው ተከሣሾች የረዱ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል::

በሰነድ ማስረጃነት ከቀረበው 1ኛው የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር የሚል በመሆኑ በክሱ ላይ በተጠቀሰው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባርም ሆነ በምስክሮች በተደጋጋሚ የሚነገረውን ይህንኑ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ነው ለማለት አልተቻለም ነው ቢባል እንኳን ምናልባት ግንኙነት መኖሩን ከሚያሳይ በቀር ይህ ግንባር እንዲቀናው ወይም እንዲመቸው በቅንጅቱ ወይም በተከሣሾች የተደረገውን እርዳታ የሚያሳይ አይደለም::

አጀንዳ በሚል ሰነድም ከኤርትራ መንግሥት ጋር በሚስጢር ግንኙነት ማድረግ የሚለውም ይኼ ግንኙነት ተመስርቷል ወይስ አልተመሰረተም የሚለው ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ከግንኙነት ባሻገር የሚፈለገውን እርዳታ ማድረግ ወይም ማገዝን አያመለክትም::

ብርሃኑ መዋ እና አንዳርጋቸው ፅጌ ኤርትራ ግዛት ውስጥ ከኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ጋር መወያየታቸው አንዱ ምስክር ቀኑን እንደገለፀው ታህሣሥ መጨረሻ 1998 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ ይኸ ክስ ለዚህ ችሎት ከቀረበ በኋላ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: በእርግጥ እነዚህ ሁለት የተጠቀሱት ግለሰቦች 1ኛ ብርሃነ መዋ እና 2ኛ አንዳርጋቸው ፅጌ ያደረጉት ተግባር በወ/ሕግ/ቁ 248 ን የተጠቀሰውን ከፍ ያለ ክደት መፈፀማቸውን ሊያመለክት ቢችልም እነዚህ በስም የተጠቀሱት ሁለቱ ግለሰቦች በዚህ የወንጀል ድርጊት ክስ ያልቀረበባቸው ከመሆኑም በለይ በምስክሮች የተጠቀሰው ጊዜም ቢሆን በክስ ማመልከቻው ከተጠቀሰው ጊዜ ጋር የሚገናኝ አይደለም ክስ የቀረበባቸው ተከሣሾች አድራጉትንም የሚያሳይ አይደለም::

ቀርበው ቃላቸውን የሰጡት ምስክሮች ጠቅለል ባለመልኩ ለማስረዳት የሞከሩት የሻዕቢያ መኰንኖች እና የኢትዩጵያ አርበኞች ግንባር አመራር አካላት ከቅንጅት ጋር የቅንጅትን የተለያዩ ግንኙነት አለን አላማቸው የእኛም ነው ሲሉ እንደነበርና የቅንጅትን የተለያዩ ፕሮግራሞች እንድንከታተል ሲነግሩን ነበር ማለታቸው ሲታይ ይህ ሁኔታ በራሱ ከቅንጅት ወይም ከአመራሮች ጋር ግንኙነት መኖሩን ሊያሳይ ብቃት ያለው አይደለም ብቃት ሊኖረው ይችል የነበረው የቅንጀት አመራሮች በክሱ በተጠቀሰው ጊዜያት ይህንን ትብብር እና ግንኙነት ለምስክሮች ቢናገሩ ነበር:: በአጠቃላይ ሁኔታ ከዐ/ሕግ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች በ6ኛ ክስ በተከሣሽነት የቀረቡት ተከሣሾች ከፍ ያለ ክደት ወንጀል መፈፀማቸውን በበቂ ሁኔታ የሚያስረዱ ባለመሆኑ በዚህ ክስ ሊከላከሉ አይገባም በማለት በአብላጫ ድምፅ ወስነናል::

ዐ/ሕግ በ7ኛ ክስ ባቀረበው የወንጀል ክስ ከ1ኛ 39ኛ፣ ከ70ኛ 90ኛ እና ከ96ኛ - 131ኛ በተጠቀሱት ተከሣሾች ላይ የወ/ሕግ/ቁ 32/1/ሀ/ለ/፣ 38፣ 34፣ 27/1 እና 269/ሀ/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ከአንድ ጎሳ የመጡ ናቸው በሚሏቸው ላይ



Scanned by CamScanner

በማጥላላት እንዲሁም የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችን ሕዝቡ ጥቃት ለመሰንዘር በማጥላላት እንዲሁም የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችን ሕዝቡ ... እንዲያገል አመራር በመስጠት እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ለማጥፋት የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል በመሞከራቸው በግብረአበርነት በፈፀሙት ተከሰዋል የሚል ነው::

ዐ/ሕግ ይህንን የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት ካቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች 1ኛው ቅንጅት ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም ለሕዝብ የቀረበ ጥሪ በማለት ያወጣው መግለጫ ሲሆን በዚህ ሰነድ ላይ ቅንጅቱ ፖርላማ ለመግባት ያቀረባቸውን 8 ነጥቦች መንግስትን ለማስገደድና ጫና ለማሳረፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች በሚልና የማህበራዊ የማግለል እርምጃዎች በማለት ከተጠቀሱት እርምጃዎች በሚልና የማህበራዊ የማግለል እርምጃዎች በማለት ከተጠቀሱት ... ሃዘንና ደስታን አብሮ አለመካፈል ቡናም አብሮ አለመጠጣት በገጠሬቱ አካባቢ እስት አለመቀባበል እቁብና እድር ውስጥ አለማሳተፍን ያካትታል የሚለውን ማየት ይቻላል::

ሌላው የቀረበው ሰነድም የስድስት ባለሥልጣናት ማለትም የአቶ መለስ ዜናዊ፣ አዲሱ ለገሰ፣ ተፈራ ዋልዋ፣ ገነት ዘውዴ፣ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ እና በረከት ስምዓን የሚገደሉ በሚል የቀረበው ሰነድና 4ኛው ተከሣሽ ከሆነው ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ቤት የተገኘ ሰነድ ነው::

ይህንን ድርጊት ለማስረዳት የቀረበው ሌላ ማስረጃ 29ኛ ተከሣሽ በድሩ አደም በምርጫ ቅስቀሳ ጊዜ የፌዴራል መንግስት ሥልጣን በትግራይ ብሔር ተወላጆች ብቻ እንደሆነ የቀሰቀሰበትና ይኸው ተከሣሽ መስቀል አደባባይ ላይ በሥልጣን ላይ ያለው በሕዝብ ጡንቻ ወደመጣበት ይመለሳል በማለት የተናገረው ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ጥቅምት 21 እና በተከታዩቹ ቀናት በተነሳው የአመፅ እንቅስቃሴ የትግራይ ብሔረሰብ እና የኢህአዴግ ደጋፊና አባላት በሆኑት በአካላቸው ላይ የደረሰውን ጉዳት ንብረታቸው በተለይም መኖሪያ ቤታቸውን ከሌላው በመነጠል የተቃጠለባቸው ከ3-4 የሚሆኑ ጉዳት የደረሰባቸው ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል እነዚህ ምስክሮች ይህን መሰል ጉዳት ያደረሰባቸው የትግራይ ተወላጆች የኢህአዴግ ደጋፊ በመሆናቸው ብቻ እንደሆነ በሰጡት ቃል ገልፀዋል::

በዐ/ሕግ የቀረቡት ማስረጃዎች ካለይ የመሰሉትን ሲሆኑ የወ/ሕግ/ቁ 269 ላይ የተመለከተውን የዘር ማጥፋት ወንጀል በሙከራ በመተላለፍ ተከሣሾች ይህንን ወንጀል ለመፈፀም ሞክረዋል ወይ የሚለውን ለማየት ይህ አንቀጽ ምን አይነት ይዘት እንዳለው ተመልክተናል::

በወ/ሕግ/ቁ፡ 269 መሠረት ማንም ሰው በሰላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ በብሔር በብሔረሰብ፣ በጎሣ፣ በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለም በሃይማኖት ወይም በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የጥፋቱን ድርጊት በማደራጀት ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ድርጊቱን በመፈፀም የማህበረሰቡን አባሎች የገደለ አካላዊ ወይም ህሊናዊ ጤንነት የጐዳ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም ያጠፋ እንደሆነ የወ/ሕግ/ቁ 269/ሀ በመጣስ ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል በአንቀጹ ተደንግጓል::

በዚህ አንቀጽ መሠረት መረጋገጥ ያለበት በአንቀጹ በተቀመጠ የማህበረሰብ አባላት ላይ ግድያ አካላዊ ወይም ህሊናዊ ጤንነት ጉዳት ከመድረሱ በተጨማሪ ይህ ጉዳት ሊደርስ የቻለው በተጠቀሱ የማህበረሰብ አባላትን በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ እንደሆነም መረጋገጥ ያለበት ነው::

ከቀረቡት ምስክሮች በእርግጥ የኢህአዴግ ደጋፊ እና የትግራይ ተወላጅ ነው የሚል ኑር ሁሴን በተባለ ምስክር በተለያዩ ስለት ባላቸው ነገሮች በመደበደቡ ጉዳት እንደደረሰበት እና ሌሎች 3 የሚሆኑ ምስክሮች ደግሞ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ በደረሰው ውድመት ለህሊና ጉዳት እንደተዳረጉ የተመሰከረ ሲሆን ይህ ጉዳት የደረሰው የኢህአዴግ አባላት እና ደጋፊ ወይም የትግራይ ተወላጅ የሆኑትን በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ ነው ወይ የሚለውን ለማየት ሌሎች ማስረጃዎችን ማየቱ የግድ ይላል:: የዚህ አይነት ሃሳብ መኖሩ እንዴት ሊረጋገጥ ይችላል የሚለው ሲታይ የተከሣሾችን በዚህ የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም የነበራቸውን ተሳትፎ እና አፈፃፀሙን በሚመለከት ሊያሳዩት የነበረ ነገር ካለ በመመልከት ነው::

ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም በቅንጅት የወጣው ጥሪ ላይ ሕብረተሰቡ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችን እንዲያገል በማለት የተጠቀሱት ነጥቦች እነዚህ ሁኔታዎች በህብረተሰቡ መካከል ያለውን ጤናማ ግንኙነትን በእጅጉ የሚፈታተኑና አንድ የማህበረሰብ አባል ጥሪውን ካስተላለፈው ድርጅት የተለየ አመለካከት ስላለው ብቻ እንዲገለል ጥሪ ማስተላለፍ በየትኛውም መመዘኛ ጤናማ የሆነ አካሄድ ባይሆንም የዚህ አይነት ጥሪ ጥሪውን ያስተላለፈው ድርጅቶችና አመራሩ ይህንን ማህበረሰብ በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት ማሰቡን ያረጋግጣል ወይ በማለት ስንጠይቅ የሰነዱ መነሻን ወይም መንደርደሪያን ማየት ያስፈልጋል:: በዚህ ሰነድ መንደርደሪያና በ1ኛ ክስ ማመልከቻ ለመረዳት የሚቻለውም የዚህ አይነት እርምጃ ለመውሰድ ያስፈለገው መንግስት ላይ ዲፕሎማሲያዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫና በማድረግ በ1ኛው ክስ ላይ እንደተጠቀሰው በሥልጣን ላይ ያለውን መንግስትና ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለማስወገድ እንደአንድ የትግል [illegible] [illegible] ነው በመሆኑም በዚህ ሰነድ ይህ

የጠቀስነው የሃሳብ ክፍልን [illegible] 29ኛው ተከሣሽ ያደረገው ንግግርም ቢሆን የጥላቻ ንግግር ከመሆን ውጭ ይህንን ሃሳብ የሚያመለክት ሆኖ አላገኘነውም::

በእርግጥ የተከሣሾችን ሃሳብ በተናገሩት ወይም በፃፉት ፅሁፍ ብቻ ወስኖ ማየት ተገቢ ባለመሆኑ በእርግጥ የደረሰውን ጉዳት መቼ እና እንዴት እንደተፈፀመ በማየት የተከሣሾች ሃሳብ ምን እንደነበር ድምደሜ ላይ ለመድረስ የሚቻል በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ተመልክተናል::

ቀርበው ቃላቸውን የሰጡት ምስክሮች ላይ ጉዳቱ የደረሰባቸው ቀናት ሲታይ ጥቅምት 21 እና በተከታዩ ቀን ሲሆን እነዚህ ቀናት ከላይ በ1ኛ ክስ እንደተገለፀው ሕገመንግስቱንና ሥርዓቱን በሃይል ለማስወገድ የተግባር እንቅስቃሴ የተደረገባቸው ቀናት ናቸው::

በእነዚህ ቀናት ከላይ በ1ኛው ክስ እንደተገለፀው ሕገመንግስቱንና ሥርዓቱን በሃይል ለማፍረስ በተደረገው የተግባር እንቅስቃሴ የመንግስት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከመድረሱም በላይ ከመንግስት ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ ግለሰቦችም ቢሆኑ የጥቃቱ ኢላማ እንደነበሩ ነው:: ይህ ማለት ግን ጥቅምት 19 በተከሣሾች የወጣው መግለጫም ሆነ በ29ኛ ተከሣሽ ሲደረጉ የነበሩ የቅስቀሳ ዓይነቶች ተጠናክረው ቢቀጥሉ እና ጊዜ ቢያገኙ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲፈፀም ሊያነሳሱ የሚችሉ መሆናቸው ግልፅ ነው ሆኖም ግን ከላይ ለማስረዳት እንደተሞከረው በተለይ የጉዳቱ ሰለባዎች ጉዳቱ የደረሰባቸው ጊዜ ሲታይ ከላይ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ሁኔታ በመሆኑ በዚህ 7ኛ ክስ የቀረበባቸው ተከሣሾች ዘርን ለማጥፋት ሃሳብ የነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም በዚህ የወንጀል ድርጊት ክስ የቀረበባቸው ተከሣሾች መከላከል አያስፈልጋቸውም በማለት በአብላጫ ድምፅ ወስነናል::

## የሀሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 የተመለከተው ዳኛ 6ኛውን ክስ በተመለከተ በአብላጫ ድምፅ ከተሰጠው ብይን በሚከተለው አኳኋን በሀሳብ ተለይቻለሁ::

በዚህ ክስ የተጠቀሱት ተከሣሾች በአቃቤ ህግ የክስ ማመልከቻ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 39 የተዘረዘሩት ተከሣሾች እንዲሁም ተከሣሾቹ አባል የሆኑባቸው ከ128 እስከ 131 የተዘረዘሩ ተከሣሽ ድርጅቶች ሲሆኑ በእነዚህ ተከሣሾች ላይ የቀረበው ክስ ፍሬ ነገር ተከሣሾቹ ቅንጅት ከተሰኘ ድርጅት ስር ተሰባስበው እና

ሪማ በማድረግ ድርጅቱን በህገወጥ አላማቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ጋር
ሀርነት የሚያደርጉ እና የኤርትራ መንግስት በሚደገፍ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች
ንባር የተባለው የኢትዮጵያ መንግስት ተቃዋሚ ተዋጊ ድርጅት እንዲቀናው በማድረግ
ፍተኛ የአገር ክህደት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ሲሆን ይሔንን ጉዳይ ለማስረዳት
ስችላል የተባሉ የሰው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበባቸዋል። በጉዳዩ ላይ
ርበው የተሰሙት ምስክሮች ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የተባለው እና
ኢትዮጵያ መንግስት ጋር የሚዋጋ በኤርትራ መንግስት የሚደገፍ ድርጅት አባላት
ነበሩ መሆናቸውን ገልፀው ድርጅቱ በሚሰጣቸው አመራር ወደ ኢትዮጵያ በመግባት
ተለያዩ የጦር ግንባሮች ከኢትዮጵያ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት ጋር ሲዋጉ እንደነበር
ና በጦርነቱ የተለያዩ የመሰረተ ልማት አውታሮችንም ማፈራረሳቸውን፣ በተለያዩ
ታደራዊ ካንፖች ላይም ጉዳት ማድረሳቸውን ገልፀው ለዚህ ተግባር መከናወኛ
ሚሆን ድጋፍ ከኤርትራ መንግስት ያገኙ እንደነበር በማብራራት ድርጅታቸው ከአገር
ውስጥ ቅንጅት ከተባለ ድርጅት ጋር ስለበረው ግንኙነት፣ የቅንጅት አላማ እና ተግባር
ነሱን በአባልነት አሰባስበው የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተብሎ ከሚታወቀው
ርጅት አላማ እና ፕሮግራም ጋር አንድነት ያለው በመሆኑ ቅንጅት የተሰኘውን
ርጅት እንደራሳቸው አድርገው እንዲቆጥሩት እና አላማውን እና ፕሮግራሙንም
ማስፈፀም እና ለመፈፀም መስራት እንደሚገባቸው በመሪዎቻቸው ጥብቅ ትእዛዝ
ተላለፍ እንደነበር፣ ስለሆነም በሀገር ውስጥ ለሚደረገው ከምርጫ ጋር የተያያዘ
ንቅስቃሴ በሚዲያ እንዲከታተሉ ሲደረግ እንደነበር ከምርጫው ውጤት በኋላም በአገር
ውስጥ የነበረውን የአመፅ ተግባር በቪዲዮ ካሴት ጭምር እንዲከታተሉ በማድረግ
ወጣቱ እና ሌሎች የብሔረሰብ ክፍሎች በባዶ እጃቸው የሚያደርጉትን ትግል በትጥቅ
መደገፍ ቅንጅት የተባለው ድርጅት በምርጫ ያሸነፈባቸውን አካባቢዎች የውጊያ
ጠናቸው በማድረግ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ውጊያ እንዲያደርጉ ቅስቀሳ እና
ልመላ ይሰጣቸው እንደነበረ፣ ይሔንን ሁኔታ ለማመቻቸትም ከድርጊቱ ከፍተኛ
ማራር አካላት መካከል ዩሀንስ ዘለቀ በተባለው የሚመራ ቡድን ከነሐሴ 1997 ዓ.ም
ምሮ እስከ መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ከቅንጅት አመራሮች
ጋር ተነጋግረው መመለሱን እና የኢትዮጵያን መንግስት በትጥቅ ለመጣል ተስማምቶ
መመለሱን በስብሰባ እንደነገራቸው በመዘርዘር ያስረዱ ሲሆን በተለይም፣ መሀመድ ሀሰን
ና እሸቱ ብርሀኑ የተባሉት ተጨማሪ የአቃቤ ህግ ምስክሮች እንደተናገሩት 40ኛ እና
44ኛ ተከሣሾች ግንባሩ ወደሚገኝበት የኤርትራ መንግስት በመሔድ ድርጅቱን በመደገፍ
የኤርትራ መንግስት ላደረገው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ምስጋና ማቅረባቸውን እና ተከሣሾቹ
የኤርትራ መንግስት ላደረገው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ምስጋና ማቅረባቸውን እና በገንዘብ ለማጠናከር ድጋፍ
የሚመሩት ድርጅትም ግንባሩን በሰው ሀይል በማጠናከር

እንደሚያደርጉ ቃል መግባታቸውን እና በጥምረት የገንዘብ እና ወታደራዊ ቁሳቁሶች እርዳታ ማድረጋቸውን መስክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሰነድ ማስረጃዎች በአቃቤ ህግ በኩል የቀረቡ ሲሆን ሰነዶቹ

1) አንደኛ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ለቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ የትግል ጥሪ አንድነት መግለጫ ሰነድ በሰነዱ ግርጌም በስብሰባ ተነበ የምስጋና ደብዳቤ ለድርጅቱ እንዲጻፍ በአንደኛው ተከሣሽ የታዘዘበት፣

2) ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ለኦሮሞ ነጻነት ግንባር የጻፈው የትግል አንድነት ግንባር መጠየቂያ ሰነድ ሲሆን በዚሁ ሰነድ ላይ ቅንጅት እና ግንባሩ እነ ኤፍሬም ባለቀቸው የኤርትራ መንግስት ተወካዮች በኩል ግንኙነት ማድረጋቸውን እና በተደረሰው ስምምነት መሰረትም በጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ለሚደረገው ምድረ አንቀጥቅጥ ላሉት አመፅ የግንባሩ አባላት እና ታጣቂዎች እንዲሳተፉ ትብብር የሚጠይቅ ፍሬ ሀሳብ የያዘ ፣ከዚህም በተጨማሪ

3) ከኤርትራ መንግስት ጋር ቅንጅት ስለነበረው ግንኙነት የሚያሳይ እና በከፍተኛ ሚስጥር መያዝ እንዳለበት የተመለከተበት አጀንዳ ለማስረዳት የቀረበ ሲሆን በዚሁ ሰነድ ከሰፈሩት ጉዳዮች መካከል በከፍተኛ ሚስጥር ከኤርትራ መንግስት ጋር ግንኙነት በማድረግ ድጋፍ ማግኘት እና በወያኔ መንግስት ባለስልጣናት የንግድ ድርጅቶች ላይ ጥቃት መፈፀም የሚል ይገኝበታል፡፡

እነዚህ ማስረጃዎች የሚያስረዱት ጠቅላላ ጉዳይ ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት የተሰባሰቡ አመራሮች በህቡእ እና በግልፅ አደራረግ የኤርትራ መንግስት እንዲሁም እንደ አቃቤ ህግ ምስክሮች አነጋገር በኤርትራ መንግስት ከሚደገፉት እና የኢትዮፒያ መንግስትን በትጥቅ ትግል ለመጣል ከሚዋጉት ኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ግንኙነት መፍጠራቸውን በተለይ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የተሰኘው ድርጅት በሚሰጠው አመራር እና በኤርትራ መንግስት ድጋፍ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለማድረግ ቅንጅት የተሰኘው ድርጅት አመራሮች በኩል ስምምነት መደረጉን እንዲሁም የግንባሩ የጦር አመራሮች እና አባሎቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሰርገው በመግባት ከኢትዮጵያ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት ጋር በመዋጋት በመሰረተ ልማት አውታሮች እና የመከላከያ ተቋማት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን፣ እና ለዚሁ አድራጎታቸው የሚያግዝ የገንዘብ እና የቁሳቁስ እርዳታ ተከሣሾች በሚመሩት ቅንጅት በሚባለው ድርጅትም

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መሆኑን፣ እንዲሁም ቅንጅት የተባለው ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በኤርትራ መንግስት አገናኝነት ልዩ ግንኙነት ሲያደርጉ እንደነበር በተመሳሳይ ሁኔታ ቅንጅት የተሰኘው ድርጅት በበኩሉ ከኤርትራ መንግስት ጋር ሚስጥራዊ ግንኙነት የነበረው መሆኑን እንዲሁም ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የትግል አንድነት እያሉ የሚገልፁት የኢትዮጺያ መንግስትን ለመጣል የታሰበ የትጥቅ ትግል ለማድረግ ግንኙነት እንደነበራቸው ማስረጃዎቹ በግልፅ ያስረዱት ጉዳይ ነው:: ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በተከሣሾች ላይ የቀረበው ክስ ተከሣሾቹ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ጦርነት ከሚያደርግ የኤርትራ መንግስት እና የኤርትራ መንግስት የሚደገፈው የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እንዲቀናው ለማድረግ አስበው እና የወንጀል ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ ሀሳባቸው በመስማማት የአገሪቱን የውጭ ወራሪ የመቋቋም አቅም እንዲዳከም በማድረግ እና የነዚህን የኢትዮጺያ ጠላቶች ድርጊት በመደገፍ ከፍ ያለ ክህደት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው በተከሣሾቹ ላይ የተጠቀሰው ይህ የወንጀል ህግ 248 እንደሚከተለው ይነበባል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው፣ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከሚያደርግ ሀይል ጋር ወይም ለዚሁ ሀይል ጥቅም የሚሰራ ድርጅት ለመተባበር ወይም ሚስጥራዊ ግንኙነት በማድረግ ይሔው ሀይል እንዲመቸው እና እንዲቀናው በማናቸውም አኳኋን የረዳ እንደሆነ ከፍ ባለ የክህደት ወንጀል ሊጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል:: የተከሣሾቹ አድራጎት ከተጠቀሰው ህግ ጋር ሲነጻጸር፣ ተከሣሾቹ ከቀረበው ማስረጃ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ከኤርትራ መንግስት ጋር እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከተሰኙት ድርጅቶች ጋር በተለያየ አኳኋን እንደ አስፈላጊነቱ ግንኙነት እንደነበራቸው በማስረጃዎቹ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው:: ካለው እውነት እና በድርጊትም በማስረጃዎቹ እንደተነገረው ደግሞ የኤርትራ መንግስትም ሆነ ግንባሮቹ የኢትዮጵያ መንግስት ጋር ጦርነት የሚያደርጉ ሀይሎች መሆናቸው ይታወቃል:: እነዚህን ሀይሎች ለመጥቀም፣ መስራት፣ መተባበር፣ ሚስጢራዊ ግንኙነት ማድረግ፣ ወይም እነዚህን ሀይሎች እንዲመቻቸው እና እንዲቀናቸው የሚያስችሉ ማናቸውንም አይነት ተፈላጊ ጠቀሜታ ያላቸውን እርዳታዎች ማድረግ እና እንዲሁ የተከለከሉ አድራጎቶች መሆናቸውን የጠቀሰው የወንጀል ህግ ያስረዳል ተከሣሾች ላይ የቀረበው ክስ እና ማስረጃ ይሔንን የሚመስል ሲሆን ተከሣሾቹ ያደርጉት ነበር ተብሎ የተከሰሰበት ግንኙነትም ሆነ መደጋገፍ ሚስጥራዊ ከመሆኑም ሌላ ግንኙነቱ የኢትዮጵያን መንግስት ከሚወጉ ሀይሎች ጋር

በመሆኑ ስማቸው የተለያየም ቢሆን በአለማ እና በግብር አንድነት ያላቸው ሀይሎች እንደመሆናቸው መጠን የስም ልዩነት እነዚህን ሀይሎች ማንነት የተከሳሾችን አድራጐት ህጋዊ ነበር ብሎ መደምደም የሚቻል አይመስለኝም ይልቁንም ተከሣሾች በማናቸውም አኳኋን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ጦርነት የሚያደርገውን ሀይል መርዳት ሚስጥራዊ ግንኙነት ማድረግ ወይም ይሔው ሀይል እንዲቀናው ማናቸውንም ትብብር ማድረግ የሚከለክለውን የወንጀል ህግ መተላለፋቸውን ያሳያል ከዚህም ሌላ በአብላጫው ድምፅ ተከሣሾች ያደረጉት ግንኙነት በስም ረገድ በክሱ ላይ ከተመለከተው ግንባር የተለየ ግንባር መሆኑ ከሚያስከትለው ውጤት እና ከተከሣሾች ሀሳብ እና አድራጐት አንጻር ሲታይ በክሱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ አያመጣም የኢትዮጲያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር የተሰኘውም ሆነ በሌላው ስሙ የኢትዮጲያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የተሰኘው በኢትዮጲያ ጠላት መንግስት የሚረዳ እና በኢትዮጲያ መንግስት ላይ ጦርነት የሚያደርግ ድርጅት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ እና ተከሣሾችም ከዚህ ግንባር ጋር ግንኙነት ማድረጋቸው በአብላጫ ድምፅም ያልተካደ በመሆኑ በስም ልዩነት ብቻ ተከሣሾችን ከወንጀል አድራጐታቸው ለመጠየቅ በቂ ምክንያት የለም በሚል ብቻ ክሱን ውድቅ ማድረጉ በእኔ እምነት ተገቢ ሆኖ አልታየኝም በሌላ በኩል ቅንጅት የተሰኘው ድርጅት በሰጣቸው በሰጣቸው ውክልና በሌላ በኩል ቅንጅት የተባለው ድርጅት በሰጣቸው ውክልና በአለም አቀፍ ደረጃ ድርጅቱን ወክለው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ 40ኛ እና 44ኛ ተከሣሾች የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር የተሰኘው ድርጅት ከሚገኝበት ዩኤርትራ ግዛት ድረስ በመሔድ ለግንባሩ ያላቸው ድጋፍ ከኤርትራ መንግስት ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት፣ እንዲሁም ግንባሩን በሰው ሀይል እና በማቴሪያል ለመርዳት ቃል መግባታቸውን እና የገንዘብ ድጋፍም ማበርከታቸው በምስክሮች የተነገረ ከመሆኑ አንጻር በተከሣሾች እና በግንባሩ የነበረውን ግንኙነት የሚያጠናክር ሆኖ ነው የሚታየው፣ የ40ኛ እና የ44ኛ ተከሣሾች በዚሁ የወንጀል ክስ አለመከሰሳቸው ሌሎችን ከወንጀል አድራጐታቸው ነጻ አያደርጋቸውም የሚል እምነት አለኝ በመሆኑም ከፍ ብለው በተገለፁት የህግ እና የፍሬ ነገር ምክንያቶች በአብላጫው ድምፅ ከተሰጠው ብይን በሀሳብ ተለይቻለሁ:: የሀሳብ ልዩነት እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 የተመለከተው ዳኛ 7ኛውን ክስ በተመለከተ በአብላጫው ድምፅ ከተሰጠው ብይን በሚከተለው አኳኋን በሀሳብ ተለይቻለሁ:: ተከሣሾች ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት ስር ተሰስበው እና አድማ በማድረግ ድርጅቱን ለህገ ወጥ አላማቸው መጠቀሚያ በማድረግ ከአንድ ጉሳ የመጡ ናቸው የሚሏቸውን የህብረተሰብ



Scanned by CamScanner

ቸራል እና የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር አባል እና ደጋፊ ሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች የዘር ማንነታቸው እና የፖለቲካ አቋማቸውን መሰረት በማድረግ የወንጀል ህግ 32/1/ሀ/ለ 38/27/1 269/ሀ/ ላይ የተመለከተውን ተላልፈው የዘር ማጠፋት ሙከራ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ የቀረበባቸው ሆኑ፣ አቃቤ ህግ ክሱን ለማስረዳት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርበው ነበሩ ተዋል፡፡ የቀረቡት የአቃቤ ህግ የሰነድ ማስረጃዎች

1) 1ኛ ቅንጅት የተሰኘው ድርጅት ለኢትዮጵያ ህዝብ የተደረገ የሰላማዊ የትግል ጥሪ በሚል ርእስ የሰጠ መመሪያ ሲሆን በመመሪያው በተላለፉት ውሳኔዎች መካከል የኢ.ህ.አ.ዲ.ግ አባላት እና ደጋፊዎች የሚሏቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ህዝቡ ከማህበራዊ ኑሮ እንዲያገላቸው ውሳኔ የተላለፈበት ክፍል ይገኝበታል፡፡
2) በ4ኛው ተከሣሽ መኖሪያ ቤት የተገኘ እና የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት እና የገዢው ፓርቲ አመራሮች እንዲገደሉ የተወሰነበት እና ስም ዝርዝራቸው የተመለከተበት፣
3) ግንቦት 10 ቀን 97 ዓ.ም በወጣው የአዲስ ዜና ጋዜጣ እትም የቅንጅት መሪዎች በሞት ጥላ ስር ናቸው በሚል ርእስ ከ 70 እስከ 72 ተከሣሾች የተሳተፉበት ህትመት ላይ ቁጥራቸው 11 የሚጠጋ የትግራይ ብሔር ተወላጆች የቅንጅት መሪዎችን በመርዝ ለመግደል አዲስ አበባ መግባታቸውን የሚያትት ሀተታ የሰፈረበት፣
4) ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ.ም አባይ በተባለው ጋዜጣ በ86ኛ ተከሣሽ አሳታሚነት እና በ87ኛው ተከሣሽ አዘጋጅነት ታትሞ በወጣው የጋዜጣው ርእስ አንቀፅ ፖለቲካን መሰረት ያደረገ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲፈፀም በማሰብ የፌደራል ስርአቱ በአንድ ብሔር ስር የተጠቀለለ እና ሌሎችን ብሔር ብሔረሰቦች ያልተካተቱበት በተለይም የአማራ የኦሮሞ ብሔሮች ከሌሎች ጋር የተዘነጉበት ስርአት አስመስሎ በማቅረብ የዘር ማጥፋት ወንጀል ቅስቀሳ የተደረገበት፣ እንዲሁም
5) 29ኛ ተከሣሽ ቅንጅትን ወክሎ በአሰላ ከተማ ባደረገው የምርጫ ቅስቀሳ የፌደራል መንግስቱ ስልጣን በትግራይ ብሔር ተወላጆች ብቻ ተጠቅልሎ የተያዘ በማስመሰል እና በዘር የተያዘውን ስልጣን ለማስመለስ በሚል ህዝቡ ለጥላቻ እና ለበቀል እንዲነሳሳ መቀስቀሱን፣ እንዲሁም ተከሣሹ በመስቀል አደባባይ ተገኝቶ በወቅቱ ለነበረው ህዝብ በጉሳ በዘር ስልጣን በቤተሰብ በአምቻ

እና በኃብቻ እየገዛ እየታለለ ይገኛል ያለውን የወያኔ መንግስት በህዝቡ ጡንቻ ወደመጣበት ጫካ ይመለሳል በማለት ሲቀሰቅስ የሚያሳይ የቪዲዮ ካሴት ይገኝበታል ከዚህም በተጨማሪ ክሱን ያስረዱልኛል ብሎ አቃቤ ህግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮች በወንጀል ድርጊቱ ሰለባ የሆነ እና ከፍተኛ የአካል እና የህሊና ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት የደረሰባቸው ሲሆኑ ተከሣሾቹ በመሩት እና ባስተባበሩት ይሔው የወንጀል ድርጊት ነር ሁሴን እንድሪስ የተባለው የትግራይ ብሔር ተወላጅ የዘር ማንነቱን ብቻ ምክንያት በማድረግ በድንጋይ እና በገጀራ ተደብድቦ ለሞት የሚያበቃ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሱበት በራሱ አንደበት እና በሌሎች ምስክሮች ተነግሯል፡፡ ኮለኔል አርአያ ገ/ዩሀንስ የተባለው ሌላው የትግራይ ብሔር ተወላጅ መኖሪያ ቤቱ ከነሙሉ ንብረቱ እንዲቃጠል መደረጉን እና በራሱም ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እንዳደረሰበት፣ እንዲሁም በክሱ ላይ ስማቸው ያልተዘረዘሩ እና የትግራይ ብሔር ተወላጆች እና የኢ.ህ.አ.ዲ.ግ ደጋፊዎች እና አባላት የሆኑ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተከሣሾቹ የወንጀል አድራጐት ከፍተኛ የህሊና እና የአካል ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት የደረሰባቸው እንዳሉ በአቃቤ ህግ ምስክሮች ተነግሯል፡፡ ይሕ አድራጐት የሚያመለክተው ተከሣሾች የአንድ ብሔር ተወላጅ ናቸው በሚሏቸው እና የኢ.ህ.አ.ዲ.ግ ደጋፊ አባላት ላይ ተከታዮቻቸው እና ደጋፊዎቻቸው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲፈፅሙ እና በእነዚህ ህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ማንነታቸውን እና የፖለቲካ አቋማቸውን ምክንያት በማድረግ በአካላቸው በህሊናቸው እና በንብረታቸው ላይ ጉዳት እንዲደርስባቸው እንዲሁም ከህብረተሰቡ ማህበራዊ ኑሮ እንዲገለሉ የሚያደርግ በአድማ እንዲሁም በግብራበርነት የወንጀል ሀሳብ እና ተግባር መክሩ ወንጀል መፈፀማቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይም እንደ ህጉ አነጋገር በሰላም ጊዜ በብሔር በብሔረሰብ በጐሳ በዘር በፖለቲካ አንድ የሆነውን ቡድን

በሙሉ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የጥፋትን ድርጊት ለማደራጀት፣ ትእዛዝ ለመስጠት ወይም ድርጊቱን በመፈፀም በማናቸውም ሁኔታ የማህበረተሰቡን አባሎች የገደለ አካላዊ ወይም ህሊናዊ ጤንነታቸውን የጎዳ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም ያጠፋ ማንኛውም ሰው በዘር ማጥፋት ወንጀል ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል:: በተከሣሾቹ ላይ የተጠቀሰው ይሔው ህግ ከተከሣሾቹ የወንጀል አድራጐት ጋር ሲነጻጸር ተከሣሾቹ የአንድ ብሔር ተወላጅ የሆኑት እና የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ደጋፊዎች ወይም አባሎች የሆኑትን ለመግደል በማሰብ የግድያ ሙከራ ወንጀል መፈፀማቸውን እንዲሁም በእነዚሁ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የደረሰውን አካላዊ ህሊናዊ ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት መፈፀማባቸውን በተለይም የወንጀል አፈጻጸማቸው ሲታይ ይህ የትግሬ ቤት ነው ብለው በማለት እሳት በማቀጣጠል ንብረት እንዲወድም በማድረጋቸው እንዲሁም ምንም አይነት የመከላከል ሁኔታ እንኳን ባላሳየ ግለሰብ ላይ ብሔሩን ምክንያት በማድረግ ብቻ ለሞት በሚያበቃ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስበት በአድማ እና በግብረአበርነት የፈፀሙትን ወንጀል ጉዳይን ለማስረዳት ከቀረቡት ሰነዶች እና ከተሰጠው የምስክርነት ቃል አኳያ ተከሣሾች የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈፀማቸውን መረዳት ይቻላል በዚህ የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም የተከሣሾች ሀሳብ የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመፈፀም እንደነበረ ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት አመራሮች ደጋፊዎች እና አባሎች ሲያስተጋቡ የነበረውን ቅስቀሳ የተሰጠው የማግለል መመሪያ ከተከሣሾቹ አድራጐት ጋር ሲታይ ተከሣሾቹ ወንጀሉን ለመፈፀም ሙሉ ሀሳብ እንደነበራቸው በዚህ ሀሳባቸው በመስማማት እና በመምራት የተጐጂዎችን የዘር ማጥፋት እና የፖለቲካ አቋም የዘር ማንነት እና የፖለቲካ አቋም እየጠሩ በሉት እያሉ በቃል በመናገር እና የተፈለገውን ጉዳት ሲያደርሱ መታየታቸው በበኩሌ ተከሣሾች የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመፈፀም የነበራቸውን ቁርጥኝነት የሚያመለክት ነው:: አንድ የወንጀል ድርጊት



Scanned by CamScanner

ተፈፅሟል የሚባለው በተጉጂዎች ብዛት ወይም ማነስ ሳይሆን የወንጀል አድራጊው ሀሳብ እና የደረሰው ጉዳት እና አድራጎቱ የተላለፈውን ህግ መሰረት በማድረግ ነው:: በተያያዘው ጉዳይ ላይ ተፈፀመ የተባለው የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል የወንጀሉ አድራጊዎች እስከመጨረሻው ለማሳካት ያልቻሉበት ምክንያት የወንጀሉ ውጤት በተወሰኑ ወገኖች ላይ ተገድቦ እንዲቀር የተደረገው እንደ ምስክሮቹ አነጋገር ከተከሣሾቹ አቅም በላይ በሆነ ሌላ ውጫዊ ሀይል በመሆኑ ተከሣሾች ይሔንን ሀሳብ እንደነበራቸው ወይም ውጤቱ የተወሰኑትን ግለሰቦች ብቻ በማጥፋት የተገደበ እንዲሆን ፈልገው እንደነበር ከሁኔታው መገመት አይቻልም በመሆኑም በተከሣሾች ላይ የቀረበው ክስ በአቃቤ ህግ ማስረጃ የተደገፈ ነው የሚል እምነት ስላለኝ ማስረጃው የወንጀል አድራጐታቸውን ባረጋገጠባቸው ተከሣሾች ላይ እንዲከላከሉ እንዲሁም ማስረጃው ባላረጋገጠባቸው ተከሣሾች በነጻ እንዲሰናበቱ ብይን መስጠት ይገባ ነበር በሚል ክሱን ውድቅ በማድረግ በአብላጫው ድምፅ ከተሰጠው ብይን በሀሳብ ተለይቻለሁ::

## ት ዕ ዛ ዝ

ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እየተከራከሩ ካሉት ተከሣሾች መካከል መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ እንዲሰናበቱ ብይን የተሰጣቸው ተከሣሾች

1) ስለሺ አንዳርጌ
2) ሀብታሙ ገ/ሕይወት
3) አስራት ጣሴ
4) ኮለኔር ታምሩ ጉልላት
5) በቀለ ግርማ
6) ታዲዮስ በየነ
7) አለማየሁ መስለ
8) ሰብለወርቅ ታደሰ
9) እስክንድር ነጋ
10) ፋሲል የኔአለም
11) ሲሳይ አጌና



Scanned by CamScanner

12) ሰርካለም ፋሲል
13) ደረጀ ሀብተ ወልድ
14) ናርዶስ መአዛ
15) ዘካሪያስ ተስፋዬ
16) ፈለቀ ጥበቡ
17) ታዬ ጌታቸው
18) እዮብ በቀለ
19) ካሳ ታደሰ
20) ወጣት ፋቃዱ አሰፋ
21) ወጣት ምናለ ገብሬ
22) ገዛኸኝ ተስፋዬ
23) ተስፋዬ ጋንታ
24) ውድነህ ተመስገን
25) ወንድሜነህ ደሳለኝ

1. የተባሉት በዛሬው እለት ከእስራት እንዲፈቱ የመፍቻ ዋራንት ለማረሚያ ቤት ይጻፍ ብለናል::
2. ጉዳያቸውን በሌሉበት በመታየት ላይ ያሉ እና የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጣቸው ተከሣሾች ላይ አቃቤ ህግ የቅጣት ሀሳቡን ለተለዋጩ ቀጠሮ ያቅርብ ብለናል::
3. 94ኛ እና 95ኛ ተከሣሾች በቀር ሌሎች ተከሣሾች ክሱ እንደተጀመረ ለክሱ አለን የሚሉትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ የታዘዘ ቢሆንም አላቀረቡም የክሱን ከባድነት ግምት ውስጥ በማስገባት አሁንም አለን የሚሉትን መከላከያ እና ዝርዝር እና ጭብጡን ተለዋጭ ቀጠሮ በፊት ሬጅስትራር ገቢ ያድርጉ ምስክሮች የሚያቀርቡም ከሆነ ከቀጠሮ በፊት መጥሪያ ያድርሱ
4. 94ኛ እና 95ኛ ተከሣሾችም አለን የሚሉትን ማስረጃ ከተለዋጭ ቀጠሮ በፊት በሬጅስትራር በኩል ገቢ እንዲያደርጉ ምስክሮችን የሚያቀርቡም ከሆነ ከቀጣይ ቀጠሮ በፊት መጥሪያ ያድርሱ ብለናል::



Scanned by CamScanner

5. አባይ አሳታሚ እና አረጋዊ የህትመት እና ማስታወቂያ የተባሉ አሳታሚ ድርጅቶች ተከሰው ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም ድርጅቶቹን በመወከል የተከራከረ ሰው ወይም ተወካይ ባመኖሩ በእነዚህ ተከሳሾች ምንም አይነት ብይን መስጠት አልተቻለም በመሆኑም አቃቤ ህግ ድርጅቶቹን በመወከል ሊከራከር ስለሚገባው ሰው ያለውን ሃሳብ በተለዋጭ ቀጠሮ ለችሎት ያቅርብ ብለናል፡፡

6. እንዲከላከሉ ብይን የተሰጣቸው 4ቱ የህትመት እና የህትመት ድርጅቶች ማለትም ፋሲል የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ሲሳይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት እና ዘካሪያስ አሳታሚ የተባሉት ይሔ የድርጅቱ ባለቤት እና ስራ አስኪያጆች ከመነሻው ጀምሮ በክሱ ተካፋይ የነበሩ እንደመሆናቸው መጠን በተለዋጭ ቀጠሮ ወይም ወኪሎቻቸው ድርጅቱን በሚመለከተ አለን የሚሉትን መከላከያ እንዲያቀርቡ አዘናል፡፡ የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ሀላፊ ተከሣሽ ካሳሁን ከበደን ለምን ከእስራቱ እንዳለቀቀው ተከሣሹን ይዞ በመቅረብ እንዲያስረዳ የማረሚያ ቤት ተወካይ ማነው? ዋስትና መብት አለን የምትሉ ተከሣሾች በፅ/ቤት በኩል አቅርቡ፡፡ የማረሚያ ቤት ተወካይ ተከሣሹን ከሰአት ይዛችሁ በመቅረብ ከአርብ ጀምሮ 4 ቀን በራሳችሁ ስልጣን ለምን እንዳቆያችሁት ስለዚህ ቀርቦ ያስረዳ፡፡

2ኛ ወንጀል ችሎት
መዝገብ ቁጥር 43246
ሰኔ 4 ቀን 1999

ዳኞች:- አዲል አህመድ
ልዑል ገ/ማርያም
መሐመድ አሚን ሣኒ

ከሣሽ :- የፌደራል አቃቢ ህግ ሽመልስ ከማል፣ ሚካኤል ተክሉ እና አብራሀም ተጠምቀ
ተከሣሾች:- እነ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል

- ሁሉም ተከሣሾች ተሟልተው ቀርበዋል በዋስ ያሉ ተከሣሾች ዳዊት ፋሲል በዋስ ቀርቦአል የሲሣይ አሣታሚ ድርጅት ተወካይ ሲሳይ አጌና ቀርቧል የሰርካለም አሳታሚ ድርጅት ተወካይ ሰርካለም ፋሲል ቀርባለች ፋሲል አሳታሚ ባለፉት ተከታታይ ቀጠሮዎች አልቀረበም ይኸው ተመዝግቧል የነፃነት እና የዳንኤል ጠበቃ ተከታታይ ቀጠሮዎች አልቀረበም ይኸው ተመዝግቧል የነፃነት እና የዳንኤል ጠበቃ ነዎት ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቀርበዋል አቶ ወንድአወቅ የማን ጠበቃ ነዎት ያስመዝግቡ
- የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው ካስመዘገብኩት አንድ አራት ሰዎች እንደገና እንትን ብለውኛል ስለዚህ የ26ኛ ተከሣሽ መቶ አለቃ አለማየሁ የኔነህ የ96ኛ ተከሣሽ መስፍን ዴቢሣ የ97ኛ ተከሣሽ ብርሃኑ አለማየሁ 98ኛ ተከሣሽ ውድነህ ጆዲ 112ኛ ተከሣሽ መላኩ ሱንቻ 113ኛ ተከሣሽ አብዮት ዋቅጅራ 117ኛ ተከሣሽ ዳንኤል በሪሁን 36ኛ ተከሣሽ መቶ አለቃ ግርማ አማረ 34ኛ ተከሣሽ መላኩ ፋንታዬ 118ኛ ተከሣሽ ቅድስት በቀለ 72ኛ ተከሣሽ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን 75ኛ ተከሣሽ አንዱአለም አየለ 78ኛ ተከሣሽ ወናክሰገድ ዘለቀ 82ኛ ተከሣሽ ዳዊት ፋሲል 89ኛ ተከሣሽ ዳዊት ከበደ 15 ናቸው::
- መዝገቡ የተቀጠረው በዋነኛነት ለሁለት ነገሮች ነው 1ኛው ተከሣሾች የቪዲዮ እና የኦዲዮ ማስረጃዎቹን ተመልክተው አለን የሚሉትን መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ከቀጠሮ በፊት እንዲያቀርቡ ታዞ 1ኛ ይኸንኑ መፈፀም ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ 2ኛ ባለፈው ዳንኤል እና ነፃነት የምስክሮችን ስም ዝርዝር በሚመለከት ለአቃቢ ሕግ ሊደርስ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ ለመስጠት ነው በዚሁ መሠረት ማረሚያ ቤቱ ይኸንን ስለመፈፀሙ እናረጋግጣለን



Scanned by CamScanner

ከዛ በኋላ ወደሚቀጥለው ስራ እንሄዳለን ማረሚያ ቤት ወይም ተወካይ እስኪ አንብብልና

- ለከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት አዲስ አበባ ቀን 4/10/99 እነ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል በተከሰሱበት ህገመንግሥታዊ ስርአትን በሀይል ለመለወጥ መሞከር ወንጀል ክስ ጉዳይ ፍ/ቤቱ በ24/08/99 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መሠረት የሰጠውን ትዕዛዝ እናስታውሳለን በዚህ መሠረት ተከሣሾቹ በ24/09/99 ዓ.ም. ከሰአት በኋላ በመጀመር ቅዳሜና እሁድ ጨምሮ የኦዲዮ እና የቪዲዮ ካሴቶችን አሣይተን እና አስደምጠን ያጠናቀቅን ሲሆን የጋራ ውይይቱን እንዲያደርጉ በ27/09/99 ዓ.ም. ቦጋ አዘጋጅተን እንዲወያዩ ብንጠይቃቸውም ታራሚዎቹ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል በህመም ምክንያት በሆስፒታል በህክምና ላይ ስለሚገኙ እና በውይይቱ ወቅት ወሣኝ ተከሣሽ ናቸው በማለት ውይይቱን ለመቀጠል ባለመቻላቸው በእለቱ ውይይቱን ማድረግ አልተቻለም ስለሆነም ተከሣሾቹ ይኸንን በመግለጽ ለፍ/ቤት ማመልከቻ አቅርበው ፍ/ቤቱም በቀረበው ማመልከቻ ላይ ትዕዛዝ የሰጠበት በመሆኑ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካቾቹ በ29/09/99 ዓ.ም. ተነቦላቸዋል ስለዚህ የጋራ ውይይቱን በ30/9/99 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ3:00 ሰአት እስከ 7:30 ሰአት ድረስ ያከናወኑ መሆኑን በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት መፈፀማችንን ለክቡር ፍ/ቤት እንገልጻለን ከሰላምታ ጋር።
- አንሰማም በስርአቱ ስነ ስርአት ያድርጉ አናዳምጥም ለምንድን ነው የማናዳምጠው የሰጠነው ትዕዛዝ አለ ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ነው የሰጠነው ይኸ ትዕዛዝ ምንድን ነው 1ኛ ባቀረባችሁት መሠረት እንወያይ ከተወያየን በኋላ ያለንን ሀሣብ ለችሎቱ እንገልጻለን ባላችሁት መሠረት ችሎቱ እንድትወያዩ ማረሚያ ቤቱን አዟል ማረሚያ ቤቱ ደግሞ ተወያይተዋል ብሏል ሌላው ፍ/ቤቱ ያዘዘው ቪዲዮ ካሴቱን ለመመልከት እንዲሰጣችሁ ጠይቃችኋል ፍ/ቤቱ ግምቱ ምንድን ነው የሚሰጠው አይተው ለመከላከያ ያስችላችኋል በሚል ሀሳባቸውንም ለማወቅ የረዳዋል በሚል ችሎቱ ይኸንን ለብቻችሁ እንድትመለከቱ አድርጉአል ማረሚያ ቤቱ ይኸንንም መፈፀሙን አረጋግጦአል ስለዚህ እኛ በዚህ መሠረት

አንዴ ቆዩ እባክዎትን ያው የተለመደ ነው የችሎት ስርአት አይከበርም ያው አዲስ አይደለም ስለዚህ ቢያንስ ልንደማመጥ ነው የሚገባው ይኸ እንደፈለጋችሁ መናገሩ ያው የከረምንበት ነው ሆኖም ቢያንስ ቢያንስ ይኸ ችሎት ልትፈሩት ነበር የሚገባው ይኸ አልሆነም ዛሬ ደግሞ በተ . . . መልክ ነው እየረበሻችሁ ያላችሁት ስለዚህ መደማመጥ ነው የሚገባው ችሎቱ፡ ችሎት በመድፈር ግዜውን ሊያጠፋ አይፈልግም ችሎት በመድፈር ተከሣሾችን ለመቅጣት ጊዜ ለማጥፋት አይፈልግም ይኸ ቢፈልግ ኖሮ ይኸ አላማ ቢኖር ኖሮ ብዙ ነገር ነበር ማድረግ የሚገባው ስለዚህ አላማችሁ አልገባነም አሁን በስነ ስርአት ቁጭ በሉ

- አይ ይቁሙ መቆም እኮ ፍ/ቤት ማንኛውም ተከሣሽ ዞሮ ዞሮ ቆሞ ነው የሚከራከረው ሆኖም እኛ ይኸንን ከሁኔታው ግምት ውስጥ በማስገባት ነው እና መቆማችሁ ክፋት ያለው ነገር አይደለም መቆም ትችላላችሁ ስርአቱም እንደውም ተከሣሽ ቆሞ ነው ለችሎቱ የሚናገረው ስለዚህ ችግር የለውም ዞሮ ዞሮ ማስረጃው ሬጂስትራር ገቢ አልሆነም ስለዚህ እኛ እንዳላቀረባችሁ ነው የምንቆጥረው
- ማስረጃ አቅርባችኋል አላቀረባችሁም?
- ፍ/ቤቱ በዋነኛነት የቀጠረው ማስረጃን በሚመለከት ምክንያቱም ተከሣሾችን ለረጅም ጊዜ ማስረጃን በሚመለከት እንዲያቀርቡ ቶሎሬት አድርጐ ቀጥሮአል ይኸንን አጀንዳ የቀጠረውም በዋነሃነት ማስረጃውን አቀራረብ እንዴት ነው ማስረጃ ካላችሁ እንዴት ነው የምንሰማው አላችሁ ወይስ የላችሁም ሀሣባችሁን አሣውቁን ብለን ለረጅም ጊዜ ለነገሩ ይኸ የሚሆነው ክስ ከደረሰባችሁ ቀን ክሱ እና ማስረጃው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ለአለፋት አንድ አመት ማለት ነው እንድታቀርቡ አዟል እስከ አሁን አልቀረበም ብይኑን ከሰጠ በኋላ ማስረጃ እንዲቀርብልን አዘናል እስከ አሁን አለቀረበም ስለዚህ እኛ በዚህ ላይ ማስረጃን በሚመለከት ተገቢውን ነገር ካልን በኋላ ያለመቅረቡ ምንድን ነው ውጤቱ ካልን በኋላ ሌሎች ነገሮች ካሉ እንሰማለን ስለዚህ ለተወሰነ ደቂቃ ቆይተን እንመለሣለን
- እስከ አሁን ድረስ የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር ያላቀረቡ ተከሣሾችን በሚመለከት የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

ፍ/ቤቱ በተከሣሾች ላይ የተመሠረተው ክስ ከነ ማስረጃው እንዲደርሣቸው ካደረገ በኋላ አለን የሚሉትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ከመጀመሪያው ቀጠሮ ጀምሮ የታዘዘ

ቢሆንም ፍ/ቤቱ እኛን ለመዳኘት ስልጣን የለውም በመሆኑም እንከራከርም በማለት የቆዩ ሲሆን ፍ/ቤቱ የክሱን ከባድ መሆን ግምት ውስጥ በማስገባት ይኸንኑ ትዕዛዝ በተደጋጋሚ በማስታወስ ማስረጃዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ሲያዝ ቆይቷል በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ሊከላከሉ የሚገባቸውን ተከሣሾች በመለየት ብይን ከሰጠም በኋላ እነዚህ ተከሣሾች አለን የሚሉትን መከላከያ ማስረጃ ለሬጅስትራር ገቢ እንዲያደርጉ በድጋሚ ያዘዘ ሲሆን ተከሣሾች የተሰጠው ብይን ይድረሰን በጋራ ለመመካከር ይፈቀድልን ቪዲዮ ካሴቱ እና ኦዲዮ ካሴቱ ይድረሰን የሚሉ ጥያቄዎችን እንደ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ለችሎቱ ጥያቄ አቅርበዋል አንድ ተከሣሽ የመከላከያ ማስረጃውን ዝርዝር የሚያቀርበው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 124 መሠረት ክሱ እና ማስረጃው እንደደረሰው ሲሆን ቢያንስ ክሱ በሚሰማበት ቀን እና ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ ክሱ ከመሰማቱ ቀን በፊት ማስረጃዎቻቸውን ለሬጅስትራር ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን ተከሣሾች ሲያቀርቧቸው የነበሩ ጥያቄዎች የመከላከያ ማስረጃን ለፍ/ቤቱ ከማቅረብ ጋር ግንኙነት ያላቸው አልነበሩም ሆኖም ግን ለተከሣሾች የመከላከል እድላቸውን በማስፋት በጠየቁት መልኩ ብይን እንዲደርሳቸው በጋራ ሆነው መወያየት እንዲችሉም ማረሚያ ቤቱ እንዲያመቻችላቸው እና እዚህ በግልጽ ችሎት የታየው የቪዲዮ እና ኦዲዮ ካሴትንም ዳግም ለብቻቸው በማረሚያ ቤቱ እንዲመለከቱ እና እንዲያዳምጡ በታዘዘው መሠረት ማረሚያ ቤቱም ይኸንን ስለማከናወኑ በ4/10/99 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አረጋግጧል ሆኖመ ግን እስከ አሁንም ፍ/ቤቱ ባዘዘው መሠረት አለን የሚሉትን ማስረጃዎች ለሬጅስትራርም ሆነ ለችሎቱ አላቀረቡም ይኸም የሚያሳየው እነዚህ ተከሣሾች መከላከያ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን ነው በመሆኑም የተከሣሾች የመከላከል እድል ታልፏል በሌላ በኩል የሊሳይዬ አላታሚ ተወካይ እና የሰርካለም አሳታሚ ተወካይ አርብ ሰኔ 1 ቀን 1999 ዓ.ም. በጽ/ቤት በኩል ባቀረቡት ማመልከቻ የቪዲዮ ካሴቱ እና ማረሚያ ቤት የሚገኙት ማስታወሻዎቻቸው እንዲደርሣቸው ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን የቪዲዮ ካሴቶች አጠቃላይ ይዘት በብይኑ ከመስፈሩም በላይ ማስታወሻ ተብሎ የቀረበው ጥያቄም አግባብነት የሌለው ሲሆን የፍ/ቤቱ ቀጠሮ ሰኔ 4 ቀን 1999 ሆኖ ጥያቄው አርብ ሰኔ 1 መቅረቡ የመከላከያ ማስረጃ የሌላቸው ነው የሚለውን ግምት ወስደናል

በመሆኑም እነዚህ ተከሣሾች መከላከያ ማስረጃ እንደሌላቸው በመቁጠር የመከላከል እድላቸው ታልፏል ስለሆነም ቀጥሎ ያለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡ -

## ው ሣ ኔ

ከፍ ሲል በዝርዝር እንደተገለፀው ተከሣሾች የመከላከያ እድላቸውን ተጠቅመው መከላከል አልቻሉም አንድ ተከሣሽ የተነገረበትን ክስ በማስረጃ ተረጋግጦ እንዲከላከል ታዞ ካልተከላከለ የጥፋተኛነት ውሣኔ ሊሰጠው እንደሚገባ ግልጽ ነው ስለዚህ ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን እንዲከላከሉ ታዞ ባልተከላከሉ ተከሣሾች 1ኛ ክስን በተመለከተ 1ኛ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል 2ኛ አቶ አባይነህ ብርሀኑ 3ኛ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ 4ኛ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው 5ኛ ዶ/ር ሀይሉ አርአያ 6ኛ አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል 7ኛ አቶ ስለሺ ጠና 8ኛ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ 9ኛ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ 10ኛ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም 11ኛ ዶ/ር ያቆም ኃ/ማርያም 12ኛ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሣ 13ኛ አቶ አስቻለው ከተማ 14ኛ ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ 15ኛ አቶ ገ/ፃዲቅ ኃ/ማርያም 16ኛ አቶ አሰፋ ኃ/ወልድ 17ኛ አቶ ብሩክ ከበደ 18ኛ አቶ ታምራት ታረቀኝ 19ኛ አቶ እንዱአለም አራጌ 20ኛ ወ/ሮ ንግስት ገ/ሕይወት 21ኛ ደበበ እሸቱ 22ኛ የኔነህ ሙላት 23ኛ ማሙሸት አማረ 24ኛ እንተነህ ሙሉጌታ 25ኛ መላኩ ፈንታዬ 26ኛ መስፍን ደቤሣ 27ኛ ብርሀኑ አለማየሁ 28ኛ ውድነህ ደቺ 29ኛ አብዮት ዋቅጅራ 30ኛ መላኩ ኡንቻ 31ኛ ዳንኤል በሪሁን 32ኛ ተስፋዬ ታሪኩ 33ኛ ዋልተንጉስ አስናቀ 34ኛ ሙሉ ጋሾ ወንድሙ 35ኛ እንዱአለም አየለ 36ኛ መስፍን ተስፋዬ 37ኛ ሲሣይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት 38ኛ ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት በ1ኛ ክስ እንዲከላከሉ በተበየነው የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1 ሀ ለ 38 34 27/1 እና 2 38/1 2 258 ስር ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥተናል በሌላ በኩል በዚሁ ድርጊስ ክስ ከተመሠረተባቸው 1ኛ ፋሲል የሕትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት 2ኛ ሰርካለም አሣታሚ ድርጅት 3ኛ ወናክሰገድ ዘለቀ በብይኑ በተመለከተው መሠረት 32/1 ሀ ለ 34 46 እና 257/ሀ ስር በተመለከተው መሠረት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥተናል እንዲሁም በ1ኛ ክስ በተመለከተው መሠረት 32/1 ሀ ለ 34 46 እና 486/ሀ ስር በተመለከተው መሠረት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥተናል 2ኛ ክስን በሚመለከት 1ኛ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል 2ኛ አባይነህ ብርሀኑ አርአያ 3ኛ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ 4ኛ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው 5ኛ ዶ/ር ሀይሉ አርአያ 6ኛ አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል 7ኛ አቶ ስለሺ ጠና 8ኛ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ 9ኛ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ 10ኛ ዶ/ር ያቆብ ኃ/ማርያም 11ኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ 12ኛ አቶ አስቻለው ከተማ 13ኛ ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ 14ኛ



Scanned by CamScanner

አቶ ገ/ፃዲቅ ኃ/ማርያም 15ኛ አቶ አሰፋ ኃ/ወልድ 16ኛ አቶ ብሩክ ከበደ 17ኛ አቶ ታምራት ታረቀኝ 18ኛ አቶ አንዱአለም አራጌ 19ኛ ወ/ሮ ንግሥት ገ/ሕይወት 20ኛ ደበበ እሸቱ 21ኛ የኔነህ ሙላት ቡብይኑ በተመለከተው መሠረት በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1 ሀ ለ 38 እና 27/1 239 ስር የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተንባቸዋል 3ኛ ክስን በሚመለከት 1ኛ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል 2ኛ አቶ አባይነህ ብርሃኑ 3ኛ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ 4ኛ ማሙሸት አማረ 5ኛ ተስፋዬ ታሪኩ በብይኑ በተመለከተው መሠረት በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1 ሀ ለ 34 46 እና 486/ሀ ስር በተመለከተው መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተናል 5ኛ ክስን በሚመለከት 1ኛ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል 2ኛ አቶ አባይነህ ብርሃኑ 3ኛ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ 4ኛ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው 5ኛ ዶ/ር ሀይሉ አርአያ 6ኛ አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል 7ኛ አቶ ስለሺ ጠና 8ኛ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ 9ኛ ዶ/ር ያቆብ ኃ/ማርያም 10ኛ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ በብይኑ በተመለከተው የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1 ሀ ለ 27 38 34 247/ሀ እና ሐ 258 ስር በተመለከተው መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተናል በዚሁ የወንጀል ድርጊት ክስ የቀረበበት መስፍን ተስፋዬ በብይኑ በተመለከተው መሠረት በወ/መ/ሕ/ቁ 257/ሀ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥተናል።

## ት ዕ ዛ ዝ

የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸው በጽሁፍ በጽ/ቤት በኩል እስከ ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ያቅርቡ የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ለሀምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም. ቀጠሮ ይዘናል 2ኛ ዳዊት ፋሲልን በሚመለከት ጥፋተኛ የተባለ ስለሆነ የቅጣት ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ማረሚያ ቤቱ እንዲቀይ ታዟል ለማረሚያ ቤት ይፃፍ በሌላ በኩል ባለፈው ሣምንት በቀረበው የማስረጃ አቀራረብ እና የምስክሮችን አቀራረብ በሚመለከት አንዳንድ ተከሣሾች ያቀረቡት እና አቃቤ ሕግ ያቀረበውን ተቃውሞ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ በሚቀጥለው ሳምንት ሰኔ 11 ቀን 1999 ይሰጣል ሰኔ 11 ቀን የሚመጡት ተከሣሾች ዝርዝር ማስረጃ እስከ አሁን ያቀረቡት 1ኛ አቶ በድሩ አደም 2ኛ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን 3ኛ መቶ አለቃ አለማየሁ የኔነህ 4ኛ መብራቱ ከበደ 5ኛ ዳዊት ከበደ 6ኛ መቶ አለቃ ግርማ አማረ 7ኛ ቅድስት በቀለ 8ኛ ዳንኤል በቀለ 9ኛ ነፃነት እነዚህ ዘጠኝ ተከሣሾች በሚቀጥለው ሣምንት ሰኔ 11 ይቀርባሉ ሌሎች ተከሣሾች ሀምሌ 1 ቀን 1999 የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ቀጥረናል ችሎቱ በዚሁ አብቅቷል።



Scanned by CamScanner

2ኛ ወንጀል ችሎት
መዝገብ ቁጥር 43246
ሀምሌ 2 ቀን 1999

ዳኞች:- አዲል አህመድ
ልዑል ገ/ማርያም
መሐመድ አሚን ሣኒ

ከሣሽ :-የፌደራል አቃቢ ህግ ሽመልስ ከማል፣ ሚካኤል ተክሉ እና አብራሀም ተጠምቀ
ተከሣሾች:- እነ ኢንጅነር ሀይሉ ሻወል

ሁሉም ተከሣሾች ቀርበዋል የአንዱ አለም አየለ፣ ወናክሰገድ ዘለቀ፣ ዳዊት ፋሲል፣ መስፍን ደቤሣ፣ ብርሀኑ አለማየሁ፣ ውድነህ ጀልዲ፣ መላኩ ኡንቻ፣ አብዮት ቀቅጅራ እና ዳንኤል በሪሁን ጠበቃ አቶ ወንድአወክ ቀርበዋል ይኸው ተመዝግቦአል መዝገቡ የተቀጠረው የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ፍ/ቤቱ መርምሮ ተገቢውን የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ነው በዚሁ መሠረት ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን የቅጣት አስተያየት ስንጠባበቅ ነበር የቅጣት አስተያየት የቀረበው አሁን ስማቸውን የጠቀስኳቸው ተከሣሾች 9 ተከሣሾች ማለት ነው በጠበቃቸው አማካይነት የቅጣት አስተያየት አቅርበዋል በዚሁ በአቀረቡት የቅጣት አስተያየት የተወሰኑ ነጥቦችን አንስተዋል 1ኛ የቅጣት አስተያየት በጽሁፍ ሊሆን አይገባም 2ኛ የአቃቢ ህግ ሀሣብ ሊደርሰን ይገባል የሚሉ ነጥቦችን በዋነኛነት አንስተዋል በዚሁ መሠረት እኛም የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግን አይተናል የቅጣት ሀሣብ በጽሁፍ ሊሆን አይገባም የሚለው የህግ መሠረት የለውም ግራ ቀኙ የቅጣት ሀሣባቸውን አስተያየታቸውን ያቀርባሉ ይላል ህጉ አስተያየት በጽሁፍም በቃል ከመሆን የሚያግደው ነገር የለም ስለዚህ አስተያየት በጽሁፍ ይቅረብ ማለቱ ከህጉ የወጣ እና የህግ ችግር ያለበት አይደለም በሌላ በኩል ግን የአቃቢ ህጉ አስተያየት ልናውቀው ይገባል ለሚለው በተወሰነ ደረጃ በህጉም ድጋፍ ያለው ሆኖ አግኝተነዋል ይኸንን የአቃቢ ህግን ሀሣብ እንዴት ያውቁታል የሚለው ሲታይ ጽሁፉን ለተከሣሾች በማድረስ ወይም አቃቢ ህጉ የሚሰጠውን አስተያየት በማድመጥ ሊሆን ይችላል ስለዚህ ይኸንን አስተያየት ከማድመጡ በፊት ወደ ውሣኔ መሄድ አልቻልንም በዚሁ መሠረት አቃቢ ህግ የቅጣት ሀሣቡን አሁን በጽሁፍ ይድረስ እና ሌሎች ትዕዛዞች ከመስጠት ያቀረበውን የቅጣት ሀሣብ በችሎት ያነብልናል ከዛ በኋላ በዚህ በቅጣት ሀሣብ ላይ ተከሣሾች ሌሎች ተከሣሾችም እስከ አሁን የቅጣት ሀሣብ ያላቀረቡትም ቢሆን በምንሰጠው በጣም አጭር ቀጠሮ ውስጥ ያላቸውን ሀሣብ በጽሁፍ እንዲያቀርቡ እናዛለን ማለት ነው ስለዚህ አቃቢ ህግ አሁን የቅጣት ሀሣቡን ያነብልናል እናዳምጠዋለን አቶ



Scanned by CamScanner

ወንድአወክ ከዚህ በፊት ያቀረቡት የቅጣት ሀሣብ አለ ስለዚህ እዛ ላይ የሚጨምሩት የሚለውጡት የሚያሻሽሉት ነገር ያለ ከሆነ የተጠበቀ ነው የሚሆነው ስለዚህ አጠር ያለ ቀጠሮ እንሰጣለን ማለት ነው ስለዚህ አቃቢ ህግ የቅጣት ሀሣቡን ለችሎቱ ታነባለህ ሲሣይ አጌና ቀርቦአል ሰርካለም አልቀረበችም ይኸው ተመዝግቦአል

➢ ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት አዲስ አበባ ጉዳዩ በ1954 ዓ.ም የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 149/3 እና ለ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 84 እና 183 እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 85 እና 184 እንዲሁም 258 ድንጋጌ መሠረት ከአቃቢ ህግ የቀረበ ህጋዊ የቅጣት አስተያየት በከሣሽ የፌ/ዓ/ሕ እና በተከሣሾች እነ አቶ ሀይሉ ሻወል መካከል በዚህ ችሎት በመታየት ላይ ባለው የወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ ጉዳያቸው በሌሉበት በመታየት ላይ በነበሩ 5 ተከሣሾች ላይ ከመጋቢት 21 ቀን እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም በነበረው የብይን ማሰማት ሂደት እና ጉዳያቸው ባሉበት በመታየት ላይ ባሉ 41 ተከሣሾች ላይ ሰኔ 4 ቀን 1999 ዓ.ም በነበረው ችሎት በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰረት የግራ ቀኝ የቅጣት ሀሣብ እንዲቀርብ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመከተል የተከሣሾቹ ዝርዝር እና ጥፋተኞቹ የተባሉባቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች በማገናዘብ የሚከተለው የቅጣት አስተያየት ቀርቦአል

➢ 1 - ተከሣሾቹ ጥፋተኞች የተባሉባቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች እና ቅጣታቸው አቃቢ ህግ ታህሣስ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በተከሣሾቹ ላይ ከመሠረተባቸው የወንጀል ክሶች ውስጥ በአራቱ ክሶች ብቻ እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ ለተደጋጋሚ ቀጠሮዎች ተጠብቀው የመከላከያ ማስረጃ ባለማቅረባቸው ህጉን በመከተል የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች **1.1.** በ1ኛ ክስ ላይ የ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ ለ 38 34 27/1 እና 238/1 እና 2 እና 258 ድንጋጌ ስር

1.2- በ2ኛ ክስ ላይ የ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1 ሀ ለ 38 27/1 እና 239 ድንጋጌ ስር

1.3- በ3ኛ ክስ ላይ በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1 ሀ ለ 38 እና 240/1 ሀ ድንጋጌ ስር

1.4- በ5ኛ ክስ ላይ የ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1 ሀ ለ 27 38 34 247/ሀ እና ሐ እና 258 ድንጋጌ ስር



Scanned by CamScanner

1.5 እንዲሁም የተወሰኑት ተከሣሾች በ1ኛ ክስ ላይ የተጠቀሰባቸውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 113/2 መሠረት በመለወጥ በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1 ሀ ለ 46 እና 257/ሀ እና 486/ሀ ድንጋጌ ስር መሆናቸው ከመዝገቡ ለመረዳት ይቻላል

2 - ተከሣሾቹ ጥፋተኞች የተባሉባቸውን የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች የቅጣታቸው መጠን ሲታይ

2.1- በ1ኛ ክስ አንፃር ጥፋተኞች የተባሉባቸው ድንጋጌዎች በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑን

2.2 በ2ኛ ክስ አንፃር ጥፋተኞች የተባሉበት ድንጋጌ እስከ 15 አመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን

2.3- በ3ኛ ክስ አንፃር ጥፋተኞች የተባለበት ድንጋጌ ከ10 እስከ 25 አመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ

2.4 በ5ኛ ክስ አንፃር ጥፋተኞች የተባሉበት ድንጋጌ ከ5 እስከ 25 አመት ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ በሆነ ግዜ በተለይም በጦርነት ወይም ጦርነት አስጊ በሆነበት ግዜ እንደሆነ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑ

2.5- በ1ኛ ክስ አንፃር በአቃቤ ህግ የተጠቀሰባቸውን የክስ ድንጋጌ በመለወጥ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 257 እና 486 ድንጋጌዎች በቀላል እስራት ወይም ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ ከፍ ያለ እንደሆነ ከ3 እና ከ10 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ መሆናቸው

2.6- በ1ኛ እና 5ኛ ክሶች አንፃር እንደ በአቃቤ ህግ ክስ አመሰራረት በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 258 ድንጋጌ ስር ጭምር የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ እና በዚህ ህግ መሠረት በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ የወንጀል ህጉ በደነገገባቸው የአቃቤ ህግ ክሶች ላይ ከ ሀ - መ የተዘረዘሩትን የወንጀል አፈፃፀሞች ተሟልተው በሚገኙበት ሁኔታ የሞት ቅጣት ሊወሰን የሚገባ መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ እና እነዚህ ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታዎች በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ትና ውጤቱ ላይ መሟላታቸው በአቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ተረጋግጦ ... ባ መተላለፍ አንፃር የጥፋተኝነት ውሣኔ

የተሰጠበት ከመሆኑ አኳያ እንደድንጋጌው መሠረት ሊወሰንባቸው የሚገባ መሆኑ

2.7- እንዲሁም በ1ኛ ክስ አንፃር በተጠቀሰባቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የፕሬስ ማተሚያ ድርጅቶች ጥፋተኞች በተባሉት ህግ ድንጋጌ አንፃር እስከ ብር አምስት መቶ ሺ ብር የገንዘብ ቅጣት እና ድርጅቱ እንዲታገድ እንዲዘጋ ወይም እንዲፈርስ ከተጨማሪ ቅጣት ጋር ሊወሰንባቸው እንደሚገባ ህጉ የሚደነግግ መሆኑን ያመለክታል

3 - የጥፋተኝነት ወሣኔ የተሰጠባቸው ክሶች እና የሚያካትቱዋቸው ተከሣሾችን በተመለከተ ተከሣሾቹ ጥፋተኞች የተባሉባቸው ድንጋጌዎች እና ቅጣታቸው ከዚህ በላይ እንደተገፀው ሲሆን በክሶቹ እና የድንጋጌዎች አንፃር የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው ተከሣሾች ደግሞ

ሀ/ በ1ኛ 2ኛ 3ኛ እና 5ኛ አራት ተደራራቢ ክሶችን አንፃር 1ኛ ተከሣሽ አቶ ሀይሉ ሻወል 2ኛ ተከሣሽ አቶ አባይነህ ብርሀኑ 3ኛ ተከሣሽ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ

ለ/ በ1ኛ 2ኛ እና 5ኛ ሦስት ተደራራቢ ክሶች አንፃር 4ኛው ተከሣሽ አቶ ግዛቸው ሽፈራው 5ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ሀይሉ አርአያ 6ኛው ተከሣሽ አቶ ሙሉነህ ዕዮኤል 7ኛ ተከሣሽ አቶ ስለሺ ጠና 8ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ 9ኛ ተከሣሽ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ 11ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ያቆብ ሀ/ማርያም

ሐ/ በ1ኛ እና 2ኛ ሁለት ተደራራቢ ክሶች አንፃር 12ኛ ተከሣሽ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ 13ኛ ተከሣሽ አቶ አስቻለው ከተማ 14ኛ ተከሣሽ ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ 15ኛ ተከሣሽ አቶ ገ/ፃድቅ ኃ/ማርያም 16ኛ ተከሣሽ አቶ አሰፋ ሀብተወልድ 17ኛ ተከሣሽ አቶ ብሩክ ከበደ 18ኛ ተከሣሽ አቶ መስፍን አማን በሌለበት 19ኛው ተከሣሽ አቶ ታምራት ታረቀኝ 20ኛ ተከሣሽ አቶ እንዱአለም አራጌ 21ኛ ተከሣሽ ወ/ሮ ንግስት ገ/ህይወት 22ኛ ተከሣሽ አቶ ደበበ እሸቱ 23ኛ ተከሣሽ አቶ የኔነህ ሙላቱ

መ/ በ1ኛ እና 3ኛ ሁለት ተደራራቢ ክሶች አንፃር 24ኛው ተከሣሽ አቶ ማሙሸት አማረ 87ኛ ተከሣሽ አቶ መስፍን ተስፋዬ 122ኛ ተከሣሽ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ



Scanned by CamScanner

ሠ/ በ1ኛ ክስ ብቻ 10ኛ ተከሣሽ ፕ/መስፍን ወ/ማርያም 33ኛ ተከሣሽ አቶ አንተነህ መለጌታ 34ኛ ተከሣሽ አቶ መላኩ ፋንታዬ 40ኛ ተከሣሽ አቶ አንዷርጋቸው ጽጌ በሌለበት 51ኛ ተከሣሽ አቶ ኤልያስ ክፍሌ በሌለበት 73ኛ ተከሣሽ ሲሣይ የህትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት 75ኛ ተከሣሽ አቶ አንዱአለም አየለ 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሣታሚ ድርጅት 79ኛ ተከሣሽ አቶ ዘላለም ገብሬ በሌለበት 85ኛ ተከሣሽ አቶ አብይ ግዛው በሌለበት 96ኛ ተከሣሽ አቶ መስፍን ደቤሣ 97ኛ ተከሣሽ አቶ ብርሀኑ አለማየሁ 98ኛ ተከሣሽ አቶ ውድነህ ጅዳ 112ኛ ተከሣሽ አቶ መላኩ ኡንቻ 113ኛ ተከሣሽ አቶ አብዮት ዋቅጅራ 117ኛ ተከሣሽ አቶ ዳንኤል በሪሁን 123ኛ ተከሣሽ አቶ ዋልታ ንጉስአስናቀ 104ኛ ተከሣሽ አቶ ሙሉ ጋሹ

ረ/ በ1ኛ ክስ አንፃር ድንጋጌው ተለውጦ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው 70ኛ ተከሣሽ ፋሲል የህትመት እና የማስታወቂያ ድርጅት 78ኛ ተከሣሽ አቶ ወናክሰገድ ዘለቀ 82ኛ ተከሣሽ አቶ ዳዊት ፋሲል መሆናቸው ውሣኔው ያረጋግጣል

4. በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 84 እና 183 እንዲሁም 85 184 እና 258 መሠረት ከአቃቢ ህግ የቀረበ የቅጣት አስተያየት

4.1- በ1ኛ ክስ ላይ የተካተቱት ተከሣሾች እና በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኞች የተባሉበት አድራጐት

ሀ/ የህዝብና እና የመንግስት ምሰሶ የሆነውን ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊ ስርአት በሀይል የማፍረስ ሙከራ እና የቀሰቀሱትን ሁከት ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን የአገር እና የህዝብ ደህንነት የሚያናጋ ውጤት ፈቅዶ በመቀበል ከፍተኛ ወንጀል የመፈፀም ተግባር መሆኑ

ለ/ በተፈፀመው ህገወጥ የአመጽ ጥሪ እና እንቅስቃሴ ምክንያት የበርካታ ሰላማዊ እና ህግ አስከባሪ ወገኖች ህይወት ያለፈበት እና የአካል ጉዳት ያስከተለ ከፍተኛ የወንጀል ድርጊት መሆኑ

ሐ/ የተፈፀመውን ህገወጥ የወንጀል ድርጊት የመፈፀም እንቅስቃሴ መንግስት በወሰደው ህግን የማስከበር ሀላፊነት እና በተከፈለው የህይወት እና የአካል ጉዳት መስዋትነት መቋቋም ባይቻል ኖሮ ሊያስከትል ይችል የነበረውን የአደጋ መጠን ከፍተኛ መሆኑ



Scanned by CamScanner

መ/ በህዝብ እና በመንግስት ንብረት ላይ ያስከተለው ጉዳት እና መጠን በቀረበው የኢ.ቃቢ. ህግ ክስ የተጠቀሰ እና የተረጋገጠ እንደመሆኑ ድርጊቱ ባይገታ ኖሮ ሊከተል ይችል የነበረው ውጤት ከደረሰው በላይ ከፍተኛ መሆኑ

ሠ/ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በህዝብ ደህንነት እና ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከተለ መሆኑ

ረ/ ድርጊቱን የተፈፀመው የምርጫ ውጤቱን ተከትሎ የታቀደው ህገወጥ የአመጽ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሲባል ለተወሰነ ግዜ የሚቆይ የስብሰባ እና የሰልፍ ክልከላ መመሪያ በመንግስት ወጥቶ በስራ ላይ በዋለበት እና የጦርነት ስጋት ባለበት ወቅት መሆኑ ሠ/ ወንጀሉ የተፈፀመው ሆን ተብሎ በአድማ እና በአድማ ስምምነት መሠረት እና በጦር መሣሪያ እና በሽብር ተግባር መሆኑ

ሸ/ ከዚህ በላይ በተገለፀው የቅጣት ማክበጃ ህጋዊ ምክንያቶች እና ጥፋቶች ጥፋተኞች በተባሉበት የ1996 ዓ.ም የወንጀልን ህግ አንቀጽ 258 መሠረት ቅጣቱ ከብዶ በሞት የሚያስቀጣ በመሆኑ በዚሁ ክስ ላይ ጥፋተኞች ከተባሉት 73ኛ እና 76ኛ ተከሣሽ ድርጊቶች በስተቀር ከተራ ቁጥር 1 እስከ 43 በተመለከቱት ሁሉም ተከሣሾች ላይ ከላይ በተጠቀሰው የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሐ እና መ እና 183 መሠረት ቅጣቱ ከብዶ ጥፋተኞች በተባሉበት የህግ ድንጋጌ ላይ የተመለከተውን የሞት ቅጣት እንዲወሰንባቸው

ቀ/ በተመሣሣይ ሁኔታ በ1ኛ ክስ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት 76ኛ ተከሣሽ ሰርካለም አሣታሚ ድርጅት ከ1ኛ ክስ ድንጋጌ በተጨማሪ በተደራራቢ ጥፋቶች በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 257/ሀ እና 486/ሀ ጭምር የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት እንደመሆኑ ከ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 85 እና 184 መሠረት ቅጣቱ ሊከብድ የሚገባው በመሆኑ እንዲሁም 73ኛ ተከሣሽ ድርጅት የፈፀመው የወንጀል ድርጊት ከፍተኛነት የ1ኛው ክስ መተላለፍ ከባድ ወንጀል እንደመሆኑ ቅጣቱ ከብዶ በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1 2 እና 93/3 እና 4 መሠረት በድርጅቶቹ ላይ ከፍተኛው የገንዘብ ቅጣት እና የድርጅቶቹ መዘጋት ተጨማሪ ቅጣት ጭምር እንዲወሰንባቸው



Scanned by CamScanner

4.2- በተራ ቁጥር 4.1 ስር በ1ኛ ክስ በተካተቱት ሁሉም ጥፋተኞች ላይ ያመለከትነውን የቅጣት ማክበጃ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ ከ1ኛ ክስ በተጨማሪ በ2ኛ 3ኛ እና 5ኛ ተደራራቢ ክሶች አንፃር ጥፋተኞች የተባለቡት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 25 የተመለከቱት ተከሣሾች ላይ በተደራራቢ ከፍተኛ ወንጀል አድራጊታቸው የተፈፀመው ድርጊት እስከ ሞት ቅጣት የሚያስከትልባቸው ከባድ ጥፋት መሆኑ በተለይም በ5ኛ ክስ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 258 ጭምር በማካተት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠ በመሆኑ እና በተደራራቢ የወንጀል ህግ መተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ ደግሞ ቅጣቱ ከብዶ ሊወሰንበት እንደሚገባ የ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 85 እና 184 የሚደነግግ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ቅጣቱ ከብዶ ጥፋተኛ በተባለቡት የህግ ድንጋጌ ስር በተራ ቁጥር 4.1 የተጠቀሰውን ከፍተኛው ቅጣት ለማስወሰን ተጨማሪ የህግ ምክንያት ተደርጐ በመውሰድ የሞት ቅጣት እንዲወሰንባቸው

4.3- አቃቢ ህግ በ1ኛ ክስ አካቶ ክስ ከመሠረተባቸው እና ፍ/ቤቱ የተጠቀሰባቸው የህግ ድንጋጌ በመለወጥ በወንጀል ህግ አንቀጽ 257 ሀ እና 486 ሀ ስር የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው ከተራ ቁጥር 44 እስከ 46 የተጠቀሱ ተከሣሾችን በተመለከተ ድንጋጌው ተለውጦ ጥፋተኞች መባላቸው የፍ/ቤቱ ስልጣን ቢሆንም ከተፈፀመው ድርጊት እና ከተከሰተው የጥፋት ውጤት አንፃር እኩል ተሣትፎ እና ሀላፊነት የወሰዱበት እንደመሆኑ በተራ ቁጥር 4.1 የተዘረዘረውን የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በነሱም ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው የቅጣት አስተያየታችን መሆናቸው ግንዛቤ ተወስዶ ጥፋተኞች በተባሉባቸው ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተው ከፍተኛው ቅጣት እንዲወሰንባቸው

5 - የቅጣት ሀሣብ ማጠቃለያ ህጋዊ አስተያየት

5.1- ተከሣሾቹ በአቃቢ ህግ የተመሠረተባቸው የወንጀል ክስ እና ጥፋተኞች የተባሉባቸው የህግ ድንጋጌዎች በተናጥልም ሆነ በተደራራቢነት የሚያስከትልባቸው ቅጣት ከባድ ቅጣት ከመሆናቸው በተጨማሪ ክሱ ከቀረበበት ጀምሮ የጥፋተኝነት ውሣኔ እስከተሰጠበት ግዜ ድረስ የህግ ልዕልና ባለመቀበል በችሎቱ ላይ ከሚያሣዩት ተግባራት አንፃር ሲታይ የመፀፀት ሁኔታ እንኳን ያልታየባቸው እንደመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 79 ስር የሚታይ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አለመኖሩን ጭምር በማገናዘብ



Scanned by CamScanner

በሁሉም ተከሣሾች ላይ ቅጣቱ ከብዶ ጥፋተኞች በተባሉባቸው የህግ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን ከፍተኛውን ቅጣት እንዲወስንባቸው

5.2- የሞት ወይም የጽኑ እስራት ቅጣት ፍርድ ከህገዘባዊ መብት የመሻርን ጉዳይ በግድ ማስከተል ያለበት መሆኑን በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 124/2 በተደነገገው መሠረት እና የከሣሾቹን የወንጀል አላማ እና ተግባር አፈፃፀም ግምት ወስጥ በማስገባት ከላይ በተጠቀሰው የወንጀል ህግ አንቀጽ 123 እና 124 ድንጋጌ መሠረት በአንቀጽ 123/ ሀ ለ ሐ ከተዘረዘሩት መብቶች የመብትን መሻር ውሣኔ ጭምር እንዲሰጥልን እናመለከታለን።

- የአቃቤ ህግ የቅጣት አስተያየትን አድምጠናል በዚሁ መሠረት የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል

## ት ዕ ዛ ዝ

1- ተከሣሾች አለን የሚሉትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ከሀምሌ 4 ቀን ከቀኑ 6:00 ሰአት ለሬጅስትራር ገቢ እንዲያደርጉ

2- የቅጣት ወሣኔ ለመስጠት ለሀምሌ 9 ቀን 1999 ቀጥረናል።



Scanned by CamScanner

2ኛ ወንጀል ችሎት

የወ/መ/ቁ. 43246

ቀን ሐምሌ 9/99 ዓ.ም.

ዳኞች፡ - አዳል አህመድ

ልዑል ገ/ማርያም

መሐመድ አሚን ሳኒ

ከሳሽ፡ - የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ሽመልስ ከማል፣ ሚካኤል ተክሉ፣ አብርሃ ተጠምቀ

ተከሳሾች፡ - እነ ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል

➢ በተከሰሱበት መዝገብ 1ኛ ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል ቀርበዋል አባይነህ ብርሃኑ ቀርበዋል ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ ቀርበዋል ኢንጂነር ግዛቸው ቀርበዋል ዶክተር ሀይሉ አርአያ ቀርበዋል ሙሉነህ እዩኤል ቀርበዋል ስለሺ ጠና ቀርበዋል ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቀርበዋል ዶክተር በፍቃዱ ደግፌ ቀርበዋል ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ቀርበዋል ዶክተር ያቆብ ኃ/ማርያም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ቀርባለች አስቻለው ከተማ ቀርበዋል ዶክተር ታዲዮስ ቦጋለ ቀርበዋል ገ/ፃዲቅ ኃ/ማርያም ቀርበዋል አሰፋ ኃ/ወልደ ቀርበዋል ብሩክ ከበደ ታምራት ታረቀኝ ቀርበዋል አንዱአለም አራጌ ቀርበዋል ወ/ሮ ንግሥት ገ/ሕይወት ቀርባለች ደበበ እሸቱ ቀርበዋል የኔነህ ሙላቱ ቀርበዋል ማሙሸት አማረ ቀርበዋል አንተነህ ሙሉጌታ ቀርበዋል መላኩ ፋንታዬ ቀርበዋል ተስፋዬ ታሪኩ ቀርበዋል ዋልተንጉስ አስናቀ ቀርበዋል ሙሉ ጋሹ ቀርበዋል መስፍን ተስፋዬ ቀርበዋል አንዱአለም አየለ ቀርቧል ወናክሰገድ ዘለቀ ቀርቧል ዳዊት ፋሲል ቀርቧል መስፍን ደቤሳ ቀርቧል ብርሃኑ አለማየሁ ቀርቧል ውድነህ ጀዳ ቀርቧል መላኩ ኡንቻ ቀርቧል አብዮት ዋቅጅራ ቀርቧል ዳንኤል በሪሁን ቀርቧለ የዘጠኙም ተከሳሾች ጠበቃ ማለትም ከአንዱአለም ጀምሮ እስከ ዳንኤል በሪሁን የተጠቀሱት ተከሳሶች ጠበቃ አቶ ወንድአወክ ቀርበዋል ይኸው ተመዝግቧል መስፍን አማን በሌለበት እንዳልካቸው ፅጌ በሌለበት ኤልያስ ክፍሌ በሌለበት ዘላለም ገብሬ በሌለበት አብይ ግዛው በሌለበት ሰርካለም አሳታሚ አልቀረበችም ሲሳይ አሳታሚ ሲሳይ አጌና ተወካይ ቀርበዋል ፋሲል የሕትመትና ባለፋት እሱ ቀጠሮዎች አልቀረበም እሺ ይኸው ተመዝግቧል፡፡



Scanned by CamScanner

መዝገቡ የተቀጠረው የቀረበውን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ነው በዚሁ መሠረት የሚከተለውን የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል። ... በዚሁ መሠረት ዓቃቤ ሕግ በሌሉበት ሰጥተናል ችሎት የቀረቡት ሁሉም ተከሳሾች እንዲሁም ጉዳያቸው በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጣቸው ተከሳሾች ማለትም 1ኛ መስፍን አማን 2ኛ አንዳርጋቸው ፅጌ 3ኛ ኤልያስ ክፍሌ 4ኛ ዘላለም ገብሬ 5ኛ አብይ ግዛው እንዲሁም ሲሳይ የሕትመትና ማስታወቂያ ድርጅት እና ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት የተባሉ ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት 1ኛ ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1ሀ፣ ለ 38 27/1፣2 38/1፣2 ሲሆን በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቅጣት የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም ሞት ሊሆን እንደሚገባ በህጉ ተደንግጓል አቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው የቅጣት አስተያየት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በተከሳሾች በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት በርካታ ሕግ አስከባሪዎች ሰላማዊ ሰዎች ሕይወት ያለፈበት እና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት መንግሥት በወሰደው ህግን የማስከበር ሀላፊነት እና በተከፈለው የሕይወት እና የአካል ጉዳት መስዋትነት መቋቋም ባይቻል ኖሮ ያስከትል የነበረው አደጋ ከፍተኛ ሊሆን ይችል እንደነበር የወንጀል ድርጊቱ በህዝብ ደህንነት እና ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከተለ መሆኑን ወንጀሉ የተፈፀመው በአድማ በስምምነት መሆኑን ጊዜው በሀገሪቱ የጦርነት ስጋት በነበረበት ጊዜ መሆኑን ቅጣቱም በወንጀል ህግ ቁጥር 84/1 ሐ፣መ እና 183 መሠረት የሚያከብድ ስለሆነ በህጉ ላይ የተመለከተው ከፍተኛው ቅጣት የሞት ቅጣት ሊወሰንባቸው ይገባል ከተጠቀሰው ምክንያት በተጨማሪም አብዛኞቹ ተከሳሾች ሁሉም ማለት በሚቻልበት ሁኔታ በክስ ማመልከቻው በቀረበው ክስ ከአንድ በላይ በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉ ስለሆነ ይህም በወንጀል ህግ ቁጥር 85 እና 184 እንደተመለከተው በልዩ የቅጣት ማክበጃነት ተወስዶ ተከሳሾቹ ላይ ከፍተኛው ቅጣት ሊወሰንባቸው ይገባል በማለት አስተያየቱን አቅርቧል በተከሳሾች በኩል በቅጣት አወሳሰኑ ላይ አስተያየታቸውን ያቀረቡት ጥቂቶች ናቸው እነሱም

1. እንዱአለም አየለ
2. ወናክስጊድ ዘለቀ

3. ዳዊት ፋሲል
4. መስፍን ደቤሳ
5. ብርሃኑ አለማየሁ
6. ጡድካህ ጀዲ
7. መላኩ ኡንጃ
8. አብዮት ዋቅጅራ
9. ዳንኤል በሪሁን ሲሆኑ እነዚህ ተከሳሾች በጠበቃቸው አማካይነት ያቀረቡት አስተያየት ወደ ኋላ እንመለከተዋለን ሌሎች ተከሳሾች ምንም አይነት አስተያየት ያላቀረቡ ሲሆን አቃቢ ሕግ ያቀረበውን የቅጣት አስተያየት ከነዚህ ተከሳሾች አንፃር ተመልክተነዋል እነዚህ ተከሳሾች ከላይ እንደተጠቀሰው ጥፋተኛ የተባሉት 1ኛ ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1 ሀ፣ለ 38 27/1 እና 2 38/1፣2 በሚታይበት ጊዜ የቅጣቱ መነሻ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሆኖ ከፍተኛው ደግሞ የሞት ቅጣት ነው በወንጀል ሕግ ቁጥር 88 ላይ እንደተደነገገው በህጉ ልዩ ክፍል የተደነገጉ ቅጣቶች ከመወሰናቸው በፊት ማለትም በህጉ ልዩ ክፍል በቅጣት መነሻ እና ጣሪያ መካከል ያለውን ከመወሰን በፊት የተለያዩ ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንደሚያስፈልግና ለምሳሌ የወንጀል ከባድ መሆን እና የአፈፃፀሙ ሁኔታዎችን ፍርድ ቤት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ይደነግጋል ይህም ማለት በዚህ በተያዘው 1ኛ ክስ ላይ የተጠቀሰውን አነስተኛውን ቅጣት ማለትም የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ከፍተኛውን የሞት ቅጣትን ከመወሰን በፊት እነዚህ የተጠቀሱትን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ክሱን ለማስረዳት ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ህገ መንግሥቱን እና ስርአቱን ለማስወገድ በተደረገው ሙከራና በወንጀል መከላከል ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ የበርካታ የፖሊስ አባላት ህይወት ከመጥፋቱም በላይ በርካቶች ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል በርካታ የመንግሥትና የግል ንብረቶች ወድመዋል በተወሰኑ ቀናት የከተማ እንቅስቃሴ ታግዷል ይህም የሚያሳየው የተደረገው የወንጀል ድርጊት ግዙፍና ከባድ መሆኑን ሲሆን የወንጀል አፈፃፀሙ ዘዴ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በሁሉም አቅጣጫዎች አመጽ በመቀስቀስ መሆኑ ደግሞ ወንጀሉ ሰፊና ቢሆን

ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ የሚጠቁም ነው በሌላ በኩል የተከሳሾች የግል ሁኔታ ሲታይ አብዛኞቹ የትምህርት ደረጃቸው ከፍ ያለ ሲሆን ይህም ሕጋዊ አካሄድን ከህገ ወጥ መንገድ በቀላሉ ለመለየት እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ይቻላል ሆኖም አድራጎታቸው ሊያስከትል የሚችለውን ከፍ ያለ አደጋ ከምንም ባለ መቁጠር ሕገ መንግሥቱን እና ሕገ መንግሥታዊ ስርአቱን ለማፍረስ ሙከራ ማድረጋቸው የሚወሰንባቸው ቅጣት ከመነሻ ይልቅ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚገባ የሚያመላክት ነው ከዚህ በተጨማሪ በብይኑ እና በውሳኔው ላይ እንደተገለፀው በተከሳሾች መካከል ይሄንን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም እና ውጤቱንም በመቀበል ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በ1ኛ ክስ የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው ብይኑን ላይ በተገለፀው ዘዴ እና አኳኋን መፈፀማቸው የወንጀል አድራጊዎቹን ቅጣት የሚያከብዱ ናቸው እነዚህ የተጠቀሱት ምክንያቶች በወንጀል ሕግ ቁጥር 84 ላይ የተደነገገውን ቅጣት የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች ውስጥ ተዘርዝረው ይገኛሉ በመሆኑም በህጉ ላይ የተጠቀሰው ከፍተኛ ቅጣት ማለትም የሞት ቅጣት ለመወሰን በቂ ምክንያት መኖሩን ለመገንዘብ ችለናል ሆኖም ግን የሞት ቅጣት ከመወሰኑ በፊት በርካታ ሊታዩ የሚችሉ ሁኔታዎች በመኖራቸው በዚህ ጉዳይ ላይ የሞት ውሳኔን ከማሳለፍ ሊያግዱ የሚችሉ ነገሮች ያሉ እንደሆነም ተመልክተናል በወንጀል ህግ ቁጥር 27 ንዑስ ቁጥር 3 መሠረት የወንጀል ድርጊት የሞከረ ሰው የሚቀጣው በመደቡ ለመፈጸም በፈለገው ወንጀል የተደነገገውን ቅጣት እንደሆነ ተደንግጓል ሆኖም በዚህ አንቀጽ እንደ ልዩ ሁኔታ ወይም ኤክሴፕሽን የተቀመጠው በወንጀል ሕግ ቁጥር 117 ላይ የተደነገገው ሲሆን በዚህ አንቀጽ መሠረት የሞት ቅጣትን ለመወሰን እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠው ወንጀሉ ፍፃሜ ያገኘ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል ሁሉም ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት አንደኛ የወንጀል ድርጊት ክሱ በአቃቤ ሕግ ሲቀርብም ሆነ ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲያስተላልፍ የወንጀል ሕግ ቁጥር 27ን በመጥቀስ በሙከራ ደረጃ

ጥፋተኛ የተባሉ መሆኑ ይታወሳል ይህም የሚያሳየው ወንጀሉ ፍፃሜ ያላገኘ መሆኑ እና በሙከራ ደረጃ የተፈጸመ እና ውጤት ያላስገኘ መሆኑ ግልፅ ነው በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላው የሞት ቅጣት ሊያስከትል የሚችል እና የተወሰኑት ጥፋተኛ የተባሉበትም ቢሆን ማለትም በክስ ማመልከቻው በ5ኛ የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት በብይኑም ሆነ በውሳኔው ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ጥፋተኛ የተባሉበት በሙከራ ደረጃ መሆኑ ሲታይ የሞት ቅጣትን ከአማራጭ ውጪ ያደርገዋል በዚህ በ1ኛ ወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ የተባሉ ተከሳሾች ከላይ እንደተመለከተው በተከሳሾች ላይ በወንጀል ህግ ቁጥር 84 እና 85 መሠረት በርካታ ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታ ባለበት እና በተከሳሾች በኩል ምንም አይነት የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ባልቀረበበት እንዲሁም ይህንን ሁኔታ የሚያሳይ ፍርድ ቤቱ ግምት ሊወስድባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች በሌሉበት ሁኔታ በህጉ ላይ ከተመለከተው አነስተኛው ማለት ከእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ዝቅ በማድረግ ቅጣት የሚያሳልፍበት ምክንያት የለም በመሆኑም እነዚህ ተከሳሾች ማለትም፡ -

1. ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል
2. አባይነህ ብርሃኑ
3. ሽለቃ ጌታቸው መንግሥቴ
4. ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው
5. ዶክተር ሀይሉ አርአያ
6. ሙሉነህ እዩኤል
7. ስለሺ ጠና
8. ዶክተር ብርሃኑ ነጋ
9. ዶክተር በፍቃዱ ደግፌ
10. ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
11. ዶክተር ያቆብ ኃ/ማርያም
12. ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ
13. አስቻለው ከተማ
14. ዶክተር ታዲዮስ ቦጋለ
15. ገ/ፃዲቅ ኃ/ማርያም



Scanned by CamScanner

16. አሰፋ ሀብተወልድ
17. ብሩክ ከበደ
18. ታምራት ታረቀኝ
19. አንዱአለም አራጌ
20. ወ/ሮ ንግሥት ገ/ሕይወት
21. ደበበ እሹቱ
22. የኔነህ ሙላት
23. ማሙሸት አማረ
24. አንተነህ ሙሉጌታ
25. መላኩ ፋንታዬ
26. ተስፋዬ ታሪኩ
27. ዋልተንጉስ አስናቀ
28. ሙሉ ጋሹ
29. መስፍን ተስፋዬ
30. መስፍን አማን በሌለበት
31. አንዳርጋቸው ጽጌ በሌለበት
32. ኤልያስ ክፍሌ በሌለበት
33. ዘላለም ገብሬ በሌለበት
34. አብይ ግዛው በሌለበት

የተባሉት ተከሳሾች በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስኗናል በዚህ በ1ኛ ወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ የተባሉት የህግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች ማለትም ሰርካለም አሳታሚ ድርጅት እና ሲሳይ የህትመትና ማስታወቂያ ድርጅቶችን በሚመለከት ጥፋተኛ የተባሉበት የህግ አንቀጽ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን በወንጀል ሕግ ቁጥር 90 ላይ እንደተደነገገው ተቀጪው ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሲሆን መቀጮው እስከ ብር አምስት መቶ ሺህ (500,000.00) ሊሆን እንደሚችል እና አወሳሰኑም የወንጀሉ ክብደት የአደገኛነት መጠን የሀብት ሁኔታ የገቢ ምንጭ እና የመሳሰሉትን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንደሆነ ተመልክቷል የወንጀሉ ክብደት ከላይ የሰፈረ ሲሆን አቃቤ ሕግ የቅጣት ሀሳቡን ሲያቀርብ ከፍተኛውን የገንዘብ



Scanned by CamScanner

መጠን እንዲቀጡ ቢጠይቅም የተከሳሾቹ ድርጅቶች ባለቤቶች ስለ ሀብታቸው መጠንም ሆነ ቅጣቱ ዝቅ ተደርጐ ሊወሰን እንደሚገባ ያቀረቡት አስተያየት የለም በብይኑ እና በውሳኔው ላይ እንደሰፈረው በሰርካለም የሕትመት እና ማስታወቂያ ድርጅት አሳታሚነት ሲሰራጩ የነበሩ የተለያዩ ጋዜጦች ድርጅቱ በተደራራቢ ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ የሚታወስ ነው እንዲህ አይነት መደራረብ ሲገኝ በወንጀል ህግ ቁጥር 184/መ መሠረት በእያንዳንዱ በተፈጸመው ወንጀል ቅጣቱን መደመር እንደሚቻል የሚደነግግ ሲሆን በወንጀል ህግ ቁጥር 90 ላይ እንደሰፈረው ከ10 ዓመት በላይ በጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር አምስት መቶ ሺ (500,000.00) የገንዘብ መቀጮ መወሰን እንደሚቻል ይደነግጋል በመሆኑም ሰርካለም የሕትመትና ማስታወቂያ ድርጅት የወንጀል ሕግ ቁጥር 32/1ለ 34 46 27/1 እና 2 38/1 እና 2ን በመተላለፍ ጥፋተኛ ለተባለው ብር መቶ ሺ እንዲቀጣ በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1ለ 34 257/ሀ ጥፋተኛ ለተባለው ብር አስራ አምስት ሺህ (15,000.00) እንዲቀጣ እንዲሁም በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1ለ 34 46 እና 486/ሀ ስር ጥፋተኛ ለተባለው ብር አምስት ሺህ (5,000.00) እንዲቀጣ በጠቅላላው ብር አንድ መቶ ሃያ ሺህ (120,000.00) እንዲቀጣ ወስነናል በተጨማሪም በወንጀል ህግ ቁጥር 34/2 መሠረት ድርጅቱ ሊፈርስ ይገባል በማለት ተወስኗል ሲሳይ የህትመትና ማስታወቂያ ድርጅት ጥፋተኛ የተባለው በ1ኛ ክስ የተመለከተውን የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1ለ 34 46 27/1 እና 2 38/1 እና 2 በመተላለፍ ጥፋተኛ የተባለ ሲሆን ይህም የወንጀል ድርጊት የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በመሆኑ በወንጀል ህግ ቁጥር 90 መሠረት ቅጣቱን ወደ ገንዘብ በመቀየር በብር አንድ መቶ ሺህ (100000) እንዲቀጣ በተጨማሪም በወንጀል ሕግ ቁጥር 34/2 መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ ተወስኗል። ከላይ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ውሳኔ ከተሰጣቸው ተከሳሾች አብዛኞቹ ከአንድ በላይ በተደራራቢ ወንጀል በ2ኛ፣ በ3ኛ እና በ5ኛ ክሶች ጥፋተኛ የተባሉ ቢሆንም በተከሳሾቹ ላይ የተወሰነው የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት በወንጀል ሕግ ቁጥር 184/1ሀ መሠረት ይህ ቅጣት ስለ ሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ ደርቦ ስለሚይዝ በሌሎች በሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ ደርሶ ስለሚይዝ በሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎት የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ አስፈላጊ አይሆንም በብይኑ እና በውሳኔው እንደተመለከተው ከአንደኛ ክስ አንፃር የተከሰሰበትን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመቀየር በወንጀል ሕግ ቁጥር 32/1ለ 34 45 እና 257/ሀ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ፋሲል የህትመትና ማስታወቂያ ድርጅት ጥፋተኛ የተባለበት የህግ አንቀጽ ከፍተኛው የቅጣት መጠን 10 ዓመት ጽኑ እስራት በመሆኑ ይህንኑ ቅጣት በ[illegible]ል

ገጽ 2

ሕግ ቁጥር 90 ንዑስ ቁጥር 3 መሠረት ወደ ገንዘብ በመቀየር በብር አስራ አምስት ሺህ (15,000.00) እንዲቀጣ ወስነናል በተጨማሪም በወንጀል ሕግ ቁጥር 34/2 መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ ተወስኗል፡፡

96ኛ ተከሳሽ መስፍን ደቤሳ

97ኛ ተከሳሽ ብርሃኑ አለማየሁ

98ኛ ተከሳሽ ውድነህ ጀዲ

112ኛ ተከሳሽ መላኩ ኡንቻ

113ኛ ተከሳሽ አብዮት ዋቅጅራ እና

117ኛ ተከሳሽ ዳንኤል በሪሁንን በተመለከተ ተከሳሾቹ ከላይ እንደተገለፀው ህገ መንግሥቱን እና በህገ መንግሥቱ መሠረት የተቋቋመውን ስርአት በሀይል ለማፍረስ ቅንጅት በተሰኘው ድርጅት አመራር ሰጪነት የተደረገውን የአመጽ ቅስቀሳ እና የአድማ ወንጀል በመላ ሀሳባቸው በመስማማት እና የሚያስከትለውንም ውጤት በመቀበል በግብረአበርነት መሳተፋቸውን በአቃቢ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል ጥፋተኛ የተሰኙበት የህግ አንቀጽ በአድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል ተደንግጓል ተከሳሾቹ የተሳተፉበት የወንጀል አድራጎት በርካታ የሰው ህይወት ያለፈበት እና ከባድ የአካል ጉድለት የደረሰ እና እንዲሁም በመንግሥት እና በህዝብ ንብረት ላይ ውድመት ያስከተለ መሆኑ ሲታይ የተከሳሾቹን የወንጀል አፈፃፀም አደገኛነት የሚያመለክት ሆኖ ተገኝቷል በተለይም 96ኛ ተከሳሽ መስፍን ደቤሳ 97ኛ ብርሃኑ አለማየሁ እና 98ኛ ተከሳሽ ውድነህ ጀዲ ጥቅምት 23 ቀን እና 24/1998 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ አካባቢ ምርጫ ተጭበርብሯል በሚል የተከሰተውን አመጽ በመምራት እና በማስተባበር የአካባቢውን ሰላም እንዲደፈርስና የህዝቡን ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዲቋረጥ ከማድረጉም ሌላ ወያኔ አይገዛንም እያሉ የአመጽ ተግባር ይፈጽሙ ከነበሩት ሌሎች ግብራበሮቹ ጋር በመሆን ድንጋይ በመወርወር የአካባቢው ቤቶች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ማድረጉን እንዲሁም ኑርሁሴን እድሪስ የተባለው የትግራይ ብሄር ተወላጅ ማንነቱን ምክንያት በማድረግ በገጀራ እና በድንጋይ በመደብደብ በግለሰቡ አካልና አእምሮ ላይ ከፍተኛ የጤና መታወክ እንዲደርስ ማድረጉን በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦበታል ይህ አድራጎቱ ህገ መንግሥቱን እና ህገ መንግሥታዊ ስርአቱን ለማፍረስ በማሰብ የተደረገውን የአመጽ ተግባር ድርጊቱን በቀጥታ በመፈፀም በወንጀል ድርጊቱ ተካፋይ መሆኑን የሚያመለክት ነው 113ኛ ተከሳሽ አብዮት



Scanned by CamScanner

ቀቅድሩ እና 117ኛ ተከሳሽ ዳንኤል በሪሁን የምርጫ ውጤት ጋር በተያያዘ ምርጫው ተጭበርብሯል በሚል ምክንያት ህገ መንግሥቱን እና ህገ መንግሥታዊ ስርአቱን በሀይል ለማፍረስ የሀሳብ አላማ በማንገብ የተደረገውን የአመጽ ተግባር በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ከጥቅምት 22 ቀን እስከ 23 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ክልል ውስጥ የተደረገውን የአመጽ እንቅስቃሴ ከሌሎች ግብራበሮቻቸው ጋር በመሆን በመምራት እና በማስተባበር የህዝብ መገልገያ የሆነውን የቀበሌውን ጽህፈት ቤት እና አዳራሽ በድንጋይ ናዳ ነዳጅ በማቀጣጠል በእሳት ቃጠሎ ጉዳት እንዲደርስበት በማድረግ የአካባቢ መንገዶች እንዲዘጉና የህዝቡ ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዲገታና በህዝብና በመንግሥት ተሽከርካሪዎች ላይ በድንጋይ በመሰባበር ጉዳት ማድረሳቸውን እና አትነሳም ወይ እያሉ ህዝቡ ለአመጽ ተግባራቸው ተሳታፊ እንዲሆን መቀስቀሳቸውን ከዚህም በተጨማሪ የትግራይ ብሄር ተወላጅ የሆነችውን 100ኛዋን የአቃቢ ሕግ ምስክር ማንነቷን ብቻ ምክንያት በማድረግ የስራ ማከናወኛ ቦታዋን ማፈራረሳቸውን እና በራሷም ላይ የሀሊና ጉዳት እንዲደርስባት ማድረጋቸውን በአቃቢ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል የቀከሳሾቹ የወንጀል አድራጎት በአጠቃላይ በ1996 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 84 ንዑስ ቁጥር 1 ሐ እና መ እና 183 መሠረት ከባድ ቅጣት የሚያስወስን የወንጀል አድራጎት ሆኖ ተገኝቷል በሌላ በኩል በሌላ በኩል አቃቢ ህግ ተከሳሾቹ ከፈፀሙት የወንጀል አድራጎት አንፃር ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን የጠየቀ ሲሆን የተከሰሳሾቹ ጠበቃ በበኩላቸው የቅጣት ማቅለያ ነው ብለው ያቀረቡት ሀሳብ ተከሳሾቹ የወንጀል ድርጊት አልፈፀሙም እርስ በእርሳቸውም ስለማይተዋወቁ የአድማ ወንጀል አልፈፀሙም ህገ መንግሥቱን እና ህገ መንግሥታዊ ስርአቱ በተራ አንባጓሮ አይፈርስም ወዘተ በማለት ተከሳሾቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን እየታወቀ እና በድህረ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊቀርቡ የማይገባቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ፍፁም ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት የሌላቸው እና ይልቁንም ክርክሩን ወደ ኋላ የሚመልሱ የክስ መቃወሚያ ወይም የመከላከያ ክርክር የሚመስል ይዘት ያላቸው እና ከዚህም አልፎ በመዝገቡ ሊሰፍሩ የማይገባቸው እና ሀላፊነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ሀሳቦች በቅጣት ማቅለያ ሀሳብ ስም አቅርበው ፍርድ ቤቱ ተመልክቷቸዋል ይሁን እንጂ የቀረቡት ሀሳቦች ቅጣትን ያቀላሉ ተብለው በህጉ ላይ ከተመለከቱት መስፈርቶች የሚጣጣሙ ሆነው አልተገኙም ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ስለ ቅጣት ማቅለል ጉዳይ 1996 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 86 የተሰጠውን ስልጣን መሠረት በማድረግ እንዲሁም በዚሁ ህግ በአንቀጽ 41 እንደተመለከተው እያንዳንዱ አጥፊ በተከፋይነቱ ደረጃ በጥፋቱ መጠን እራሱና ድርጊቱ ሊያስከትል ...



Scanned by CamScanner

በሚችለው የአደጋ ከባድነት መጠን እራሱ ባደረገው ወንጀል ብቻ መቀጣት ስላለበት ተከሳሾቹ እያንዳንዱ በየግላቸው ስላደረሱት ጉዳት ተመጣጣኝነት ያለው ቅጣት ከሌሎች በአመራር ሰጪነት ወንጀሉን የፈፀሙ ጥፋተኞች ተለይተው ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚገባ አምነንበታል ፍርድ ቤቱ በተከሳሾቹ ላይ የሚወሰነውን ቅጣት ለማቅለል ምክንያት የሚሆነው ተከሳሾቹ ድርጊቱን የፈፀሙት በአመራር ሰጪዎቹ ምርጫ ተጭበርብሯል በሚል የተደረገውን አሳሳች እና ለአመጽ የሚገፋፋ ቅስቀሳ እንዲሁም ተከሳሾቹ በድርጅቱ አመራር ላይ የነበራቸውን የተሳሳተ እምነት ተከሳሾቹ ለፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት ሆነዋል የሚል ከክርክሩ ሂደት የታየ ጠቅላላ ግንዛቤ ነው በመሆኑም የእድሜ ልክ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 179/ለ መሠረት በማቅለል፡

96ኛው ተከሳሽ መስፍን ደቤሳ

97ኛው ተከሳሽ ብርሃኑ አለማየሁ

98ኛው ተከሳሽ ውድነህ ጃዲ እና

112ኛው ተከሳሽ መላኩ ኡንቻ እያንዳንዳቸው በ18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ

በ113ኛው ተከሳሽ አብዮት ዋቅጅራ እና

117ኛ ተከሳሽ ዳንኤል በሪሁን ደግሞ እያንዳንዳቸው በ15 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል። በማስተከልም ተከሳሽ እንዱአለም አየለን በተመለከተ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተወሰነበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ የሚያስቀጣው በእድሜ ልክ እስራት ወይም በሞት ቅጣት ነው የቅጣት ውሳኔ ፍርድ ቤቱ ሲወስን በወንጀል ህግ ቁጥር 88 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ነው ከተከሣሹ የወንጀል አፈፃፀም አንፃር ብንመለከት እንኳን ተከሳሹ በጋዜጣ በፃፈው ጽሁፍ የሚከተለውን አስፍሯል ዘራፊዎች በተሰበሰቡበት ፍርድ ቤት ፍትህ እንደማይኖር ድምጽ የተቀማው ህዝብ ኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ ቤተ መንግሥቱን ለተረኛው እንዲለቅ ማስገደድ እንደሚገባ ቤተ መንግሥቱንም አለቅም ካለ ሰላም መታወኩ እንደማይቀር የመለስ ዜናዊ አገዛዝን አስጨንቆ ለመጣል አድማ ፍቱን መንገድ የስራ ማቆም አድማ ሰልፍ እምቢ አልገዛም የረሀብ አድማ በአገዛዙ የንግድ ተቋማት ላይ ማዕቀብ ማድረግ እንደ ትግል ስልት አቅርቧል ከዚህ በተጨማሪ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድን እና ፍርድ ቤትን ጠራርጎ ማስወገድ የሚቻለው በብሄራዊ አንድነት መንግሥት በመመስረት መሆኑን በመግለጽ በተለያዩ ቀናት በፃፋቸው ጋዜጦች ገልጿል በተጨማሪ አ.ቀበ. ሕግ ባቀረበው የቅጣት አስተያየት በተከሳሹ ላይ ቅጣት ሊያከብዱ የሚችሉ



Scanned by CamScanner

ምክንያቶችም ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለበት የህግ አንቀጽ ፍፃሜ ያላገኘ ወንጀል ከመሆኑ አንፃር በእድሜ ልክ እስራት ባለፈ መልኩ በሞት ሊያስቀጣው አይችልም በሌላ በኩል የተከሳሽ ጠበቃ ባቀረበው የቅጣት አስተያየት በተከሳሹ ላይ ቅጣት ሊያቀሉ የሚችሉ ምክንያቶችም ያላቀረበ ቢሆንም ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለበት የህግ አንቀጽ ፍፃሜ ያላገኘ ወንጀል ከመሆኑ አንፃር በእድሜ ልክ እስራት ባለፈ መልኩ በሞት ሊያስቀጣው አይችልም በሌላ በኩል የተከሳሽ ጠበቃ ባቀረበው የቅጣት አስተያየት የቅጣት ውሳኔው እንዲቀል እንዲሁም የቀለለው የቅጣት ውሳኔ በገደብ እንዲታገድ የሚጠይቁ ቢሆንም ይህ የቅጣት አስተያየት የሕግ ድጋፍ የሌለው ስለሆነ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በተከሳሹ ላይ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ...ስኗል:: ሌላው 78ኛ ተከሳሽ ወናክሰገድ ዘለቀን በተመለከተ በዚህ ተከሳሽ ላይ ...ሰ... ...ዐ ወንጀል ሕግ አንቀጽ የሚያስቀጣው በቀላል እስራት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተወ... ... በተለይ በጣም ከፍ ያለ ወይንም ይህ አድራጎት ሊያስከትል ይችል የነበረውን ለ... ... እንደሆነ ከ10 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ ህጉ ይደነግጋል በዚህ አንፃር ፍርድ ቤቱ ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ ለመወሰን እንዲያስችለው በወንጀል ህግ ቁጥር 88 የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የቀረበውን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተከሳሹ በ3 ዓመት ጽኑ እስራት ወይንም በመቀጮ ወይንም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከ3 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ሲሆን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 88 መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የአደገኝነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን የወንጀል አፈፃፀም ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት 1 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ቤቱ ወስኗል::

የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጥተናል::

## ትዕዛዝ

1. በተከሳሾች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ተከሳሾች ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ የታሰሩትን በማሰብ እንዲያስፈጽም ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይፃፍ::

2. በድርጅቶች ላይ የተላለፈውን የገንዘብ መቀጮ አቃቢ ህግ በመከታተል ያስፈጽም እንዲፈርሱ ውሳኔ የተላለፈባቸው ድርጅቶችን በሚመለከት ለሚመለከተው ይፃፍ

3. በወንጀል ህግ ቁጥር 123 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት የሞት ወይም የጽኑ እስራት ቅጣት ፍርድ ከህዝባዊ መብት የመሻርን ጉዳይ በግድ ማስከተል እንዳለበት እና ከዚህ መብት የመሻሩ ጉዳይም ለዘወትር ሆኖ የሚቆይ



Scanned by CamScanner

መሆኑ በተደነገገው መሠረት ከላይ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነባቸው ሁሉም ተከሳሾች ከህዝባዊ መብቶቻቸው በተለይም ከመምረጥና መመረጥ መብታቸው ተሽረዋል ለሚመለከተው ይፃፍ፡ ቅጣቱ ቀሉ ጽኑ እስራት የተወሰነባቸው ሌሉች ተከሳሾች ለ5 ዓመት ያህል ከህዝባዊ መብቶቻቸው በተለይም ከመምረጥ እና ከመመረጥ መብቶቻቸው ተሽረዋል ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡

4. በሌሉበት ውሣኔ የተሰጠባቸውን በሚመለከት፡ የፌዴራል ፖሊስ ካሉበት በማደን ለማረሚያ ቤትም እስራቱን ያስፈጽም

5. በተሰጠው ውሣኔ ቅር [illegible] ተጦበኑ ወገን ይግባኝ የመጠየቅ መብቱን በተሉት ነግረናል ችሉቱ አብቅቷል።

# ማስታወሻ

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ /ሀ/ /ለ/፣ 38፣ 34፣ 27/1/ እና 238/2/ /258/ ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሕገመንግስትና በሕገመንግስት ስርዓት ላይ ወንጀል በመፈፀም እነ ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል በሚል መዝገብ ተከሰው የነበረ ሲሆን በመዝገቡ ላይ የጥፋተኛነት ውሣኔ ተሠጥቶበታል፡፡ ነገር ግን ተከሣሾቹ በድርጊታቸው መፀፀታቸውንና ለወደፊቱም ተመሣሣይ አፍራሽ ተግባር እንደማይፈፅሙ በመግለፅ ይቅርታ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 395/96 አንቀፅ 11 መሠረት የይቅርታ አላማ የሕዝብ ደህንነትና ጥቅም ማስከበር ስለሆነ በሀገሪቱ ርዕሠ ብሔር አማካኝነት ይቅርታ ተደርጉላቸዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተከሣሾች ላይ ያረፈው ውሣኔ በምህረት የታለፈ ስለሆነ ተፈፃሚ አልሆነም፡፡

Scanned by CamScanner